# ጅቡቲ
## የጥገኝነታችን መስፈሪያ

በለጠ በላቸው ይሁን

© መፅሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ፀሐፊው ፈቃድ
መልሶ ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።
2006 ዓ.ም.

ምስጋና

- የመፅሐፉን ረቂቅ በማረም እና ገንቢ አስተያየታቸውን በመለገስ ላገዙኝ ለወ/ሮ ወርቀዘቦ ተገኝ እና ለአቶ በላቸው ይሁን
- ይህንን መፅሐፍ ለህትመት በሚሆን መልኩ ላሰናዳልኝ ለአቶ አያሌው ወርቁ

ለአስተያየትዎ: beletebelachewm@gmail.com

# ለ ወርቀዘቦ

## ማውጫ


ገፅ

መቅድም ....7

1. ምዕራፍ ፩፡ መግቢያ ....14
2. ምዕራፍ ፪፡ ጅቡቲን የማጣት መጀመሪያ ....27
   - 2.1. የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት ጅምር ....27
   - 2.2. የድንበር መካለል ....35
   - 2.3. የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ጅምር ....43
   - 2.4. የታላቋ ሱማሌ ህልም፣ የግብፅ ምኞት እና የቀዘቀዘው ጦርነት ተፅዕኖ...48
3. ምዕራፍ ፫፡ የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ዳሰሳ ....54
   - 3.1. የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ....54
   - 3.2. ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ እና ጅቡቲ ....85
   - 3.3. ድህረ-1983 የግንኙነት አቅጣጫ ....122
4. ምዕራፍ ፬፡ ጅቡቲ–አዲስ አበባ ምድር ባቡር ....128
   - 4.1. የባቡር መሥመሩ ህልውና ጅምር ....128
   - 4.2. ደርግ እና የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር ....135
5. ምዕራፍ ፭፡ የጅቡቲ ወደብ፡ የጥገኝነታችን ቁልፍ ....163
   - 5.1. በጅቡቲ ወደብ የመጠቀም መብት በንጉሳዊያን ዘመን ....163
   - 5.2. ደርግና የጅቡቲ ወደብ ....169
   - 5.3. ድህረ-1983 ገፅታ ....178
6. ምዕራፍ ፮፡ መደምደሚያ ....199

ዋቢ ጽሑፎች ....218

# መቅድም

በቀይ ባህር ደቡባዊ ጫፍ ወደ ህንድ ውቅያኖስ መዳረሻ የሚገኘው የጅቡቲ የጠረፍ ግዛት ኢትዮጵያን ከሚያዋስኑ መንግስታት በመጠን ትንሹ ነው። ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም ወሰን ከሚጋሩት እንዲሁም ታሪካዊ ቁርኝታቸው ጎልቶ ከሚታዩ እንደ ሱዳን፣ ሶማሊያ እና ኬንያ ካሉ አገሮች ሲወዳደር ጅቡቲ ዝቅተኛ ግምትና ቦታ ይዞ የቆየ እና የተረሳ ይመስል ነበር። ግዛቱ ካለው አነስተኛ የህዝብ ቁጥር፣ የተፈጥሮ ሐብት ወዘተ አንፃር ሲገመት በእርግጥም እዚህ ግባ የሚባል ፋይዳ ያልተሰጠው ቢመስል አያስገርምም። ይህ ግምት በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ የሚስተዋል ሲሆን አገሪቱን በመሩ ተከታታይ መንግስታት የግንኙነት ታሪክ ውስጥም ተንፀባርቋል።

በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ታሪክ ውስጥ በተለምዶ የቀዳሚነት ቦታ ሲሰጣቸው የቆዩ ሌሎች የጎረቤት አገሮች ያላቸው ሁለንተናዊ ባህሪይ የጅቡቲን ወሳኝነት ማደብዘዙ ዕሙን ነው። የሶማሊያ ሪፐብሊክ ሲያራምደው የቆየው የታላቋ ሱማሌ መርህና አጋዴንን ወደ ግዛቱ የመጠቅለል ምኞት ዋነኛው የትኩረት ነጥብ ሆኖ ቆይቷል። ይህንንም አደጋ ለመቀልበስ በኢትዮጵያ በኩል ዘርፈ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል። ከሱዳን መንግስታት ጋር ሲያወዛግብ የቆየው የድንበር ክለላ ጥያቄ ብሎም ተከታታይ የካርቱም መንግስታት ይፋ የሆነ የኤርትራ ተገንጣዮችን ዓላማ መደገፍ እና ሌሎች ተቃዋሚ ኃይሎችን ማበረታታቸው ወዘተ በኢትዮጵያ በኩል የቅድሚያ ትኩረት እንዲያገኝ መንገድ ከፍቷል። በተለይ የሶማሊያና የኤርትራ ጉዳይ የተከታታይ የኢትዮጵያ መንግስታት ዋነኛ የውጭ ፖሊሲ አጀንዳ መሠረት ሆኖ እስካለንበት ወቅት ዘልቋል። ከኬንያ ጋር መመስረት የተቻለውን የወዳጅነት እና የትብብር ግንኙነት ጠብቆ ማቆየቱም የዘውትር ክትትል የሚሻ ጉዳይ ነበር። የዚህ አከባቢያዊ ውጥረት አንዱ ውጤት ለጅቡቲ የተሰጠው ትኩረት በአንፃራዊ መልኩ የተቀዛቀዘ መምሰሉ ነው።

ከሰላሳ ዓመታት ጦርነት በኋላ ኤርትራ ነፃ አገር ስትሆንም ችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሳይሰጠው ታለፈ። በኢትዮጵያና አድሲቷ ኤርትራ መካከል ተመስርቶ በነበረው ጊዜያዊ ወዳጅነት መሠረት አሰብን በተለይ ለመጠቀም ተችሎ ነበር። ይህ የልዩ ተጠቃሚነት መብት ግን በተጨባጭ ውል ላይ ሳይሆን በመንግስታቱ መካከል በነበረው መቀራረብ ላይ ብቻ የተንተራሰ ስለነበር ብዙም ሊዘልቅ አልቻለም። በግንቦት 1990 የመንግስታቱ ግንኙነት በድንገት ከፍፁማዊ ፍቅር ወደ ለየለት ጠላትነት ለማምራቱ ዋነኛው ምክንያት የአሰብ የወደብ አጠቃቀም ጉዳይ ሆነ። የዚህ ሁሉ እውነታ ድምር ውጤትም አስደናቂ በሆነ መንገድ ከቀይ ባህርም ይሁን ከህንድ ውቅያኖስ በአስርትና መቶ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ላይ የምትገኝ የባህር በር አልባ አገር መፈጠር ነው። ሌላኛው እውነታ ደግሞ የጅቡቲ ወደብ እና የባቡር ሐዲዱ ከተቀረው ዓለም ጋር ለመገናኘት ብቸኛ አማራጭ ሆነ።

በዘመናዊው ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጅቡቲን ዋነኛ የንግድ በር ሆኖ ለመቆየት ያስቻሉ አሳማኝ ምክንያቶች ነበሩ። ቀዳሚው ምክንያት የአገሪቱ በቅኝ ገዢዎች ከበባ ሥር መዋል ነው። ይህ እውነታ ከቀጥተኛ አገዛዝ በመለስ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ህልውና በአውሮፓውያኑ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ሥር እንዲሆን መንገድ ጠረገ። ተያይዞም በፍጥነት እየተቀያየረ በመጣው የዓለም የፖለቲካና የኢኮኖሚ መስተጋብር ውስጥ የሉዓላዊ አገርን ቁመና ለማስጠበቅ ወሳኝ የሆነውን የባህር በር የማግኘቱ አማራጭ አጣብቂኝ ገጠመው። ኤርትራን መልሶ ማግኘት አስከተቻለበት እስከ 1940ቹ አጋማሽ ድረስም ጅቡቲ ብቸኛው ከተቀረው ዓለም ጋር የመገናኛ በር ሆኖ ቆየ። ይህም እውነታ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበረ።

በነዚህ ጊዜያት ኢትዮጵያ ተደጋጋሚ የወረራ አደጋ ተጋርጦባት የነበረ መሆኑና ይህንንም ለመቀልበስ የከፈለችው መስዋዕትነት የአገሪቱን ለአደጋ ተጋላጭነት በይፋ ያሳየ ነበር። ከግብፆች፣ ደርቡሾችና ጣሊያኖች የተቃጡ መስፋፋቶችን ለመቀልበስ የተቻለው በጅቡቲ በር ለመጠቀም እና የጦር መሳሪያ





ለማስገባት በመቻሉ መሆኑ ግልፅ ነው። በተለይ አፄ ምንሊክ በ1888 ጣሊያንን አድዋ ላይ ለማሸነፋቸው አንዱና ዋነኛው ምክንያት በጊዜው ጦራቸውን ሊያስታጥቁ የቻሉት ዘመናዊ መሳሪያ ነበር።

በወቅቱ ከወራሪው ኃይል እምብዛም የማይተናነሰውን ትጥቅ ለማግኘት የተቻለው ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ሊመሠርቱት በቻሉት ጥብቅ ወዳጅነትና በጅቡቲ በር ለመጠቀም የሚያስችል የልዩ ተጠቃሚነት መብት ማስከበር በመቻላቸው መሆኑ አያከራክርም። ይህንን መብት ማስጠበቅ ባልተቻለባቸው ጊዜያት ደግሞ የአገሪቱ ህልውና ታላቅ አደጋ ሲጋረጥበት ቆይቷል። በአንፃራዊነት ወዳጅ የነበረቸው ፈረንሳይ ጀርባ በሰጠችበት ወቅት ከ1928 እስከ 1933 ባሉት አምስት ዓመታት ኢጣሊያ በቀላሉ ኢትዮጵያን መያዝ ችላ ነበር። እንዲሁም የሲያድ ባሬ ሶማሊያ ወረራ በፈፀመበትም ጊዜ ለመጠቃታችን አንዱ ምክንያት የጅቡቲ የእጅ አዙር ወገንተኝነት ነበር።

ጅቡቲን ተመራጭ ያደረገው ሌላኛው ምክንያት ግዛቱ በቀጠናው አጠቃላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ወታደራዊ አሰላለፍ አንፃር የያዘው ቁልፍ ቦታ ነው። በገቢር የአረብ ባህር ለመሆን ችሎ የነበረው የቀይ ባህር ዳርቻ በተጋሬ የአረብ መንግስታት ተፅዕኖ ሥር መዋሉ እና አገራቱ ይህንን እሳቤ ከግብ ለማድረስ በብርቱ መንቀሳቀሳቸው በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ችግር ማስከተሉ አልቀረም። ስለሆነም በ1940ቹ አጋማሽ እውን የሆነውን የኤርትራን መመለስ ተከትሎ አገሪቱ ሉዓላዊ የባህር በሮች ባለቤት መሆን ችላ የነበረ ቢሆንም የምፅዋና የአሰብ ወደቦች ይሰጡ የነበረው አገልግሎት የጅቡቲን ሚና ሊተካ አልቻለም።

በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ የተከናወነው የእርስ በርስ ጦርነት የቀይ ባህር ወደቦችን አስተማማኝነት በእጅጉ አኮስምኖታል። ተከታታይ መንግስታትም ከምፅዋና አሰብ ይልቅ ምስራቃዊውን በር የአገሪቱ ህልውና መሠረት አድርገው መውሰዳቸው ከዚህ እውነታ የመነጨ ነው። ከ1983

# ምዕራፍ ፩
# መግቢያ

ስለ ጅቡቲ በተወሳ ቁጥር ዳግማዊ ምንሊክ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ባለ ሙሉ ስልጣን ሚኒስትር ከሙሴ ላጋርድ ጋር በመጋቢት 12፣ 1889 (20 March 1897) የተፈራረሙት የአዲስ አበባው ስምምነት በቀደምትነት ይነሳል።[1] የዚህ ስምምነት ፋይዳ የግዛቱን ለፈረንሳይ ተላልፎ መሰጠት ከማረጋገጥ ባሻገር፤ የድንበር ወሰንን እና የግዛት አለኝታ ጥያቄን በተጨባጭ ለማስረገጥ መሞከሩ ነው። በተጨማሪም ስምምነቱ በተጠቀሰው የግዛት ክልል የማንኛውንም ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት የሚከለክል ሲሆን በክልሉ የሚገኘውን የአሳል ሐይቅ የኢትዮጵያ ቋሚ ውርስ መሆንና የአገሪቱን ያልተገደበ ጨው የማምረት መብት ያረጋግጣል። ይህ ስምምነት በ1891 እ.ኤ.አ. ምንሊክ ለአውሮፓ አገራት በላኩት ዘዋሪ ደብዳቤ ያስረገጡትን እስከ አሳል ሐይቅ ይደርስ የነበረውን የግዛታቸውን ድንበር አሳልፎ የሰጠ ነው።

የ1889ኙ ውል ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ለነበራት የግዛት አለኝታ ጥያቄ እንደ ህጋዊ ማረጋገጫ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል። የአውሮፓ አገራት የስዊዝ ካናልን መከፈት ተከትሎ የአፍሪካ ቀንድን ከመቀራመታቸው እና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አደጋ ላይ ከመጣላቸው በፊት አብዛኛው የቀይ ባህር አከባቢ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር የነበረ መሆኑን የሚያስረግጠው አፈሴላዊው አቋም የተለያዩ ቀደምት የታሪክ መረጃዎችን በዋቢነት በማንሳት የባለቤትነት መብትን ይጠይቃል።

[1] ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (ውጉሚ)፤ አቃፊ -ፋይል፦ ጅቡቲ 52-D3፤ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ ስምምነት፡ መጋቢት 12፣ 1889





በ5ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ካሌብ የናግራን (የመን) ክርስቲያኖችን ለመርዳት ሲዘምቱ ሠራዊታቸው ከጅቡቲ በመነሳት በባብኤል መንደብ መሻገሩ፤ የአውሮፓውያን ተጓዦችን ዘገባ በመመርኮዝ የኢትዮጵያ ወሰን በሰሜን ምሥራቅና በምሥራቅ እስከ ቀይ ባህርና ኤደን ባህረ ሰላጤ እንዲሁም በደቡብ ምሥራቅ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ መድረሱ በተደጋጋሚ የሚነሱ መከራከሪያዎች ናቸው። በተጨማሪም በ16ኛው ክፍለ ዘመንና ከዚያም ወዲህ የኦቶማን ቱርክ መንግሥት የመስፋፋትና የመግዛት ፍላጎቱን ለማርካት ወደ አፍሪካ ቀንድ ከመምጣቱ በፊት ጅቡቲ የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋንና ወራሪው ኃይልም በኢትዮጵያ ወታደሮች በየጊዜው ከዚሁ ሥፍራ የተባረረ መሆኑ፤ እንዲሁም እስከ አፄ ምንሊክ ዘመነ መንግሥት ድረስ የታጁራና ሌሎችም የጅቡቲ ሱልጣኖች ለኢትዮጵያ መገበራቸው በመረጃነት ይቀርባሉ።[2]

በተጨማሪም አስተዳደራዊ መዋቅሮችንና የህዝቦችን አሰፋፈር ይዘት መሠረት በማድረግ የአሁኑ የጅቡቲ ግዛት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር እንደነበር ይታሰባል።

[2] ውጉሚ፦ ሱማሌ 15-D1። Also see Francisco Alvares, *The Prester John of the Indies*. Trans. Lord Stanley of Alderley (The Hakluyt Society, second series, nos. 104 and 105), p. 300; Daniel D. Kendie, "Towards Northeast African Cooperation: Resolving the Ethiopia-Somalia Disputes," *in Northeast African Studies*, Vol. 10, No. 2 (2003), 67-70. Merid Wolde-Aregay, "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508-1708, with Special Reference to the Galla Migration and Their Consequences," PhD Thesis in History (University of London, School of Oriental and African Studies, January 1971), pp.18-60. *ያዕቆብ ኃይለማርያም፣ አሰብ የማን ናት? የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ* (ንግድ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ፣ 2004 ዓ.ም.)፣ ገፅ 27-31.

የግዛቱ ሰሜናዊ ክፍል በትግሬ ራሶች ሲተዳደር የተቀረው ደቡባዊው ክፍል ደግሞ የሸዋ ነገስታት ይዞታ መሆኑ በመንግስታዊው ክርክር እንደመረጃ ሲቀርብ ቆይቷል። የታጁራ ሽለቆ (Gulf of Tadjura) በሚል ስያሜ የሚታወቀው ሰሜናዊ ክፍል አዱሊስ (ዙላ)፣ ቤይሉል፣ አሰብ እና ሮሂዮ የተሰኙ ቀጠናዎች ሲኖሩት በአብዛኛው ቀድሞ ሩስ አሁን ደግሞ አፋር/ ደንከል ተብለው የሚጠሩ ህዝቦች ሰፍረውበታል። ከአጠቃላይ የአፋር/ደንከል ህዝቦች ውስጥም ሦስት-አራተኛው በቋሚነት የሚኖሩት አዳል እና ሰርዶ በተሰኙ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሲሆን እነሱም በአውሳና ራህየቶ ሱልጣኖች ይመራሉ። ይህ የአፋር ህዝቦች የመኖሪያ ቀጠና በተለምዶ "የአፋር ትሪያንግል" በመባል ይታወቃል። ከዘይላ በስተደቡብ እስከ ጋርዳፊያ ያለው ግዛት በበኩሉ የሶማሌ ህዝቦች ይኖሩበታል።

እስከ 1840 ባለው ጊዜ የአሁኑ የጅቡቲ ግዛት ከተወሰኑ የመካከለኛው ምስራቅ አረቦች በስተቀር በአብላጫው በአፋር/ ደንከሎች የተያዘ እንደነበር ይታመናል። ነገር ግን ዱልሃንቴና ወሰንግሌ የተሰኙ የዳሮድ ሶማሌ ንዑስ ጎሳዎች ወደ ሰሜን አቅጣጫ ያካሄዱት የግዛት መስፋፋት የጅቡቲን የህዝብ መዋቅር ቀየረው። የሶማሌዎቹን ጫና ተከትሎ የግዛቱ ጎሳዎች ይዞታ ከመቀየሩም ባሻገር የዱልሃንቴና ወሰንግሌዎችን የኃይል እርምጃ መቋቋም ያቃታቸው የኢሳ ሶማሌዎች ወደ ጅቡቲና ኢትዮጵያ ምስራቃዊ ክፍሎች (በዋነኝነት ሐረር) እንዲሸሹ ገፋቸው። ሂደቱም በጅቡቲ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ትግል በደንከል/አፋር እና ኢሳ ሶማሌዎች መካከል የቁጥር የበላይነት ሽኩቻን አስከተለ። ከአጠቃላይ የኢሳ ህዝቦች መካከል ሁለት-ሶስተኛው ያክል የሚኖሩት በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን የጎሳው መሪ (ኡጋዝ) ቋሚ መቀመጫም ድሬዳዋ ሆነ።[3]

[3] ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት





የአሁኑ የጅቡቲ የህዝብ አወቃቀርና አሰፋፈር እንደሚያመለክተው የኢሳ ጎሳ አባላት የአጠቃላዩ ቁጥሩን 35 ፐርሰንት አካባቢ የሚይዙ ሲሆን አፋር/ደንከሎቹ ደግሞ ወደ 20 ፐርሰንት አካባቢ ይሸፍናሉ። ኢሳዎች የግዛቱን አንድ-ሦስተኛ ክፍል በሚያካልለው ከታጁራ ሸለቆ በስተደቡብ እና ከአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር ሐዲድ ምስራቃዊ ክፍል ሰፍረዋል። የአፋር/ ደንከል ጎሳዎች ደግሞ ከታጁራ ሸለቆ በስተሰሜንና ከባቡር ሐዲዱ በስተምዕራብ ባለው የጅቡቲ ሁለት-ሦስተኛ ክልል በቋሚነት ይኖራሉ። ከተቀረው የግዛቱ ነዋሪ ህዝቦች መካከል ገደቡርሲና ኢሳቅ የተሰኙት ሶማሌዎች ከሰሜን ሶማሊያ በቅርብ ዘመን እንደመጡ ይታመናል። እንዲሁም ፈረንሳዊያን፣ አረቦችና ጥቂት አውሮፓውያን በግዛቱ ሰፍረው ይገኛሉ።

ከሁለቱ ዋነኛ የግዛቱ ሕዝቦች መካከል ኢሳዎቹ ጠንካራ የሆነ በጎሳ አስተዳደር ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት መመስረት ችለዋል። የኢሳ ማህበረሰብ በሦስት ጎሳ የተከፈለ ሲሆን ከነዚህም ሁለቱ እንደገና በንዑስ ጎሳዎች ይከፈላሉ። ከሦስቱ ጎሳዎች መካከል የአብጋል ጎሳ በአፍሪካ ቀንድ ከሚኖሩ ኢሳዎች ሦስት-አራተኛውን እንዲሁም በጅቡቲ ከሚኖሩት ሁለት-ሦስተኛውን ያህል ይሸፍናል።

አብጋሎች በአራት ንዑስ ጎሳ የሚከፈሉ ሲሆን እነሱም ዩኒስ-ሙሳ፣ ሳድ-ሙሳ፣ ማማሳን እና አርዌን ይሰኛሉ። ሁለተኛው ጎሳ - ዳሎል - የግዛቱን ኢሳዎችን አንድ-ሦስተኛ ሲሸፍን በተራው ፎርላባ፣ ሆሮኔ እና ዋላዶን በሚባሉ ሦስት ንዑስ ጎሳዎች ይከፋፈላል። ዋርዲክ የተባለው ሦስተኛው የኢሳ ጎሳ በአመዛኙ በሶማሌና አፋሮች የጋብቻ መተሳሰር የተፈጠረ እንደሆነ ይታመናል። አብጋሎች በተለይም የማማሳን ንዑስ ጎሳ ከቁጥር ብልጫቸው በመነሳት ግዛቱን የማስተዳደር ተፈጥሮአዊ መብት እንዳላቸው የሚያምኑ ሲሆን ዳሎሎች ደግሞ ዋነኛ የስልጣን ተቀናቃኝ ሆነው ኖረዋል። ዋርዲኮች በተራቸው የኢሳዎች መንፈሳዊ መሪ - ኡጋዝ - ከነሱ ጎሳ የሚመረጥ መሆኑን ለፍላጎቶቻቸው ማራመጃነት ይጠቀሙበታል።

[4] Peter J. Schraeder, "Ethnic Politics in Djibouti: From "Eye of the Hurricane' to 'Boiling Cauldron'", in *African Affairs*, Vol. 92, No. 367 (April 1993), pp. 204-206.

አፋሮችም በተመሳሳይ ለጎሳ ድርጅትና አባልነት ቅድሚያ የሚሰጡ ቢሆንም ከኢሳዎች በተለየ ግን ከባህላዊ የጎሳ መሪዎቻቸው - ሱልጣኖች - በተዋረድ በሚተላለፉ መመሪያዎች ላይ ይመረኮዛሉ። ከኢሳዎች በተቃራኒ የጎሳውን ሁለንተናዊ ሰብዕና በሚነኩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚያስተላልፉት ሱልጣኖቹ ናቸው። ለዚህም ዓላማ የሚቋቋም በንዑስ ጎሳ መሪዎችና ሌሎች ባላባቶች የተዋቀረ የአማካሪዎች ምክር ቤት ለሱልጣኖቹ የማማከር ድጋፍ ያደርጋል። ሌላው የአፋር/ደንከል ልዩ ባህሪይ ጎሳው በሁለት ማህበራዊ ክፍሎች መከፈሉ ነው። በዘልማድ በከፍተኛ ቦታዎች የሚኖሩ አፋሮች አሳሂመራ (ቀይ) ጎሳዎች ሲባሉ በዝቅተኛ አከባቢዎች የሚገኙት ደግሞ አዶሂመራ (ነጭ) ጎሳዎች ተብለው ይታወቃሉ።








Probable extent of the Ethiopian empire at the beginning of the sixteenth century.

በ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ የኢትዮጵያ ግምታዊ የግዛት ክልል[5]

[5] Meried, p. 22




በ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ የኢትዮጵያ የደቡብ ምሥራቅ የግዛት ክልል[6]

በኢትዮጵያ መንግስት የተጠናቀሩ የጥናት ወረቀቶች ጅቡቲ ለፈረንሳይ ተላልፎ የተሰጠበትን አግባብ ከአጠቃላይ የ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዕውነታዎች አንፃር ለመተንተን ሙከራ ያደርጋሉ። እንግሊዝ፣ ጣሊያን እና ፈረንሳይ ያሳዩት የአፍሪካ ቀንድን በተለይም ኢትዮጵያን የመቀራመት ፍላጎት፤ የአገሪቷ የመከላከያ መዋቅር በሰሜን ከጣሊያን፣ በምዕራብ ከማህዲስቶች ለረጅም ጊዜ መፋጠጡ፤ ትልቁ ቅኝ የመገዛት አደጋ አድዋ ላይ በትልቅ መስዋዕትነት መቀልበሱ እና ይህ



[6] Merid, p. 43



ያስከተለው የወታደራዊ አቋም መኮስመን ወዙተ የጠረፍ ክልሎችን በአስተማማኝ ለመከላካል አላስቻለም።
ስለሆነም እንግሊዝ ሶማሊላንድን፣ ፈረንሳይ ጅቡቲን እና ጣሊያን ቤናድር ሱማሌን በወረራና ባላባቶቹን በገንዘብ በመደለል መያዝ ቻሉ። እያፈጠጠ የመጣውን ሉአላዊነትን ለዘለቄታው የማጣት ዕውነታ በጊዜያዊነት ለመቅረፍ ብቸኛው አማራጭ ከነዚህ ተስፋፊ መንግስታት ጋር ዓለም አቀፍ ይዘት ያላቸው ስምምነቶችን መፈራረም እና በዚህም አማካይነት ለሀገሪቱ ህልውና ዋስትና ማበጀት ነበር።

በጅቡቲ የይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ ኢትዮጵያ ስታራምደው የነበረውን ፖለቲካዊ አቋም መልክ ለማስያዝ የተቀናጀ ሙከራም መደረጉ አልቀረም። ለምሳሌ በሐምሌ 1957 የኢትዮጵያን ታሪካዊ የባለቤትነት መብት እንዲያጠና ለአንድ የታሪክ ባለሙያዎች ቡድን ኃላፊነት ተሰጥቶ ነበር። በጥናቱ ማጠቃለያ በቀረበው ሪፖርት እንደተብራራው በአውሮፓ የታተሙ ወደ 14 የሚጠጉ ጥንታዊ ካርታዎች በግልፅ እንደሚያመለክቱት ከ1500 እስከ 1850 ባሉት ጊዜያት ከዘይላ እስከ ሱዳን ወደብ (ፖርት ሱዳን) ያለው የቀይ ባህር ዳርቻ የኢትዮጵያ ሉአላዊ ግዛት አካል ነበር። በተጨማሪም የ1899ኙን አጠቃላይ ውል እና የድንበር ስምምነት በዋቢነት በማቅረብም ፈረንሳይ ግዛቱን ከኢትዮጵያ በስተቀር ለሌላ ሦስተኛ ወገን ላለማስተላለፍ የገባችውን የውዴታ ግዴታ እና ኢትዮጵያ በአሳል ሐይቅ ላይ ያስከበረችውን የባለርስትነት መብት ያስረግጣል።[7]

[7] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፎች ላይ ስላላት መብት የቀረበ የጥናት ሪፖርት (በፒ. ፔትሪዲስ እና ጓደኞቻቸው ተክለማሪያም)፡ ጥቅምት 1961። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 26፤ የጥናት ሪፖርት፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 26፣ 1966

[8] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1 ጥራዝ 2፤ በኢጣሊያን ወረራ ወቅት ንጉሰ ነገሥቱ በታውን ሽጠውት የነበረ ሲሆን ከነፃነት በኋላ መልሰው ገዝተውታል። ጅቡቲ ነፃነቷን ስትቀዳጅ በታውን የወረሰችው ቢሆንም በ1967 ደርግ ወደ ኢትዮጵያ ይዞታነት እንዲመለስ አድርጓል።

በአስገዳጅ ምክንያቶች የፈረንሳይ ቅኝ በሆነው ግዛት የኢትዮጵያን ልዩ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በባቡር ሐዲዱ እና በወደቡ ላይ በተለይዩ ጊዜያት ከተገኙ የልዩ ተጠቃሚነት መብቶች በተጨማሪ በንጉሰ ዘመን ከፈረንሳይ መንግሥት በስጦታ የተገኘው 15,888 ካሬ ሜትር ቦታ እና ቪላ (በጅቡቲ ከተማ Plateau du Serpent በሚባለው ውድ ሠፈር ውስጥ የሚገኘው) ለቆንስላ ጽ/ቤት ከተፈቀደው ሁለት ተጨማሪ ቦታ ጋር የአገሪቱን የተለየ መብት ባለቤትነት ያረጋግጠለ፡፡[8]

አፋምቦን ወደ ኢትዮጵያ ለማስመለስ የተደረጉ ስኬታማ እንቅስቃሴዎች እና በአሳል ሐይቅ የመጠቀም ቅ አካያ የጅቡቲ በር መብትን በዘላቂነት ማስከበሩ ይህንኑ ስለ ጅቡቲ የተደረገውን ትግል ስፋትና ጥልቀት ያመላክታል፡፡ ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በ1897 እ.ኤ.አ. በአፍሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የከፈተችው የቆንስላ ጽ/ቤት የሚገኘው በጅቡቲ መሆኑ ለግዛቱ የተሰጠው ልዩ ትኩረት ዋነኛው አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ቀደምት የኢትዮጵያ መንግስታት ፈረንሳይ በሂደት ቅኝ ግዛቷን ስትለቅ እና የጅቡቲ ህዝብ የራሱን ዕድል የመወሰን መብቱን ሲተገብር ያለፈ ታሪኩን ከግንዛቤ በማስገባት ወደ እናት ሀገሩ በፈቃዱ ይመለሳል የሚል ፅኑ እምነት ነበራቸው፡፡ ይህም ኢኮኖሚያዊ፣ ስትራቴጂካዊ/ጂኦግራፊያዊ እና ማህበራዊ እሳቤዎችን ከግምት በማስገባት ነው፡፡ ጠቅላላ ስፋቱ 23,000 ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሆነው እና እስከ 1980ቹ መጨረሻ ከ300,000 ያነሰ ህዝብ የሚኖርበት ጅቡቲ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት ላይ ጥገኛ መሆኑ፤ አጠቃላይ የወሰን ክልሉ ርዝመት 500 ኪሎ ሜትር ሆኖ ከዚሁ 400 ኪሎ ሜትሩ የሚዋሰነው ከኢትዮጵያ ጋር መሆኑ፤ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ለማስጠበቅ ያለው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፤ የጅቡቲ ሁለት ዋነኛ ጎሳዎች - አፋርና ኢሳ - ተፈጥሮአዊ መገኛ እና መቀመጫ በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ ወዘተ ለዚህ እምነት እንደ ማረጋገጫ ሲቀርቡ ቆይተዋል፡፡





ከሁሉም በላይ ጅቡቲን ተፈላጊ ያደረገው ግን የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ነው፡፡ የሃገሪቱ ዋነኛ ወደቦች የነበሩት አሰብና ምፅዋ በሰሜን በግብፃዊው የስዊዝ ካናል በደቡብ በጠባቡ ባብ ኤል ማንደብና በፔሪም (ማዩን) ደሴት ታንቀው የዓረብ ሐይቅ ተብሎ ሊጠራ በተቃረበው ቀይ ባሕር ውስጥ መገኘታቸው የጅቡቲን ወደብ አጠቃላይ አስፈላጊነት ያጎላዋል፡፡ ይህ ስትራቴጂካዊ ከበባ ከብሔራዊ ወደቦቹ ይልቅ ወደ ህንድ ውቅያኖስ በቀላሉ ለመድረስ ጅቡቲን የተሻለ አማራጭ ያደርጋል፡፡

የኢትዮጵያን ወጪና ገቢ ትራንዚት ከማስተናገድ ረገድ እ.ኤ.አ. ከ1962 ጀምሮ ጅቡቲን መወዳደር የጀመረው የአሰብ ወደብ በሃያ ስድስት ሚሊዮን ብር ተሻሽሎ እና የነዳጅ ማጣሪያ ተተክሎለትም እንኳ የጅቡቲ ወደብ ድርሻ 49 ከመቶ፣ የአሰብ 27 ከመቶ እና የምፅዋ 18 ከመቶ ነበር፡፡ በ1970ቹ አጋማሽ በኋላ ደግሞ የጅቡቲ ወደብ ወደ 75 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ትራንዚት ማስተናገድ ችሎ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር የጅቡቲ ወደብ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም ባሻገር የኢትዮጵያ ዋነኛ የጥቅም በር ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም ነው፡፡[9]

ከዓለም አቀፋዊ እና አከባቢያዊ ጠቀሜታው አንፃርም ሲታይ ጅቡቲ የአውሮፓን የአፍሪካንና የእስያን አህጉሮች የሚያገናኝ፣ በቀይ ባህር፣ በኤደን ባህረ ሰላጤና በህንድ ውቅያኖስ መዳረሻ ስትራቴጂካዊ አቀማመጥ የያዘ በመሆኑ የዓለም የንግድ መተላለፊያ በር ነው፡፡ በተለይም የምዕራብ አገሮች ከሚጠቀሙበት ነዳጅ 70 ከመቶው ያህል የሚተላለፈው በቀይ ባህር ላይ በመሆኑ ይህ ዕውነታ የጅቡቲን ስትራቴጂካዊ ቁልፍነት ያጎላዋል፡፡

---

[9] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ታህሳሥ 27፣ 1967፡፡ ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 2፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ሰኔ 28፣ 1968፡፡ Seyoum Haregot, *The Bureaucratic Empire: Serving Emperor Haile Selassie* (Red Sea Press: Trenton, New Jersey, 2013), 168.

በዘመናዊ መልክ የተደራጀው የጅቡቲ ወደብም ከሚሰጠው የወደብ አገልግሎት በተጨማሪ ግዛቱ በአውሮፓ፣ ምሥራቅ አፍሪካ፣ መካከለኛው ምሥራቅ እና በህንድ መካከል ትራንስርት መረብ ለመዘርጋት የተመቸ ነው።[10] የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ ሲታይም በዝቅተኛ መሬት ላይ መገኘቱ፣ የታላቁ ስምጥ ሸለቆ አፍ መሆኑ እና በተራራ ያልተጋረደ መሆኑ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ለመግባት ተመራጭ ያደርገዋል። ይህም በፀጥታ ረገድ ለኢትዮጵያ ህልውና ቁልፍ የሆነ አቀማመጥ እንዲይዝ ያስችለዋል። በተጨማሪም ግዛቱ በወደቡና በሐዲዱ አማካኝነት የኢትዮጵያ የንግድ መተላለፊያ በር በመሆኑ ተቀናቃኝ የሆነ መንግስት ጅቡቲን ቢይዝ በኢትዮጵያ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ለማሳደር ይችላል።

ተከታታይ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሲነደፉና ሲተገበሩም ከነዚህ መሠረታዊ ዕወነታዎች በመነሳት ነበር። ሆኖም በዓለም የፖለቲካ ምህዳር እና በተለይም በአፍሪካ ቀንድ በተከሰቱ ተከታታይ ለውጦች ምክንያት በኢትዮጵያ በኩል ከወቅቱ ተጨባጭ ዕውነታዎች የተዛመዱ የፖሊሲ ማስተካከያዎች ሲደረጉ ቢቆዩም የቆየውን የግዛት አለኝታ ብሎም የልዩ ተጠቃሚነት መብት በዘላቂነት ማስጠበቅ አልተቻለም። ይልቁንም ትግሉ በሂደት ጅቡቲን በታላቋ ሶማሊያ ከመታቀፍ ወደመከላከሉ ምዕራፍ ተሸጋገረ። ብሎም የግዛቱን ህልውና ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅሞች አንፃር መቃኘት እና ማስጠበቅ አዲሱ የግንኙነት መርህ እየሆነ መጣ።

በተለይ የአፄ ኃይለ ሥላሴ እና የደርግ መንግስታት በእነኚህ መርሆዎች አተገባበር ዙርያ ወሳኝ የሆነ ሚና ለመጫወት ችለዋል። የዚህ ዋነኛ ነፀብራቅ ከሆኑት ጥረቶች

---

[10] T.N. Dupuy, *The Almanac of World Military Power* (Dunn Loring, Virginia, 1970), 199. Thomas A. Marks, "Djibouti: France's Strategic Toehold in Africa." In *African Affairs*, Vol. 73, No. 290 (Jan. 1974): 95. Peter Schwab, "Cold War on the Horn of Africa." In *African Affairs*, Vol. 77, No. 306 (Jan. 1978): 6.





መካከል ከቅኝ ገዥዋ የፈረንሳይ መንግስታት ጋር በየወቅቱ የተደረጉ የሁለትዮሽ ስምምነቶች፤ በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ አወቃቀር ዙሪያ የተከናወኑ ቀጣይነት ያላቸው ጣልቃ ገብነቶች፤ የታላቋ ሶማሊያን የተስፋፊነት ዓላማ ለማክሸፍ የተደረጉ እልህ አስጨራሽ ትግሎች፤ የወደብ እና የባቡር መስመሩን በበላይነት ለመቆጣጠርና የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የጥቅም በሮች መሆናቸውን ለማስረገጥ የተሠሩ ሥራዎች ይገኙባቸዋል።

ይህ መፅሐፍ ከ1940ቹ መጨረሻ አንስቶ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ዙሪያ ስታራምድ የቆየቻቸውን ፖሊሲዎች ለመዳሰስ እና ለመተንተን ጥረት ያደርጋል። በዘመናዊው የሀገራችን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የዚህ ግዛት ሚና በእጅጉ ወሳኝ የነበረ መሆኑ ቢታወቅም ይህንን በተመለከተ የተደረገ ሁሉን ዓቀፍ የታሪክ ጥናት አይገኝም። ጅምር ጥረት ቢኖር እንኳ ስለ ባቡር ሐዲዱ አመሠራረት እና ስላስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በደምሳሳው ከመዘገብ የዘለለ አይደለም። በፈረንሳይኛ የተፃፉ መፅሐፍትና የምርምር ወረቀቶች በብዛት ቢኖሩም ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ካላቸው ተደራሽነት አንፃር ፋይዳቸው እምብዛም ነው። ይህንን ክፍተት ከመሙላት አኳያ የዚህ ጥናት ዳራ ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ የተከተለቻቸውን ፖሊሲዎች እና ይህንኑ ለማስፈፀም የወሰደቻቸውን እርምጃዎች በተጨባጭ መረጃ በማስደገፍ መተንተን ነው።

እስከ 1983 ድረስ የምዕዋና አሰብ ወደቦች ባለቤት የነበረች ሀገር በጅቡቲ ጉዳይ የነበራት የማይናወጽ የባለቤትነት ስሜት ከምን የመነጨ ነበር፤ የባህር በር አልባ ከተሆነስ በኋላ የተከሰቱ ዕውነታዎች ተጨባጭ ገፅታ እንዴት ይመዘናል፤ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ መካከል የወደብና ባቡር መስመር አጠቃቀምን አስመልክቶ የተስተዋሉ ለውጦች መሠረታዊ መገለጫዎች ምንድን ናቸው፤ ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት ሁለንተናዊ ጥቅምን ከማረጋገጥ አኳያ በጅቡቲ የውስጥ ጉዳይ ያደረጓቸው ጣልቃ ገብነቶች እስከ ምን ይደርሳሉ፤ በሁሉም አቅጣጫዎች የተገኙ ውጤቶች በሂደት ከታጡ ጥቅሞች ጋር ሲወዳደሩ አገራቱ በጅቡቲ ላይ የተከተለቻቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎች እንዴት ይገመገማሉ ወዘተ የዚህ መፅሐፍ መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ኢትዮጵያ በታሪክ ሂደት በጅቡቲ ላይ የነበራትን የጥቅም


ERITREA
YEM
Ash Shaykh Sa'id
Rehayto
Debaysima
Red Sea
Mayyūn
Moussa Ali
2063 m
(6768 ft)
Sidiha Monghella
Fagal
Ālito
GREAT
Manda
Khor Angar
Dadda'to
RIFT
Dorra
VALLEY
Lofefle
Balho
Serdo
Obock
Deda'ī
ETHIOPIA
Tadjoura
Gulf of Aden
DENAKIL
Golfe de Tadjoura
Djibouti
DJIBOUTI
Yoboki
Āfambo
Loyada
Tokhoshi
Holhol
'Ali Sabīh
Dikhil
SOMALIA
HARERGE

ለኮምብ የተባለ ወኪሉ ወደ ቀይ ባህር በማቅናት "በኢትዮጵያ የባህር ድንበር በአስረኛውና በ16ኛው ማዕረግ መካከል" አንድ የንግድ ቦታ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሰጠ። የፈረንሳይ መንግስትም ኩባንያው የሚይዘውን ቦታ መልሶ ሊገዛ፣ወጪውንም ሊተካ እና ለኩባንያው አንድ ለመጋዘን የሚሆን ቦታ ሊሰጥ መግባባት እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ሙሴ ለኮምብ ከስፍራው ደርሶ ኤድ አኮዋያ የሚባል አከባቢ ላይ ከግለሰቦች በዘጠኝ ሺህ ዘጠኝ መቶ ፍራንክ (ወደ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር) አርባ ሁለት ሊግ ካሬ (እርግጠኛ ያልሆነን ርቀት ለመለካት ያገለግል የነበረ፡ አንድ ሊግ 5 ኪሎ ሜትር ወይም 3 ማይል) ከሰሜን ወደ ደቡብ አሥራ አራት ሊግ ከወደቡ ወደ ውስጥ ሦስት ሊግ ጥልቀት ያለው ቦታ ገዛ።[12]

ይሁን እንጂ ምጽዋ የነበረው የፈረንሳይ ቆንሲል ግገሩን ውድቅ በማድረጉ መንግስት የለኮምብን መሬት ሳይገዛው ቀረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ቆንሲሉ ራሱ (ሙሴ ዴጉቲን) ቦታውን ከኩባንያው በሃያ አምስት ሺህ ፍራንክ ገዝቶ ለሌላ የፈረንሳይ ድርጅት በሃምሳ ሺህ ፍራንክ እ.ኤ.አ. በ1858 መልሶ ሸጠው። በዚህ መንገድም በጅቡቲ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ተጠነሰሰ።

በተጨማሪም እ.ኤ.አ. በሰኔ 1843 የፈረንሳዩ ንጉሥ ሉዊ ፊሊፕ ወኪል ነኝ በሚል ሮሽ ደሪኩር (Rocket d'Hericourt) የተባለ ግለሰብ ከሸዋው ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ጋር የንግድና የወዳጅነት ስምምነት ይፈራረማል። በስምምነቱ አንቀጽ 6 መሠረት የሸዋው ንጉሥ የፈረንሳይ ዜጎች በግዛቱ ውስጥ ርስት እንዲገዙ የፈቀደ ሲሆን የፈረንሳይ ንጉሥ በበኩሉ ወደ ኢየሩሳሌም ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ጥበቃ ሊያደርግ ይስማማሉ።
የሚገርመው ነገር ይህን ስምምነት ሲፈራረሙ ፈረንሳይ

[12] ውጉሚ፡- ጅቡቲ፡ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፎች ላይ ስላላት መብት የቀረበ የጥናት ሪፖርት (በፒ. ፔትሪዲስ እና ጓደኞቻው ተክለማሪያም)፡ ጥቅምት 1961። ውጉሚ፡- ጅቡቲ፡ 52-D3 26፤ የጥናት ሪፖርት፡ እ.ኤ.አ. የካቲት 26፣ 1966፣ ገጽ 20





በኢየሩሳሌም ምንም ዓይነት ሥልጣን ያልነበራት መሆኑ ነው። የስምምነቱ ዋነኛ ዓላማ በሸዋ መንግስት ቁጥጥር ሥር የነበሩ የጅቡቲ የጠረፍ ግዛቶችን ወደ ፈረንሳይ ለማዛወር ሕጋዊ መሠረት መፍጠር ነበር።

ከሸዋው ንጉሥ የተፈራረሙትን ውል ለግዛቱ ባላባቶች በማሳየትም እ.ኤ.አ. ከ1945-1959 ባሉ ዓመታት ኮምብ (Combes)፣ ብሮኛ (Broguant)ና ላምበር (Lambert) የተባሉ የፈረንሳይ ዜጎች ኦቦክ እና ኢድ ላይ ቦታ ገዝተው ለፈረንሳይ መንግስት ይሸጣሉ። እነዚህ ግለሰቦች ከ1882-1884 ባሉ ዓመታት ከጅቡቲ ባላባቶች ቁራሽ መሬት ብቻ ሳይሆን የይዞታ ባለመብትነትንም ጭምር የሚያረጋግጥ ስምምነት ተፈራረሙ።

እ.ኤ.አ. በመጋቢት 1862 በአዳል የባህር ጠረፍ የሚገኙ ባላባቶች በኦቦክ የሚገኘውን የመርከብ ማረፊያና ከራስ አሊ እስከ ራስ ዱሜራ ያለውን ሜዳ በአስር ሺህ ብር፤ እ.ኤ.አ. በታህሳሥ 1884 ከራስ አሊ ጀምሮ እስከ ጉቡት ካራብ ድረስ ላለው አገር ባላባት የሆነው አሕመድ ቤን ሞሐመድ በወር 180 ብር ለመጦሪያ እየተቀበለ በስሩ ያለውን አገር የፈረንሳይ ጥገኛ እንዲሆን ከፈረንሳዮች ጋር ስምምነት አደረገ። በተከታታይም የጉባድ ባላባት አህመድ ሉይታ እና ከጉባት ካራብ እስከ እምባዶ ዜይላ ያሉ የኢሳ ባላባቶች የፈረንሳይ ጥገኛ ለመሆን ፈቃደኛ ሆኑ። የፈረንሳይ መንግስትም በግል የተገዙትን ቦታዎች በአገዛዙ ሥር እንዲመዘገቡ ማድረግ ይጀምራል።[13]

ነገር ግን ከግዛቱ ባላባቶች ጋር በተናጠል የተደረጉ የግገር ውሎች ህጋዊነታቸው የተሟላ እንዳልሆነ የተረዱት ፈረንሳዮች ከኢትዮጵያ መሪዎች ዘላቂ የባለቤትነት ማረጋገጫ ለማግኘት

[13] ዝኒ ከማሁ። ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት
[14] ባህሩ ዘውዴ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983* (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999ዓ.ም.)፣ ገፅ 23-26፣ 42-44፣ 53-64፣ 80-88.

ተንቀሳቀሰ። በእርግጥም እ.ኤ.አ. እስከ ጥቅምት 1883 ድረስ በኦቦክ የባህር ዳርቻ ተገድቦ የነበረው ይዞታ በዓመት ከ62,000 የፈረንሳይ ፍራንክ የማይበልጥ በጀት ያለውና ሁለት ፈረንሳዊ ነጋዴዎች ብቻ የሚኖሩበት ነበር። ከኢትዮጵያ የተፈለገውን ማረጋገጫ ለማግኘትም ፈረንሳዮቹ ብዙ አልተቸገሩም። አጠቃላይ ሂደቱም በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ ተጠናቀቀ።

እ.ኤ.አ. ከ1845-1885 በነበሩ ወቅቶች ኢትዮጵያ ምስራቃዊ ጠረፏን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የቀይ ባህር ይዞታዎቿን ከአውሮፓውያን ቅኝ ለመከላከል የምትችልበት አቅም አልነበራትም። ጊዜው አገሪቱ ከ1740 እስከ 1840 ከቆየው የዘመነ መሳፍንት የእርስ በርስ መቆራቆስ እየተላቀቀች የነበረበት፣ ነገር ግን ወዲያውኑ እስከ ምዕተ-ዓመቱ መገባደጃ ወደዘለቀ የፖለቲካ ሽኩቻ የተሸጋገረችበት ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ፣ ዮሃንስ እና ምንሊክ ዘመናት የተደረጉ የሥልጣን ይገባኛል ትግሎች ለዚህ ዋነኛ አመላካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። በተጓዳኝ ደግሞ እጅግ የጠነከረ ወታደራዊ አቅም የነበራቸው ተስፋፊ ኃይሎች የአገሪቱን ነፃነትና ሉዓላዊነት የፈተነ ተደጋጋሚ ወረራ እያደረጉ ነበር።[15]

እንግሊዞች በ1860/61 እስከ መቅደላ አምባ መድረስ ቻሉ፣ በ1860ቹ መጨረሻ ግብፃውያን ተከታታይ ወረራ ፈፀሙ፣ በ1880/81 ደርቡሾች/መሐዲስቶች እስከ ጎንደር ዘለቁ፣ ጣሊያኖች በበኩላቸው አድዋ ላይ እስከተሸነፉበት ድረስ የአገሪቱን ህልውና በእጅጉ የፈተነ የቅኝ መግዛት ጥረት አደረጉ። ምንም እንኳን ወረራዎቹ በከባድ መስዋዕትነት ሊከሽፉ ቢችሉም የተገኙት ድሎች ስትራቴጂካዊ ፋይዳቸው ትልቅ የሆኑ የዳር አገር ግዛቶችን በአውሮፓውያን ከመያዝ አላዳኑም። ፈረንሳይ ከኢትዮጵያ ጅቡቲን በቅኝ የመያዝ ማረጋገጫ ስትሻ የአፄ ምንሊክ መንግስት ይህንን ለመቃወም ብሎም እንዳይሆን ለመከላከል የሚያስችል አቅም አልነበረውም።

[15] ውጉሚ፡- ቀይ ባህር 158-D22 6፣ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር የጠረፍ ግዛቶች ላይ ስላላት የግዛት መብት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት





በኢትዮጵያ በኩል የነበረው አቅም አልባነት አፄ ምንሊክ ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ሳድ ካርኖ እ.እ.አ. ጥቅምት 30፣ 1890 በላኩት የተማጽኖ መልዕክት ተንጸባርቋል። ፈረንሳይ እንደ መያገሮ ስትጠቀምበት ስለነበረው በጅቡቲ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ስለፈቀደችው የጦር መሳሪያ ምስጋናቸውን ከገለፁ በኋላ፡-

> ...አሁን የጠረፉን ግዛት ከያዛችሁና ጎረቤታችን መሆናችሁን ካረጋገጣችሁ ዘንድ ሁሉንም የባህር ጠረፍ እንዳትይዙ ይልቁኑም የተወሰነ መተላለፊያ ነጥብ እንድትተዉልን እንጠይቃችኋለን። ይህንንም መተላለፊያ ቀጠና ማስተዳደር እስክንችል ወደ ሦስተኛ ወገን ይዞታ አታስተላልፉብን...።

ሲሉ ጠይቀው ነበር። ከአምስት ወራት በኋላ በሚያዝያ 1883 (April 1991) ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት በላኩት ደብዳቤ ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ የኢትዮጵያን አቋም እና የግዛት ድንበሯን ዳርቻ ጠቅሰው ተመሳሳይ ወደባህር የመተላለፊያ በር የማግኘት መብቷ እንዲከበር ጠየቁ።

> ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የግዛት ዳርቻ ከባህሩ ይደርስ ነበር። አስፈላጊው አቅም ስላልነበረን ... የጠረፍ ግዛቶቻችን በአረቦች እጅ ወደቀ። አሁንም የባህር ዳርቻ ግዛታችንን በኃይል የማስመለስ እቅድ የለንም። ነገር ግን ክርስቲያን የሆናችሁ ወንድሞቻችን የባህር ጠረፍ ግዛታችንን እንደምትመልሱልን ካልሆነም ቋሚ የባህር መዳረሻ በር እንደምትሰጡን እናምናለን። ... ጥንታዊው የአገራችን ግዛትም ከሐምቦስ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እስከ አሳል ባህር፣ ከዚያም ከጥንት ጀምሮ ገባራችን የሆነውን የሞሐመድ አንፈሬን ግዛት ወደኛ በመተው እስከ አራፋል ይደርሳል።[16]

[16] ዝኒ ከማሁ

ነገር ግን ከኢትዮጵያ የጅቡቲ ህጋዊ ቅኝ ገገር ስለመሆንዋ መተማመኛ ለፈለገችው ፈረንሳይ ይህ የምንሊክ አቋም በቂ አልነበረም። በተደጋጋሚ በጅቡቲ ይዞታዋ በኩል የጦር መሳሪያ መተላለፍን እንደ መደራደሪያና መያዣ ለተጠቀመችበት ለፈረንሳይ ይህንን እውቅና ማግኘቱ አልከበዳትም። ከስድስት ዓመታት በኋላ ከኢትዮጵያ የተገኘው እውቅና ቅድመ ሁኔታ ነበረው። ፈረንሳይ አምና ከተቀበለቻቸው ቅድመ ሁኔታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የጅቡቲን ግዛት ከኢትዮጵያ ማግኘቷን፤ ግዛቱን በቅኝነት ስትይዝ ለመልቀቅ ባሰበች ጊዜ ለኢትዮጵያ ልትመልስ መስማማቷን፤ እና ግዛቱንና የወደፊት ዕጣ ፈንታውን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ መንግስታት ብቻ ኃላፊነቶች መሆናቸውን የሚገልጹ አንቀጾች ይገኙባቸዋል። የጅቡቲ ግዛትንም በሚመለከት ሁለቱ አገሮች በጥር እና መጋቢት 1889 (January and March 1897) የተፈራረሟቸው ስምምነቶች እነዚህን ከላይ ተጠቀሱ ግዴታዎችና መግባባቶች የሚያንጸባርቁ ናቸው።[17]

ለአርባ ዓመታት የተደረገው በቀይ ባህር ጠረፍ ቅኝ ግዛት የመፍጠር ጥረት በመጨረሻ ውጤት አግኝቶ እ.ኤ.አ. በሰኔ 22፣ 1885 የፈረንሳይ ምክር ቤት ስለ አዲሱ የፈረንሳይ ግዛት አደረጃጀት የቀረበለትን ሃሳብ ያጸድቃል። በነሐሴ ወርም የፈረንሳይ መንግስት በአዋጅ "የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛትና አከባቢዎቿ" የሚል መዋቅር በማቋቋም የጅቡቲ ግዛትን ሕጋዊ ሰውነት አረጋገጠ። በተለይም እ.ኤ.አ. በየካቲት 1889 ፈረንሳይና እንግሊዝ በፈረንሳይ ሱማሌና በእንግሊዝ ሱማሌ መካከል ያለውን ድንበር ለመከለል ያደረጉት ስምምነት ስለ ግዛቱ መፈጠር ዓለም አቀፋዊ ማረጋገጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ታላቋ ብሪታንያ ፈረንሳይ በታጁራና በኦቦክ የያዘችውን አገር የፈረንሳይ ግዛት

---

[17] ዝኒ ከማሁ። ስለስምምነቶቹ ዝርዝር እና እንድምታ ቀጣይ ምዕራፎችን ተመልከት።

[18] Shehim and Searing, 210-211.





ነው ብላ በማወቋ ምክንያትም ፈረንሳይ ከ1885 ጀምሮ በቀይ ባህር ምሥራቃዊ ጠረፍ የቅኝ ግዛት እንዳላት በይፋ አሳወቀች። በእንግሊዝና ፈረንሳይ የወሰን ስምምነት እንደሚያስረዳው አዲሱ የፈረንሳይ ሱማሌ ጠቅላላ ክልል 250 ሜትር ርዝመት እና ከ5-20 ኪሎ ሜትር ስፋት ነበረው። እ.ኤ.አ. በ1896 ታጁራን፣ ኦቦክን እና ጅቡቲን ያካተተው የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት (Côte Français des Somalis) በይፋ ተመሠረተ።[18]




የጅቡቲ ሁልጣኔቶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ

---

[18] Shehim and Searing, 210-211.




የጅቡቲ ሡልጣኔቶችን አቀማመጥ የሚያሳይ ንድፍ




እ.ኤ.አ. በ1886 የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት የድንበር ክልል (በቀይ የተመለከተው





## 2.2. የድንበር መካለል

አፄ ምንሊክ በጥቅምት 1883 ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ለሙሴ ሳድ ካርኖ በጻፉት ደብዳቤ "በቀይ ባህር ያለውን የባህሩን ጠረፍ፡ ፈረንሳይ መያዟን በምንቀበልበት በአሁኑ ጊዜ መብታችን ታውቆ አንድ ነጥብ ሊኖረን እንደሚገባ እናስታውቃለን:: ይህንንም ለማግኘት የምንደሰት ስንሆን በምንም ምክንያት የቀይ ባህር ጠረፋችን ለሌላ ሦስተኛ መንግስት እንዳይተላለፍ፡ እያስጠነቀቅን ነው" ሲሉ አስታወቁ:: ዳግመኛም በሚያዝያ 1883 (10 April 1891) የግዛታቸውን ክልል ለማሳወቅ ለአውሮፓ መንግስታት በላኩት ዘዋሪ ደብዳቤ የቀይ ባህር ጠረፍ፡ ቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር፣ አገሪቱ በደከመችበት ወቅት እንደተነጠቀች እና ቅኝ ገገርዎቹ "የክርስቲያን መንግስታት" የባህር ድንበሩን ይመልሳሉ ብለው እንጠሚጠብቁ አስታወቁ:: በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መካከል ስለነበረው የድንበር ወሰን ሲገልጹም "ከሐምቦስ አንስቶ ያሰልን [አሳል] ባህር ጨምሮ የጥንቱ ዜጎችንን የመሐመድ ሐንፋሪን ግዛት ሁሉ ይዞ በባህር ዳር ዳር እየሄደ አልፋሌ ይደርሳል" ብለው ነበር::[19]

ፈረንሳይ የጅቡቲ ግዛቷን ለማስፋት ለአፄ ምንሊክ የፈቀደችውን በወደቡ በነፃ የመጠቀም መብት እንደ ውለታና ማስፈራሪያ መጠቀም ጀመረች:: በተለይ ኢትዮጵያ የተጋረጠባትን የቅኝ ገዢዎች የመስፋፋት አደጋ ለመቋቋም በብርቱ የምትፈልገው የጦር መሣሪያ ማስገቢያ የሆነውን ብቸኛ የባህር በር ላለማጣት ምንሊክ የተጠየቁትን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በፈረንሳይ ዘንድ ግምት የተወሰደ ይመስላል:: ስለዚህም ከባህር ወደቡ አንስቶ ወደ ውስጥ ከሃምሳ እስከ ሰባ አምስት ኪሎ ሜትር ጥልቀት ያለው መሬት እንዲኖራቸው መወትወት ጀመሩ::

ሙሴ ላጋርድ ይህንኑ አስመልክቶ ለሐረሩ ገገር ለልዑል ራስ መኮንን ባቀረበው ጥያቄ ለወደቡ መብት ውለታ ኢትዮጵያ በበኩልዋ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሱማሌ ወሰን የመጨረሻ

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 34–38




እ.ኤ.አ. በ1886 የፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት የድንበር ክልል (በቀይ የተመለከተው)

ነጥብ ከባይዱ ወደ ራሂሌ እንዲመጣ እና ጉባድ በከፊልና የአውሳ ሱልጣን ግዛት በሙሉ ለፈረንሳይ እንዲሆን አመለከተ:: ፈረንሳይ በበኩልዋ የጠየቀችው ከታጁራ፣ አቦክና ከጅቡቲ ወደብ ጀርባ የሚገኘው የኢትዮጵያ መሬት በልዩ አጠራር "የውስጥ ክፍለ ሀገር" እንዲባልና ይህ ክፍለ ሀገር ከፈረንሳይ የባህር ጠረፍ ጋር የተያያዘ ሆኖ ይዞታው ግን የተለየ እንዲሆን፤ በዚሁ "የውስጥ ክፍለ ሀገር" ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ መንግስትና ዜጎች መብትና ጥቅም በተለይ የተጠበቀና የተከበረ እንዲሆን፤ ከዚህ "የውስጥ ክፍለ ሀገር" ፈረንሳይ መሬት ቆርሳ ለሌላ የውጭ መንግስት ሳትሰጥ እና ግዛቱን ለቃ በምትሄድበት ጊዜ ይህንኑ መሬት ለኢትዮጵያ መልሳ ልታስረክብ ግዴታ ልትገባ እንደምትፈልግ ሙሴ ላጋርድ አስታወቀ::

ይህን ጥያቄ ራስ መኮንን መጀመሪያ በብርቱ የተቃወሙት ቢሆንም እምቢታው በወደቡ በኩል መሣሪያ እንዳይገባ ሊያስከለክል ይችላል በሚል ፍራቻ ጉዳዩን ለንጉሠ ነገሥቱ አስተላለፉ:: አፄ ምንሊክም በሃሳቡ በመስማማት በመጋቢት 12፣ 1889 (20 March 1897) ከሙሴ ላጋርድ ጋር ስምምነት ተፈራረሙ:: በዚህም መሠረት የባህር ጠረፉ ከእንግሊዝ ሶማሊያ ሰሜናዊ ቀበሌ ከጃሌሎ በመነሳት በራሃሌ በኩል የዳጋን ተራራ አቋርጦ በጉባድ፣ በሮሮሌ፣ በአቤ ሐይቅ፣ በሜርጋዶ፣ በአሊ ሐይቅ ዳርቻ፣ በዳይሞሌ፤ በኢታጋ በኩል አድርጎ በራሄይቶ በማለፍ ዱሜራ ይደርሳል:: እንዲሁም ስምምነት በተደረገበት ክልል ሦስተኛ ወገን ጣልቃ እንዳይገባበት እና የአሳል ሐይቅ የኢትዮጵያ መንግስት ርስት ሆኖ ኢትዮጵያ ዘላቂ ጨው የማምረት መብት እንዳለት ተረጋገጠ:: በመጋቢት 1889 ስምምነት መሠረትም ፈረንሳይ ተጨማሪ 12,000 ኪሎ ሜትር መሬት ከኢትዮጵያ አገኘች::[20]

[20] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 41-49:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3፤ የኢትዮጵያና ፈረንሳይ ስምምነት፡ መጋቢት 12፣ 1889

[21] ውጉሚ:- ጅቡቲ 52-D3 21፤ Franco-Ethiopian Boundary Commission Agreement on Djibouti Frontier: Addis Ababa, 6 May 1953፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ያቀረበው የወሰን ክለላ ሥነ ሥርዓት ንድፍ ፕሮቶኮል፡ ግንቦት 1945





በኢትዮጵያ እና በፈረንሳይ መንግሥታት የጋራ ኮሚሽን ሚያዝያ 28፣ 1945 ዓ.ም. (6 May 1953) ይፋ የሆነው የድንበር መካለል አፈፃፀም መርሐ ግብር (Procès-verbal) በአፍሪካ ቀንድ የአንድ ተጨማሪ ሉአላዊ ግዛት የመፈጠር ሂደትን በተጨባጭ ያበሰረ ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል:: ከሃምሣ ሰባት ዓመታት በፊት የተደረገው ስምምነት በግዛት ይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ የመደራደሪያ ክፍተት ቢኖረውም እንኳ የኋለኛው የኢትዮጵያን መብት አሳልፎ የሠጠና ለፈረንሳይ ሱማሌ ግዛት ዕውን መሆን ህጋዊ ሰውነትን ያላበሰ ነው::[21]




የመጋቢት 12፣ 1889 የድንበር ስምምነት ንድፍ ካርታ




የመጋቢት 12፣ 1889 የድንበር ስምምነት ንድፍ ካርታ

ከጣሊያን የአምስት ዓመታት ወረራ ነፃ ተወጥቶ ሉዐላዊ ቁመናን መልሶ ለመገንባት በሚሞክርበት፣ የመንግሥት ሁለንተናዊ መዋቅር ከገጠመው በእንግሊዝ የመታሬን አደጋ ለማምለጥ በሚንፈራገጥበት አስቸጋሪ ወቅት እና የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ጠብቆ ማቆየት የጊዜው አንገብጋቢ አጀንዳ በነበረበት ሁኔታ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የተደረጉ የድንበር ስምምነቶችን በነበሩበት ማስቀጠሉ የስኬት አካል ተደርጎ ቢወሰድ ብዙም አያጨቃጭቅም። ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ ጋር በጅቡቲ ድንበር ጉዳይ ያደረገችው የ1945ቱ ውል ከዚህ የታሪክ ዕውነታ አንፃር መታየቱ አግባብ ቢሆንም ከግዛቱ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በመነሳት ሲገመገም ግን በሂደት የታየው የባለቤትነት መብትን ለዘለቄታው አሳልፎ የመስጠቱ ሁለተኛው ምዕራፍ ተደርጎ ሊወሰድ ይቻላል።

ከዚህ በፊት ሁለቱ መንግሥታት በ1937 በድንበር ጉዳይ የመግባቢያ ፕሮቶኮል የፈረሙ ሲሆን በሰኔ 1939 ገጽ የሆነ ማስታወሻ ተለዋውጠዋል። በነኝህ ጊዜያት በተደረሱ ስምምነቶች በመጀመሪያ ከጃሌሎ (ኢትዮጵያ፣ እንግሊዝ ሱማሌ እና ፈረንሳይ ሱማሌ መገናኛ ነጥብ) እስከ ዲኮር-ኮማ ቀጥሎም ከዲኮር-ኮማ እስከ ዳዳቶ (ኢትዮጵያ፣ ጅቡቲ እና ኤርትራ መገናኛ ነጥብ) ያለው ድንበር ተከለለ። የድርድሩ ዋነኛ ነጥብ ፈረንሳይ እስከ ኤርትራ ድንበር መዳረሻ ብቻ ለመካለል ያቀረበችው አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ነበር። የመካለል ሂደቱንም የሚከታተል የጋራ ኮሚሽን ተቋቋመ።[22]

የሚያዝያ 1945ቱን ስምምነት ተከትሎ በኢትዮጵያ በኩል የታየው ለጉዳዩ አፋጣኝ ዕልባት የመስጠት ፍላጎት ከዘልማዳዊው እሳቤ በተፃራሪ ግፊቱ በተለይ የአንድ ወገን እንደነበር ያመላክታል። ለምሳሌ በወቅቱ የተላለፈ አንድ መመሪያ ከጃሌሎ እስከ ዳዳቶ ያሉትን የድንበር ምልክቶች የማስቀመጡ ተግባር ቢበዛ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ

[22] ውጉሚ፡- ኬንያ 64-D4 11፤ የ1955-56 የድንበር ጥናት ሪፖርት





እንዳለበት ሲያሳስብ፤ የተለየ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን የተቀላቀለችው ኤርትራ ከጅቡቲ ጋር የነበራት ድንበር ጣሊያን እ.ኤ.አ. በ1935 ከፈረንሳይ ጋር በተናጠል በተፈራረመችው የድንበር ውል መሠረት መቀበሉ እምብዛም ችግር እንደማያስከትል ይከራከራል።[23]

ይህም በመጀመሪያ አከባቢ የኤርትራን እና የጅቡቲን ድንበር በአዲስ መልክ ስለመካለል ኢትዮጵያ ስታራምደው የነበረውን አቋም ሙሉ በሙሉ የቀየረ ነበር። የቀደመው አቋም የድንበር መስመሩ ከዳደቶ ተነስቶ በቀጥታ መስመር ከራስ ዱሜራ በስተደቡብ በሙሉየሌ (Mouloule) ትይዩ እንዲሆን ነበር። በሂደት የተስተዋለው መለሳለስ ኤርትራን ከማስመለስ ትግሉ አንፃር የፈረንሳይን ሁለንተናዊ ድጋፍ ከስሌት በማስገባት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በተጨማሪም ጅቡቲን ለዘለቄታው የኢትዮጵያ አካል የማድረጉ እሳቤ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ተደርጎ መወሰዱም የመለሳለሱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። በተከታታይ በኢትዮጵያ ባለሥልጣናት መካከል የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች የንጉስ ነገስቱ መንግስት የድንበር መካለሉን ሥራ በአፋጣኝ ለመጨረስ የነበረውን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ ሲሆን ይህም መሆኑ ለአገሪቱ የኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚኖረው አበክረው ያስገነዝባሉ።[24]

ይልቁንም በጊዜው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ጥረት ያተኮረው አፋምቦ የተሰኘውን ስትራተጂካዊ አከባቢ ማስመለሱ ላይ ነበር። ከ1945ቱ የጋራ የድንበር ኮሚሽኑ ውል በኋላ ይህ ጉዳይ ከንጉሰ ነገሥቱ ጀምሮ ያሉትን አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ የጠየቀ አስቸኳይ ሃገራዊ አጀንዳ ሆነ። በዚህ ስምምነት መሠረት ፈረንሳይ አፋምቦን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ለመመለስ በጎ ፈቃድ ብታሳይም እስከ ጥር 1946 ድረስ ግን ተግባራዊ አላደረገችውም። ይህም በሁለቱ መንግስታት መካከል አዲስ የዲፕሎማሲ ትግልን አስከተለ።

[23] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር፡ ግንቦት 12፣ 1945፤ የሀገር አስተዳደር ሚኒስቴር ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 24፣ 1945

[24] ዝኒ ከማሁ

በንጉስ ነገስቱ ትዕዛዝ በፓሪስ ስለጉዳዩ እየተነጋገሩ የነበሩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተወልድ የላኩት ሪፖርት ስለ አጠቃላይ ሁኔታው የተሻለ ምስል ይሰጣል:: ፈረንሳይ አፋምቦን በመውረር ከጅቡቲ ግዛቷ የቀላቀለችው እ.ኤ.አ. በ1944 ሲሆን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለውዝግቡ ሠላማዊ ዕልባት ስትሻ ቆይታለች:: ሆኖም በተከታታይ በተደረጉ የድንበር መካለል ንግግሮች በሙሉ ፈረንሳይ የአፋምቦን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ከተቀረው የጋራ ወሰን ክለላ መጠናቀቅ ጋር በማቆራኘት በመያዣነት ስትገለገልበት እንደነበር ሪፖርቱ ያትታል::[25]

አክሊሉ በፓሪስ ቆይታቸው ለአሥር ዓመታት ያህል ያለመፍትሄ የዘለቀውን ችግር በሠላማዊ መንገድ ለመቅረፍ በተደረገው ጥረት የመንግሥታቸው ትዕግስት መሟጠጡን እና ካስፈለገም ኢትዮጵያ አፋምቦን በኃይል የማስመለስ አማራጭን ለመከተል እንደምትገደድ ለፈረንሳይ ባለሥልጣናት ገልፀዋል:: ይልቁንም በነኚህ ጊዜያት አገራቸው የፈረንሳይ ጥቅምና ተዕዕኖ በኢትዮጵያ እንዲስፋፋ ከመጠን ያለፈ በጎ ፍቃድ ማሳየቷን እና በተለዋጭ ኢትዮጵያ ለጠየቀችው የአፋምቦ መመለስ የፈረንሳይ ምላሽ አፍራሽ መሆኑን አብራርተዋል::

እንደ አክሊሉ መከራከሪያ ከጣሊያን ወረራ በፊት በምድር ባቡሩ ብቻ ይገለፅ የነበረው የፈረንሳይ ጥቅም ከነፃነት በኋላ በሊሴ ትምህርት ቤት፣ በፓስተር ኢንስቲትዩት፣ በአርኪዮሎጂ ጥናት ዘርፍ፣ የኢትዮጵያን የፍታሐ ብሔር ህግ በማዘጋጀት ወዘተ የተሰጣቸው የልዩ ተጠቃሚነት መብት በአፋምቦ ዙሪያ ለተነሳው ጥያቄ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጡ ያስገድዳቸዋል:: በመጨረሻም የፈረንሳይን ቸልተኝነት እና ከተፈራረሙቻቸው ውሎች ማፈግፈግ በመረጃ በማስደገፍ በማብራራት እና ስለ አፋምቦ የመንግሥታቸውን ቁርጥ አቋም በመግለፅ ፈረንሳይ በኃይል የያዘችውን ግዛት በአስቸኳይ እንድትመልስ ማሳመን ቻሉ::

[25] ውጉሜ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ አክሊሉ ሐብተወልድ ለጃንሆይ፡ እ.ኤ.አ 7 ህዳር 1953 (ጥቅምት 1946 ዓ.ም.)





የፓሪሱን ንግግር ተከትሎ ሁለቱ መንግሥታት በጥር 7፣ 1946 ዓ.ም. (16 January 1954) አዲስ አበባ ላይ በተፈራረሙት የፕሮቶኮል ስምምነት እና ባወጡት የጋራ መግለጫ ላለፉት አሥር ዓመታት ሲከናወን የነበረው የኢትዮጵያ እና ጅቡቲ የጋራ የድንበር ኮሚሽን ሥራ በስኬት መጠናቀቁን እና አፋምቦም በስድስት ሳምንታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለኢትዮጵያ እንደሚመለስ በይፋ ተገለፀ::[26] በተያያዥም ሁለቱ ተደራዳሪዎች የአጠቃላይ ድንበሩን አቀማመጥ (የኤርትራ-ጅቡቲን ድንበር ጨምሮ) ለመወሰን (delemitation) ከስምምነት ተደረሰ:: የሚመለሰውን መሬት ጉዳይ እና የድንበሩን አጠቃላይ መካለል የሚከታተል የጋራ ኮሚሽን ለማቋቋም በተወሰነውም መሠረት ኢትዮጵያ አቶ አበበ ገብረፃድቅን ሙሉ ስልጣን በመስጠት በተለይ የአፋምቦን መመለስ ጉዳይ እንዲያስፈፅሙ ሾመች::

ሁለቱም ወገኖች አፋምቦን የመረካከቢያው ቀን እሁድ የካቲት 20፣ 1946 ዓ.ም. (28 February 1954) እንዲሆን ቢስማሙም የተለያዩ እንቅፋቶች አተገባበሩን መፈታተናቸው አልቀረም:: የመጀመሪያው ተቀማጭነታቸውን በፓሪስ ያደረጉ የጅቡቲ ተወላጆች ያስነሱት ተቃውሞ ሲሆን የዚህን አሉታዊ ውጤት በመፍራት ኢትዮጵያ ያቀረበችው ከቀነ ገደቡ በፊት አፋምቦን የመረከብ ጥያቄ በፈረንሳይ ተቀባይነት ማጣቱም ለመንግሥት ባለሥልጣናት ፈታኝ ነበር:: በተለይም ፈረንሳይ ለቅኝ ግዛቶቿ በሙሉ በሰጠችው አዲስ የውስጥ አስተዳደር መብት (Loi-Cadre) በመጠቀም ሁለት ዋና የጅቡቲ ፖለቲከኞች - ሴናተር ሐሰን ጉሌድ አፕቲዶን እና የዩንየን ፍራንሴዝ ምክር ቤት አባሉ ማህሙድ ካሚል - የአከባቢው ነዋሪዎች ፍላጎት

[26] ውጉሜ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የአዲስ አበባው የፕሮቶኮል ስምምነት እና የጋራ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. 16 January 1954፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ (ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሩ (Ambassador Roux)፡ እ.ኤ.አ. 26 January 1954

ሳይጠየቅ የአፋምቦ ለኢትዮጵያ መመለስ አግባብ አይደለም በማለት ለፈራንሳይ ምክር ቤት ክስ ማቅረባቸው ጉዳዩን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር::[27]




የኢትዮጵያና ጅቡቲ ድንበር (ምንጭ፡ ውጉማ ፈረንሳይ ሶማሌ 4 8)

[27] ውጉማ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለአክሊሉ ሐብተወልድ፡ ጥር 27፣ 1946፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ ለኮሎኔል ክፍሌ እርገቱ (የአገር አስተዳደር ሚኒስትር)፡ የካቲት 18፣ 1946፤ ብላታ ዳዊት ዕቁበእግዚ ለአምና ዘለቀ (በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈፃሚ)፡ የካቲት 24፣ 1940፤ አምና ዘለቀ ለጃንሆይ፡ የካቲት 27፣ 1946





በስተመጨረሻ የኢትዮጵያ መንግስት ባሳሰበው መሠረት የፈረንሳይ ምክር ቤት ስምምነቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዲከናወን በመወሰኑ አፋምቦ እንዲመለስ ሆነ። የጋራ ኮሚሽኑ መሐንዲሶችም ከጃሊሎ እስከ ቀይ ባህር ድረስ ያለውን የኢትዮ-ጅቡቲ የድንበር ምልክቶችን ትክክለኛ አቀማመጥ (coordinates) በጥር 1948 አጠናቀቁ:: በዚህ መካከል ግን የድንበር መለያ ምልክቶቹ ዝርዝር (geodesic and topography fiches) የተጠናቀረው በአንድ ግልባጭ የነበረ መሆኑና ይህንኑ ጥቅል ሰነድ ህጋዊ የድንበር ካርታውን ለመስራት ኃላፊነት ወስዶ የነበረው የፈረንሳይ ቡድን በውሰት ወስዶት የተወሰነውን ክፍል ለኢትዮጵያ ሳይመልስ መቅረቱ የዚህ ድርድር ያልተቋጨ ክፍል ሆኖ ቀረ::[28]

## 2.3. የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ጅምር

እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ድረስ የግዛቱ ህዝብ በአስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አልነበረውም:: ከቅኝ ገዢው እገዳም ባሻገር የአፋርና ኢሳ ጎሳዎች ንቃተ ህሊና ያለመዳበሩና ፍላጎት ማጣት ለፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አለመታየት እንደምክንያት ይጠቀሳል:: ፖለቲከኞች ቢኖሩ እንኳን ከመጤዎቹ የፈረንሳይና አረብ ሰፋሪዎች የተውጣጡ ነበሩ:: ፈረንሳይ በ1938/39 (እ.ኤ.አ. 1946) የመጀመሪያውን የተወካዮች ምክር ቤት መቋቋም ስትፈቅድም ወንበሮቹን መያዝ የቻሉት እነዚሁ መጤ ፖለቲከኞች ሆኑ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በሃይት በጅቡቲ ለተከሰተው ፖለቲካዊ መነቃቃት ሁለት አካባቢያዊ ክስተቶች አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይታመናል:: እነሱም በጋማል አብዱል ናስር መሪነት በግብፅ የተነሳው አብዮት እና በአልጄሪያ ከፈረንሳይ ቅኝ ለመላቀቅ የተደረገው የረጅም ጊዜ

[28] ውጉማ፡- ጅቡቲ 52-D3 21፤ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ለወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ መጋቢት 15፣ 1948:: ከነዚህ ሰነዶች (fiches) መካከል ከምልክት 1-22 ያሉት በሃይት ለኢትዮጵያ የተመለሱ ቢሆን ከምልክት 23-89 ያሉት ግን ስለመመለሳቸው የሚገልጽ መረጃ አልተገኘም::




የኢትዮጵያና ጅቡቲ ድንበር (ምንጭ፡ ውጉሚ ፈረንሳይ ሶማሌ 4 8)

ጦርነት ናቸው። የመጀመሪያው የጅቡቲን የብሔረተኝነት ስሜት ለመቀስቀስ የረዳ ሲሆን ሁለተኛው የፈረንሳይን ቅኝ ገገርነት ማስወገድ እንደሚቻል መልዕክት አስተላለፈ። በተጨማሪም ከ1950ቹ በኋላ በእንግሊዝ እና ጣሊያን የሶማሊያ ግዛቶች የተቀጣጠለው የፓን ሶማሌ የፖለቲካ ንቅናቄ በተለይ የጅቡቲ ኢሳዎችን ለትግል ያነሳሳ ሌላኛው ኃይል ነበር። በዚህ ረገድ አፋሮቹ ተሳትፎ ዘግይቶ የመጣና የተቀናጀ አልነበረም።[29]

በሰኔ 1949 ፈረንሳይ ለቅኝ ግዛቶቿ የፈቀደችው የውስጥ አስተዳደር መብት (Loi-Cadre) ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ለረጅም ጊዜ ስታራምድ ለቆየችው የግዛት አለኝታ ጥያቄ መደናቀፍ ሁለተኛው ምክንያት ሆነ። ቀድሞ የነበረው የግዛቱ ምክር ቤት (Conseil Représentatif) ስለግዛቱ ሁኔታ የቀረቡለትን ጉዳዮች መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለአገረ ገገርው የመመለስ ድርሻ ቢኖረውም የመጨረሻውን ውሳኔ የማስተላለፉ ስልጣን ግን የባህር ማዶ ግዛቶች ሚኒስቴር (France d' outremer) ነበር። ይህ ምክር ቤት 25 አባላት የነበሩት ሲሆን ከነዚህ 12ቱ ፈረንሳዮች የተቀሩት የአገር ተወላጆች ናቸው።[30]

በአዲሱ ህግ መሠረት የተቋቋመው ምክር ቤት (Assemblie Territoriale de la C.F.S.) ግን ከቀድሞው የበለጠ

---

[29] Shehim and Searing, 211-212. Thompson and Adloff, 61-71. Saadia Touval, *Somali Nationalism* (Cambridge, 1963), 123-131; David D. Laitin, "Somali Territorial Claims in International Perspective," in *Africa Today*, Vol. 23 (April-June 1976), 29-38. Mohamed Kadamy, "Djibouti: Between War and Peace," in *Review of African Political Economy*, Vol. 23, No. 70 (Dec. 1996), 513-515. Nancy A. Shilling, "Problems of Political Development in a Ministate: The French Territory of the Afars and the Issas," in *The Journal of Developing Areas*, Vol. 7, No. 4 (Jul. 1973), 619-620.

[30] ውጉማ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለአክሊሉ ሐብተወልድ፡ ሰኔ 27 እና ሐምሌ 1፣ 1949





ሥልጣን እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን፤ ከፈረንሳዮችና ያገር ተወላጆች የሚመረጡ 30 አባላት ይኖሩታል። በተጨማሪም ከነዚሁ የምክር ቤት አባላት መሐከል ወይም ከውጭ የተውጣጡ የሚኒስትር ዓይነት ሥልጣን የሚኖራቸው ስድስት ያገር ተወላጆች ተመርጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት (Conseil du gouvernement) ያቋቁማሉ። ፈረንሳዊው አገረ ገዥም የካቢኔው ፕሬዚደንት ወደመሆን ሲሸጋገሩ ከስድስቱ መካከል አንዱ የምክትል ፕሬዚደንትነት ሥልጣን ይዞ ፕሬዝደንቱ በሌሉበት ተክተቸው ይሠራል። የዚህ ህግ መሠረታዊው ልዩነት ሁለቱ ምክር ቤቶች ጅቡቲን በተመለከተ ማናቸውንም ጉዳዮች የመወሰን ሙሉ ሥልጣን ማግኘታቸው ነው።

እ.ኤ.አ. ሰኔ 23፣ 1957 በተደረገው የምክር ቤት አባላት ምርጫ ሁለት ቡድኖች ዕጩዎቻቸውን አቀረቡ። በሐሰን ጉሌድ አፕቲዶን የሚመራው አንጃ አሥራ ሦስት ከሶማሌ እና ከደንከል ጎሳዎች የተውጣጡና አምስት ፈረንሳዊያን የሚገኙበት ተወዳዳሪዎችን ሲያቀርብ፤ በማህሙድ ሐርቢ የሚመራው ተቀናቃኝ ቡድን ደግሞ አምስት ፈረንሳዊያን፣ ሦስት አረቦች እና አሥር ሶማሌዎችን ለውድድር አሰለፈ። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአብዛኛው ታዛቢ ዘንድ የሐርቢ ፖለቲካ የጋማል አብዱል ናስርን ፓን-አረብ ፍልስፍና ወደ ግዛቱ ለማስገባት ስለሚጥር ተቀባይነት አያገኝም በሚል የማሸነፍ ቅድሚያ ግምት ለምሰራብ ዘመሙ የአፕቲዶን ቡድን ሰጥተው ነበር። ሁሉንም ባስገረመ መንገድ ግን ማህሙድ ሐርቢ ማሸነፋቸው ይፋ ሆነ።

የውስጥ አስተዳደር መብቱ ሲፈቀድ ስድስት ያገር ተወላጆች የሚኖሩት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይቋቋማል የሚለው ደንብ የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጎበት ከሠላሳው የምክር ቤት አባላት የተውጣጡ ስምንት ሚኒስትሮች ያሉት ካቢኔ እ.ኤ.አ. በሐምሌ 23፣ 1957 ተመረጠ። ማህሙድ ሐርቢ በከፍተኛ

ድምፅ የምክትል ፕሬዚደንትነቱን ቦታ ሲያገኝ አጠቃላይ የካቢኔ ተዋጽኦው ሦስት የኢሳ ጎሳ አባላትን፣ ሁለት ደንከል (አፋር)፣ አንድ ሐበራወል፣ አንድ ፈረንሳዊ እና አንድ አረብ ያካተተ ነበር። የአፋር ጎሳ ተወካዮቹ የተሰጣቸው የሥራ ድርሻ እምብዛም ወሳኝ ያልነበሩት የጤና እና የእርሻ ሚኒስትርነት መሆኑ በስብጥሩ የነበራቸውን ዝቅተኛ ሚና ያመላክታል። ከምክር ቤቱ አባላትም ስድስቱን ፈረንሳዊያን ሳይጨምር አብላጫውን ወንበር የያዙት የኢሳ፣ ሱማሌና አረብ ዝርያ ያላቸው ግለሰቦች ነበሩ። ይህ አወቃቀር በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ የሱማሌ-አረብ ጥምረትን የበላይነት የሚያንፀባርቅ ሲሆን በተለይ የኢትዮጵያን ቀጣይ የፖሊሲ አቅጣጫ ለዘለቄታው ከመቅረፅ አንፃር ትልቁን አስተዋፅኦ አበርክቷል።[31]

በጅቡቲ ይህን የመሰለ ለውጥ እየተከናወነ በነበረበት ወሳኝ ወቅት የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት ግንዛቤ ከሂደቱ ጋር የሚመጣጠን ነው ብሎ ለመገመት ያዳግታል። ከውስጥ አስተዳደር መብቱ መሰጠት እና ከምርጫው ጋር በተገናኘ የተያዘው አቋም በአጭሩ የፈረንሳይ ሶማሌ (ጅቡቲ) ራሱን ችሎ ለመተዳደር የሚችልበት ደረጃ ላይ አለመድረሱን ያትታል። ይልቁንም ፈረንሳዮች ምርጫ እንዲደረግ መፍቀዳቸው ለቅኝ አገሮቻቸው የናሽናሊዝም መንፈስ ማረጋጊያ ካቀዱት ፖሊሲ የመነጨ ስለመሆኑ ይከራከራል። በኢትዮጵያ ግምት የፈረንሳዮች ዋነኛ አጀንዳ ጎረቤት የሆነው በጣሊያን ሞግዚትነት የሚተዳደረው ሱማሌ በቅርቡሙሉ ነፃነት የሚያገኝ በመሆኑ ይህ በጅቡቲ ሊያስከትል የሚችለውን ፖለቲካዊ መነቃቃት የማለዘብ ጥረት ተደርጎ ተወስዷል።[32]

³¹ ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ለወጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ሐምሌ 25 እና ነሐሴ 16፣ 1949፤ ስለ ጅቡቲ የምክር ቤት እና የካቢኔ ምርጫ የተዘጋጀ ሪፖርት፡ ነሐሴ 29፣ 1949

³² ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ አክሊሉ ሐብተወልድ ለቆንስል ምንዳ ምካኤል፡ ሐምሌ 12፣ 1949





የተመረጡ የካቢኔ አባላትን አገር የማስተዳደር ብቃት በእጅጉ ያናናቀው የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ወቅታዊ ትንታኔ ትኩረቱን ያደረገው በጊዜው ታላቋ ሱማሌን የማቋቋም አጀንዳ በብርቱ ይቃወሙ የነበሩት የጅቡቲ ገገር (Mr. Petitbon) ወደ ፓሪስ የመጠራታቸው እና ያለመመለሳቸው ጉዳይ ላይ ነበር። በተጨማሪም እምነት ተጥሎባቸው የነበሩት ሐሰን ጉሌድ እና አጋሮቻቸው በሽንፈታቸው ማግስት ወደ ፈረንሳይ አቅንተው ያቀረቡት የተጭበረበረናልና የምርጫው ይደገም ክስ ሂደትንም መከታተል ሌላው የትኩረት አቅጣጫ ተደርጎ በስፋት የመስተናገድ ዕድል ተችሮታል። የኢትዮጵያን መፃኢ የፖሊሲ አቅጣጫ ከወሰኑ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ይህ በሱማሌ-አረብ ጥምረት እና የበላይነት ላይ እያደገ የመጣው ጥርጣሬ ነው።[33]

የማህሙድ ሐርቢ ወደ ታላቋ ሶማሊያ እና ግብፅ ያደላ የፖለቲካ መሥመር በኢትዮጵያ እና በቅኝ ገገርው የፈረንሳይ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ስጋት ማስከተሉ አልቀረም። ሁለቱ አካላት በመቀናጀት ያደረጉት እንቅስቃሴም ሐርቢን ከሥልጣኑ ማስወገድ አስቻለ። በተደጋጋሚ የተደረገበት የመግደል ሙከራ በጅቡቲ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ ከደረሰበት መገለል ጋር ተደማምሮ ግዛቱን ለቆ እንዲሰደድ አደረገው።[34] ይህም ሆኖ የሐርቢን ግቦት ተከትሎ የግዛቱን ፖለቲካ ይመሩ የነበሩት እንደነ አህመድ ዲኒ፣ ሴናተር ካሚል (አፋር)፣ አሊ አሬፍ እና ሐሰን ጉሌድ (ኢሳ) ያሉት መሪዎች በሂደት የብሔረተኝነት ስሜት ማዳበራቸው እና የጅቡቲን አፋጣኝ ነፃነት መሻታቸው አጠቃላይ የግዛቱ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ፍላጎትና ቁጥጥር እየወጣ መምጣቱን አመላካች ሆነ።

³³ ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ አክሊሉ ለቆንስል ምንዳ፡ ነሐሴ 30፣ 1949

³⁴ ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ሚካኤል (ጅቡቲ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር። በጅቡቲ ፖለቲካና በሐርቢ ፀረ-ፈረንሳይ እንቅስቃሴ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ጥር 2፣ 1951፤ ጅቡቲ ቆንስል ለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር። ሐርቢን ስለመግደል የታቀደ የኢትዮ-ፈረንሳይ ውጥን፡ መጋቢት 24፣ 1951

የወቅቱ ክስተቶች በጅቡቲ የፖለቲካ ህይወት ላይ የየራሳቸውን አሻራ ትተው አልፈዋል:: ግዛቱ የውስጥ አስተዳደር መብት ባገኘ ማግሥት ወሳኙን የሥልጣን እርከን የተቆናጠጡት የኢሳ-ሱማሌ ተወላጆች የግብፅ ውጥን አቀንቃኞች መሆናቸውና ለታላቋ ሱማሌ ውጥን ዕውን መሆን ያሳዩት በጎ ፈቃድ የዚህ ዋነኛው መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: በተለይም ምክትል ፕሬዚደንቱ ማህሙድ ሐርቢ ይህንን ለማሳካት በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በግብፅ እና በሱማሊያ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ለኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አስደንጋጭ ነበሩ:: ከሁሉም በላይ ከግብፁ መሪ ጋማል አብዱል ናስር ጋር መገናኘቱና ለዓላማው ማስፈፀሚያ የሞራል እና የገንዘብ ድጋፍ ማግኘቱ በተለየ ክትትል ውስጥ እንዲወድቅ አደረገው::[42]

በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ እየታየ የመጣው የፓን-ሱማሌ/ፓን-አረብ አመለካከት የፈረንሳይ መንግስትንም ያሳሰበ በመሆኑ ከኢትዮጵያ እሳቤ ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ እንዲከተል ተገፋፉ:: በሂደትም ሁለቱም መንግሥታት የደንከል (አፋር) ጎሳ የበላይነትን የሚያረጋግጥ መርህ በስፋት ወደማስፈፀሙ አዘነበሉ:: ፈረንሳዮች ይህን ሲያደርጉ በግዛቱ ያላቸውን የበላይነት መብት በዘለቄታው ለማስጠበቅ በማሰብ ሲሆን ኢትዮጵያ ደግሞ የታላቁ ሱማሌን እቅድ ከማክሸፍ ባሻገር ፈረንሳይ ግዛቱን ለቃ በምትሄድበት ወቅት አሳልፋ ትሰጣኛለች ከሚል እሳቤ በመነሳትም ነበር:: የሁለቱ አገራት ጥምረት እስከ መጨረሻው ቢዘልቅም ከየወቅቱ ነባራዊ ዕውነታ በመነሳት መሠረታዊ ለውጦችን አስተናግዷል::

በግዛቱ ኦፊሴላዊ ስያሜ ዙሪያ የተነሳው ውዝግብ እና ፍፃሜው የኢትዮጵያና ፈረንሳይን ጥምረት መሠረታዊ

[41] ውጉማ:- ጅቡቲ 54-D3 16፤ በጅቡቲ ጉዳይ የተደረገ የከፍተኛ ባለሥልጣናት ምክክር ቃለ ጉባኤ፡ ነሐሴ 25፣ 1956

[42] ውጉማ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ግብፅ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ሚያዝያ 8፣ 1951:: ውጉማ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ቆንስል ፍጡር አብርሃ (ታዲዝ-የመን) ለንጉሰ ነገሥቱ፡ ግንቦት 19፣ 1951፤ ፍጡር ለደልማ ደሬሳ፡ ግንቦት 20፣ 1951





መርሆዎች ከሚያመለክቱ ክስተቶች መካከል በዋነኛነት ይጠቀሳል:: ሐምሌ 1959 የተጠናቀቀውን ህዝበ ውሳኔ ተከትሎ ፈረንሳይ "የአፋርና ኢሳ ግዛት" የሚል መጠሪያ በህጋዊነት እንደምትጠቀም አስታወቀች:: ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ጅቡቲ የሚለውን ስም ብትመርጥም አዲሱ መጠሪያ የቀድሞውን "ፈረንሳይ ሱማሌ" የሚሽር በመሆኑ በፀጋ መቀበሏን ገለጸች:: የሁለቱም ዓላማ የነበረው ሶማሊያን ከጅቡቲ ጉዳይ ማግለል ሲሆን በተለይ ኢትዮጵያ ከጉዳዮ ጋር በተያያዘ የሞቃዲሾው መንግሥት ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አአድ) እና ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያቀረበውን አቤቱታ ማክሸፍ ችላለች::[43]

ይህ ማለት ግን ፈረንሳዮች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የተናጠል ጥረት አላደረጉም ማለት አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያን ፍላጎት በቀጥታ በመፃረር ሲንቀሳቀሱ ይስተዋሉ ነበር:: በተለይ በጅቡቲና በኢትዮጵያ የሚገኙትን አፋሮች በበላይነት የሚመሩትን ሱልጣን አሊሚራን ለመስበክ ያደርጉት የነበረው ጥረት ከኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ጋር ለግጭት ከዳረጋቸው አጋጣሚዎች ይመደባል:: ለምሳሌ በ1952 አጋማሽ አከባቢ የጅቡቲ ደንከል የፖለቲካ መሪዎችን ወደ ግለሰቡ ዘንድ በመላክ ከጅቡቲ ነፃነት በማግበር አፋሮችን በሙሉ ወደ አዲሱ አስተዳደር እንዲቀላቀሉ በስፋት ይሰብኩ ነበር:: በተጨማሪም በኢትዮጵያ በሚገኙት የአፋርና ኢሳ ጎሳዎች መካከል በግጦሽና በውሃ ይዞታ ሳቢያ ግጭት እንዲነሳ በስውር መንቀሳቀሳቸው በመረጃ መታወቁ ሌላው አፍራሽ ድርጊት ነበር:: ለፈረንሳዮች ማስጠንቀቂያ እንዲሆን በማለት የጎሳ ችግሩን ለመቅረፍ በሚል ሰበብ የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ጅቡቲ እንዲገቡ ተደረጉ::[44] እነኚህ አጋጣሚዎች ጅቡቲን በተመለከተ በፈረንሳይ በጎ ፈቃድ ላይ ሙሉ በሙሉ ላለመተማመን መንገድ ከፈቱ::

[43] ውጉማ:- ሱማሌ 20-D1፤ ውጉማ ፈረንሳይ ሱማሌ 5 8-1B

[44] ውጉማ:- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776–2፤ ጅቡቲ ቆንስላ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 16፣1952፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለጅቡቲ ቆንስላ፡ ሰኔ 29፣ 1952

# ምዕራፍ ፫

# የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ዳሰሳ

## 3.1. የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት

ሰኔ 1949 በጅቡቲ የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ ኢትዮጵያ በግዛቱ የወደፊት ሁኔታ ላይ የምትከተላቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በስፋት መዳሰስ ጀመረች። ከውስጥ አስተዳደር መብቱ መሰጠት ጋር በተያያዘ ወደ ሥልጣን የመጣው የሐርቢ ወገን ያራምድ የነበረው አቋም በፍፁም ተቀባይነት አልነበረውም። በምርጫው ሂደት በአንፃራዊነት የተሻለ መርህ ይከተል የነበረውን የሐሰን ጉሌድና መሐመድ ካሚል ወገን በገንዘብ ለመደገፍ ጥረት አለመደረጉም ስህተት እንደነበር ከግንዛቤ የገባው ወዲያውኑ ነበር። በግዛቱ ሊቀለበስ የማይችል የታሪክ ዑደት ቢጀመርም ያለፈውን ስህተት ለማረም ያለመ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ተግባራዊ መሆን ጀመረ። ተሸናፊው ፓርቲ ለፈረንሳይ መንግስት ያቀረበውን የምርጫ መጭበርበር ክስ ተከትሎ የንጉሰ ነገስቱ መንግስት ለጉሌድ ጥረቶች መሳካት የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግም ባሻገር በፓሪስ የሚገኘው አምባሳደር ምርጫው የሚሰረዝበትን መንገድ ፈረንሳዮች እንዲያጤኑ በተዘዋዋሪ ግፊት እንዲያደርግ ታዘዘ።[45]

በጊዜው ጥረቱ የተጠበቀውን ውጤት ባያስገኝም በተለዋጩ ግን አጋጣሚው በሐሰን ጉሌድ እና በኢትዮጵያ መካከል የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ወዳጅነት ለመመስረት አስቻለ። ፈረንሳይ ሁሉንም ቅኝ ግዛቶቿን በተመለከተ በሐምሌ 1950 እንዲደረግ የፈቀደችውን ባለ ሦስት አማራጭ ህዝበ ውሳኔ ተከትሎ በጅቡቲ የታዩ ለውጦች በኢትዮጵያና በጉሌድ መካከል የነበረውን ትስስር ይበልጥ አጠበቀ። አጠቃላይ ህዝበ ውሳኔው ቅኝ ግዛቶቹ ከፈረንሳይ ጋር በፌደሬሽን መዋሐድን፣ በሥራ ላይ ያለውን የውስጥ አስተዳደር መብት ማስቀጠል ወይንም እንደ አንድ አውራጃ መቆጠርን ይመርጡ እንደሆን ይጠይቅ ነበር። በዚህ መሐል ከፈረንሳይ እና በጉሌድ ከሚመራው ፓርቲ ፍላጎት በተቃራኒው ምክትል ፕሬዚደንቱ ሞሐመድ ሐርቢ አፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጥ ማሳሰቡ የፖለቲካ ሞትን አስከተለበት።

በህዝበ ውሳኔው ማግስት በመስከረም 1951 በተደረገው የምክር ቤት ምርጫ የሐሰን ጉሌድ ፓርቲ (Parti de defense des Interits économiques et sociaux du territoire, D.I.E.S.T) ከሠላሳ ሁለቱ ወንበር ሃያ አምስቱን ማሸነፍ ሲችል የሐርቢ ወገን ሰባት አማካሪዎችን ብቻ ማስመረጥ ቻለ። የምርጫውን ሂደት በአንክሮ ሲከታተሉ እና አስፈላጊውን የገንዘብ ድጋፍ ሲሰጡ ለነበሩት የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የተገኘው ውጤት ከበቂ በላይ ነበር። ላለፉት ሁለት ዓመታት ያህል የጅቡቲን የውስጥ ፖለቲካ ተቆጣጥረውት የነበሩ ኃይሎች ለዘለቄታው ተሰናብተው በምትካቸው የኢትዮጵያን ወዳጅነት የሚሹ ቡድኖች ወደ ስልጣን መጡ። በተከታታይ መሪዎች የነበሩት አህመድ ዲኒ እና አሊ አሬፍ (ደንከሎች) ምንም እንኳን ለጅቡቲ ነፃነትን የሚሹ ብሔረተኞች ቢሆኑም ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር የመሥራት ፍላጎትም ነበራቸው። ይህንን በዘላቂነት ማስጠበቁና በሂደትም ወደ ኢትዮጵያ የመቀላቀሉን እሳቤ እንዲቀበሉ የማሳመኑ ሥራ ቀጣዩ የቤት ሥራ ተደርጎ ተወሰደ።[46]

---

[45] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ስለጉዳዩ በከፍተኛ ባለስልጣናት የተነደፈ የድርጊት መርሐ ግብር፡ መጋቢት 25፣ 1950፤ ጋሻው ዘለቀ (ውጉሚ ምክትል ሚኒስትር) ለአምባሳደር አካለወርቅ ሐብተወልድ (ፓሪስ)፡ ሚያዝያ 17፣ 1950፤ ቆንስል ምንዳ ለ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ግንቦት 14፤ 1950

[46] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776፤ ቆንስል ምንዳ ለይልማ ደሬሳ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) - ስለ ምርጫው አጠቃላይ ሪፖርት፡ ህዳር 19፣ 1951። ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 776-2፤ ቆንስል ምንዳ ለውጉሚ - ሪፖርት በጅቡቲ የካቢኔ ምርጫ ዙርያ፡ ግንቦት ፲7፣1951

ለዘለቄታው እንዲያስከብሩ ማድረግ እና የውጭ ፖለቲካቸው ወደ ሶማሌ ኅብረት እንዳያመራ የሚያስፈልጋቸውን የቁሳቁስና የሞራል እርዳታ ለማቅረብ የኢትዮጵያን ዝግጁነት ማስገንዘብ፤ ለ) ጎን ለጎን በግዛቱ ያለውን የደንከል (አፋር) "ማይኖሪቲ" ፓርቲ በማስጠር ማጠንከር፤ ሐ) ግዛቱ ነፃ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያን ፍላጎት በግዛቱ የሚያሰርፁና የፖለቲካ አስተያየትን በተፅዕኖ ሥር ሊያውሉ የሚችሉ የንግድ ቤቶችን ማደራጀትና ለኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ማስረጫ እንዲሆኑ ማድረግ፤ መ) የኢትዮጵያ ቀዳሚ የተጠቃሚነት መብትና ማንኛውም የሃገሪቱ ጥቅም በተነካ ጊዜ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለውን የባቡር ሐዲድ አቅጣጫ ለመቀየር (divert) የሚቻል መሆኑን የጅቡቲ መሪዎች እንዲገነዘቡ ማድረግና ይህንንም ለማድረግ ጥናቱን ሶማሊያ ነፃነቷን ከማግኘቷ በፊት ማጠናቀቅ ወዘተ ናቸው።

ከዚህ የፖ.ሊ.ሰ. ውሳኔ ማጠናቀቂያ የተቀመጠው ሐሳብ በወቅቱ የነበረውን አስቸጋሪ አከባቢያዊ የፖለቲካ ምህዳር ያንፀባርቃል። መመሪያው በተለይ ያሳሰበው በሃገሪቱ ባለሥልጣናት ዘንድ የሚታመነው በጅቡቲ ያለው የደንከል የቁጥር ሳይሆን የሥልጣን "ማይኖሪቲ" ወደ ኢትዮጵያ ይጠቅለል የሚለውን አመለካከት አደገኝነት ነው። ለዚህም የተሠጠው ምክንያት በሚገኙበት ግዛት ያልተደሰቱ ነዋሪ "ማይኖሪቲዎች" ጎሳቸው የፖለቲካ ሥልጣን የበላይ (majority) ወደሆነበት ክፍል ይጠቅለሉ የሚለውን ዕንሰ ሐሳብ መቀበል በግልባጩ ሲታይ ተመልሶ ኢትዮጵያ ስለ ኦጋዴን ያላትን የራሷን ክርክር የሚያፈርስ መሆኑ ነው። እንዲያውም ይህ ሐሳብ ፈረንሳዮች በስውር የሚገፋፉትን በኢትዮጵያ የሚገኙትን የአፋርና ኢሳ ጎሳዎችን የማጋጨት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚያስችል በጥንቃቄ መታየት እንዳለበት በአንክሮ ያሳስባል።

ለአጠቃላይ ተልዕኮው አፈፃፀም ይረዳ ዘንድም ጠንካራ ቆንስል መመደብ እንደሚያስፈልግና የግዛቱን ጉዳይ በቀጣይነት መከታተል እንደሚገባ በቀረበው ሐሳብ መሠረትም በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ወሳኝ ሚና የተጫወቱት ሻለቃ ደመቀ ረታና አቶ አሰፋ ገብረ ማርያም ተከታታይ ቆንስል ሆነው ተሾሙ።





የእንግሊዝና ጣሊያን ሱማሌዎች ተዋህደው በሰኔ 1952 ነፃነታቸውን ሲቀዳጁ በጅቡቲ ግዛትም በኩል የፖለቲካ ትኩሳቱ መፋፋም ጀመረ። የኢሳና ገደቡርሲ ጎሳዎች በስደት ቻይና የሚገኘውን የሞሐመድ ሐርቢን የቀደመ አቋም በመቀስቀስ ከታላቋ ሶማሊያ የመቀላቀል ፍላጎታቸውን ሲገልፁ ደንከሎች በተቃራኒው አፋጣኝ ነፃነትን አሰበለዚያም ከኢትዮጵያ ጋር የመዋሃድ አጀንዳ ማራመድ ጀመሩ። በሂደትም የደንከል የጎሳ መሪዎችና ፖለቲከኞች በተደጋጋሚ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ተደርጎ ከንጉስ ነገስቱና ከሌሎች ባለሥልጣናት በመገናኘት ፍላጎታቸውን እና ታማኝነታቸውን ገለፁ።[49]

በዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ መሐል ግን ኢትዮጵያ ስለ ጅቡቲ የወደፊት ዕጣ ፈንታ መልስ የፈለገችው ከፈረንሳይ መንግስት ነበር። በአፍሪካ ቀንድ እየተካሄደ በነበረው ፈጣን ለውጥ ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ አጣብቂኝ ውስጥ እየገቡ የመጡት ፈረንሳዮች በጅቡቲ ለገጠማቸው ፈተና የራሳቸውን አማራጭ መፈለጋቸው አልቀረም። የካቢኔው ምክትል ፕሬዚደንት አሊ አሬፍና ሴናተር ሐሰን ጉሌድ አፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጣቸው በማሳሰብ ተደጋጋሚ ንግግር ሲያደርጉ በዝምታ መታለፋቸው ሳያንስ የፈረንሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሙሴ ሚቼል ደብሬ (Michel Debre) እ.ኤ.አ. ነሐሴ 18፣ 1960 ለአሊ አሬፍ በላኩት ቴሌግራም መንግስታቸው ለጅቡቲ ተጨማሪ የውስጥ አስተዳደር መብት የመፍቀድ ዕቅድ እንዳለው ማሳወቁ ለኢትዮጵያ ይበልጥ አሳሳቢው ጉዳይ ሆነ።[50]

---

[49] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ቆንስል ሻለቃ ደመቀ ረታ (ጅቡቲ) ለፅንዮይ እና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር - ስለ ጅቡቲ ጎሳዎች የፖለቲካ አቋም፡ መስከረም 12 እና 19፤ ጥቅምት 2 እና 3፣ 1953

[50] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚቼል ደብሬ ለምክትል ፕሬዚደንት አሊ አሬፍ፡ እ.ኤ.አ. ነሐሴ 18፣ 1960

የሚቴል ቴሌግራም ይፋ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግስት መጀመሪያ ፓሪስ በሚገኘው አምባሳደሩ ቀጥሎም በጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ በኩል ከፈረንሳይ መንግስት ማብራሪያ ጠየቀ። በሁለቱም ጊዜያት የተነሳው ዋነኛ ነጥብ ጀኔራል ቻርለስ ደጎል ለአፄ ኃይለ ሥላሴ የገቡት ፈረንሳይ ከጅቡቲ ለቃ አትወጣም ይህን ካደረገችም ግዛቱን ለኢትዮጵያ ብቻ ታስረክባለች የሚለው የተስፋ ቃል ነበር። ለዚህ ጥያቄ የፈረንሳይ መሪዎች ይፋዊ መልስ የቀደመ ቃላቸውን አለመሻራቸው ሲሆን የጠቅላይ ሚኒስትራቸው መልዕክት የጅቡቲ ሶማሌዎችን ጥያቄ ለማስታገስ ያለመ እንደነበር አስረድተዋል። ሆኖም በዚህ ያልረኩት አክሊሉ ሐብተወልድ በፓሪስ ከፈረንሳይ ባለሥልጣናት ጋር ባደረጉት ድርድር በጅቡቲ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ተጨባጭ ዋስትና እንዲሰጣቸው አጥብቀው ተከራከሩ።

ኢትዮጵያ በህዳር 1951 ስለ ምድር ባቡር ጉዳይ አዲስ ስምምነት የተፈራረመችውና በጅቡቲ ወደብ ላይም ሆነ በባቡር መስመሩ ላይ ከፍ ያለ ገንዘብ ለማውጣት የወሰነችው ግዛቱ በፈረንሳይ ይዞታነት ይቀጥላል ከሚል ግንዛቤ በመነሳት እንደነበር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ገልፀዋል። በንግግራቸው ፍፃሜም የፈረንሳይ መንግስት እየሰጠ ካለው የተስፋ ቃል ባሻገር ከኢትዮጵያ ጋር በመቀናጀት ሊያከናውናቸው የሚገቡ አጀንዳዎችን በማቅረብ ተቀባይነት እንዲያገኙ አደረጉ።

እነዚህም ሀ) በፈረንሳይ ሶማሌ በቁጥር የሚበዙት ደንከሌዎች እንደሆኑ በማስመሰል ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ በዚሁ መጠን በፓርላማው ውስጥ ተወካዮቻቸው እንዲበዙ ማድረግ፤ ለ) በጅቡቲ ያሉ ሶማሌዎችና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ጥርጣሬና ያለመግባባት ተቀርፎ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ጉዳዮች የሚቀራረቡበትና የሚስማሙበትን ዘዴ እየፈለጉ እንዲሠሩ አዲስ አበባ ላለው የፈረንሳይ አምባሳደር እና ለጅቡቲ ባለሥልጣኖች ትዕዛዝ እንዲሰጥ፤ ሐ) በጅቡቲ የሶማሌ ቁጥር ይበዛል ለማሰኘት ከቀድሞው የእንግሊዝ ሶማሌ ግዛት (ሰሜን





ሶማሊያ) ሶማሊዎች ወደ ግዛቱ በብዛት እየገቡ በመሆኑ ይህ እንዲታገድ እንዲደረግ፤ መ) በጠቅላላው ስለ ታላቋ ሶማሊና ስለ ጅቡቲ ጉዳይ በፖለቲካውና በጸጥታው ዘርፍ ሁለቱ አገሮች ተባብረው መሥራት ስላለባቸው ይህ ትዕዛዝ ለሚመለከታቸው ሃላፊዎች እንዲሰጥ ወዘተ የጋራ ስምምነት ተደረሰ።

አክሊሉ ከፕሬዚደንት ደጎል ጋር ባደረጉት ንግግርም ስለ ጅቡቲ የፈረንሳይ ፖለቲካ የተቆረጠና ዘላቂ የሆነ አመራር ካልያዘ - ኢትዮጵያም ካላወቀችው - በየጊዜው ችግር የሚፈጥርና በኢኮኖሚም በኩል መዋዕለ ንዋይ ለማፍሰስ የሚያዳግት መሆኑን ገለፁላቸው። ፕሬዚደንቱም ታላቋ ሶማሊያ የሚለውን ሐሳብ ፈረንሳይ መቼም እንደማትቀበል ከማረጋገጣቸውም ባሻገር ሃገራቸው ጅቡቲን መቼም የማትለቅ መሆኗን በድጋሚ አረጋገጡ። ይህ የፈረንሳይ ማረጋገጫ የኢትዮጵያ መንግስት በነሐሴ 1952 ያረቀቀውን የፖሊሲ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ለመተግበር የሚያስችል መሠረት ጣለ።[51]

ከሰኔ 1955 ጀምሮ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ለንጉሠ ነገሥቱ የቀረቡ ተጨማሪ ማስታወሻዎች በአፍሪካ እየተስተዋለ ከመጣው የብሔረተኝነት ስሜት እና ፈረንሳይ ከገባችበት አጣብቂኝ አንፃር ኢትዮጵያ በግዛቱ ለምታራምደው የይገባኛል ጥያቄ አፋጣኝ እልባት ማበጃት እንደሚጠበቅባት ያሳስባሉ።[52] በተለይ ግንቦት 1955 የተፈረመው የአፍሪካ መሪዎች ቃል ኪዳን ኮሎኒያሊዝምን የሚቃወምና ቅኝ ገገርዎች ከአህጉሪቱ በአፋጣኝ

---

[51] ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሶማሌ 1 778፤ አምባሳደር አካለ ወርቅ ሐብተ ወልድ (ፓሪስ) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ መስከረም 7፣ 1953፤ በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሐብተ ወልድ የፓሪስ ቆይታ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ጥቅምት 10፣ 1953

[52] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 17፤ ለግርማዊ ንጉሰ ነገስት የቀረበ ማስታወሻ፡ ሰኔ 12፣ 1955። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 18፤ ለግርማዊ ንጉስ ነገስት የቀረበ ማስታወሻ፡ ሰኔ 22፣ 1955። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 17፤ ማስታወሻ በጅቡቲ ጉዳይ፡ መስከረም 8፣ 1956

በተጠየቀው መሠረት የወቅቱ ብቸኛ አማራጩ የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር መብት የተጠናከረ ሆኖ ግን በፈረንሳይ አስተዳደር ሥር ለመቀጠል እንደሚፈልግ አስታወቀ።[54]

ከፖለቲካ ፓርቲና ከጎሳ መሪዎቹ ከተገኘው መተማመኛ በተጨማሪ ግን የደንከሉን ወገን ነጥሎ በገንዘብና በሞራል የመደገፉ አማራጭ በስፋት ተግባራዊ ተደረገ። እስከ ነሐሴ 1955 ድረስ የገንዘብ ድጋፉ በቆንስል አሰፋ እና በደንከል ተወካዮች ጣምራ ፊርማ ይከናወን ነበር። በኋላ ግን የዚህ ድርጊት መታወቅ ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ከግንዛቤ በማስገባት በጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ መመሪያ ልገሳው በሦስተኛ ወገን በኩል በስውር እንዲከናወን ተወሰነ።[55]

በኢትዮጵያ የሚገኙ አፋሮችን ታሳቢ ያደረገ መሠረተ ልማት መዘርጋት፣ በቋንቋቸው የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ማድረግ እና የጅቡቲ ፖለቲከኞችን በስብከት ወጣቶቹን ደግሞ በትምህርት ዕድል ለመሳብ ለኢትዮጵያ ጥቅሞች ታማኝ የሆነ ክፍል መፍጠር ወዘተ በተጨማሪ ከታቀዱ የድርጊት መርሐ ግብሮች መካከል ይጠቀሳሉ። ለዚህም ሲባል አፄ ኃይለ ሥላሴ በሐምሌ 1956 ለ20 ጅቡቲያውያን የነፃ ትምህርት ዕድል ፈቀዱ።[56]

ሌላው እንቅስቃሴ በጅቡቲ የደንከሎች የቁጥር የበላይነት እንዲረጋገጥና በቀጣይነት በሚደረጉ የጅቡቲ ምርጫዎች

54 ውጉሚ፡- ፈረንሳይ ሱማሌ 1 778፤ ሻለቃ ደመቀ ረታ ለጃንሆይና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ ጥቅምት 3፣ 10፣ 16፣ 17፣ 24፣ 1953፤ አምባሳደር አካለ ወርቅ (ፓሪስ) ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ከሐሰን ጉሌድ ጋር ስላደረጉት ውይይት፡ ህዳር 16፣ 1953

55 ውጉሚ፡- ጅቡቲ 19-D1 21፤ ማስታወሻ ለቆንስል አሰፋ፡ ነሐሴ 14፣ 1955

56 ውጉሚ፡- ጅቡቲ 19-D1 5፤ ውጉሚ ለጅቡቲ ቆንስላ፡ ሐምሌ 21፣ 1956



ጅቡቲ፡ የጥገኝነታችን መስፈሪያ

አብላጫውን መቀመጫ እንዲያገኙ ይረዳ ዘንድ በኢትዮጵያ የሚገኙት የአፋር ጎሳ አባላት በብዛት ወደ ግዛቱ እንዲገቡ ማድረግ ነበር። "ፕሮጀክት ኦሬንጅ" (project orange) ተብሎ የተሰየመው ይህ ፕላን ደንከሎችን በብዛት ወደ ጅቡቲ ማስረግ፣ በቋሚነት ማስፈር እና የከፊል አርሶ አደር ህይወት እንዲመሠርቱ ማድረግን ያካትታል። ይህ በተለይ የሶማሊያ መንግሥት የኢሳና ሌሎች የሶማሌ ጎሳ አባላትን ከሰሜን ሶማሊያ (ሶማሊላንድ) ወደ ጅቡቲ በማስረግ የፖለቲካ ሂደቱን በራሱ በተፅዕኖ ስር ለማዋል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ለማክሸፍ ከማሰብ የመነጨ ነበር።[57]

የዚህ ጥረት ፍሬ በህዳር 11፣ 1956 በተጠናቀቀው የጅቡቲ ምክር ቤት አባላት ምርጫ በተግባር ታየ። ኢትዮጵያ በገንዘብ የደገፈቻቸው የደንከል ፓርቲ አባላት በሙሉ ማሸነፍ የቻሉ ሲሆን 32 መቀመጫ ካለው ምክር ቤት 16ቱን ደንከሎች (አፋር) መቆጣጠራቸው ትልቅ ስኬት ተደርጎ ተወሰደ። በተለይ በይበልጥ ትኩረት ተሠጥቶት የነበረው 'Parti de L'Union Democratique Afar" የተሠኘው ፓርቲ ሙሉ በሙሉ ውጤታማ መሆኑ ባለሥልጣናቱን አስደስተ። ከተቀረው መቀመጫ ኢሳዎች፣ ሐበራወሎችና ገደቡርሲዎች በጥምረት አስራ አንዱን ሲያገኙ፤ ፈረንሳዮች አራት እና ዓረቦች አንድ ተወካይ ብቻ ማስመረጥ ቻሉ። በዚህ አጠቃላይ ስኬት መካከል የአሊ አሬፍ በድጋሚ መመረጥ ለኢትዮጵያውያኑ ብዙም የሚያሳስብ አልነበረም።[58]

በምርጫው ሂደትም የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አብሮዋቸው ይሰሩ የነበሩት ሐሰን ሐንፈሬና ኢብራሂም ሡልጣን የተባሉ የደንከል ፖለቲከኞች ከተቃዋሚዎች በመሰለፋቸው (የመጀመሪያው በመሸነፉ አኩርፎ ሁለተኛው ሃሳቡን ቀይሮ)

57 አምባሳደር ፍትጉ ታደሰ (በውጭ ጉዳይ የጅቡቲ ጥናት ቡድን አባል እና በጅቡቲ የኢትዮጵያ አምባሳደር)። Seyoum Haregot, 166.

58 ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 26፤ በጅቡቲ የምክር ቤት ምርጫ ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ህዳር 11፣ 1956። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 10፤ ቆንስል አሰፋ (ጅቡቲ) ለአቶ በፍቃዱ ታደሰ (ውጉሚ ረዳት ሚኒስትር)፡ ታህሣስ 16፣ 1956

ኢትዮጵያም እንደ ሶማሊያ ያለ የራሷን ፍላጎት ሊያስፈፅም የሚችል እና ለሚመጣው ኮሚቴ ይህንን በአግባቡ የሚያስረዳ አንድ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር መመሥረት እንዳለባት በአንክሮ አሳሰበ::[61]

በንጉሡ ትትጓችነት ስለ ጉዳዩ ለፈረንሳይ መንግስት የቀረበው የድጋፍ ጥያቄ ፈረንሳይ በማንኛውም መንገድ ለአፍሪካው ኮሚቴ ዕውቅና እንደማትሰጥና እንደማታስተናግደው በማሳወቋ ከሸፈ:: ይህንንም ተከትሎ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው ፖሊሲ የተሳሳተ እንደነበር በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ ተፈጠረ:: በአስቸኳይም ከደንከሎችና ኢሳዎች የተውጣጣ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር በድሬዳዋ እንዲቋቋም እና ለአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴ ልዑካን አቀባበል ዝግጅት እንዲጀመር ተወሰነ:: ደንከሎችን ለማስደሰት በማሰብም በኢትዮጵያ የሚገኘው የአውሳ አውራጃ ግዛት መቀመጫ ከባቲ ወደ አሳይታ እንዲዛወር ተደረገ::

በጅቡቲ ድንበር አካባቢ የሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በተመለከተ ከአሳይታ እስከ አፋምቦ ያለውን መንገድ እንዲሠራ በመከላከያ ሚኒስቴር ለምድር ጦር መሐንዲሶች ቡድን፣ የሥራና መገናኛ ሚኒስቴር የውሃ ጉድጓዶችን እንዲቆፍር፣ ትምህርት ሚኒስቴር ትምህርት ቤቶችን ለመገንባትና የአስር ደንከሌዎችንና አስር ኢሳዎችን ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያስፈፅም፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አሥር ክሊኒኮችንና አንድ ጤና ጣቢያ እንዲገነባ፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በጅቡቲ ከተማ አንድ የንግድ ማህበር እንዲያቋቁም ወዘተ ኃላፊነት ተሰጣቸው::[62] እንደሚገመተውም እነዚህ ውሳኔዎች ፈረንሳይን አላስደሰቱም::

በፈረንሳይ መንግሥት አቋም ላይ ያደረው ቀየሜታ የጅቡቲ ገገሮች ከኢትዮጵያ ወደ ግዛቱ የሚገቡ ሁሉ የፈቃድ ወረቀት እንዲኖራቸው በመደንገጋቸው ይበልጥ

[61] Belete Belachew, *Black Ethiopia: a Glimpse into African Diplomacy*. (Tsehai Publishers: Los Angeles, 2014), pp. 122-124.





ተባባሰ:: የኢትዮጵያን ፖሊሲ ከማስፈፀምም አንፃር ብርቱ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የቆዩት ቆንስል አሰፋ ገብረ ምርያም ከሥልጣን እንዲነሱ መጠየቃቸውም ሌላው እየተበላሸ ለመጣው የሁለትዮሽ ግንኙነት አመላካች ሆነ:: የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንኑ በማስመልከት ፓሪስ በሚገኘው አምባሳደሩ በኩል ያቀረበው አቤቱታ በእምቢታ መጠናቀቁን ተከትሎ ኢትዮጵያም ቆንስሏን ላለማንሳት ወሰነች::[63] ከፈረንሳይ ፈቃድና ዕውቅና ውጭ ኢትዮጵያ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን በሐምሌ 1957 ያቋቋመች ሲሆን በኤርትራ፣ በኢትዮጵያ እና በጅቡቲ ያሉ የደንከል ባላባቶችን በማማከር እና የኢሳ ጎሳ መሪዎችን በመያዝ የተ.መ.ድ. እና የአ.አ.ድ. የነፃ አውጭ ኮሚቴዎች ጉብኝትን ተከትሎ አፍጥጠው የመጡ አደጋዎችን በጊዜያዊነት መቀልበስ ተቻለ:: እነኚህ ጥረቶች በተለይ የሶማሊያን የይገባኛል ትግል ከማክሸፍ አንፃር ተጨባጭ ውጤት አስገኝተዋል::[64]

ነገር ግን ችግሩን ለመቅረፍ የተነደፈው እና የተተገበረው የኢትዮጵያ አካሄድ ከህጸፅ የፀዳ ነበር ማለት አይቻልም:: ኢትዮጵያ ለተ.መ.ድ. ኮሚቴ ለምታቀርበው ማስታወሻ ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት በተለይ በአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ ከተስተዋለው የፖሊሲ አለመጣጣም በመነሳት አፋጣኝ ማሻሻያ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ታመነበት::

[62] ውጉሚ:- ጅቡቲ 57-D3 1-B፣ በከፍተኛ ደረጃ የተደረገ የባለሥልጣናት ውይይት እና ውሳኔ ሪፖርት፡ ነሐሴ 7፣ 1956:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 57-D3 5፣ ስለ ድሬዳዋው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ግንባር አመሠራረት ለከተማ ይፍሩ የቀረበ ማስታወሻ፡ ነሐሴ 7፣ 1956፣ሻለቃ ደመቀ ረታ (ውጉሚ የጅቡቲ ጥናት ክፍል) ለከተማ ይፍሩ፡ ህዳር 8፣ 1957፣ ስለ አአድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ጉብኝት፡ ነሐሴ 30፣ 1956፣ መስከረም 7-21 እና ከጥቅምት 5-30፣1957 ያሉትን ሪፖርቶች ተመልከት:: ውጉሚ:- ጅቡቲ 55-D3 ጥራዝ 3፣ በጅቡቲ ጠረፍ ስለሚከናወኑ የመሠረተ ልማት ሥራዎች፡ ህዳር 12፣ 1957፣ ታህሣስ 13፣ 1957

[63] ውጉሚ:- ጅቡቲ 55-D3 ጥራዝ 3፣ አምባሳደር ብ. ጄነራል መኮንን ደነቀ (ፓሪስ) ለጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ፡ ህዳር 9፣ 1957፣ አምባሳደር መኮንን ደነቀ ለከተማ ይፍሩ፡ታህሣስ 13፣ 1957

የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ይመራበት የነበረው ግዛቱ ነፃ እንዲወጣና ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የሚለው አቋም በአ.አ.ድ. ኮሚቴ ተቀባይነት አለማግኘቱ ለፖ.ሊ.ሲ. ማሻሻያው አስፈላጊነት ዋነኛው ምክንያት ተደርጎ ቀረበ። የአፍሪካውያኑ እና የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች መከራከሪያ የነበረው ንቅናቄው በኢትዮጵያ የተቋቋመና የሚመራ እንጂ በጅቡቲ ሕዝብ ሃሳብና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ ነው። ይህም በንቅናቄው ተአማኒነት ዙርያ ጥርጣሬ ከማስነሳቱም በላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የድንበር ማስፋፋት ዓላማ ያለው ስለሚያስመስል መቀላቀል የሚለው ሃሳብ ለጊዜው እንዲቀር ተመከረበት። ሁለተኛው መከራከሪያ ነጥብ በጎሳ መመሳሰል ላይ የተመሠረተው ጅቡቲን የማስመለስ ጥያቄ በአጋዴን ሶማሌዎች ዙርያ ካለው ውዝግብ አንፃር ለኢትዮጵያ የማያዋጣ መሆኑ ነው።

ሦስተኛውና ዋናው ነጥብ ግን ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ያለት ቁርኝትና ይህ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ ያስከተለው መወሳሰብ ነው። የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ በአ.አ.ድ. ነፃ አውጭ ንዑስ ኮሚቴ ፊት ቀርቦ ባደረጋቸው ማብራሪያዎች ሁሉ በፈረንሳይ ላይ ምንም ዓይነት የተቃውሞ ስሜት አለማንፀባረቁ በአፍሪካውያኑ ዘንድ ትዝብትን አሳድሮ ነበር። በተለይ ነፃነትን ይፈልጉ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ

[64] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 56-D3 1፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ለማቋቋም ሲባል ለደንከል የጎሳ መሪዎች የተደረገ የገንዘብ ልገሳ፡ ሚያዝያ 28፣ 1957፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ስለማቋቋም፡ ሐምሌ 9 እና 10፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 26፤ የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄን ስለማቋቋም የቀረበ ፕላን፡ ግንቦት 18፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 51-D3 4፤ ስለ ተመድ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ልዑካን አቀባበል፡ ሰኔ 4፣ 1957። ውጉሚ፦ ሶማሌ 15-D1 1፤ የሶማሊያን ውጥን ስለማክሸፍ፡ ሰኔ 9፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ ሪፖርት 10 824-1፤ የአፋር ባላባቶችን ስለማሳመን፡ ሰኔ 19፣ 1957። ውጉሚ፦ ጅቡቲ 56-D3 8፤ በተመድ ኮሚቴ ጉብኝት ዙሪያ የቀረበ ሪፖርት፡ ሰኔ 3፣ 1958። Belete, p. 124-125.





የንቅናቄው መሪ አህመድ ቡርሃን እንዲሰጡ የተመከሩት "አዎ ነፃነት እንፈልጋለን፣ ነገር ግን የኢኮኖሚያችን ዋስትናም እንዲረጋገጥልን እንፈልጋለን" የሚለው አካሄድ ደካማነታቸውን እና ጥገኝነታቸውን አጉልቶ አሳየ። በዚህ መንገድ መቀጠሉ የሚያስከትለውን አደጋ የተገነዘቡት የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች አፋጣኝ የፖ.ሊ.ሲ. ማሻሻያ ይደረግ ዘንድ መወትወቱን ገፉበት። የኢትዮጵያን እና የፈረንሳይን ግንኙነት የሚነካ ቢሆንም እንኳን ንቅናቄው ለወደፊቱ የፈረንሳይ ቅኝ ገገርነትን ተቃዋሚነቱን የሚገልፅበት መንገድ መቀየስ እንዳለበት ተመከረ።[65]

ከዚህ ጋር በተያያዘ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ከተማ ይፍሩ ሰኔ 1፣ 1958 ስለ ጅቡቲ ጠቅላላ ሁኔታ በኒውዮርክ ለተ.መ.ድ. የቅኝ ግዛት አስወጋጅ ኮሚቴ የሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ ያላትን የማይናወፅ የባለቤትነት ጥያቄ ያንፀባረቀ ነበር። በደምሳሳው የአውሮፓውያንን ቅኝ ገገርነትን የኮነነው ማብራሪያ የፈረንሳይ በጅቡቲ መገኘት ኢትዮጵያን የጎዳ እና ከታሪካዊ የግዛት ድንበሯ የለየ መሆኑን መረጃ በመጥቀስ ይተነትናል። ይልቁንም ፈረንሳዮች ከመምጣታቸው በፊት ጅቡቲ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ክልል እንደነበረ፣ የግዛቱ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ከታላቁ የስምጥ ሸለቆና ከአዋሽ ተፋሰስ ጋር የተቆራኘ መሆኑ የኢትዮጵያ አካል መሆኑን እንደሚያመላክት፣ ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕውነታ አንፃር ጅቡቲ በኢትዮጵያ ላይ ጥገኛ መሆኑን እና ከዘመናዊው ዓለም የንግድ ግንኙነት መርህ አኳያም የኢትዮጵያን ምሥራቃዊ፣ መካከለኛና ደቡባዊ ክፍል ከተቀረው ዓለም የሚያስተሳስረው ዋነኛ ወደብ መገኛ መሆኑ ወዘተ ለሃገሪቱ የግዛት አለኝታ ጥያቄ እንደ መከራከሪያ ሆነው የቀረቡ ምክንያቶች ነበሩ።[66]

[65] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 52-D3 26፤ በጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ዙርያ የፖ.ሊ.ሲ. ወረቀት፡ ግንቦት 18፣ 1957

[66] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 57-D3 8፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከተማ ይፍሩ ንግግር፡ ሰኔ 1፣ 1958

ጄኔራል ቻርለስ ደጎል በነሐሴ 1958 ጅቡቲና ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት የተከሰቱት ኩነቶች ይህንን ሁሉ ውዥንብር ይፋ አወጡ:: የግዛቱንም መፃኢ ዕድል ለዘለቄታው የወሰነ ክስተት ፈጠሩ:: የፕሬዚደንቱ ጉብኝት ይፋ ከሆነበት ከሐምሌ 1958 ጀምሮ በሁለት ጎራ በመከፈል የኢሳው ወገን ለግዛቱ በአፋጣኝ ነፃነት እንዲሰጥ ሲጠይቅ ደንከሉ ደግሞ በአሊ አሬፍ የሚመራውን የውስጥ አስተዳደር በመደገፍ አሁን ያለው ሥርዓት ለተወሰነ ጊዜ እንዲቀጥል መወትወት ጀመረ:: የነዚህ ህዝባዊ ጥቅናቄዎች መጀመር ከግዛቱ መፃኢ ዕድል አንፃር ለኢትዮጵያ ባለስልጣናት አሳሳቢ ሆነ:: ሆኖም ከቆንስላው ጽ/ቤት የጅቡቲ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በገንዘብ ኃይል በመደለል በደጎል ጉብኝት ወቅት የኢትዮጵያን ፍላጎት በሚያንፀባርቅ መልኩ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ የቀረበው ሃሳብ ተቀባይነት አላገኘም::[67]

ፕሬዚደንት ደጎል ጅቡቲ ሲደርሱ የገጠማቸው ህዝባዊ ተቃውሞና የነፃነት ጥያቄ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉንም ያስደነገጠ ነበር:: በኢሳዎች መሪነት የተቀነባበረው ሠልፍ ከቁጥጥር ውጭ በመሆኑ የህይወት መጥፋት እና ከፍተኛ የንብረት ውድመት አስከተለ:: ፖለቲካዊ ትኩሳቱ ያሳሰባቸው የፈረንሳዩ መሪና የጅቡቲ ገዥ ለተሰበሰበው ህዝብ የጠየቀው ነፃነት በአፋጣኝ እንደሚፈፀምለት ቃል መግባታቸው ሌላ የታሪክ ምዕራፍ ከፈተ:: ቀጥሎም ጄኔራል ደጎል በተገኙበት

[67] ውጉሚ፦ ጅቡቲ ሪፖርት 10 825፤ ቆንስል ቀኛዝማች አስፋው ሀብተ ማርያም (ጅቡቲ) ለከተማ ይፍሩ፤ ዶ/ር ተስፋዬ ገብረግዚ (ውጉሚ ደኤታ) ለቆንስል ቀኛዝማች አስፋው፡ ሐምሌ 18 እና 25፣ 1958፤ ቆንስል ቀኛዝማች አስፋው ለውጉሚ፡ ነሐሴ 17፣ 1958፤ በጄኔራል ደጎል የጅቡቲ ጉብኝት ወቅት ስለተከሰተው ረብሽ ሪፖርት፡ ጳጉሜ 4፣ 1958. I.M. Lewis and Harold G. Marcus, "After the Referendum: Prospects in the Horn", Africa Report (April 1967), 37-41. I.M. Lewis, "The Referendum in French Somaliland", *The World Today* (July 1967), 308-314. Shehim and Searing, 214-214.





የፈረንሳይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 11፣ 1959 ባደረገው ስብሰባ የጅቡቲ ህዝብ እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 1፣ 1967 በፊት በሪፈረንደም የሚስማማውን አስተዳደር ይመርጥ ዘንድ ውሳኔ አስተላለፈ:: በስተመጨረሻም ህዝበ-ውሳኔው መጋቢት 10፣ 1959 እንዲደረግ ቀን ቀጠሮ ተያዘለት:: ይህንንም ተከትሎ ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች በጅቡቲ እና በተለይም በሶማሊያ ተበራከቱ::



የጅቡቲ ህዝብ ነፃነት ለመጠየቅ ካደረጋቸው ሰልፎች አንዱ[68]

[68] "New Trouble for French Colony on Red Sea", *MERIP Reports*, No. 45 (March 1976), 23.



የጅቡቲ ህዝብ ነፃነት ለመጠየቅ ካደረጋቸው ሰልፎች አንዱ[68]

ክስተቱ የንጉሰ ነገስቱ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አገሪቱ ጅቡቲን በተመለከተ ስለምትከተለው ፖሊሲ የተብራራ የውሳኔ መግለጫ እንዲሰጥ አስገደደ። አንደኛው የውሳኔው ፍሬ ነገር ኢትዮጵያ በጅቡቲ ጉዳይ ትክክለኛ የሆነ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መርህ (self determination) የማትቃወም መሆንዋን ማሳወቅ ነበር። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ጅቡቲ በኢኮኖሚ፣ በሶሻል፣ በፖለቲካና በተለይም በእስትራቴጂ (በጂኦግራፊ አቀማመጥ) ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረና ያለ ኢትዮጵያ ለመኖር የማይችል እንዲሁም ለሃገሪቱ ዋነኛው የመከላከያ በር ስለሆነ የግዛቱ የወደፊት ዕድል በሰልፍ ዲተርሚኔሽንም ሆነ በሌላ ረገድ ሲወሰን እነኚህን ዕውነታዎች መሠረት ማድረግ እንዳለበት ያሳስባል። ይህንን መሠረት የማያደርግ ማንኛውንም ውሳኔ ግን ኢትዮጵያ በምንም አኳኋን የማትቀበል መሆኗን በማያወላውል ሁኔታ ገለፀ።

በወቅቱ በተ.መ.ድ. ለኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን የተላለፈው መመሪያ በጥቅሉ የጅቡቲን የራስን ዕድዕ በራስ የመወሰን መብት ሳይቃወሙ ከላይ የተመለከተውን ኢትዮጵያ በግዛቱ ላይ ያላትን አቋም መሠረት በማድረግ እንደ ጉዳዩ አመጣጥ ለመከላከልና ለማስረዳት እንዲሞክሩ ነበር።[69]

የፈረንሳይ መንግስት በጅቡቲ ህዝበ-ውሳኔ ለማድረግ ቁርጠኛ አቋም መያዙ እንደተረጋገጠ በኢትዮጵያ በኩል ሂደቱን ለመቆጣጠርና ከሃገሪቱ ብሔራዊ ጥቅም አንፃር ለማስኬድ እንዲቻል ጠንካራ የድርጊት መርሐ-ግብር ተነድፎ እንቅስቃሴ ተጀመረ። መጀመሪያ በጅቡቲ ጉዳይ ፖሊሲ ለማውጣትና በፖለቲካውም አመራር ረገድ ሊፈጠር የሚችለውን ለውጥ እየመረመረ ውሳኔ የሚሰጥ በጸሐፊ ትእዛዝ እክሊሉ ሐብተ ወልድ የሚመራና የተመረጡ ሚኒስትሮች በአባልነት የሚገኙበት አንድ የበላይ ኮሚቴ ተቋቋመ። የበላይ አካሉን ማሳሰቢያ ተከትሎም ንጉሠ ነገሥቱ መስከረም 6፣ 1959 ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ጋዜጠኞች ኢትዮጵያ ስለጅቡቲ የወደፊት ዕድል ያላትን ፖሊሲ ገለፁ።





ንጉሰ ነገስቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጡት ኦፊሴላዊ መግለጫ "የፈረንሳይ ሱማሌ" በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኮሎኒያሊስቶች ከመያዙ በፊት የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበር፤ ግዛቱ በኢኮኖሚ፣ በህዝብና በጂኦግራፊ ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረና ያለኢትዮጵያ ለመኖር የማይችል መሆኑን፤ የጅቡቲ ወደብ ለኢትዮጵያ ዋና የንግድ በር መሆኑን ያትታል። በተጨማሪም ኢሳና አፋል የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነገዶች በብዛት የሚገኙት በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ በጅቡቲ የሚኖሩት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው እነዚሁ ጎሳዎች ተቆራርጠው ወደሌላ እንዲሆኑ ኢትዮጵያ የማትፈቅድ መሆንዋን፤ የጅቡቲን ሕዝበ-ውሳኔ ሃገራቸው ስትደግፍ የግዛቱ ህዝብ ለራሱ ጠቃሚ ባልሆነ በተቃራኒ መንገድ እንደማይጎዝ በማመን እና ከኢትዮጵያም እንዳይለይ ለማድረግ ማንኛውንም እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ሃሳብ እንዳላት በአጽንኦት ያወሳል። እንዲሁም ጅቡቲን በሚመለከት ወደፊት የሚሰጡ ማናቸውም ውሳኔ ከላይ ከተመለከቱት ዋና ዋና ሁኔታዎች ጋር የማይያያዝና ግዛቱን ከኢትዮጵያ የሚነጥል ከሆነ መንግስታቸው በምንም አይነት እንደማይቀበለው አሳውቀዋል።[70]

ይህንን ከፍተኛ የፖሊሲ መመሪያ ተከትሎ ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ተግባር ላይ መዋል ጀመሩ። በጥቅምት 1959 የጅቡቲን ህዝብ ባህልና የፖለቲካ ጠባይ የሚያውቁ እና የመንግስታቸውን ፖሊሲ ተከትለው ለመስራት ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ግለሰቦች ቁልፍ የሥራ ኃላፊነት ተሰጣቸው። በዚህም መሠረት አቶ አሐዱ ሳቡሬ ከሞቃዲሾ ተዛውረው በአምባሳደርነት ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል ጀኔራል ሆኑ። እንዲሁም

---

[69] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 4፤ ከተማ ይፍሩ ለልጅ እንዳልካቸው መኮንን (ኒውዮርክ) - በጅቡቲ ዙርያ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ዘዋሪ መመሪያ፡ ጳጉሜ 4፣ 1958። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 55-D3 3፤ ጅቡቲ ለኢትዮጵያ በምትሰጠው ጠቀሜታ ዙሪያ የተዘጋጀ ማስታወሻ፡ ጳጉሜ 5፣ 1958

[70] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 20፤ የንጉሰ ነገስቱ የፖሊሲ ንግግር፡ መስከረም 6፣ 1959፤ በጅቡቲ ጉዳይ ከፍተኛ የፖሊሲ ውሳኔዎች፡ ህዳር 24፣ 1959. Seyoum Haregot, 170-173.

ቀድሞ በጅቡቲ ቆንስል የነበሩት ሻለቃ ደመቀ ረታ የአዳልና ኢሳ አውራጃ ገገር፤ አቶ አሰፋ ገብረማርያም የድሬዳዋ አውራጃ ገገር ተደርገው ሲሾሙ ፊታውራሪ አስጋኸኝ አርዓያ የአውሳ አውራጃን አቶ አሰፋ ድፋዬ የአሰብ አውራጃን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ።

እነኚህ ግለሰቦች ሀገራቸው በጅቡቲ ላይ ያላትን ፖሊሲ ተከትለው የፖለቲካ ዘመቻውን በቀጥታ እንዲመሩና እንዲያስፈፅሙ አደራ ተጣለባቸው። ከፍተኛው የፖሊሲ መመሪያ በሁለት መንገድ - በፅሑፍና በቃል ትዕዛዝ - የተላለፈ ሲሆን ሁለቱም ዓይነት መመሪያ በጥብቅ ሚስጥር ደረጃ የተያዘ ነበር። የአውራጃ ገገሮቹ በተለይ የጅቡቲ ህዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ተዋህዶ ለመተዳደር ፈቃደኝነቱን ሊገልፅ በሚችልበት ሁኔታ፣ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዝንባሌና ስሜት እንዲሠርፅበት ለማድረግ እና የግዛቱ ህዝብ በምንም መንገድ ከሶማሊያ ጋር ለመዋሃድ ምኞት ወይም ፍላጎት እንዳያድርበት በተገኘው ዘዴና ስብከት ለመከላከል ያቀደ የሥራ ድርሻ ተሰጣቸው። ቆንስሉ ደግሞ ለፈረንሳይ ባለሥልጣኖች የሚታይ ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት ሳያደርግ በግዛቱ ከሚገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ስውር ግንኙነት የመፍጠርና በሂደቱም የኢትዮጵያ እጅ በጅቡቲ ውስጥ እንዲሠርግ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጣለበት።[71]

የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄንም በተመለከተ የተላለፈው መመሪያ ድርጅቱን በማደርጀት ኢትዮጵያ ለግዛቱ ነፃነት ያላትን ምኞት ለዓለም ማሳወቂያ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ እንዲሆን ነው። በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ አቋም እንደሚያመለክተው የዚህን ንቅንቄ መቋቋም ፈረንሳዮች ቀደም ብለው የሚያውቁት ስለሆነ በሁለቱ አገሮች መካከል አለመግባባት ይፈጥራል ተብሎ አልተገመተም። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ኢትዮጵያ በአ.አ.ድ. ቃል ኪዳን አባልነቷና ካላት ልዩ ተሰሚነት የተነሳ ይህን ድርጅት ከነዓላማው ከመደገፍ ቸል ለማለት እንደማትችል ፈረንሳዮችን ማስገንዘብ እንደሚያሻ ተመልክቷል። በሌላ በኩል ደግሞ

[71] ዝኒ ከማሁ





ሶማሊያና አጋሮቿ ኢትዮጵያ ኮሎኒያሊስት ከሆነው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር በመሻረክ ጅቡቲ በፈረንሳይ አስተዳደር ውስጥ እንዲቆይ ትገፋፋለች ተብሎ የሚነገረውን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለመቃረን ንቅናቄውን በፖለቲካ መሣሪያነት መጠቀሚያ ማድረግ እንደሚያሻ ተብራርቷል።

የጅቡቲን ህዝበ-ውሳኔ አስመልክቶ ለነኚህ አስፈፃሚ አካላት በቃል የተላለፈው ትዕዛዝ የግዛቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በተመለከተ የኢትዮጵያን ትክክለኛ አቋም ያንፀባርቃል። የፈረንሳይ መንግሥት ለጅቡቲ የሰጠው የምርጫ ዕድል በሁለት አቅጣጫ ብቻ የተመራና የተወሰነ መሆኑን የፖሊሲ መመሪያው ያትታል። ይህም በመሆኑ ህዝቡ የወደፊት ዕድሉን ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ጋር ለማስተሳሰር እንዲያስችለው ሐሳቡን የሚገልፅበት አማራጭ እንዳልተሰጠው በአፅንዖት ያወሳል። ስለዚህም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል የጅቡቲ ህዝብ ለራሱ ዘላቂ ጥቅምና ለኢትዮጵያ ዓላማ የሚበጅ መንገድ እንዲመርጥ በመምራትና በመገፋፋት የግዛቱን በሂደት ከኢትዮጵያ ጋር መዋሃድ በሚያረጋግጥ መልኩ መሆን እንዳለበት ያሳስባል።

ይህንን ዕቅድ ለማሳካት በመጪው መጋቢት በጅቡቲ ከሚደረገው ሪፈረንደም ጋር በተያያዘ ኢትዮጵያ ሁለት የፖለቲካ ስምሪት ምርጫ እንደሚጠብቃት ታመነበት። አንደኛው የጅቡቲ ህዝብ በፈረንሳይ ጥበቃ ሥር መተዳደሩን ነቅፎ የተሟላ ነፃነት እንዲጠይቅ በመገፋፋት ከነፃነት በኋላ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የፖለቲካ ዘመቻ ማድረግ ነው። ይህን አማራጭ መከተሉ በራሱ የሚያስከትለው መዘዝ አለ። በመጀመሪያ ደረጃ ትግሉ ከሶማሊያ ሪፐብሊክ ጋር ብቻ መሆኑ ይቀርና ኢትዮጵያን ሲደግፍ ከነበረውና በጅቡቲ ለመቆየት ዕኑ ፍላጎት ካለው ከፈረንሳይ መንግሥት ጋርም ይሆናል። በሁለት ግንባር የሚደረገው ዘመቻ በሰው ኃይልና በገንዘብ ከሚያስከትለው ጉዳት በተጨማሪ የጅቡቲ ህዝብ በኢትዮጵያ፣ በሶማሊያና በፈረንሳይ ዝንባሌ ለሦስትዮሽ ሲከፋፈል የኢትዮጵያ ደጋፊ ሆነው የሚገኙት ክፍሎች መጠናቸው ይቀንሳል። በዚህም የተነሳ በሠላማዊ መንገድ ጅቡቲን የማስመለሱ ጥረት እንቅፋት ያጋጥመዋል።

በሌላ በኩል በሪፈረንደሙ ማግስት ጅቡቲ ነፃ ቢሆን ደግሞ ኢትዮጵያ ተፈላጊነቷንና ተወዳጅነቷን በህዝቡ ዘንድ በአስተማማኝ መንገድ ማስረፅ ከመቻሏ በፊት ይሆናል። ስለዚህም ፈረንሳይ ግዛቱን ለቃ በምትሄድበት ወቅት በሚፈጠረው ክፍተት (vacume) ምክንያት ኢትዮጵያ በቂ የመደራጃ ጊዜ ሳታገኝ አሉታዊ ገፅታ ሊኖረው የሚችል ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ ትገደዳለች። ይህ አካሄድ አገሪቱን በወራሪነት በማስፈረጅ ለተ.መ.ድ. እና አ.አ.ድ. ውግዘት ሊያጋልጣት ከመቻሉም በላይ በዓለም መድረክ ያላትን ክብር ሊያጎድፈው እንደሚችል ተገመተ።

ሁለተኛው አማራጭ የጅቡቲ ህዝብ ለነፃነቱ በቂ ጊዜና ዝግጅት እስኪያገኝ ላልተወሰነ ጊዜ በፈረንሳይ ጥበቃ ሥር መተዳደሩን እንዲመርጥ ውስጥ ውስጡን መገፋፋት ነው። ይህ ዕውን ከሆነ እስከ ነፃነት ባሉት ዓመታት ኢትዮጵያ የህዝቡን ድጋፍና ዝንባሌ በሚያስተማምን አኳኋን ለማግኘት የሚያስችላትን የረጅም ጊዜ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘመቻዋን አጣምራ ለማቀድና ለማስረግ ዕድል ይኖራታል። የዚህ አማራጭ ሌላኛው በጎ ገፅታ ተደርጎ የተወሰደው ከፈረንሳይ ጋር ያለውን ወዳጅነት ማስጠበቅ መቻሉ እና ህዝቡ ከኢትዮጵያ ለመዋሃድ ባይፈልግ ሊወሰድ ለሚገባው ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት የመዘጋጃ በቂ ጊዜ መስጠቱ ነው። በመጨረሻም ሁለተኛውን አማራጭ በመከተል ኢትዮጵያ የጅቡቲ ህዝብ በሪፈረንደሙ የተሟላ ነፃነቱን መጠየቁን በይፋ ሳትቃወምም ሳታደፋፍርም ግን በፈረንሳይ አስተዳደር ሥር መቆየቱን እንዲመርጥ እንድትገፋፋ የፖ'ሊሲ ውሳኔ ተላለፈ።[72]

የኢትዮጵያንየፖ'ለቲካ ዘመቻ በቀዳሚነት እንዲያስተባብርና እንዲመራ ኃላፊነት የተጣለበት ኮሚቴ (የጅቡቲው ቆንስልና አራቱ የአውራጃ አስተዳዳሪዎች የሚገኙበት) ከህዳር 29 እስከ ታህሣሥ 5፣ 1959 ባደረገው የፖ'ሊሲ ግምገማ ከላይ የተሠጠውን መመሪያ በብርቱ ተቃወመ። በተለይም የቀደመው

[72] ዝኒ ከማሁ





ውሳኔ የተመሠረተበትን በጅቡቲ ህዝብ ዘንድ ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት የለም፣ የግዛቱ ተቀዳሚ ምርጫም ከሶማሊያ ሪፐብሊክ መቀላቀል ወይም ነፃነት ነው የሚለውን እሳቤ ትክክለኛ እንዳልነበር በመረጃ በማስደገፍ አመላከተ። ይልቁንም የፈረንሳይ በግዛቱ ለተወሰኑ ዓመታት መቆየት ለኢትዮጵያ የመዘጋጃ ጊዜ ይሰጣታል የሚለውን እሳቤ በብርቱ አጣጣለ። በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአፍሪካና በተቀረው ዓለም ሊፈጠር ከሚችለው የፖ'ለቲካ መለዋወጥ አንፃር ይህንን ማስፈፀሙ እንደታሰበው ቀላል ሊሆን እንደማይችል በአፅንዖት ለመከራከር ተሞከረ። ለአገሪቱ የሚበጀትም እስከ ሪፈረንደሙ ያሉትን ወራት በመጠቀም የጅቡቲ ህዝብ ነፃነቱን እንዲያገኝ መጣርና በተከታይም ከኢትዮጵያ መዋሃዱን እንዲተገብር መሥራት መሆኑን ተከራከረ።[73] ይህ ሐሳብ በከፍተኛ ባለሥልጣናት ዘንድ ተቀባይነት ቢያጣም በኋላ እንደታየው ትክክል ነበር።

ንጉሰ ነገሥቱ በተገኙበት ጥር 25 የተደረገው ከፍተኛ የፖ'ሊሲ ስብሰባ በቀደመው አካሄድ እንዲቀጠል ከመወሰኑም በላይ በአተገባበሩ ላይ ተጨማሪ መመሪያዎችን አሳለፈ። ለኢትዮጵያ ዕቅድ ቁልፍ የሆኑት አዳሎች (አፋሮች) ለዚሁ ሲባል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጣቸው። በምክትል ፕሬዚደንቱ መሐመድ ካሚል መሐመድ እና በቀድሞው ምክትል ፕሬዚደንት ዓሊ አሬፍ ቡርሃን መሪነት ለሁለት ተከፍለው ሲታመሱ የነበሩት የጅቡቲ አፋሮች በጎሳው መሪዎች አማካኝነት እንዲታረቁና የጋራ ግንባር እንዲፈጥሩ ተወሰነ። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ አፄ ኃይለ ሥላሴ የራሂታውን ሱልጣን ደጃዝማች ዳውድን እና የአውሳውን ፊታውራሪ ያዩን አስጠርተው እንዲያናግሩ፤ እንዲሁም ቆንስል አሊዱ ሳቡሬ በጅቡቲ ያሉትን የጎባድ፣ የኦቦክና የታጁራ ሱልጣኖች እንዲያስተባብሩ ኃላፊነት ተሰጣቸው።

ከዚህም በላይ የጅቡቲ አፋሮች ውድድሩን ለመቋቋምና ብሎም ለማሸነፍ እንዲችሉ የ200,000 ብር ድጋፍ ተደረገላቸው።

[73] ውጉሚ፦ ጅቡቲ 55-D3፤ የፖ'ሊሲ ወጁይትና የውሳኔ ሐሳብ፡ ታህሳሥ 12፣ 1959

ዕቅድ ተስማሚ አልነበረም። ከሪፈረንደሙ ማግሥት በተደረገ የፖ.ሊ.ሰ. ውይይት ላይ ይህ ጉዳይ በስፋት አከራክሮ ነበር። ከተወሰኑ ክፍሎች የተነሳው ነጥብ በአንድ በኩል የሶማሌዎችን የብሔረተኝነት ስሜት ለማድከም እየተጣረ በሌላ በኩል አፋሮችን ብቻ በማጎልመስ ሂደት ውስጥ ወደፊት ሊያውክ የሚችል የአፋር ናሽናሊዝም (bloc Afar) እንዳይፈጠር ነው።

የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ያስጀመሩት በጅቡቲ አፋሮችና ስሜታቸውና ዓላማቸው በትክክል በማይታወቀው ደጃዝማች ዓሊ ሚራህ መካከል የተጀመረው የትብብር ንግግር ከህዝበ-ውሳኔውም በኋላ መቀጠሉ አደገኛ መሆኑ ተወስቷል። ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት ቀድሞ ተግባራዊ ሆኖ የነበረውን ኢሳዎችን የመነጠሉ ፖለቲካ በፍጥነት እንዲቋረጥና በተለይ የኢሳ ህዝባዊ ንቅናቄ ፓርቲ (movement popular) ከሶማሊያ ጋር የመሠረተውን ጠንካራ ግንኙነት ለመስበር ጥረት እንዲደረግ ተወሰነ።

ሌላኛው ውሳኔ የሚያሻው ጉዳይ በድሬዳዋና በአሳይታ መቀመጫውን ያደረገው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ጉዳይ ነበር። አሁንም የተደረሰው መግባባት ንቅናቄው ተግባሩን እንዲቀጥል የማድረግና ይህን ለማድረግ የተፈለገበትን ምክንያት ለፈረንሳይ መንግሥት በቅድሚያ የማሳወቁ አስፈላጊነት ነው። ስለ ሪፈረንደሙም ቢሆን ከአፍሪካ ነፃ አውጭ ኮሚቴ ለንቅናቄው ጥያቄ በሚቀርብለት ወቅት ውጤቱን ሳይነቅፍ በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ አንድ እመርታ መሆኑን እንዲያስረዳ ተወሰነ። በተጨማሪም ንቅናቄው ዓላማው ጅቡቲ ራስዋን ችላ ነፃ እንድትወጣ እንደሆነ እንዲያስረዳ ቢጠየቅ ደግሞ ራስን ችሎ ለመኖርም ሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል ወደፊት ተጨማሪ ህዝበ-ውሳኔ መደረግ እንደሚኖርበት ማስታወቅ እንደሚኖርበት ተወሰነ።[77]

[77] ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሰ. ውሳኔ፡ ሰኔ 20፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 2፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሲ ውሳኔ፡ ሚያዝያ 30 እና ሰኔ 30፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 57-D3 3፤ በጅቡቲ ጉዳይ የፖ.ሊ.ሰ. ጥናት፡ ሐምሌ 17፣ 1959





ነገር ግን ህዝበ-ውሳኔው ሶማሊያን ጨምሮ ከአፍሪካውያን እና ከተቀረው ዓለም የገጠመው ተቃውሞ ከሚጠበቀው በላይ ጠንካራ ነበር። ገለልተኛ የውጭ ታዛቢዎች ሂደቱን አለመታዘባቸው፣ ውጤቱ በዋነኛነት የጎሳ ልዩነትን የተከተለ መሆኑ፣ የግዛቱ የነፃነት ጥያቄ በቀይታ መያዙ ወዘተ የተቃውሞው መሠረቶች ነበሩ። ከአሥሩ አንዱ የአ.አ.ድ. የነፃ አወጭ ኮሚቴ አባላት ስድስቱ ሪፈረንደሙን አወገዙ። በተጨማሪም በድሬዳዋ ያለው የጅቡቲ ንቅናቄ ውጤቱን በመቀበሉ በአ.አ.ድ. እንዲወገዝና ከድርጅቱ የሚያገኘው የገንዘብ እርዳታ እንዲቋረጥበት ማሳሰባቸው ለኢትዮጵያ ባለሥልጣናት አሳሳቢ ነበር።

የተ.መ.ድ. ነፃ አውጭ ኮሚቴም በጉዳዩ ላይ ሊሰጥ የሚችለው አሉታዊ መግለጫ ኢትዮጵያውያኑን ስላሳሰባቸው በሪፈረንደሙ ውጤት ዙሪያ በተ.መ.ድ. ስብሰባዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት እንዲቆጠቡ አስገደዳቸው። በተለይ የራስን ዕድል በራስ ከመወሰን መርህ አንፃር በጅቡቲ የተከናወነው ምርጫ ውጤት አጠራጣሪነት፣ የተ.መ.ድ. ታዛቢዎች በሂደቱ ያለመሳተፍ ወይም በሪፈረንደሙ ዋዜማ ሶማሌ የሆኑ የግዛቱ ነዋሪዎች እንዲባረሩ ስለመደረጋቸው ንግግር መደረጉን ኢትዮጵያ አልፈለገችውም ነበር። ጉዳዩ በተ.መ.ድ. ጉባኤ ለውሳኔ የሚቀርብ ከሆነ ግን በነኚህ ነጥቦች ላይ ገለልተኛ እንዲሆኑ (abstain) ለኢትዮጵያ ልዑካን መመሪያ ተሰጠ።[78]

የመጋቢት 1959ኙን የጅቡቲ ህዝበ-ውሳኔ ተከትሎ የንጉሡ ነገሥቱ መንግስት ሂደቱን ለመቆጣጠር እና ላመነበት ፖ.ሊ.ሰ. ተፈፃሚነት ያሳየው ቁርጠኝነት ከምርጫው በኋላ ሊቀጥል ሳይችል ቀረ። በረጅም ጊዜ ሊተገበሩ ታቅደው የነበሩ

[78] ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 3፤ ማስታወሻ ለጃንሆይ፡ ነሐሴ 18፣ 1959። ውጉማ፡- ጅቡቲ 55-D3 2፤ በተመድ የኢትዮጵያ ልዑካን የተላለፈ መመሪያ፡ ጥቅምት 1960

ነገር ግን በደርግ ባለሥልጣናት መካከል ግዛቱን በተመለከተ ፍፁም መግባባት ነበር ማለት አይቻልም። ወታደራዊውን አንጃ ያምሱ የነበሩ ርዕዮተ-ዓለማዊ አመለካከቶች ጅቡቲንም በተመለከተ በፖለቲከኞቹ መካከል የሃሳብ ልዩነት ፈጥረው ነበር። ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በዶ/ር ሠናይ ልኬ (መኢሶን) መሪነት የተወሰነው ቡድን ለግዛቱ አፋጣኝ ነፃነት ስለመስጠት አስፈላጊነት መከራከሩ ነው። ቡድኑ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ፍራቻ የነበረውን የጅቡቲ ከሶማሊያ የመቀላቀል አማራጭ እምብዛም ከግንዛቤ ሊያስገባ አለመፈለጉ ለተቀረው የደርግ ክፍል አስደንጋጭ ሆኖ ነበር። እነ ዶ/ር ሰናይን ከዚህ አንፃር ለማሳመን የተደረገው ጥረት መክሸፉ በደርግ መዋቅር ውስጥ ከአገራዊ እሳቤ ባሻገር ለፖለቲካዊ አስተሳሰብ ቅድሚያ ይሰጥ እንደነበር አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።[80] በሂደት ግን ይህ ቡድን ተሰሚነት እያጣ መምጣቱ ለዘላቂው የደርግ ፖሊሲ መቀረጽና ተግባራዊ መሆን በር ከፈተ።

በወቅቱ የጅቡቲ ሁኔታን አሳሳቢ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል እየተጠናከረ የመጣው የቀይ ባሕር በዓረብ መንግሥታት ብባ ሥር መውደቅ እና ይህም በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርሰው ተጠቂነት፣ ጅቡቲ ከሶማሊያ ጋር እየተደረገ ለቆየው ትግል አንዱ አካል መሆኑ፣ ግዛቱ በኤደን ባህረ ሠላጤ በኩል ከህንድ ውቅያኖስ ጋር የሚያገናኝ ቁልፍ በር መሆኑ ወዘተ ይገኙባቸዋል። ይህንን ለማስፈፀም ኢትዮጵያ ከሶማሊያም ሆነ ከጅቡቲ ፖለቲካ አይላ መገኘት እንዳለባት፤ በሃገር ውስጥ አስተዳደር የጅቡቲ አዋሳኝ አውራጃዎችን አስተዳደራዊና ኢኮኖሚያዊ ድርጅት ማጎልበት፣ በማናቸውም የጅቡቲ ምርጫዎችና እንቅስቃሴዎች የኢትዮጵያ እጅ፣ ዓይንና ጆሮ በቅርበት እንዲገኝ እና በጅቡቲና በፓሪስ ከፍተኛ የፖለቲካ ችሎታ ያላቸው አምባሳደሮች እንዲሾሙ ተመከረ።[81]

---

[80] አምባሳደር ፍትጉ ታደሰ (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጅቡቲ ጥናት ቡድን መሪ እና በአምባሳደር ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል)

[81] ውጉማ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የውሳኔ ሐሳብ፡ ታህሳሥ 27፣ 1967





ይህን ተከትሎ ለረጅም ጊዜ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጅቡቲ ጥናት ክፍል ኃላፊ የነበሩት ዶ/ር ፍትጉ ታደሰ በአምባሳደር ማዕረግ በጅቡቲ ቆንስል ሆነው ተሾሙ።

ዘርፈ ብዙው የጅቡቲ ጉዳይ ግን እንዲሁ በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም። የመጀመሪያው ፈተና የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር መሪ ዓሊ አሬፍ ከፈረንሳይ እና ሶማሊያ በመቀናጀት ሊተገብሩት የሞከሩት የትልቁ አፋር ሪፐብሊክ (ብሎክ አፋር) ውጥን ነው። ከ1967 የመሬት ዓዋጅ በኋላ ወደ ጅቡቲ የተሰደዱት የአፋሩ ባላባት ቢትወደድ ዓሊ ሚራህ በዓሊ አሬፍና በግዛቱ ገዢ ሙሴ ደብሩን የተደረገላቸው አቀባበልና ድጋፍ፤ የዓሊ ሚራህ ልጆች ሐንፍሬ ዓሊና አዳይስ ዓሊ ከሞቃዲሾ ይህንኑ ለመተግበር መንቀሳቀሳቸው በኢትዮጵያ የግዛት ሉዐላዊነት ላይ እንደተቃጣ ወንጀል ተቆጠረ። የብሎክ አፋርን ውጥን ለማክሸፍ በሚል በአውሳና በአሰብ በኩል ያለው የጅቡቲ ድንበር በጥብቅ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ከመታዘዙም በላይ ዓሊ ሚራህን በራሳቸው ሰዎች ለማስገደል ታቀደ። ነገር ግን ሁለተኛው እቅድ ከመተግበሩ በፊት ጭምጭምታው በመሰማቱ በአፋሮች ዘንድ የተከሰተውን አለመረጋጋት ለማስቀረት ሲባል ቢሰረዝም ቢትወደዱ ከጅቡቲም እንዲወጡ ግፊት ስላሳደረባቸው ቋሚ አድራሻቸውን በጅዳ አደረጉ፤ ልጃቸው ሐንፍሬም ወደ ሰንዓ (የመን) ተሰደደ።[83]

የደርግ ሌላው እርምጃ በኢትዮጵያ በተከናወነው የመንግሥት ለውጥና አገሪቷ በተከተለችው ግራ ዘመም

---

[82] ውጉማ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ በመገኘት የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 14፣ 1967፤ ቆንስል ዶ/ር ፍትጉ ታደሰ ለብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ (የደርግ ሊቀ መንበር) - ከጅቡቲ ገዢና ከዓሊ አሬፍ ጋር የተደረገ ውይይት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 15፣ 1967። ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ *እኛና አብዮቱ* (ሎስ አንጀለስ- ካሊፎርኒ፡ ፀሐይ አሳታሚ፣ 2006 ዓ.ም.)፣ ገፅ 203-204. Yasin Mihammed Yasin, "Political History of the Afar in Ethiopia and Eritrea," in *Africa Spectrum,* Vol. 43, No. 1 (2008), 44-50.

ፖለቲካ ጥርጣሬ ያደረባትን ፈረንሳይን የማግባባቱ ጥረት ነበር። እየተጠናከረ በመጣው የጅቡቲ ፓርቲዎች የነፃነት ጥያቄ እና የሶማሊያ ግዛቱን የመጠቅለል ፍላጎት የተረበሹት ፈረንሳዮች አጋራቸው በነበረችው ኢትዮጵያም መተማመን አልቻሉም። በመጋቢት 1967 የፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ዠስካር ደስታንግ በሴኔጋሉ መሪ በኩል ለብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ በላኩት መልዕክት ሃገራቸው ለጅቡቲ ነፃነትን ለማቀዳጀት እንደምትሻ በመልሱ ግን በጅቡቲ ወደብም ሆነ በአጠቃላይ ግዛቱ አንዳንድ ፋሲሊቲ እንዲኖራት ዋስትና እንደምትፈልግ ጠየቁ። በተጨማሪም ኢትዮጵያና ሶማሊያ ጅቡቲን በኃይል ለመያዝ እንደማይፈልጉ ፈረንሳይ አስተማማኝ ዋስትና እንደምትፈልግ አስታወቁ።[83]

የብሎክ አፋር መርህን በመደገፍ በኢትዮጵያ የውስጥ ፖለቲካ ፈረንሳይ የምታደርገውን ጣልቃ ገብነት የሚያወግዘው የደርግ አቋም ጎን ለጎን በጅቡቲ ያለውን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የፈረንሳይን በጎ ፈቃድ መፈለጉ አልቀረም። ጅቡቲን ለዘለቄታው ከኢትዮጵያ ጋር በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር ተወጥኖ በነበረው ፖሊሲ ከፈረንሳይ ጋር በመተባበር በጅቡቲ ከተማ የነዳጅ ማጣሪያና የጋራ ባንክ ለማቋቋም እንዲሁም በአፋር የጂኦተርማል ኢነርጂ ልማት ለማድረግ የተደረገው ጥረት የዚህ አንዱ አካል ነበር። ፈረንሳይም በበኩሏ ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበርና ለመመካከር ዝግጁነቷን አሳይታ ነበር። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ በጅቡቲ ላይ ያላትን አቋም እና በተያያዘም ከኢትዮጵያ ጋር የነበራትን የመተባበር መንፈስ ቀየረች።

በኢትዮጵያ በኩል ለዚህ መለዋወጥ እንደ ምክንያት ከቀረቡት መካከል የአረብ አገራት በነዳጅ ሃይላቸው (petro-clout) በመጠቀም በፈረንሳይ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ፣

[83] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጉዳዩ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ ሚያዝያ 2፣ 1967። Julian Crandall Hollick, “French Intervention in Africa in 1978,” in *The World Today*, Vol. 35, No. 2 (Feb. 1979), pp. 71-72.





ሶማሊያ በእጅ አዙር የአረቦችን ድጋፍ ከመጠቀምም በላይ ሞቃዲሾ በሚገኘው የጅቡቲ ነፃ አውጭ ድርጅት (F.L.C.S.) እና ጅቡቲ ግዛት ውስጥ በሚገኘው ዋነኛ የተቃዋሚ ፓርቲ (Liberation populaire Africains pour l'independance — L.P.A.I.) አማካይነት በግዛቱ ብጥብጥ እንዲነሳ በማድረግ በፈረንሳይ ላይ ያሳደረችው ተፅዕኖ፣ የፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ሙሴ ዠስካር ዴስታን አገራቸው በጅቡቲ ጉዳይ ስትከተለው የነበረውን አቋም መቀየራቸውና አፋጣኝ ነፃነት ለመስጠት ማቀዳቸው፣ የአረብ ሊግ አባል የሆነችው ሶማሊያ ከሰኔ 1974 እስከ ሐምሌ 1975 ድረስ የአ.አ.ድ. ሊቀ መንበር መሆን ወዘተ ይገኙበታል።[84]

ከየአቅጣጫው የተከሰተባትን ጫና ከጥቅሟ አንፃር ለማራመድ በመሻትም ፈረንሳይ ከሶማሊያ ሪፐብሊክ ጋር ወደመስማማቱ ያዘነበለች ሲሆን ለዚሁም የሚሆን አስታራቂ ሐሳብ (modus vivendi) አገኘች። በዚህም መሠረት በአንድ በኩል ሶማሊያ ጅቡቲን ከግዛቱ እቀላቅላለሁ ማለቷን በይፋ ከማሳወቅ እንድትቆጠብና የፈረንሳይን ጦር ሠፈር በጅቡቲ ውስጥ መኖር እንድትቀበል ተደረገ። በተለዋጩ ደግሞ F.L.C.S. የተባለው ሞቃዲሾ የመሠረተችው የጅቡቲ ነፃ አውጪ ሠራዊት በአዲስ መልኩ በጅቡቲ ጦር ኃይል ውስጥ እንዲካተት ፈረንሳይ ልታመቻች፣ ጥረቱንም በገንዘብም ልትረዳ፣ በግዛቱም የሶማሊያ

[84] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ጅቡቲን ከኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የተላለፈ መመሪያ። ብ/ጄኔራል ተፈሪ ባንቲ ለጳውሎስ አብርሃም (ፕላን ኮሚሽን ኮሚሽነር)፡ ግንቦት 14፣ 1967፤ በፕላን ኮሚሽን ስለተደረገ ውይይትና ውሳኔ ክፍሌ ወዳጆ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ያቀረቡት ማስታወሻ፡ ሐምሌ 10፣ 1967። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ ጳውሎስ አብርሃም ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሰኔ 13፣ 1967፤ በፈረንሳይ አቋም መለዋወጥ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ መስከረም 1968። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3፤ በጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ መጋቢት 30፣ 1968፤ ቆንስል ፍትጉ ታደሰ ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሐምሌ 20፣ 1968። ውጉሚ፡- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 1፤ ቆንስል ፍትጉ ታደሰ ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሐምሌ 23፣ 1968

ከቀደመው መንግሥት ፖሊሲዎች ጋር በተመሳሰለ ግን በሶማሊያ ይደገፍ የነበረውን እንቅስቃሴ ለመቀልበስ ሲባል በድሬዳዋ የሚገኘውን የጅቡቲ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ማጠናከሩ እና የአፋር ወገኖችን የማሰልጠኑና የማስታጠቁ ሥራ ተጠናክሮ ቀጠለ:: በተጨማሪም በግዛቱ የውስጥ አስተዳደርና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጉዳይ እያየለ የመጣውን ሶማሊያ ዘመም የሆነውን የኢሳ ወገኖች ፓርቲ (L.P.A.I.) ሊቋቋም የሚችል በዓሊ አሬፍ የሚመራ የአፋሮች ፓርቲ (Union Nationale pour l'independendance - U.N.I. በዘልማዳዊው የኢትዮጵያ ባለስልጣናት አጠራር – ዩኒ) በኢትዮጵያ አነሳሽነት በህዳር 1968 ተመሠረተ:: እንዲሁም በሐሰን ጉሌድ ከሚመራው የጅቡቲ ተቃዋሚ ፓርቲ ጋር የመጀመሪያ ደረጃ ንግግር ተጀምሮ ነበር::[86]

በታህሳሥ 16፣ 1969 የቀረበው የሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርት ጅቡቲን በሚመለከት ያሳለፋቸው ውሳኔዎች በግዛቱ እየተካሄዱ ከነበሩ ፈጣን ለውጦች አንፃር የዘገየ ቢሆንም የኢትዮጵያን አጠቃላይ የፖሊሲ አቅጣጫ የወሰነ ነበር:: የፖሊሲ ውሳኔው በተለይ ከዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆነውን የጅቡቲን ነፃነት ከግንዛቤ በማስገባት፤ በሂደቱም ሥልጣን ሊይዙ የሚችሉ የፖለቲካ ሃይሎችን ለማዘጋጀት፣ የሶማሊያን የተቀናጀ ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እና ወታደራዊ

[86] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 11፤ በጅቡቲ በመገኘት የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ ሚያዝያ 14፣ 1967፤ ጳውሎስ አብርሃም ለክፍሌ ወዳጆ፡ ሰኔ 13፣ 1967፤ በፈረንሳይ አቋም መለዋወጥ ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ መስከረም 1968፤ ለጅቡቲ አፋር ወጣቶች የውትድርና ስልጠና ስለመስጠትና ስለማስታጠቅ፡ ግንቦት 3፣ 1968:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 1፤ በአውሳ የማሰልጠኛ ካምፕ ስለተደረገ ጉብኝት፡ ግንቦት 4፣ 1968::ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3፤ በጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተደረገ ጥናት ሪፖርት፡ መጋቢት 30፣ 1968:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3 11፤ በጅቡቲ ጉዳይ የኢትዮጵያ ፖሊሲ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. ታህሳሥ 7፣ 1975:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3 24፤ በጅቡቲ ጉዳይ የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች አስመልክቶ የወጭ ጉዳይ መግለጫ፡ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 28፣ 1976:: ውጉሚ፡- ጅቡቲ 49-D3 4፤ በአዲስ አበባ ከጉሌድ ጋር የተሰጠ የጋራ መግለጫ፡ እኤአ ሰኔ 22፣ 1976



ጅቡቲ፡ የጥገኝነታችን መስፈሪያ

ዝግጁነት እንዲሁም በጊዜው በግዛቱ የነበረውን ወደ ሞቃዲሾ ያዘነበለ ስሜት ለማክሸፍ ወዘተ በማቀድ የተላለፈ የሥራ መመሪያ ነበር:: በደርግ ባለልጣናት በኩል ለጅቡቲ የተሰጠውን ትኩረት እንደሚያመላክተው የግዛቱ ሁኔታ በኢኮኖሚ፣ ስትራቴጂና በፖለቲካ መስክ ከወቅቱ የኤርትራ ችግር ጋር በእኩልነት ደረጃ የሚታይ ተደረጎ ተመደበ::[87]

የዚህ የፖሊሲ መመሪያ መሠረታዊ ነጥብ ኢትዮጵያ ልትወስዳቸው የምትችላቸውን እርምጃዎች በጊዜው ካልወሰደች በቅርብ ጊዜ ውስጥ በጅቡቲ ያለቀለት ሁኔታ ሊገጥማት እንደሚችል መገመቱ ነው:: ይህ ፍራቻ በተለይ የግዛቱ ህዝብ ወኪሎች በድምፅ ብልጫም ይሁን በኃይል ተዕፅኖ ከሶማሊያ የመቀላቀሉን ዕቅድ የሚያራምዱ መሪዎች ሥልጣን እንዲይዙ ቢወስኑ የሚፈጠረውን አደጋ ታሳቢ ያደረገ ነበር:: በዚህ መልክ ያለቀለት ሁኔታ ያጋጠመ እንደሆን በኢትዮጵያ በኩል ሊኖር የሚችለው ብቸኛ ምርጫ ሁኔታውን በቀጥታ በጦር ኃይል መቋቋም ይሆናል:: በተለይ ሶማሊያ ቀድማ ወደ ጅቡቲ የጦር ኃይሏን ካስገባች በኢትዮጵያ በኩል ይህንን ወታደራዊ እርምጃ መቀልበሱ በፖለቲካ በኩል አስቸጋሪ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ የኤርትራ ችግር እስከቀጠለና በኦጋዴን ግንባር ሥጋት እስካለ ድረስ የኃይል እርምጃው እንደማያስተማምን ታመነ::

ይልቁንስ ወታደራዊ ፍጥጫው የመጨረሻው አማራጭ ሆኖ ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያ የሚበጁ ሌሎች የድርጊት አቅጣጫዎች ተነደፉ:: እነዚህም አቅጣጫዎች የሶማሊያን ዓላማ የሚቃወሙ ክፍሎችን በመደገፍና በማጠንከር የጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ሂደት ወደ ሶማሊያ ፍላጎት እንዳያመራና ከሶማሊያ ጋር ለመቀላቀል የሚፈልጉ ወገኖች ሥልጣን እንዳያገኙ መከላከል፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ሶማሊያ የሚደግፏትን ክፍሎች (በምርጫ ወይም ይህ ካልተሳካ ከግዛቱ ነፃነት በኋላ በመፈንቀለ መንግሥት)

[87] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3፤ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ሪፖርትና የፖሊሲ መመሪያ፡ ታህሳሥ 16፣ 1969

ሥልጣን ላይ ለማውጣት ብትፈልግ ይህን ለመቋቋም እንዲቻል ኢትዮጵያም በጅቡቲ ውስጥ ተመሳሳይ ፖለቲካዊና ወታደራዊ ድርጅት ያላቸው ኃይሎች እንዲኖሩት ማድረግን ያካትታሉ። በተጨማሪም ሶማሊያ በተዘዋዋሪ መንገድ ዓላማዋን ከግብ ለማድረስ እንደማትችል ተገንዝባ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነትን ለመተግበር ብትፈልግ ኢትዮጵያ አፀፋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደምትገደድ ሶማሊያ በማያጠራጥር ሁኔታ እንድታውቀው ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተወሰነ። ይህንንም ለማረጋገጥ ሲባል የሃገሪቱ የጦር ኃይሎች በአፋጣኝ እንዲደራጁና ዝግጁነታቸውንም ሶማሊያ በቅድሚያ እንድትረዳ እንዲደረግ ተወሰነ።

እነዚህ እርምጃዎች ኢትዮጵያ በጅቡቲ ያለቀለት ሁኔታ እንዳያጋጥማት እንደሚያስችሉ ታመነባቸው። ከአጠቃላይ የጅቡቲ ጉዳይ አስጊነትና አስቸኳይነት በመነሳትም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በአስተማማኝ ለመጠበቅ እንዲቻል አስፈላጊውን የገንዘብ መስዋዕትነት የመክፈሉ ግዴታ ታመነበት። አጠቃላይ ሃገሪቱ በጂቡቲ የምትከተለው ይህ ፖሊሲ "እያደገ የሚሄድ የአጸፋ ፖሊሲ" (policy of graduated response) ተብሎ ተሰየመ።

ይህንን ፖሊሲ ከመተግበር አኳያ የመጀመሪያው አማራጭ በጅቡቲ ፖለቲካ ውስጥ የሶማሊያን ዓላማ የሚቃወሙ ክፍሎችን መለየት፣ ማደራጀትና መርዳት ነበር። በግዛቱ ከነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከልም ዩኒ (U.N.I.) እና ኤም.ፒ.ኤል ለዚህ ሥራ ታጩ። የዩኒን እንቅስቃሴ በቅርበት እንዲከታተል ጅቡቲ ተልኮ የነበረ ቡድን ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ፓርቲው 90 በመቶ የአፋሮች ድጋፍ የነበረውና ብዙ ተከታዮችም ያፈራ ቢሆንም የተቀናጀ ድግፍ ባለማግኘቱ የተዳከመና ሶማሊያ በኤል.ፒ.ኤ.አይ. በኩል የምታደርገውን ግፊት ለመቋቋም የማይችልበት ደረጃ ደርሶ ነበር።

በጊዜው ዩኒ ከኢትዮጵያ ሰፊና አስቸኳይ ዕርዳታ ጠይቆ ስለነበር እስከ ጅቡቲ ነፃነት የሚዘልቅ የዕርዳታ ፕሮግራም ተነደፈ። ድጋፉ ፓርቲው የፖለቲካ ድርጅቱን የሚያጠናክርበትና





የሚስፋፋበት፣ በምርጫው ውድድር ወቅት የሚጠቀምበትና የምርጫውን አካሄድ በተጽዕኖው ሥር የሚያውልበት በሦስት ዙር የሚደርሰው 6,000,000 ብር የሚያወጣ የዕርዳታ ፕሮግራም ነበር። አብዛኛው ዕርዳታ በገንዘብ ሳይሆን በዕቃ ሆኖ እነኚህ ዕቃዎች በከፊል ከኢትዮጵያ የሚገኙ እንዲሆን ታቀደ። ከዚህ ቀደም በዩኒ ጥያቄ ድርጅቱንና የአፋሩን ህዝብ እንዲከላከሉ በኢትዮጵያ መንግሥት በውትድርና ሞያ ሰልጥነው በጅቡቲ ከተሠማሩት 131 ወጣቶች በተጨማሪም እስከ 600 የሚደርሱ የአፋር ወጣቶችን በውትድርና ለማሰልጠን አስፈላጊው ዝግጅት ተደረገ።

ኤም.ፒ.ኤል. (Mouvement Populaire Djiboutien — M.P.L.) የሶሺያሊስት አቋም ባላቸው የአፋር ወጣቶች በ1968 የተቋቋመ ሲሆን ከጥቂት የጅቡቲ ከተማ ነዋሪዎች በስተቀር ብዙም ድጋፍ ያልነበረው ፓርቲ ነበር። ድርጅቱ ከላይ ለተጠቀሰው ዓላማ ሲታጭ እስከ ግዛቱ ነፃነት ድረስ በቀረው ጊዜ ውስጥ ከፍ ያለ የፖለቲካ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ አልነበረም። ይልቁንም ሁኔታው ከተረጋጋ በኋላ ለዘለቄታው በነፃይቱ ጅቡቲ ውስጥ ከጎብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር የሚችል ቡድን ስለነበር እንጂ። የተነደፈው የዕርዳታ መርሐ ግብር እንደሚያመለክተው ድርጅቱ በጠየቀው መሠረት የረጅም ጊዜ ዓላማውን ለማደርጀት ለመሪዎቹና ለካድሬዎቹ የትምህርት ዕድል እንዲሰጥ፤ በአጭር ጊዜ ደግሞ ለአሥር ካድሬዎች በየካቲት 66 ትምህርት ቤት የፖለቲካ ትምህርትና የውትድርና ኮርስ እንዲሰጣቸው ተወሰነ። ለዚህም ማስፈፀሚያ አስፈላጊው በጀት ተያዘ።[88]

በተያያዘም የእነዚህን ፖሊሲዎች አተገባበር የሚከታተል ከፍተኛ የአስፈጻሚዎች ኮሚቴ ተቋቋመ። ኮሚቴው ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሁለት፣ ከአገር መከላከያ ሚኒስቴር እና ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴሮች አንድ አንድ እንዲሁም

---

88 ዝኒ ከማሁ

ከካቢኔ ልዩ መምሪያ ሁለት ተወካዮችን በማካተት ተዋቀረ። ቡድኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ኮሚቴ ሆኖ በጅቡቲ ጉዳይ ላይ በማዕከላዊ መንግሥትም ሆነ በጠረፍ አውራጃዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እንዲከታተልና እንዲያቀናጅ ኃላፊነት ተሰጠው።[89]

ቅድሚያ የተሰጠው የድርጊት መርሐ-ግብር መጪውን የጅቡቲ ምርጫ ለኢትዮጵያ ፍላጎት ተስማሚ በሆነ አካላት ተዕፅኖ ሥር እንዲሆን ማስቻል ነበር። በተለይም የአፋሩ ጎሳ በምርጫው በስፋት እንዲሳተፍ ማድረግ ይህንን ዕቅድ የማስፈጸሚያ ዋነኛ መሳሪያ ተደርጎ ተወሰደ። "ፕሮጀክት አቃቂ" የዚህ ውጥን ተግባራዊ መገለጫ ነበር። የፕሮጀክቱ ዓላማ በጥር ወር 10,000 የኢትዮጵያ አፋሮችን ወደ ጅቡቲ በማስገባት የምርጫ መታወቂያ ካርድ እንዲወስዱ ማድረግ ነበር።

ዝርዝር ፕሮግራሙ እንደሚያመለክተው 1,000 አፋሮች ከአሰብ ወደ ሙላሒሌ በእግር ተጉዘው ወደ አቦክ የምርጫ ቀበሌ ይገባሉ፣ 4,000 ከአውሳ በዳደቶ በኩል በመኪና ጠረፍ ከደረሱ በኋላ እነሱም ወደ አቦክ ያቀናሉ፣ 2,000ዎቹ ከገዋኔ እስከ አሳይታ በመኪና ከዚያም ወደ አፋምቦ በእግር ተጉዘው ወደ ዲኪል ምርጫ ጣቢያ የሚገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ 3,000 አፋሮች ከሚሌ፣ ከሎጊያና ከኤሊዳሬ ወደ በልሆና ዳይሞሌ መቃረቢያ ድረስ በመኪና ከተጓጓዙ በኋላ ወደ ታጁራ ቀበሌ እንዲገቡ ተደረገ። አፋሮቹ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አደጋ እንዳይደርስባቸው በኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አስፈላጊው ጥበቃ የተደረገላቸው

አትመው (ከአገር አስተዳደር ሚኒስቴር)፣ እና አቶ ተወልደብርሃን ታዕዛዝ (ገንዘብ ያዥ)ና መ/አ እንዳርጌ ብርሃኔ ከካቢኔ ልዩ መምሪያ ነበሩ.

[89] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 8፤ የአስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት መመሪያ፡ የካቲት 15፣ 1969። የኮሚቴው አባላት አቶ ወሰን በሻህ (ከውጉሚ-ሊቀ መንበር)፣ አቶ ዓለማየሁ መኮንን (ከውጉሚ-ጸሐፊ)፣ ሌ/ኮሎኔል ዓለሙ ጥበቡ (ከአገር መከላከያ ሚኒስቴር)፣ ኮሎኔል ተስፋዬ

[90] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 54-D3 24፤ ብርሃኑ ዲንቃ (ውጉሚ- አፍሪካ መምሪያ ኃላፊ) ለከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ስለ ፕሮጀክት አቃቂ የቀረበ ማስታወሻ፡ ታህሳሥ 21፣ 1969





ሲሆን ጅቡቲ ሲገቡም ችግር እንዳያጋጥማቸው ለዩኒ ፓርቲ ተወካዮች በጅቡቲ ቆንስል በኩል መመሪያ ተላለፈ። አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ወደ 150,000 ብር ወጪ ጠየቀ።[90]

በዚህ መሐል የኢትዮጵያን ጥረት ያቀዘቀዘ ክስተት ተፈጠረ። የጅቡቲን ነፃነት ታሳቢ ያደረገና በቀጣይነት የሚመሠረተውን ፓርላማ አወቃቀር ለመወሰን ፈረንሳይ በመጋቢት 1969 በፓሪስ የግዛቲን ፓርቲዎች ያሳተፈ ስብሰባ አዘጋጀች። በስብሰባው ከተሳታፊ ወገኖች ጋር በሂደቱ ዙሪያ ስምምነት ላይ ከመድረስም ባሻገር ስለ አፈፃፀሙ ውሳኔ እንዲተላለፍ አደረገች። በዚህ ስብሰባ አብዛኛዎቹ የኢሳ-ሶማሌ ፓርቲዎች እና በካሚል የሚመራው የጅቡቲ አስተዳደር ተካፋይ የነበሩና ውሳኔውን የተቀበሉ ሲሆን ዋነኞቹ የአፋር ፓርቲዎች (በተለይ ዩኒ፣ ኤም.ፒ.ኤል እና ኤም.ኤል.ዲ.) በኢትዮጵያ መንግሥት ገፋፊነት በፓሪሱ ስብሰባ ሳይሳተፉ ቀሩ።

ይህ የኢትዮጵያ ውሳኔ ከመነሻው ከአንዳንድ የአገሪቱ ዲፕሎማቶች ተቃውሞ ገጥሞት የነበረና ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖ የተዘረዘረ ቢሆንም ተግባራዊ ተደረገ። የዚህ ውጤት የፓሪሱ ስብሰባ ተሳታፊዎች ከአፋር ፓርቲዎች ጋር በቀጣዩ የግዛቱ መንግሥት አወቃቀር ዙሪያ ለመደራደር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። የፓሪሱ ስምምነት ህዝበ-ውሳኔው ሚያዝያ 30፣ 1969 እንዲካሄድ ከመወሰኑም ባሻገር አዲሱ የጅቡቲ ምክር ቤት ስልሳ አምስት መቀመጫ እንዲኖረው ተደረገ። በአምስት በተከፈለው የምርጫ ክልል ድልድል መሠረትም አፋሮች 29፣ ሶማሌዎች 3፣ አረቦች 2 እና ኢሳዎች 31 ወንበር ይኖራቸዋል። [91]

በኢትዮጵያ ገፋፊነት የአፋር ፓርቲዎች የተሳተፉበት ቀጣይ ስብሰባ በጋና አክራ ተደረገ። ዋነኛው የድርድር ነጥብ አፋሮች ያቀረቡት፡ በምክር ቤቱ ከኢሳዎች እኩል 31 መቀመጫ

[91] Shehim and Searing, 219-222. Kadamy, 512-513.

ነፃነት የምትደግፈው የግዛቱ ነፃነት እውነተኛና ከማንኛውም ውጫዊ ተፅዕኖ የፀዳ ከሆነ ብቻ እንደሆነ ለጅቡቲው መሪ ተገለፀ።[96]

በሁለቱ አገሮች መካከል የመጀመሪያዎቹ ወራት ግንኙነት የተጠበቀውን ያክል አዎንታዊ ገፅታ አልነበረውም። የምድር ባቡሩ መስመር ግንቦት 24፣ 1969 በሶማሊያ ሠርጎ ገቦች መሰበር፣ የዚያድ ባሬ የጅቡቲ ጉብኝትና ሊያሳድረው የሞከራቸው ፀረ-ኢትዮጵያ አቋሞች፣ የሐሰን ጉሌድ በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን በድንበር ጥሰት መወንጀል፣ የሐምፍሬ አሊ ሚራህ በአረብ መንግስታት ድጋፍ በጅቡቲ የሚገኙ አፋሮችን ለውትድርና ዘመቻ እያዘጋጀ መሆኑ፣ በኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት ወቅት (1969/70) የጅቡቲ መንግስት ገለልተኛ ቢመስልም በተዘዋዋሪ ለሶማሊያ ያደላ አቋም መያዙና የሶማሊያ ጦር በግዛቱ እያለፈ ኢትዮጵያን እንዲያጠቃ መፍቀዱ፣ የወደብ ስምምነቱን በመጣስ በጅቡቲ በኩል ነዳጅ ወደ ኢትዮጵያ እንዳያልፍና በወደብ ላይ የተራገፉ ዕቃዎች እንዳይነሱ መከልከሉ፣ ፕሬዚደንት ጉሌድ ገንዘብ ፍለጋ በአረብ አገራት ያደረጉት ጉብኝት (ነሐሴ 1969) እና ከነዚህ መንግስታት በኩል ጅቡቲ ለሶማሊያ በመወገን የኢትዮጵያን ጥቅሞች እንድታጠቃ የቀረበላት ጥያቄ፣ የጉሌድ በይፋ የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጭ ድርጅትን መደገፍ ወዘተ ለዚህ የጥርጣሬ መንፈስ አስተዋፅኦ አበርክተዋል። ከዚህም ባሻገር በኢሳ-ሶማሌ የበላይነት የተያዘው የጅቡቲ ጦር ተከታታይ

[96] ውጉማ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ከ/ል ዶ/ር ፈለቀ ለፕሬዚደንት ሐሰን ጉሌድ፡ ሰኔ 1969

[97] ውጉማ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ማስታወሻ ለሌ/ኮ መንግስቱ ኃይለማርያም፡ ሐምሌ 1969። ውጉማ፡- የጅቡቲ ሁኔታ ሪፖርት 9 2፤ ኮማንደር ሙሳ ያሲን (ጅቡቲ) ለዶ/ር ፈለቀ፡ ነሐሴ 7፣ 1969፤ ዶ/ር ፈለቀ ለደርግ ጽ/ቤት፡ ዳጉማ 3፣ 1969፤ ምንዳዬ ደሬሳ (ውጉማ አማካሪ) ለኮማንደር ሙሳ ስለ ጅቡቲ ከሶማሊያ ወገን መቆም፡ ዳጉማ 5፣ 1969። Harry Ododa, "Somalia's Domestic Politics and Foreign Relations since the Ogaden War of 1977-78," in *Middle Eastern Studies,* Vol. 21, No. 3 (July 1985), 290-293.





የተጨማሪ ሥልጣን ጥያቄ እና ከአፋር ጎሳ የጦር አባላት ጋር በተደጋጋሚ የተደረጉ ግጭቶች በግዛቱ የውስጥ ጉዳይ የሶማሊያ መንግስት እጅ እየበረታ ለመምጣቱ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ።[97]

ይህ አጣብቂኝ በኢትዮጵያ በኩል አፋጣኝ የፖሊሲ ክለሳ እንዲደረግና የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በር ከፈተ። የአስፈፃሚ ኮሚቴው በመስከረም ወር 1970 የመጀመሪያ ሳምንት ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ የተጠቀሱትን ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴዎች በማጤን የፖሊሲ ሃሳቦችን አቀረበ። የፖሊሲ ሃሳቡ የተንደረደረው ሃገሪቱ በጅቡቲ ጉዳይ ስትከተለው የነበረውን አቋም ህጸፆች በመጠቆም ነው። ከዚህ አንፃር ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ተነቅሰው ወጡ፡ አንደኛው የሶማሊያ የምንግዜም የመስፋፋት እቅድ ሲሆን ሁለተኛው በጅቡቲ ላይ የሚስተዋለው የምዕራባውያን (በፈረንሳይ መሪነት) እና "የአረብ አድሃሪ ኃይሎች" ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነው።[98] የዚህ ሁለንተናዊ ተፅዕኖ ውጤትም ጅቡቲ ሶማሊያ በኢትዮጵያ ላይ ለነበራት የመስፋፋት ዓላማና ለፈፀመችው ወረራ ግልፅ ተባባሪ መሆን ነው። በሂደትም ኢትዮጵያ ስትከተለው የነበረው ፖሊሲ በጅቡቲ ውስጥ ያስገኘው ውጤት ከሶማሊያ ስኬት ጋር ሲነፃፀር ኢምንት ሆኖ ተገኘ።

በአስፈፃሚው ኮሚቴ ግንዛቤ መሠረትም በጅቡቲ መንግስት፣ አስተዳደርና የጦር ኃይል ውስጥ የሶማሊያ መንግስት ዓላማ ደጋፊዎች በብዛት መሰግሰግ በግዛቱ መፈንቅለ መንግስት ለማድረግ በሶማሊያ በኩል የነበረውን ፍላጎት አመላካች ተደርጎ ተወሰደ። ይህ እቅድ የሚፈፀም ከሆነ ደግሞ የጅቡቲ ወደ ሶማሊያ መቀላቀል በህጋዊ መንገድ የሚከናወን ያለቀለት ጉዳይ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ኢትዮጵያ የምትከተለው የነፃ ጅቡቲ መርህ የሶማሊያን ሴራ ለማክሸፍ ያለመ መሆን ይኖርበታል። በኮሚቴው ግምገማ መሠረት ኢትዮጵያንና ጅቡቲን ካራራቃቸው

[98] J.P. Anand, "Horn of Africa: Superpowers' Manoeuvres," in *Economic and Political Weekly*, Vol. 12, No. 35 (Aug. 27, 1977), pp. 1537-1538.

ጋር ሰፊ ውይይት አካሄዱ። ወገናቸውን ለመታደግም ኢትዮጵያ አፋጣኝ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እርዳታ እንድትሰጣቸው ጠየቁ። በተለይም በጎሳቸው ላይ እየተፈፀመ የሚገኘውን በደል በመቃወም የጠቅላይ ሚኒስትር ሙሴ አህመድ ዳኒና ሌሎች አምስት የካቢኔ አባሎች ሥልጣን መልቀቅ እና አፋር የምክር ቤቱ አባላት ፓርላማውን ረግጠው መውጣታቸውን ተከትሎ በሁለቱ ዋነኛ ጎሳዎች መካከል ግጭት ሊነሳ ስለሚችል የኢትዮጵያ አፋጣኝ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ገለፁ።

የአፋሮችን ደህንነት በአስተማማኝ ለመጠበቅም ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ያሰለጠነቻቸው የዩኒ እና ኤም.ፒ.ኤል. ወጣቶችና ሌሎች ለተመሳሳይ ዓላማ የተዘጋጁ የኢትዮጵያ አፋር ወታደሮች ተሰብስበው በአስቸኳይ ለእርዳታ ሊደርሱ በሚችሉበት ቦታ እንዲቀመጡ፤ እና የኢሳዎችን ማንአለብኝነት ለመቀነስ እና ከአፋሮች ጀርባ አንድ ኃይል መኖሩን ተረድተው ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ለማድረግ የኢትዮጵያ መንግስት በምስጢር እስከ 5,000 ለሚደርሱ የጅቡቲና ኢትዮጵያ አፋሮች የሦስት ወር ወታደራዊ ስልጠና እንዲሰጥና ለግዳጅ እንዲያዘጋጅ፤ የረጅም ጊዜ እቅድ ተይዞ ደግሞ በርዕሰ ከተማዋ በጅቡቲ የአፋሮችን ቁጥር ከኢሳዎች የበለጠ ወይም እኩል ለማድረግ ወደ 50,000 የሚጠጉ የኢትዮጵያ አፋሮችን ወደ ግዛቱ ለማስረግ እንዲቻል የጅቡቲው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊቀ መንበር መንግስቱን ጠየቁ።[101]

በጥያቄው ዙሪያ የኢትዮጵያን መልካም ፈቃድ የገለፁት ሊቀ መንበሩ ወደ አፈፃፀም ከመገባቱ በፊት በጅቡቲ በመገኘት ጉዳዩን የሚመረምር የመልዕክተኞች ቡድን ለመላክ ወሰኑ። የልዑካን ቡድኑ ከሌሎች የአፋር መሪዎች ጋር ተገናኝቶ ከኢትዮጵያ የሚፈለገው እርዳታ ዓይነትና መጠን ምን መሆን እንዳለበት በምንስ መንገድ እንደሚሰጥ እንዲነጋገር ታቀደ። በዚህም መሠረት በአቶ ብርሃኑ ዲንቃ (የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)

101 ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3፤ በጉዳዩ ዙሪያ የተዘጋጀ ማስታወሻ፡ ታህሳሥ 21፣ 1970





የሚመራ ዶ/ር አሰፋ መድኃኔና አቶ ወሰን በሻህ የሚገኙበት ቡድን ከታህሳሥ 17-24፣ 1970 በጅቡቲ በመገኘት ያለውን ሁኔታ አጥንቶ ሪፖርት አቀረበ። በተለይም ቡድኑ ከአፋር ፓርቲ ተወካዮች ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች የጅቡቲ አፋሮች በሙሴ አሃመድ ዳኒ መሪነት አንድነት መመስረታቸውን እና ከኢትዮጵያ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋገጠ። ይህ የአፋሮች አንድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ ለኢትዮጵያ ዓላማ አመቺ ሁኔታን መፍጠሩንም አሳሰበ።

የቡድኑ የማጠቃለያ አስተያየት ካቀረባቸው የውሳኔ ሃሳቦች መካከልም ለሦስት ሺ ሰዎች ትጥቅ የሚሆን ልዩ ልዩ መሣሪያና ፈንጂ በአስቸኳይ ወደ ጠረፍ ተልኮ በኢትዮጵያ ጦር ቁጥጥር ሥር እንዲቀመጥ፣ ከዚህ በፊት ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሰልጥነው የነበሩት 500 አፋሮች ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ላይ ስለሆኑ እነሱንና 500 ከዚህ ቀደም የሰለጠኑ ኢትዮጵያውያን አፋሮች እንዲታጠቁና እንዲዘጋጁ፣ ከጅቡቲ በመምጣት ላይ ከሚገኙ ወጣት አፋሮችና ከኢትዮጵያውያን የተውጣጡ ከ4,000-5,000 የሚሆኑ ሰዎች በሚቀጥሉት ሦስት ወራት በውትድርና ትምህርት እንዲሰለጥኑ፣ እና ጅቡቲ ውስጥ ግጭት ቢፈጠር እዚያ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ለማውጣት እንዲቻል አንድ ፕላን እንዲያዘጋጁ የአገር መከላከያና የመገናኛ ሚኒስቴሮች እንዲታዘዙ የሚሉት ይገኙበታል።[102]

ከላይ በቀረቡ ጥያቄዎች መሠረትም የኢትዮጵያ ወታደሮች በጅቡቲ ድንበር አከባቢ ንቅናቄ ያደረጉ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውም በግዛቱ ላሉት አፋሮች የሞራል ድጋፍ ለመስጠት ነበር። ለአፋር ወጣቶችም ወታደራዊ ስልጠናው እና የመሳሪያ አቅርቦቱ ተጠናክሮ ቀጠለ። አጠቃላይ ግፊቱ ከፈጠረው ተፅዕኖ ባሻገር የጅቡቲ አፋር ፖለቲከኞች በጉሌድ ላይ ባሳደሩት ጫና የተነሳ በአብደላ ካሚል ጠቅላይ ሚኒስትርነት የሚመሩ አፋሮች የሚበዙበት መንግስት ተመሠረተ።[103]

በተለይ ከሶማሊያ ወረራ መቀልበስ በኋላ በጉሌድ

102 ዝኒ ከማሁ

103 ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3፤ ከማንደር ሙሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ጥር 2 እና 24፣ 1970፤ ከማንደር ሙሳ ለዶ/ር ፈለቀ፡ ጥር 29፣ 1970

መንግስት ላይ የደረሰው የሞራል ውድቀት እና የውስጥ መከፋፈል ለኢትዮጵያ ሌላኛው ድል ነበር። ይህን ተከትሎ የተወሰደው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲና ፖለቲካ የትግል መስመር ካተኮረባቸው ግቦች መካከል ዋነኞቹ የጉሌድ መንግስት ከግተር ብሔረተኝነት ወጥቶ ለአፋሮች ተገቢ መብታቸውን በማጎናጸፍ የውስጥ ፖለቲካውን እንዲያረጋጋ፣ የውጭ ፖለቲካውን በፍፁም ገለልተኛነት ላይ እንዲመሰርት፣ በጅቡቲና በኢትዮጵያ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ እንዲዳብር አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ እና በባቡር ሐዲዱና በጅቡቲ ወደብ በኩል የሚተላለፈው የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ አለምንም እክል በጋራ ተጠቃሚነት መርህ እንዲካሄድ ማስቻል ነበር። ለዚህም በኢትዮጵያ በኩል እንደ መሳሪያ የተጠቀመችው በአህመድ ዲኒ አህመድ መሪነት የተመሠረተውን የአፋሮች አንድነት ነው። ይህን ቡድን በገንዘብ ለማጠናከር ሲባልም በአፍሪካ እና አውሮፓ እየተዘዋወረ ለሚያከናውናቸው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የሚውል ተጨማሪ 100,000 ብር ተመደበለት።[104]

ሶማሊያ በጅቡቲ ታደርገው የነበረውን ጣልቃ ገብነት ለዘለቄታው ለማክሸፍ ታስቦም በደወሌ አከባቢ ያለው የኢትዮጵያ ጦር እንዲጠናከርና በአቅራቢያው ባሉ የሶማሌ ወታደሮች ላይ ድብደባ እንዲፈፀም ተደረገ። በግንቦት ወር 1970 ሊቀ መንበር መንግስቱ ሞቃዲሾ ጅቡቲን ብትወር ኢትዮጵያን ለዳግም ጦርነት መጋበዝ መሆኑን በይፋ አስታወቁ። የአፋር ታጣቂዎች በተመረጡ የጅቡቲ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተቋሞች ላይ አደጋ እንዲያደርሱ ተደረገ። ለጅቡቲ መንግስት ይሠራሉ ተብለው የተጠረጠሩ ፈረንሳዊያንም በተለያዩ ጊዜ

---

[104] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 52-D3 5፤ ብርሃኑ ዲንቃ (አፍሪካ መምሪያ) ለክ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ መጋቢት 15፣ 1970። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ማስታወሻ ለሊቀ መንበር መንግስቱ፡ መጋቢት 15፣ 1970

[105] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ ብርሃኑ ዲንቃ ለሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ (ውጉሚ ቋሚ ተጠሪ)፡ መጋቢት 15፣ 1970፤ ኮማንደር ሙሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ነሐሴ 17፣ 1970፤ ጅቡቲ ቆንስላ ለክ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሰኔ 6፣ 1971። አዲስ ዘመን ግንቦት 11፣ 1970። ውጉሚ፡- የጅቡቲ





በኢትዮጵያ መንግስት በሚደገፉት የአፋር ወታደራዊ ቡድኖች ይጠለፉ ጀመር። ከሁሉም በላይ ከጅቡቲ ተሰደው የነበሩት የኑ እና ኤም.ፒ.ኤል. በኢትዮጵያ አደራዳሪነት በሰኔ 1971 አር.ፒ.ኤል (Rassemblement populaire pour l'progres) የተሰኘ የጋራ ግንባር ፈጠሩ። እነኚህ እርምጃዎች ከጅቡቲና ሶማሊያ በተጨማሪ የፈረንሳይ መንግስትንም ወደ ድርድር ለማምጣት ያለሙ ነበሩ።[105]

በኢትዮጵያ በኩል አሁንም በጅቡቲ ላይ የተፈለገውን ያክል አመኔታ ሊፈጠር ስላልቻለ ተጨማሪ እርምጃዎች ተወሰዱ። አንዱና ዋነኛው የአሰብ አውራጃ አስተዳደርን ማጠናከር ነበር። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥር 16፣ 1970 ባካሄደው ስብሰባ ላይ እንደተብራራው ይህንን እርምጃ ለመውሰድ የተፈለገው በወቅቱ አሰብ የኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ንግድ የሚከናወንበት እና ከውጭ የመገናኛ ብቸኛ በር ስለነበር ነው። የምዕዋ ወደብ መዘጋትና የአዲስ አበባ ጅቡቲ የባቡር መስመር መቋረጥ፤ የአሰብን ወደብ፣ የነዳጅ ማጣሪያውንና ሌሎችንም የኢኮኖሚ አውታሮች ከውጭ ጠላትና ከኤርትራ አማፅያን ጥቃት ለመጠበቅ፤ ከኤርትራ ክፍለ ሀገር ርዕሰ ከተማ ሆኖ አሰብን ማስተዳደሩ አስቸጋሪ እየሆነ መምጣቱ ወዘተ አስተዳደራዊ ለውጥ እንዲደረግ ምክንያት ነበሩ። ስለሆነም ወደቡ የሚገኝበትን አውራጃ አስተዳደር በማሻሻልና በማጠናከር ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት ሲባል የአሰብ አውራጃን በማዕከላዊ መንግስት መዋቅር ስር ማድረግ አስፈለገ።

የውሳኔው ዋነኛ ነጥቦች የአሰብ አውራጃ አስተዳደር በጊዜያዊነት መልክ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለማዕከላዊ መንግስት መዋቅር እንዲሆን፤ በዚሁ መሠረት አሰብ አውራጃ የሚገኙ

---

ሁኔታ ሪፖርት 9 1፤ ኮማንደር ሙሳ ለብርሃኑ ዲንቃ፡ ግንቦት 19፣ 1970። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 1፤ መሐመድ አ. ሩፋ (የዩኒ ፖለቲካ ቢሮ ዋና ጸሐፊ) ለሊቀ መንበር መንግስቱ ያቀረቡት የሥራ ሪፖርት፡ መስከረም 24፣ 1972። Jeff Crisp, "The Politics of Repatriation: Ethiopian Refugees in Djibouti, 1977-83," in *Review of African Political Economy*, No. 30 (Sept. 1984), 75.

የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ቅርንጫፎች ተጠሪነታቸው ለጊዜው በቀጥታ አዲስ አበባ ለሚገኙት ለሚመለከታቸው ሚኒስትሮች ወይም ድርጅቶች እንዲሆን፣ ቅርንጫፍ የሌላቸውም እንደአስፈላጊነቱ እንዲያቋቁሙ፤ እና በዚህ ውሳኔ መሠረት የአሰብ አውራጃ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶቻቸውን ለማጠናከር አስፈላጊው በጀትና የሰው ኃይል እንዲመደብ ተደረገ። የአውራጃውን አስተዳደራዊ አቋም ይበልጥ ለማጠናከር ሲባልም የአውራጃው የአብዮት ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ የክፍለ ሀገር አቻውን ሥልጣንና ተግባር ደርቦ እንዲሰራ፣ ለኮሚቴው ሰብሳቢነትም ቋሚ የደርግ አባል እንዲመደብና ተጠሪነቱም በቀጥታ ለማዕከላዊ ዕዝ እንዲሆን ተወሰነ። በጉዳዩ ላይ ንግግር በተደረገበት ወቅት በግልፅ የተብራራው ነጥብ ይህ ውሳኔ በኢትዮጵያ አፋሮች ቀርቦ የነበረውን የአፋር ህዝብ ክፍለ ሀገር የመመስረት ጥያቄ ጋር በፍፁም ግንኙነት የሌለው መሆኑ ነው።[106]

በተያያዘም ሰኔ 22፣ 1970 ሊቀ መንበር መንግስቱ በተገኙበት በተካሄደ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ የአሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ የተሰኘ መዋቅር ተጠሪነቱ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ ሆኖ በአዋጅ ተቋቋመ። በመሐል አገር የተከሰተው የሸቀጣ ሸቀጥ እጥረት እና በአሰብ ወደብ የነበረው ከፍተኛ ክምችት ለትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴው መቋቋም ዋነኛው ምክንያት ነበር።[107] በዚህ መካከል ግን የአሰብ ወደብ በመጣበቡ ምክንያት የተፈለገውን ውጤት ሊሰጥ ባለመቻሉ በጅቡቲ ወደብና በጅቡቲ-ጋላፊ መንገድ በይበልጥ መጠቀሙ አማራጭ የሌለው መሆኑ ስለታመነበት በጉዳዩ ዙሪያ ከጅቡቲ ባለስልጣናት ጋር የሚነጋገር ከፍተኛ የልዑካን ቡድን መላኩ ግድ ሆኖ ነበር።[108]

---

[106] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 1፤ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ፡ የካቲት 10፣ 1970

[107] ዝኒ ከማሁ፤ ኃይሉ ይመኑ ለኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ፡ ሰኔ 26፣ 1970፤ የአሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ የድርጅት አቋምና የአስተዳደር አመራር አዋጅ፡ ሰኔ 1970





ከሶማሊያ ወረራ መክሸፍ በኋላ የሐሰን ጉሌድ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ለመግባባትና ለመተባበር በተደጋጋሚ ፍላጎት ማሳየቱን አልቀረም። በተለይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በሙሴ መሚን ብህድን በኩል ዓላማውን ለማሳካት ተደጋጋሚ ጥረቶች ሲያደርግ ቆየ። ነገር ግን ይህንን ጥረት አስመልክቶ በደርግ በኩል የነበረው ግንዛቤ የጅቡቲው የኢሳ ሶማሌ መንግስት ዓይነተኛውና የመጨረሻ ዓላማ አፋሮችን ከኢትዮጵያ መነጠል ነው። ጅቡቲያውያኑ ለዚህ እቅዳቸው መሳካት ሁለት የትግበራ አማራጮችን እንዳሰቡ ተገመተ። አንደኛው የወደፊት ዕጣ ፈንታቸው ያለየለትን የምድር ባቡሩንና የጅቡቲን ወደብ ተጠቃሚነት በመደራደሪያነት በማቅረብ በስልጣን ላይ ካለው የኢሳ ሶማሌ መንግስት ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዲደረግና በዚያም ሳቢያ ኢትዮጵያን ከአፋሩ ወገን ማራራቅ፤ ሁለተኛው አማራጩ ደግሞ ኢትዮጵያ ከጉሌድ መንግስተ ጋር ለመተባበር ካልፈለገችና የጅቡቲ አፋሮችን መርዳቷን ከቀጠለች በሥልጣን አሊሚራ የሚመራውን የብሎክ አፋር ውጥን በማጠንከር አፀፋዊ እርምጃ መውሰድ ነው።[109]

በስተመጨረሻ ግን ዘርፈ ብዙውን የኢትዮጵያ ጫና ተከትሎ በመስከረም 1971 በጅቡቲ የካቢኔ ለውጥ ተደረገ። የፕሬዚደንቱ ካቢኔ ሹም እና የአገሪቱ የፀጥታ ኃላፊ ሙሴ እስማኤል ኡመር ጊሌ በተለይ በጅቡቲ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እንደገለፁት የለውጡ ዋነኛ ዓላማ የውስጥ አስተዳደሩን ማሻሻል እና የጎሳ ሚዛኑን ማስተካከል ነበር። በማያያዝም የኢትዮጵያ መንግስት በጅቡቲ መንግስት ላይ አመኔታ እንዲኖረውና የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ለማበላሸት የሚጥር የየትኛውንም የውጭ ኃይሎች ቅስቀሳ እንዳያዳምጥ ጥሪ አስተላለፉ።[110] ግንኙነቱን ይበልጥ ከማጠናከር አንፃር ግን የሁለቱ መንግስታት አለመተማመን ተጨማሪ የአንድ

---

[108] ስለዚህ ጉዳይ ቀጣዩን ምዕራፍ ተመልከት

[109] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 57-D3 ፡ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የቀረበ ማስታወሻ፡ የካቲት 1971



ምንጭ፡ አዲስ ዘመን መጋቢት 13፣ 1973

ጎድ መንግስቱ እ.ኤ.አ. በ1984 ጅቡቲን በይፋ በጎበኙ ጊዜም የጋራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ፣ የዲፕሎማቲክና ልዩ ፓስፖርት የያዙ የሁለቱ አገሮች ባለስልጣኖችና ግለሰቦች ያለ ቪዛ እንዲዘዋወሩ የሚያስችሉ ስምምነቶች ተፈረሙ:: የጋራ ኮሚሽኑ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ በተሰበሰበበትም ወቅት ተጨማሪ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች ተፈርመዋል:: ከነዚህም መካከል የቱሪዝም ማስፋፊያ ስምምነት፣ የጠረፍ አስተዳዳሪዎች/ኮሚሽነሮች የጋራ ኮሚቴ ማቋቋሚያ እና የጋራ የደህንነት ኮሚቴ ማቋቋሚያ ስምምነት ይገኙበታል:: በመጨረሻም እ.ኤ.አ. በ1987 ሁለቱ መንግስታት የመንገድ ትራንስፖርት ስምምነቱን አጸደቁ::[113]

የእነዚህ ስምምነቶችና ፕሮቶኮሎች መፈረም ከጅቡቲ ነፃነት በኋላ በሁለቱ አገሮች መካከል ተፈጥረው የነበሩ ችግሮች እልባት ለማግኘታቸው አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል:: ነገር ግን ሁሉን አቀፍ መግባባት ላይ ተደረሰ ለማለት አያስደፍርም:: የፕሬዚደንት ጉሌድን ጉብኝት ተከትሎ በነበሩት አምስት ተከታታይ ዓመታት በሁለቱም መንግስታት በኩል ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን የሌላኛውን ወገን አጸፋ በመፍራት ጥንቃቄ ሲደረግ ነበር:: በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችለው ለጅቡቲ መንግስት ተቃዋሚዎች ጥገኝነት ላለመስጠት የተላለፉ ውሳኔዎች ናቸው:: በሂደት ግን ተቃዋሚዎችን የማደራጀቱ እና የመርዳቱ እንቅስቃሴ ስለመበራከታቸው መረጃዎች ያመላክታሉ::

በአገራቱ መካከል ለተፈጠረው መግባባት ዋነኛ አመላካች ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው በምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታዊ ድርጅት (Inter-Governmental Authority on Drought and Development, IGADD) ምሥረታና (ጥር 1978) ሂደት ወቅት የተስተዋሉ የጋራ ጥረቶች ናቸው:: የድርጅቱ ቋሚ መቀመጫ በጅቡቲ እንዲሆን ሐሳብ ያቀረበችውና ለዚሁም ተፈጻሚነት



የግዛቱን ባለሥልጣናት ያሳመነችው ኢትዮጵያ ነበረች:: ይህም ከሱዳን በኩል ተነስቶ የነበረውን ተመሳሳይ ጥያቄ ለማከላሸትና ክፍለ አህጉራዊው ተቋም በአረብ/እስላማዊ መንግስታት (ሱዳንና ሶማሊያ) ተጽዕኖ ስር እንዳይወድቅ በማሰብ የተከናወነ ነው:: ለኢትዮጵያ ይህንን ለማስፈፀም በወቅቱ ወዳጅነቱን አድሶ ከነበረው ከጅቡቲ መንግስት የተሻለ አማራጭም አልተገኘም:: በተጨማሪም የጅቡቲ ሰዎች እንደዚት ጥያቄውን ማቅረብ እንዳለባቸው፣ አባል አገራቱን ለማሳመን መውሰድ ያለባቸው የቅድሚያ እርምጃዎች (initiatives) እንዲሁም የድርጅቱን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብ እንዲያዘጋጁ ወዘተ ጥቆማ ቀረበላቸው:: የኢትዮጵያ እርምጃ ከጅቡቲ ጋር የተመሰረተውን ወዳጅነት ከማጠንከሩም ባሻገር ክፍለ-አህጉራዊው ድርጅት በቅርብ ክትትል ሥር እንዲውል መንገድ ጠረገ::[114]

ኢትዮጵያም ኢጋድ የሚያራምዳቸውን የማህበራዊና ኢኮኖሚዊ የልማት ፕሮጀክቶች እውን ከማድረግ ባሻገር በዚሁ ተቋም ጥላ ሥር ከጅቡቲ ጋር የሚያስተሳስሩትን የጋራ እቅዶች ነድፋ ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ጀመረች:: ለምሳሌ በድርጅቱ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ አሥር ያህል ክፍለ-አህጉሩን የሚያስተሳስሩ ፕሮጀክቶች አቅርባ ከነዚሁ ውስጥ ስድስቱ በተግባር እንዲውል ማስጸደቅ ችላ ነበር:: ጅቡቲን በተመለከተ የተፈቀዱት በ150,000 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ሊከናወን የታቀደው የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የባቡር ሐዲድ መሥመር ጥገና እና 230,000 ሚሊዮን ዶላር በጀት የተመደበለት የኢትዮ-ጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ መሥመር ዝርጋታ ናቸው:: ከነዚህም በተጨማሪ ከፍተኛ በጀት የተያዘላቸው የአዘዞ-መተማ-ገዳሪፍ መንገድና ፓን አፍሪካን ቴሌኮሚኒኬሽን ማይክሮዌቭ መሥመር (ከሱዳን ጋር)፤ የፊስገወይን-ቀለም-ናማሪፒት-ሎዲታኡንግ-ሎድዋር መንገድ (ከኬንያ ጋር) ይገኙባቸዋል::[115]

[113] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ግንኙነት፤ በሁለቱ አገሮች ግንኙነት ዙሪያ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ጥቅምት 7፣ 1984



[114] Belete Belachew, *Black Ethiopia: a Glimpse into African Diplomacy* (Tsehai Publishers: Los Angeles, 2014), pp. 41-43.

[115] ዝኒ ከማሁ, pp. 48-49.

ነገር ግን በህዳር 1979 የጅቡቲ መንግስት በድብቅ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲገባ ያደረገው የጦር መሳሪያ ጉዳይ በኢትዮጵያ በኩል ለተወሰዱ አጸፋዊ እርምጃዎች መነሻ ሆነ። መሳሪያው በኢትዮጵያ የሚገኙት የኢሳ ጎሳ አባላት ከአፋሮች ጋር ለሚያደርጉት ውጊያ እንዲውል የታሰበ መሆኑ የጅቡቲ መንግስት የውስጥ ፖለቲካ ሚዛኑን ከጋራ ድንበሩም ባሻገር ለማስረፅ እየሞከረ ስለመሆኑ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ። በወቅቱ በተካሄዱ የአፋር-ኢሳ ግጭቶች አፋሮች የበላይነት ነበራቸው። በጅቡቲው የኢሳ-ሶማሌ መንግስት እምነት ይህ ሊሆን የቻለው የኢትዮጵያ መንግስት ከአፋሮች ጋር በመወገኑ ነበር። የመሳሪያ አቅርቦቱ ይህንን ለመቀልበስ ያለመና በሂደቱም ኢሳዎችን ለማደራጀት ያቀደ እንደነበር በኢትዮጵያ በኩል ተገምቷል።[116]

በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ የጎሳ ግጭቱን ለመፍታት አንዱ መፍትሄ የሆነውን አፋሮቹንና ኢሳዎችን በእኩል ትጥቅ ማስፈታት የሚለውን መፍትሄ ለመቀበል አልተፈለገም። ይልቁንስ የአፋሩን ወገን ማጠናከሩና የሐሰን ጉሌድን ተቃዋሚዎች ማደራጀቱ እና መርዳቱ የጅቡቲን ሁኔታ ለመቆጣጠር አማራጭ የተጽዕኖ መሳሪያ ሆኖ እንዲቀጥል ታቀደ።

1981 መጀመሪያዎቹ ላይ በኢትዮጵያ በኩል የሁለቱን አገሮች ግንኙነት እንደገና ለማጤን ያስገደዱ ውስብስብ ችግሮች ተከሰቱ። ከነዚህ መካከል ዋነኛዎቹ በጅቡቲ እየተባባሰ የመጣው ጭፍን የሶማላይዜሽን ፖሊሲ እና የሥልጣን ውርርስን በሚመለከት በኢሳ ጎሳ ውስጥ የተከሰተው ትግል ነበሩ። የሐሰን ጉሌድ መንግስት የተከተለው ኢሳ-ሶማሌዎችን በብዛት የማስፈርና የማደራጀት፣ አፋሩን ከምርጫ መዝገቦች የመሰረዝና የዜግነት መብት የመንፈግ እንዲሁም ከፖለቲካውና ኢኮኖሚው ሥልጣን የማግለል ይፋ ፖሊሲ፣ 75 ከመቶ የሚሆነውን የጅቡቲን ጦር ከኢሳ-ሶማሌ በተውጣጡ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ማድረጉ ወዘተ በኢትዮጵያ በኩል በአደገኛነት እንዲፈረጅ አደረገው። አጠቃላይ ሂደቱ በኢሳውና በአፋሩ መሀከል የፈጠረው ከባድ ቅራኔ የጅቡቲን የውስጥ መረጋጋት ከማደፍረሱም በላይ በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው እሙን ነበር።[117]

ከነፃነት በኋላ በተደረጉ የሕዝብ ቆጠራዎች የኢሳ-ሶማሌውን ፍፁም የበላይነት ለማረጋገጥ ሲባል የጅቡቲ አፋሮች ብዛት የግዛቱን 20 ከመቶ ብቻ በሚወክል መልኩ ተስተካከለ። ቀደም ባሉ ወቅቶች በቁጥር አብላጫ የነበሩት አፋሮች በ1980ቹ መጀመሪያ ብዛታቸው በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ ተደርጎ 60,000 ብቻ እንደሆኑ በይፋ ተገለጠ። የኢሳ-ሶማሌው ቁጥር በአንፃሩ በ1947 በተደረገው ቆጠራ ከነበረበት 16,000 ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ወደ 200,000 ከፍ እንዲል ተደረገ። ይህ በግዛቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህልውና ውስጥ የኢሳዎችን ፍፁም የበላይነት ለማረጋገጥ የተወጠነ እቅድ ነበር። በተጨማሪም እንደ አገር አስተዳደር፣ ኢኮኖሚና ፋይናንስ፣ ውጭ ጉዳይ፣ ንግድ፣ ትራንስፖርትና ቱሪዝም፣ ወደብና የባህል ጉዳይ ያሉ ቁልፍ የሚኒስትር መሥሪያ ቤቶች በኢሳ-ሶማሌዎች የተያዙ ሲሆን የመከላከያ ሚኒስትርነቱ ለአፋር ቢሰጥም ዕውነተኛ ሥልጣኑ የፕሬዚደንቱና የኢታ ማገር ሹሙ ነበር።

አፋሮቹ በጎጥ መከፋፈላቸው የጋራ ግንባር እንዳይመሠርቱ ካገዳቸው ምክንያቶች ዋነኛው ነበር። በሂደትም ከጅቡቲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ህይወት በከፍተኛ ሁኔታ የተገለሉበት

[116] ውጉማ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 5፤ ብርሃኑ ባዩህ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ለተስፋዬ ገብረኪዳን (የአገር መከላከያ ሚኒስትር)፡ ህዳር 9፣ 1979፤ አምባሳደር ወሰን በሻህ ለአምባሳደር ይልማ ታደሰ (ውጉማ የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)፡ ህዳር 9፣ 1979፤ ብርሃኑ ባዩህ ለተስፋዬ ገብረኪዳን ለተስፋዬ ወልደሥላሴ (የሀገርና ሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ሚኒስትር)፡ ህዳር 10፣ 1979፤ እንዳለ ተሰማ (የአገር አስተዳደር ሚኒስትር) ለብርሃኑ ባዩህ፡ ታህሳሥ 27፣ 1979

[117] ውጉማ፡፤- ኢትዮ-ጅቡቲ ግንኙነት፤ ስለ ጅቡቲ የቀረቡ የጥናት ሪፖርቶች፡ ጥቅምት 13፣ 1981፤ ጥቅምት 7፣ 1984.

ደረጃ ላይ ደረሰ። በተቃራኒው የጉሌድ ወገኖች ከኢትዮጵያ ጋር የተፈጠረውን የመግባባትና የመተባበር ፖሊሲ በመጠቀም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጡንቻቸውን ይበልጥ አጎለበቱ። በተለይ በኢኮኖሚው ረገድ በባቡርና በመንገድ ትራንስፖርት የሚካሄደው ተመላላሽ ንግድ በኢሳ-ሶማሌዎች ተያዘ፣ የጫት ንግድ በሞኖፖል ለአንድ ኢሳ-ሶማሌ ተሰጠ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እና የቁም ከብት ንግድ በኢሳ-ሶማሌዎች እጅ ሆነ ይህንኑም ተከትሎ የኮንትሮባንድ ንግዱንም ተቆጣጠሩት። የባቡሩ መስመር ሙሉ በሙሉ በኢሳ-ሱማሌ ግዛት ውስጥ ማለፉ ለዚህ ዕውነታ የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል።[118]



የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር መሥመር በጅቡቲ ግዛት ውስጥ
(ምንጭ፡ ውጉሚ)

[118] ዝኒ ከማሁ. Schraeder, 206-211.





በኢትዮጵያ በኩል የጅቡቲን ጉዳይ ለማጤን ያስገደደው ሁለተኛው ምክንያት በኢሳዎች መካከል የተከሰተው የሥልጣን ሽኩቻ ነበር። የፕሬዚደንት ጉሌድ በዕድሜ መግፋት (በጊዜው ከ70 ዓመት በላይ መሆን) እና ጤና ማጣት በኢሳው መካከል ለተከሰተው የሥልጣን ፉክክር እና መከፋፈል ዋነኛው መንስኤ ነበር። ከህገ መንግስታዊ ድንጋጌና ከፓርቲው ሥነ ሥርዓት ውጭ በኢሳዎች የጎሳ ፖለቲካ ላይ የተመሠረተው የሥልጣን ውርርስ ሌላኛው የችግሩ ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ኢሳዎች በሁለት ታላላቅ ቤቶች (አብጋልና ዳሎል) የተከፈሉ ሲሆን አገሪቱን የመምራቱ ሥልጣን በሁለቱ ቤቶች ተወካዮች በፈረቃ እንዲያዝ የሚያስችል ያልተፃፈ ስምምነት እንደነበር ይታመናል። የውጥረቱ አንደኛው መነሻ በሥልጣን ላይ የሚገኘው የአብጋል ቤት ሥልጣኑን ለማስቀጠል ካሳየው ፍላጎት ባሻገር ከራሱ ንዑስ ጎሳ (ማማሳን) አባላት መካከል ቀጣዩን መሪ ለመሾም መፈለጉ ነው። በጅቡቲ ከሶማሌይዜሽን እንቅስቃሴው ጎን "የማማሳናይዜሽን" ፖሊሲ መካሄዱ እና የመንግስቱን ስልጣን በጉሌድ የሥጋ ዘመዶች ቁጥጥር ሥር ለማቆየት እየተደረገ ያለው ጥረት በሶማሊያ እንደታየው የሥልጣን ተዋረዱ ቤተሰባዊ አዝማሚያ እየያዘ ስለመምጣቱ አመላካች ተደርጎ ተወሰደ።

ሁኔታውን ይበልጥ ያወሳሰበው የሥልጣን ውርርሱ ቤተሰባዊ ገፅታ መያዙን የሚቃወሙ ማማሳኖች መኖራቸውና ይህም በአብጋል ቤት ውስጥ የፈጠረው ልዩነት፤ ጉዳዩ በአብጋልና በዳሎል ቤቶች መካከል ይፋ የሆነ ሽኩቻ ማስከተሉ፤ እና ይህን ተከትሎ የፕሬዚደንት ጉሌድን መንግስት የሚቃወሙ የኢሳ ወገኖች በውጭና በውስጥ መደራጀት መጀመራቸው ነው። በተከሰተው የሥልጣን ሽኩቻ በተለይ ኢስማኤል ኦማር ጌሌ፣ ሙሜን ባህዶን ፋራህ፣ ኢስማኤል ጌዲ ሀሬድ እና ሞሀመድ ጃማ ኤላቤ ለፕሬዚደንታዊው ወንበር ዋነኛዎቹ ተቀናቃኞች እንደሆኑ ተለይቶ ታወቀ። የስልጣን ሽኩቻውም በሚያዝያ 1991 ሲጠናቀቅ ኢስማኤል ኦማር ጌሌ አጎታቸውን ተክተው ቀጣዩ የጅቡቲ ፕሬዝደንት ሆኑ።[119]

[119] Amedee Bollee, "From French Outpost to US Base", in *Review of African Political Economy*, Vol. 30, No. 97 (Sept. 2003), 481-484.




የጅቡቲ-አዲስ አበባ ምድር ባቡር መሥመር በጅቡቲ ግዛት ውስጥ

(ምንጭ፡ ወ.ገ.ሚ.)

## 3.3. ድህረ-1983 የግንኙነት አቅጣጫ

በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት ከላይ በተዘረዘሩት ተቃዋሚዎች አማካኝነት የእርስ በእርስ ጦርነት ገፅታ ያለው ውጊያ በጅቡቲ እየተካሄደ ነበር። ከ1984 መጀመሪያ እስከ 1986 ድረስ F.R.U.D. የአገሪቱን ሰሜናዊ ክፍል ከታጁራና ከኦቦክ ከተሞች በስተቀር በቁጥጥሩ ሥር ማዋል ችሎ የነበር ሲሆን በኤደን ሮብሌ እና በኦማር ኤልሚ ካይሬ የሚመሩት ሁለት የኢሳ ታጣቂ አንጃዎችም በደቡባዊ ጅቡቲ (በአይሻና በአሊ-ሳቢየ) በስፋት መንቀሳቀስ ጀመሩ። ምንም እንኳን በስተመጨረሻ F.R.U.D. በታህሳስ 1987 ጦርነቱን ለማቆም ቢስማማም ከተወሰኑ መሪዎቹ (አሊ ሞሐመድ ዳውድ እና ኦጎሬ ክፍሌ አህመድ) በስተቀር የተቀሩት የአመራር አካላት ቃል የተገባላቸውን ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን ሳያገኙ ቀሩ። እነኚህም ተሿሚዎች ቢሆኑ ስልጣናቸው ዘለቄታ አልነበረውም። FRUD-Armé የተሰኘው በአህመድ ዲኒ የሚመራው አንጃ ግን የተኩስ ማቆሙን ስምምነት ባለመቀበሉ እስከ የካቲት 1992 ድረስ በትጥቅ ትግሉ ቀጠለ። በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅትም ኤርትራ የጅቡቲ ወደብ ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን ግልጋሎት እንዲያጨናግፍላት ተጠቅማበት ነበር።[122]

ከ1983 በኋላ ባሉ ዓመታት የኢትዮጵያንና ጅቡቲን የግንኙነት አቅጣጫ የወሰኑ ክስተቶች ነበሩ። በታህሳስ 1987 በፍሩድ (F.R.U.D.) አንጃና በጉሌድ መንግስት መካከል የተፈረመው የተኩስ አቁምና የትብብር ስምምነት በግዛቱ የተፈለገውን መረጋጋት አለማምጣቱ አንዱ እክል ነበር። ስምምነቱን ተከትሎ ይፋ የተደረገው የሚኒስትሮች ሹመት ሁሉንም ክፍሎች ያላስደሰተ መሆኑ፣ መንግስት ከተቃዋሚዎች ጋር ላደረጋቸው ጦርነቶች ማካካሻ በሠራተኞች ላይ ጥሎት

---

[122] ገዚ ከማሁ፤ አምባሳደር ወሰን በሻህ ለሥዩም መስፍን (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ስለ ጅቡቲ ወቅታዊ ሁኔታ የቀረበ ማስታወሻ፣ ታህሳሥ 8፣ 1984. Bollee, 481-482.





የነበረው ቀረጥ (patriotic tax) ከሠላም ስምምነቱ በኋላ ከነበረበት 10 ፐርሰንት ወደ 15 ፐርሰንት እንዲያድግ መደረጉ ያስከተለው የስራ ማቆም አድማ ወዘተ የፖለቲካ አለመረጋጋቱን ደረጃ ያመላክታል።

በአዲሱ የካቢኔ ድልድል ውስጥ ሁለት የፍሩድ አመራር አባላት ብቻ እንዲገቡ መደረጉ ከድርድሩ ተጠቃሚ ባልሆነው አህመድ ዲኒ የሚመራ የትጥቅ ትግል በሰሜናዊ ጅቡቲ እንዲቀጥል ምክንያት ሆኖ ነበር። በአብዛኛው ታዛቢ ዘንድም የሰላም ስምምነቱና የካቢኔ ሽግሽጉ የታይታ (cosmetic) እንደሆነና መንግስቱ የመድብለ ፓርቲ እንደመሠረተ ለማስመሰል የተደረገ እንደሆነ ግምት ተወስዷል። ምንም እንኳን ፍሩድ በጅቡቲ መንግስት እንደ አራተኛ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ተመዝግቦ መንቀሳቀስ የቻለ ቢሆንም ይህም ቢሆን ኢስማኤል ኦማር ጌሌ ለስልጣን ምኞታቸው መወጣጫ እርካብ አድርገው ለመጠቀም ያዋሉት እንደሆነ ይታመናል። በተቃራኒው የጉሌድ መንግስት በአፋሮች አነሳሽነት በሰሜኑ የጅቡቲ ግዛት የተከሰተውን ችግር በወታደራዊ እርምጃ የመፍታቱን አማራጭ ማስቀደሙ የፖለቲካ አለመረጋጋቱን ይበልጥ አባባሰው።[123]

የግዛቱን ፖለቲካዊ ህይወት ይበልጥ ያወሳሰበው ችግር የገዢው ፓርቲ በሁለት ተቀናቃኞች የስልጣን ሽኩቻ ሥር መውደቁ ነበር። የፕሬዚደንት ጉሌድን እድሜ መግፋት ተከትሎ በኢስማኤል ኦማር ጌሌ እና ኢስማኤል ጌዲ ሀሬድ የሚመራ ጎራ ተፈጠረ። በአብጋል-ማማሳንና እና ዳሎል ጎሳ አባላት መካከል የተከሰተው ውጥረት ወትሮውንም በአንድ ቤተሰብ ቁጥጥር ሥር የነበረውን የበላይነት በእጅጉ የፈተነ ሆነ። ፕሬዚደንቱም ለቅርብ ዘመዳቸው የማድላት አዝማሚያ አሳዩ። በሂደቱም በ1988 በተላለፈ ፕሬዚደንታዊ መመሪያ የካቢኔ ኃላፊ የሆኑት

---

[123] ወጉሚ፦ የጎረቤት አገሮች ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት፣ ህዳር 17 እና ታህሳስ 3፣ 1988

ኢስማኤል ጊሌ የአጎታቸውን ሥልጣን ለመረከብ የሚያስችል መደላድል የፈጠረ ወሳኝ የሆኑ የደህንነት፣ መከላከያ፣ የአገር ደህንነትና መረጃ፣ ዓለም አቀፍ ጉዳዮችና ትብብር፣ የፍትህ ጉዳዮች ወዘተ በተደራቢ እንዲመሩ ተደረገ። ኢስማኤል ኦማር ጊሌም ቀድሞም ጎልብቶ ይታይ የነበረው የወሳኝነት ሚናቸው አሁን በይፋ በተቆጣጠሯቸው ቁልፍ የሚኒስቴር መ/ቤቶች አማካኝነት ይበልጥ ተጠናከረ።

የግዛቱ የስልጣን ሽኩቻ በዚህ አላበቃም። ከህዳር እስከ ጥር 1988 ባሉ ወራት በሁለት ቡድን የወገኑ ከፍተኛ ባለስልጣናት ሌላ ዙር የፖለቲካ ውጥረት ፈጠሩ። የሽኩቻው መንስኤ የነበሩት አካላት በፍትህ ሚኒስትሩ በሙሚን ባህዶን ፋራህ እና በካቢኔ ጉዳዮች ኃላፊው በኢስማኤል ኦማር ጊሌ ወገን በተፃራሪነት ተሰልፈው ይፋ በሆነ መልኩ በአደባባይ ያካሰሱና ይዘላለፉ ነበር። በነዚህ ወራት ደግሞ ፕሬዚደንት ጉሌድ ለከፍተኛ ህክምና ፈረንሳይ ስለነበሩ ለችግሩ የማዳግም መፍትሔ ሊያበጁ አልቻሉም። ፕሬዚደንቱ ከህክምና ቆይታቸው ሲመለሱም የፍትህ ሚኒስታሩንና ዋነኛ ደጋፊያቸውን የመከላከያ ሚኒስተሩን (መሐመድ ቡላሌ ባሬህ) ከስልጣን ማስወገዳቸው ለተከሰተው ውጥረት ሁሉን አቀፍ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ የጎሳቸውንና የቤተሰባቸውን ጥቅም ማስቀደማቸውን ያመላክታል። ይልቁንም ኢስማኤል ጊሌ የአገሪቱ ቀጣይ መሪ ለመሆን የሚያስችላቸውን መደላድል እንዲያበጁ መንገድ ጠረገ።[124]

በኢትዮጵያ ውስጥም በተለይ በአፋር ህዝቦች መኖሪያ አከባቢዎች የተከሰቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ለአገሪቱ ግንኙነት መቀዛቀዝ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው አልቀረም። ደርግ ከስልጣን በተወገደበት ወቅት በአፋር ሁለት ዋነኛ የፖለቲካ ድርጅቶች - የአፋር ብሔራዊ የነፃነት ንቅናቄ (Afar National Liberation Movement, ANLM) እና የአፋር ነፃነት ግንባር (Afar Liberation Front, ALF) - በክልሉ ይንቀሳቀሱ ነበር። ከሁለቱ

[124] ውጉሚ፡- የጎረቤት አገሮች ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት፡ ግንቦት 23፣ 1988





መካከልም በሱልጣን አሊ ሚራህና በልጃቸው ሐንፈሬ አሊ ሚራህ የሚመራው የአፋር ነፃነት ግንባር (ALF) በድህረ 1983ቱ የኢትዮጵያ መንግስት መዋቅር ውስጥ በአጋርነት መሳተፍ ቻለ። የሱልጣኑ ሌላኛው ልጅም የአፋር ክልል ፕሬዚደንት ሆኖ ተመረጠ። ነገር ግን በአፋሩ ግንባርና በአዲሱ የኢትዮጵያ መንግስት ገዢ መደብ መካከል የነበረው ፍቅር ረጅም ዕድሜ ሊዘልቅ አልቻለም። የፖለቲካ ቅራኔውም ከግንቦት 1986 በኋላ ALF በሐንፍሬ እና በታናሽ ወንድሙ በኡመር መሪነት ለሁለት እንዲከፈል መንገድ ጠረገ። በመጨረሻም በነሐሴ ወር 1987 የALF ፖለቲካዊ ህልውና አክትሞ ክልሉ አዲስ በተመሠረተው የአፋር ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (Afar Peoples' Democratic Organization, APDO) አመራር ሥር እንዲውል ተደረገ።[125]

ከዚህ የውስጥ ፖለቲካ ውጥንቅጥ ማግስትም ኢትዮጵያ ከጅቡቲ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ጀመረች። መንግስት በግዛቱ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ከገፋፉት ነገሮች መካከል የጅቡቲ መሪዎች ከዓለም የገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ባገኙት ከፍተኛ የገንዘብ ብድር የጅቡቲን ወደብ አገልግሎት ለማደርጀት የጀመሩት ጥረት ነው። ይህም እርምጃ ለበርካት ዓመታት በአንድ ተመን ተወስኖ የቆየውን የወደቡን የአገልግሎት ዋጋ ተመን ለመቀየር መንገድ እንደሚጠርግ ግንዛቤ ተወሰደ። በመካከሉም በ1987 መጨረሻ አከባቢ የኢትዮጵያ መንግስት ለሁለት አሥርት ዓመታት ያክል ለውጥ ሳይደረግበት የቆውን የአትክልትና ፍርፍሬ ምርቶች የዋጋ ተመን ለማሻሻል ማሰቡን ለጅቡቲ ገለጸ። እቅዱ ከተመን ማሻሻልም ባሻገር እስከዚያን ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ ብር ሲከናወን የነበረውን ንግድ በአሜሪካን ዶላር ለመቀየር ያለመ ነበር። ወሳኔው ከጅቡቲ በኩል ተቃውሞ ያስከተለ ከመሆኑም በላይ የግዛቱ ባለስላጣናት የአትክልትና

[125] Yasin Mohamed Yasin, pp 48-52. Dereje Feyissa, "Centering the Periphery? The Praxis of Federalism at the Margins of the Ethiopian State," in Ethiopian Journal of Federal Studies. Vol. 1, No. 1 (June 2013), pp. 178-179.

ፍርፍሬ ምርቶች እንዳይገቡ በመከልከላቸው የሁለቱ አገራት ንግድ ለበርካታ ወራት ተቋርጦ እንዲቆይ መንገድ ጠረገ። እነዚህ እርምጃዎች በኢትዮጵያ በኩል ሲወሰዱ አገራቱ በአሰብ ወደብ የመጠቀም አማራጭን ከግንዛቤ አስገብታ መሆኑ መታሰብ ይገባዋል።[126]

ቀጣዩ የኢትዮጵያ መንግስትም እንደቀደሙት መንግስታት ሁሉ የጅቡቲን ሁኔታ ግዛቱ ካለው ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ አንፃር በመመዘን መንቀሳቀስ ግዴታው ነበር። ነገር ግን እስከ 1990ቹ መጀመሪያ በጅቡቲ የተከሰተው የስልጣን ሽኩቻ እስኪበርድ፤ በኢትዮጵያም በኩል የአፋር የውስጥ ፖለቲካ አሁን ያለውን ገፅታ እስኪያገኝ ሁለቱ አገሮች በከረሙ መግባቢያዎች ላይ በመመርኮዝ በዘልማድ ሲንቀሳቀሱ ለመቆየት ተገደዋል። በሚያዝያ 1986 በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና የጋራ ፀጥታ ጉዳዮች ላይ የመግባቢያ ስምምነት የተፈራረሙ ቢሆንም አፈጻጸማቸው እምብዛም ነበር። ከረጅም ፍትጊያ በኋላ የእስማኤል ኦማር ጌሌ ወደ ስልጣን መምጣት እና የነሱልጣን አሊሚራህ የአፋር ግንባር (ALF) አፍቃሬ መንግስት በሆነው ግንባር (APDO) መተካት ለአገራቱ ግንኙነት መሻሻል አስተዋጽኦ አበርክቷል። ይህንንም ተከትሎ ፕሬዚደንት ጌሌ በጥቅምት 1992 ኢትዮጵያን ለአራት ቀናት በይፋ ጎበኙ፤ አገራቱም በተለያዩ ዘርፎችም የትብብር ስምምነት ተፈራረሙ።[127]

[126] ወጉማ፡- የጎረቤት አገሮች ወቅታዊ ሁኔታ ሪፖርት፡ ህዳር 17፣ ታህሳስ 3 እና ጥር 16፣ 1988

[127] አዲስ ዘመን፡ ጥቅምት 22-25፣ 1992.







ምንጭ፡ አዲስ ዘመን ጥቅምት 25፣ 1992

በሁለቱ አገሮች የግንኙነት ስሌት ውስጥ አዲስ የተፈጠረ እውነታ ቢኖር የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን ነው። የቀደሙ መንግስታት ስለ ጅቡቲ ስትራቴጂካዊ ወሳኝነት ሲከራከሩ የሁለት ብሔራዊ ወደቦች (አሰብ እና ምፅዋ) ባለቤት ሆነው ነበር። ከ1983 በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ለመገልገል ከኤርትራ መንግስት ተፈቅዶላት ስለነበር ጅቡቲን በተመለከተ የነበራት አቋም በምርጫና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሆኖ ቆይቷል። ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት (1990-1992) ጀምሮ ግን የግንኙነቱ መርህ በከፍተኛ ደረጃ ተለወጠ። ጅቡቲ ብቸኛ መውጫ በር የመሆኑ ጉዳይ በብዙ መንገድ የግዛቱ መሪዎች ፍላጎታቸውን በኢትዮጵያ ላይ እንዲጭኑ መብት ሰጣቸው። ለዚህ እውነታ ዋነኞቹ መገለጫዎች በምድር ባቡሩ እና በወደቡ አጠቃቀም ላይ የተከሰቱ ለውጦች ናቸው።



የትብብር ስምምነቱ ሲፈረም

ምንጭ፡ አዲስ ዘመን ጥቅምት 25፣ 1992

# ምዕራፍ ፬

# ጅቡቲ–አዲስ አበባ ምድር ባቡር

## 4.1. የባቡር መሥመሩ ህልውና ጅምር

ዳግማዊ ምንሊክ በመጋቢት 1886 (March 1894) ለሙሴ አልፍሬድ ኤልግ በሰጡት ፈቃድ (concession) መሠረት ከሁለት ዓመት በኋላ ሥራው የተጀመረው የጅቡቲ አዲስ አበባ ምድር ባቡር ዝርጋታ በሰኔ 1909 (7 June 1917) ተጠናቆ ተመርቆ ተከፈተ:: የመጋቢት 1886ቱ ውል እንደሚያመለክተው የምድር ባቡሩ በግል ንብረትነት የሚተዳደር ሆኖ ከ99 ዓመታት በኋላም ከባንያው ከነቋሚ ንብረቶቹ ለምንሊክ ይመለሳሉ::[128] ኩባንያው ሕጋዊ ህልውና ኖሮት ሥራ ከጀመረበት ከነሐሴ 1888 ጀምሮ እስከ 1900 የኢትዮጵያ ምድር ባቡር በመባል ሲጠራ ቆይቷል:: መጋቢት 1901 (8 March 1909) የተደረገውን ተጨማሪ ስምምነት ተከትሎ የኢትዮ-ፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያ በመባል እስከ 1952 ቆየ:: በ1952 በኢትዮጵያና በፈረንሳይ መንግስታት በተደረገው ድጋሚ ስምምነት አዲስ የአስተዳደር አቋም ይዞ መተዳደር ጀመረ::

የኢትዮ-ፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያ (Chemin de Fer Franco-Ethiopien) በተለይ ከወቅቱ አውሮፓዊ ልዕለ-ኃያላን አንዷ የነበረችው ፈረንሳይ በነዓይቱ ኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ ቅኝ ለመመሥረት የነበራት ውጥን ዋነኛ መገለጫ ተደርጎ ሊወሰድ

128 Shiferaw Bekele, "The Ethiopian Railroad and British Finance Capital, 1896-1902," in *Africa: Rivista trimestrale di studi e documentazione dell'Istituto italiano per l'Africa e l'Oriente*, Anno 46, No.3 (Sept. 1991), 351-359.





ይችላል:: የኩባንያው አስተዳደር እና የገንዘብ ምንጭ ሙሉ በሙሉ ተቀማጭነቱ በፓሪስ ፈረንሳይ በሆነ የግል ድርጅት (Compagnie Chemin de Fer Franco-Ethiopien de Djibouti á Addis-Ababa) ኃላፊነት ሥር መደረጉ የዚሁ ግብ መገለጫ ነበር:: ነገር ግን የሐዲዱ ሰባት-ስምንተኛ ክፍል በሉዓላዊ ግዛት ውስጥ መገኘቱ ለፈረንሳይ የኢኮኖሚ ቅኝ ፍላጎት የተመቸ አልነበረም:: ይህንንም ለመቀልበስ የኢትዮጵያን ህልውና ሊጎዳና የፈረንሳይን ብቸኛ ባለመብትነት የሚያስረግጥ የአንድ ወገን ህገ-ደንብ (convention) እስከማጽደቅ ደርሰው ነበር::[129]

ይልቁንም እስከ 1952 ባለው ጊዜ ኩባንያው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ ለሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች የአገልግሎት ክፍያ (rent) እንዲፈፅምና በሐዲዱ መሥመር ላይ አገሪቱ ያላትን የሉዓላዊነት መብት እንዲያከብር የውዴታ ግዴታ እንዲገባ ተገደደ:: የፈረንሳይ መንግስት ኩባንያውንና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማቋቋምና ለማደራጀት ካፈሰሰው መዋዕለ ንዋይ አንጻር ኢትዮጵያን የምንጊዜም የኢኮኖሚ ቅኝ ግዛቱ አድርጎ ቢቆጥር አይፈረድም:: ነገር ግን የኢትዮጵያ መንግስታት የኩባንያውን እንቅስቃሴ ከራሳቸው የኢኮኖሚና የደህንነት አጀንዳ ጋር አቆራኝቶ ለማራመድ ከነበራቸው ብርቱ ፍላጎት የተነሳ ፈረንሳዊያኑ የተመኙትን ለመፈጸም ሳይቻላቸው ቀረ::[130]

129 ዝኒ ከማሁ:: ይህም በጅቡቲው ገዢ ቦንሆር (Bonhoure) እና የባቡር ኩባንያው አስተዳዳሪ ሼፍኑ (Chefneux) መካከል በጥር 1896 (5 February 1902) የተፈረመው መግባቢያ ነው:: የውሉ ዋነኛ ዓላማ የፈረንሳይ መንግስት በከፍተኛ የገንዘብ እጥረት ምክንያት ሥራው በእጅጉ የተጓተተውን የሐዲድ ግንባታ ለማፋጠን የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግ ለማስቻል ነበር:: በተጨማሪም የኩባንያውን ህልውና አደጋ ላይ ጥሎት ነበረውን የእንግሊዞች ጣልቃ ገብነት ለመግታትና ያፈረንሳይን ያልተገደበ የበላይነት ለማረጋገጥ የታለመ እርምጃ ነበር::

የባቡር ሐዲዱ ክብደትና ዋጋ ያላቸውን ዕቃዎች በማመላለስ የሚሰጠው አገለግሎት የታመነበት ቢሆንም የአገልግሎት ክፍያው ለረጅም ጊዜ ከየብስ መገናኛ የሚበልጥ ሆኖ ቆይቷል።ይህንኑ ዋጋ ለመቀነስም ተደጋጋሚ ሙከራዎች ተደርገዋል። ለምሳሌ በ1940 አምስት ሺህ የነበሩት የኩባንያው ሠራተኞች ተቀንሰው 2500 ብቻ እንዲቀሩ ከመደረጉም በላይ ከተቀናሾቹ አብዛኛዎቹ ከፍተኛ ደመወዝ የነበራቸው የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ። በንጉሡ እና በደርግ ባለሥልጣናት ዘንድ የነበረው ግንዛቤ እንደሚያመለክተው ጅቡቲን ከአዲስ አበባ የሚያገናኘው አውራ ጎዳና በአስፋልት እስካልተሰራ እና የአሰብ ወደብንና አሰብን ከአዲስ አበባ የሚያገናኘውን መንገድ በአግባቡ መጠቀም እስካለተቻለ ድረስ ችግሩ ለኢትዮጵያ ጠቃሚ በሆነ መልኩ ሊቀረፍ አይችልም።[132] ከዚህ በመነሳት ተከታታይ ፖሊሲዎች ሲነደፉ የምድር ባቡር ኩባንያውን ጉዳይ በተቻለ መጠን ከአሰብ ወደብ እና የአሰብ-አዲስ አበባ አውራ ጎዳና ተጠቃሚነት ደረጃ ጋር ማያያዙ የተለመደ እየሆነ መጣ።

የ1952ቱ ስምምነት በተፈረመ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተፈራው ኪሳራ በመከሰቱ የኩባንያውን ህልውና በእጅጉ ፈተነ። ከ1959/60 በጀት ዓመት ጀምሮ ሲንከባለል የመጣው ኪሳራ በግንቦት 1962 ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ መድረሱ በሁለቱ መንግስታት መካከል ሽኩቻ አስከተለ። ፈረንሳዮች ለኢትዮጵያ መንግስት በላኩት ማስታወሻ (aide-mémoire) ለችግሩ መከሰት በዋነኛነት ያስቀመጡት ምክንያት (ከስዊዝ ካናል መዘጋት ባሻገር) በአመዛኙ ኢትዮጵያ በአሰብ ወደቧ እና ከአዲስ አበባ አሰብ ባለው አውራ ጎዳና መጠቀም ማዘውተሯን ነው። በፈረንሳይ ባለሥልጣኖች አስተሳሰብ ውድድሩ ኩባንያውን ሊጎዳው የቻለው ቀድሞ በጅቡቲ በኩል ይገቡና ይወጡ የነበሩት ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ የንግድ እቃዎች ወደ አሰብ በመዞራቸውና አሰብም በኢትዮጵያ መንግስት በጀት የሚደገፍ ወደብ በመሆኑ ነው።

[132] ውጉማ፡- ጅቡቲ 51-D3 2፤ ስለ ጅቡቲ የተቀናበረ አጠቃላይ ሪፖርት፡ ሰኔ 28፣ 1968





በኢትዮጵያ በኩል ጉዳዩን እንዲያጣራ የተቋቋመው ኮሚቴ በበኩሉ የኩባንያውን የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት፣ የተጠራቀመ ብድር፣አግባብ ያለሆነና የተበላሸ የግዢ ሥርዓት፣ ከኢትዮጵያውያን የድርጅቱ ሠራተኞች ጋር ሲነፃፀር ለፈረንሳይ ተወላጆች የሚፈፀመው ከፍተኛ የደመወዝና የአበል ክፍያ ወዘተ ለኪሳራው መንስኤ እንደሆኑ ሪፖርት አቀረበ። ሪፖርቱ የኩባንያው የኪሳራ ምንጭ አስተዳደራዊ እንጂ የአሰብ ወደብ ውድድር አለመሆኑን በአፅንኦት አሰረዳ። ለምሳሌ ያህልም በ1952ቱ ስምምነት መሠረት ኩባንያው ኪሣራ ቢደርስበት ከላይ የተጠቀሰውን የተንከባለለ የዕዳ ውርስ ከወለዱ በስተቀር መክፈል ባይገደድም በ1960 ኩባንያው ኪሣራ ላይ እያለ ዕዳውን እንዲከፍል ተደርጓል።

በ1960/61 የሂሳብ ዓመት ኩባንያው ካገኘው 13,338,000 ብር ገቢ ውስጥ 60 ከመቶውን ለሠራተኞቹ ለደመዎዝና ለጥገና ወጪ ከመሆኑም በላይ አከፋፈሉ በጅቡቲ ወገን ላሉ ሠራተኞች በእጅጉ ያደላ ነበር። የባቡር ጎታቾች (locomotives) እና ማንኛውም የመለዋወጫ እቃዎች የሚገዙት ከፈረንሳይ አገር እንዲሆን ቢወሰንም ግዢው በሦስተኛ ወገን በኩል ኦፌሮም (Offerom) በተባለ ድርጅት አማካኝነት መከናወኑ የዋጋ መናርን አስከትሏል። በቴክኒክ ጉድለት ምክንያት በተደጋጋሚ የሚደርሱ የመገልበጥ አደጋዎች ያስከተሉት ከፍተኛ ወጪ፣ የፉርጎዎቹ አስተማማኝ አለመሆን ወዘተ የሪፖርቱ ተጨማሪ መከራከሪያዎች ነበሩ።[133]

የጥናት ሪፖርቱ በማጠቃለያ ያቀረባቸው የማሻሻያ ሐሳቦች በወቅቱ የምድር ባቡሩን ኩባንያ በተመለከተ የነበረውን ጉድለት ያንፀባርቃል። አንዳንዶቹ አስተያየቶች ለፈረንሳይ መንግስት የሚከፈለው ዕዳ ቢቻል እንዲሰረዝ አሊያም ለረጅም ጊዜ ተላልፎ ገንዘቡ ላረጀው የባቡር ሐዲዱ ማሻሻያ እንዲውል ማድረግ፤ በኦፌሮም (Offerom) በኩል ዕቃ ግዢ መደረጉ ቀርቶ በቀጥታ በዓለም አቀፍ ጨረታ እንዲከናወን፤ ኢትዮጵያዊ

[133] ውጉማ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1፡ 13፤ የኩባንያውን ኪሳራ ምክንያቶች ለማጥናት የተቋቋመው ኮሚቴ ሪፖርት፡ ግንቦት 11፣ 1962

ለ) የኢትዮጵያና የፈረንሳይ መንግስታት ለኩባንያው በያንዳንዱ የሥራ ዘመን የሚሰጡት ብድር ቢበዛ የሚከፍሉትን የብድር ጣሪያ ስልሚያመለክት የገንዘቡ መጠን መቀነስ አስፈላጊ አይደለም። ሐ) የኢትዮጵያና የፈረንሳይ መንግስታት ከምድር ባቡር መስመር ተወዳዳሪ የሚሆን ሌላ ማናቸውም ሥራ እንዲሰራ ፈቃድ እንዳይሰጡ የገቡት ግዴታ መሠረቱ እንደዚሁ ተቀባይነት አላገኘም። ለዚህ የተሰጠው ምክንያት "የፈረንሳይ ጥቅም በኢትዮጵያ እንዳይነካ ማድረግ የኢትዮጵያ ዐቢይ የፖሊሲ ዓላማ" በመሆኑ ነው። ይልቁንም ከውጭ ጉዳይ የህግ ባለሙያዎች የቀረበው መከራከሪያ እንደሚያመለክተው የማሻሻያ ስምምነት ማድረጉ በ1952 ውል የኢትዮጵያን ጥቅም በሚጠብቁ አንቀጾች (ለምሳሌ የነፃ ወደብና የመተላለፍ መብት) አተገባበር ዙሪያ መሠረታዊ የሆነ ክርክር ሊያስነሳ ይችላል። ስለዚህ የ1952 ስምምነት ተሻሽሎ አዲስ ስምምነት ከመፈራረም ይልቅ በስምምነቱ እንዲገቡ የታሰቡ ማሻሻያዎች ብቻ ተለይተው በማሻሻያ ፕሮቶኮል መልክ እንዲፈረሙ ማድረጉ ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን መቀሚታ ያጎላዋል። ይህ መሆኑ ደግሞ የ1952 ስምምነት በመሠረቱ ተጠብቆና ተከብሮ እንዲቆይ እንደሚያደርግ ተብራራ።[135]

ከጅቡቲ ነፃነት በፊት ለማድረግ ታቅዶ የነበረው የማሻሻያ ስምምነት ካለመሳካቱም በላይ፤ የግዛቱ ነፃነት እየተቃረበ ሲመጣ የደርግ ባለሥልጣናት አዲሷ አገር የ1952 ውልን ስለመቀበሏ የነበራቸው ተስፋ እየተመናመነ መጣ። የፈረንሳይ መንግስትም በምድር ባቡር ኩባንያ ውስጥ ከነበረው ተሳትፎ የመንሸራተት አዝማሚያን ማንፀባረቅ ጀመረ። በጥቅምት 1969 የፈረንሳይ ባለሥልጣናት በምድር ባቡር ኩባንያው ዙሪያ ከኢትዮጵያ ጋር ለመነጋገር ፍላጎታቸውን ገለፁ። ከጅቡቲ ነፃነት በኋላም

[135] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 13፤ ፀቀለ ገለታ (የፈረንሳይና የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኩባንያ ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅ) ለጌታቸው ክብረት (ውጉሚ በምክትል ሚኒስትር ማዕረግ ቋሚ ተጠሪ)፡ ሰኔ 20፣ 1967





ኢትዮጵያ ከሐሰን ጉሌድ መንግስት ጋር አዲስ ስምምነት መፈራረም እንደሚጠበቅባትም ፍንጭ ሰጡ። ፈረንሳይም ከሁለቱ አገሮች ጋር በተናጠልም ይሁን በጋራ ለመተባበር እንዲሁም የምትጠየቀውን እርዳታና ትብብር ለማድረግ መዘጋጀቷ ተነገረ። በኢትዮጵያ በኩልም የምድር ባቡሩን በተመለከተ አዲሱ የጅቡቲ መንግስት በ1952 የተፈረመውን ስምምነት መቀበል አለመቀበሉ በሂደት የሚታይ መሆኑን አመልክቶ እስከዚያው ድረስ ግን ይህ ውል ጸንቶ እንደሚቆይ ተገለፀ።[136]

በጅቡቲ የነፃነት ዋዜማ ግንቦት 24፣ 1969 የሶማሊያ ሰርጎ ገቦች ባደረሱት ጥቃት የምድር ባቡሩ አገልግሎት መቋረጥ በኩባንያው ህልውና ላይ የበኩሉን ጫና አሳደረ። በቅርቡ ነፃነት የሚጎናጸፉት ጅቡቲያውያንም በምድር ባቡሩ ዙሪያ አዲስ አቋም ማራመድ ጀመሩ። የጅቡቲ ዋነኛው መከራከሪያ የ1952 ስምምነት የተደረገው ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ስለነበርና ፈረንሳይም ከሰኔ 20፣ 1969 ጀምሮ በጅቡቲ ላይ የግዛት ሥልጣን ስለሌላት ስምምነቱ ከዚህ ቀን ጀምሮ ቀሪ ይሆናል። የአዲሱ አገር መሪዎች ኢትዮጵያና ጅቡቲ ሌላ ስምምነት መፈራረም ይኖርባቸዋል የሚል አቋም ያዙ።

የደርግ ባለሥልጣናት ጅቡቲ የ1952 ስምምነትን ለመቀበል የሚያስገድዳት ነገር እንደሌለ ማመናቸው እና ለአዲስ ስምምነት መዘጋጀታቸው በአብዛኛው ጅቡቲን ከሶማሊያ ጎራ ለመነጠል ያለመ የፖለቲካ ውሳኔ እንደሆነ መገመት አያዳግትም። በወቅቱ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ባካሄዱት ጦርነት ጅቡቲ ወደ ሶማሊያ ያጋደለ ፖሊሲ ትከተል እንደነበርና በብዙ መንገድ የኢትዮጵያን ጥቅሞች የሚፃረሩ እርምጃዎችን ትወስድ እንደነበር ማስታወሱ ተገቢ ነው።

[136] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 13፤ ጌታቸው ክብረት (ውጉሚ ቋሚ ተጠሪ) ለአምባሳደር ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ (ፓሪስ)፡ ጥቅምት 15፣ 1969፤ አምባሳደር ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ ለጌታቸው ክብረት፡ ጥቅምት 26፣ 1969፤ ኮ/ል ዶ/ር ፈለቀ ጊዮርጊስ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ለዮሱፍ አህመድ (ትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር)፡ ሚያዝያ 13፣ 1969

የባቡር መሥመሩ ከተቋረጠበት ቀን አንስቶ እስከ መስከረም 1970 ባሉት ወራት ኩባንያው የነበረውን ገንዘብ እና የድርጅቱ ቦርድ በፓሪስ ተሰብስቦ (ሐምሌ 1969) የፈቀደውን 2 ሚሊዮን ብር የኦቨርድራፍት ብድር አሟጦ በመጠቀሙ ባዶ ካዝና ይዞ ለመቀመጥ ተገደደ:: ኩባንያው ሥራውን በአስቸኳይ ካልጀመረም ለሠራተኞቹ ደመወዝ ለመክፈል የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ:: የዚህ ዓይነት ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ የኩባንያው ቦርድ ተሰብስቦ ውሳኔና መመሪያ ማስተላለፍ ይችል ነበር:: ሆኖም የጅቡቲ ነፃነት ተከትሎ በተነሳው የኩባንያው የባለቤትነት ውዝግብ ምክንያት ቦርዱ ሳይሰበሰብ ቀረ::

በግንቦት ወር 1969 የጅቡቲው ፕሬዚደንት ለሊቀ መንበር መንግስቱ በጻፉት ደብዳቤ የኢትዮጵያ መንግስት ከጅቡቲ ጋር አዲስ ስምምነት ለመፈራረም ዝግጁ ከሆነ ድርድሩ እስካለቀ ድረስ የነበረው ሁኔታ እንዲቀጥል የሚስማሙ መሆናቸውን ገልጸው ነበር:: ኢትዮጵያም አዲስ ስምምነት ለመደራደር ዝግጁ መሆኗን እና እስከዚያው ድረስ ፕሬዚደንቱ ባቀረቡት ሃሣብ እንደምትስማማ ገለጸች::[137]

በዚህ መንፈስ በመመራት አስቸኳይ የቦርድ ስብሰባ ለማድረግ እንዲቻል ጅቡቲ በበኩሏ የቦርድ አባሎቿን እንድትመርጥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሐምሌ 1969 ለጅቡቲ መንግስት ደብዳቤ ጻፈ:: የጅቡቲ መንግስት ግን የተፈጠሩትን ችግሮች አጥንቶ በጋራ መፍትሄ የመፈለጉን አስፈላጊነት ቢቀበልም ቀደም ሲል ፕሬዚደንት ጉሌድ አቅርበውት የነበረውን ሃሳብ የሚቃረን አጀንዳ ይዞ ቀረበ:: ከነዚህ ዋነኞቹ የ1952 ስምምነት በጅቡቲ በኩል ተቀባይነት ስለሌለው ሊደረግ ለታቀደው የቦርድ ስብሰባ ሕጋዊ አቋም አለመኖሩ፤ የሁለቱ መንግስታት የጋራ ንብረት የሆነ አዲስ ኩባንያ ለማቋቋም

[137] ዝኒ ከማሁ፤ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ (ውጉሚ ቋሚ ተጠሪ) ለኃይሉ ይመኑ (በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀዳሚ ሚኒስትር)፡ መስከረም 12፣ 1970





ፍላጎት እንዳላቸው፤ "የምድር ባቡር ጊዜያዊ የቦርድ ስብሰባ" ተብሎ መሰየም ባለበት ጉባኤ ለመሳተፍ ፈቃደኞች እንደሆኑ፤ እና በጊዜያዊ ስብሰባው የፈረንሳይ ግለሰብ ባለሀብቶች መሳተፍ እንደሌለባቸው የሚገልጹት ነበሩ::

የምድር ባቡር ኩባንያው የገጠመውን አጠቃላይ ችግር ለመመርመር የተቋቋመው ኮሚቴ ባቀረበው ሪፖርት እንደተገለጸው ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ለሠራተኞች ደመወዝና ለጡረታ አበል ብቻ 6,221,206 ብር ያስፈልጋል:: ለነዳጅ፣ አስፈላጊ ለሆኑ መለዋወጫዎችና ለሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች ተጨማሪ 2,461,050 ብር እንደሚያስፈልግ ተገመተ:: የጅቡቲ መንግስትን አቋም በመመርመርም ኮሚቴው ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ "ጊዜያዊ የቦርድ ስብሰባ" ማድረጉ ለዚሁ ቦርድ ሁለቱ መንግስታት በስምምነት የተለየ ሥልጣን ካልሰጡ በስተቀር ቦርዱ ሕጋዊ አቋም እንደማይኖረው አሳሰበ:: የኢትዮጵያ መንግስትም "የጊዜያዊ ቦርድ" ሃሳብን መቀበል እንደሌለበት ተከራከረ:: ለዚህም የቀረበው ምክንያት ይህን ማድረጉ የ1952 ስምምነትን ፈቅዶ እንደማፍረስ ስለሚያስቆጥር ነው::

በተለዋጩ ግን የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያዘለ መልስ ለጅቡቲ መንግስት ለመላክ ታቀደ:: እነሱም ሀ) ኢትዮጵያ አዲስ ስምምነት ለመፈራረም ዝግጁ መሆኗን እና ድርድሩን ጅቡቲዎች በጠቀሱት ጊዜ (መስከረም ወይም ጥቅምት 1970) ለመጀመር መዘጋጀቷን፤ ፕሬዚደንት ጉሌድ አስቀድሞ በላኩት ደብዳቤ መሠረትም አዲስ ስምምነት እስኪፈረም ድረስ የ1952 ስምምነት ሥራ ላይ እንዲቆይ፣ ጊዜያዊ የቦርድ አባሎች እንዲመረጡና ጊዜያዊ አስቸኳይ የቦርድ ስብሰባ እንዲደረግ፤ በቀረበው ሃሳብ የሚስማሙ ከሆነ "በጊዜያዊ ቦርድ ስብሰባው" የፈረንሳይ የግል ባለአክሲዮኖች ጉዳይ በአዲስ ስምምነት ውሳኔ እስኪያገኝ በስብሰባው ባይካፈሉ የኢትዮጵያ መንግስት የማይቃወም መሆኑን፤ እና ይህ ሃሳብ ተደግፎ እስከ እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20፣ 1977 (ጥቅምት 1970) የቦርድ ስብሰባ ካልተደረገ ለሚፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግስት የበኩሉን መፍትሄ ለመፈለግ የሚገደድ መሆኑን ማሳወቅ ናቸው::

የባለሙያዎቹ ቡድን የቀረበለትን ረቂቅ ስምምነቶች ከመመርመሩ በፊት ከዓለም አቀፍ ህግ አንፃር በምድር ባቡሩ ላይ የኢትዮጵያን መብቶች ለመተንተን ሙከራ አድርጓል። ቡድኑ ጅቡቲ የ1952 ስምምነትን በተመለከተ የያዘችውን አቋም ኢትዮጵያ የማትቀበልበትን ሦስት መሠረታዊ ምክንያቶች በመዘርዘር ይከራከራል። እነዚህም ሀ) ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ያላት የመተላለፍና በጅቡቲ ወደብም በነፃ የመጠቀም ቋሚ መብቶች ከ1952ቱ ስምምነት በፊትም ለረጅም ጊዜ የነበሩ መብቶች (established rights) በመሆናቸው የጅቡቲ መንግስት የፈረንሳይን መንግስት በመተካቱ ምክንያት ብቻ ቀሪ ሊሆኑ አይችሉም። ለ) የ1952 ስምምነት እነዚህኑ መብቶች ያረጋገጠ ስልሆነ በቆየው ልማዳዊ ሕግም (customary international law) ሆነ በዘመናዊው (conventional) የዓለም ሕግ መሠረት ቀሪ የማይሆንና የአንድ አገር መንግስት በሌላ ቢተካም (state succession) ተተኪው መንግስት ሊወርሰው የሚገባ ዓይነት ስምምነት ነው።

በተለይ በዘመናዊው የዓለም አቀፍ ህግ (ኢትዮጵያ የተሳተፈችበትና በአፅንኦት የተከራከረችበት የ1977ቱ የቪየና ስምምነት - The Vienna Convention on Succession of States in Respect of Treaties) አንድ አገር በሌላ በመተካቱ ምክንያት ቀሪ የማይሆኑ ሁለት ስምምነቶች ለዚህ ክርክር መሠረት እንደሚሆኑ ኮሚቴው አስረግጦ ይከራከራል። እነሱም የወሰን ስምምነቶች እና አንድ አገር በሌላ አገር ግዛት ላይ ያለውን የመጠቀም መብቶች የተመለከቱ ናቸው። የኋለኛው ክፍል በወንዞች ላይ የመተላለፍ መብትን፣ የባቡር ሐዲዶችን፣ ዓሣ ማጥመድን፣ በጠቅላላው በየብስና በባህር ላይ የሚደረግ መተላለፍንና የነፃ ወደብ መብትን የሚመለከቱ ናቸው። በተለይ የመተላለፍ መብት (transit right) እና ነፃ ወደብን የሚመለከቱ ስምምነቶች ከወሰን ስምምነት ሌላ ተደጋግመው የሚጠቀሱ (localized ወይም dispositive) ስምምነቶች እንደሆኑ ተብራርቷል።





ሐ) ጅቡቲ በፈረንሳይ ቦታ የተተካ በመሆኑ ብቻ የ1952 ስምምነት ቀሪ ነው የሚለውን አቋም ኢትዮጵያ ብትቀበል በሌሎች ተመሳሳይ ስምምነቶች ላይ አገሪቱ ያላትን አቋም የሚለውጥ መስሎ ሊታይ ይችላል። ይህን ማድረጉ በሌሎች ተዛማጅ ስምምነቶች ዙሪያ ከሚኖረው አሉታዊ እንድምታ አንጻር ኢትዮጵያ የጅቡቲን አቋም መቀበል እንደማይኖርባት ከመግባባት ተደረሰ። የኤክስፐርት ኮሚቴው ባቀረበው ሪፖርት እንደገለጸው እነዚህን ነጥቦች በማይነካ መልኩ ኢትዮጵያ ከጅቡቲ ጋር እንደገና ለመደራደር ፍቃደኛ ልትሆን ትችላለች። የሚደረገው ስምምነት የግድ በቅርጹም ሆነ በይዘቱ ከ1952ቱ ስምምነት ጋር አንድ ዓይነት መሆን ባይኖርበትም የኢትዮጵያን ቋሚ መብቶች እንደገና የሚያረጋግጥ እንዲሆን ከመግባባት ተደረሰ።

ኮሚቴው በጅቡቲ በኩል የቀረበውን ረቂቅ የትራንስፖርት ስምምነት በተለይም የምድር ባቡሩን ክፍል በጥልቀት ከመረመረ በኋላ የኢትዮጵያን ዋና ዋና የመደራደሪያ ነጥቦች የያዘ ረቂቅ አዘጋጀ። ረቂቅ ውሉ የ1952 ስምምነትን ስለማሻሻል የሚያትትና ከጅቡቲ ነፃነት መቀዳጀት ጋር የተያያዙ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ያስገባ እንደሆነ ተብራራ። ጅቡቲም የ1952ቱ ስምምነት ለኢትዮጵያ የሰጣቸውን የመተላለፍና የነፃ ወደብ መብት እንድታከብር በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ረቂቅ ያስገድዳል። እንዲሁም ሁለቱ ወገኖች በወደብ፣ መንገድ፣ ባቡርና አውሮፕላን ማረፊያ አጠቃቀምና በነዳጅ፣ በኤሌክትሪክ ኃይል፣ መብራትና ውሃ ጭምር በማግኘት በኩል ለየሃገሮቻቸው ተወላጆች የሚደረገውን የቀደምትነት መብትና የብልጫ አስተያየት (national treatment) አንዱ ለሌላው ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያው ረቂቅ እንደሚገልጸው የጦር መሣሪያዎችን፣ ፈንጂዎችንና ሌሎች ለሕዝብ ጤና አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አንዱ አገር በሌላው አገር ግዛት ላይ ለማስተላለፍ ሲፈልግ በቅድሚያ በዲፕሎማቲክ መንገድ ማስታወቅ ያስፈልጋል፤ ወታደሮችን ለማጓጓዝ ግን በቅድሚያ ፈቃድ ያስፈልጋል። ፀጅቡቲ በኩል የቀረበው ረቂቅ ግን

ለመጓሪያዎችም ሆነ ለወታደሮች በቅድሚያ ፈቃድ ያስፈልጋል የሚል ነበር። በስተመጨረሻም ረቂቅ ስምምነቱ የጅቡቲን ዓለም አቀፋዊ ገለልተኝነት (international neutrality) የሚደነግና ሁለቱ ወገኖች አንዱ በሌላው ላይ ብቻውንም ሆነ ከሌሎች አገሮች ጋር በመተባበር ወረራ ወይም ሌላ የጠላትነት አድራጎት ከመፈጸም ስለመቆጠብ በጅቡቲ በኩል የተቀመጠውን ግዴታ የሚያጠቃልል አንቀጽ ተጨመረበት።[141]

የአጠቃላዩ የትራንስፖርት ውል አካል የሆነ ስለ ኢትዮ-ጅቡቲ የምድር ባቡር ኩባንያ የሚያወሳ የስምምነት ረቂቅ በኤክስፐርት ኮሚቴው ተዘጋጅቶ ነበር። ይህ የስምምነት ረቂቅ የተዘጋጀው የ1952ቱን ውል መሠረት በማድረግና ከጅቡቲ በኩል ከቀረበው ረቂቅ ጋር በማገናዘብ ሲሆን የሁለቱ አገራት ስምምነት በተቻለ መጠን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች እንዲያስጠብቅ ጥረት ተደርጓል። በ1952 ስምምነት ላይ የተደረገው አንዱና ዋነኛው ማሻሻያ ኢትዮጵያና ጅቡቲ እያንዳንዳቸው በኩባንያው ውስጥ የሃምሣ በመቶ የይዞታ እኩልነት እንዲኖራቸው መወሰኑ ነው። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ግንቦት 17፣ 1970 ባደረገው ስብሰባ "እንደገና ስለሚቋቋመው" ኩባንያ በሰጠው መመሪያ፡

> ...ስለ ምድር ባቡር ንብረትና አስተዳደር በሚደረገው ንግግር ጅቡቲ ከኢትዮጵያ ጋር 50 % እኩል አክሲዮን እንዲኖራት ኢትዮጵያ በመሠረቱ የምትደግፍ መሆኗንና ሆኖም ይህን ለመፈጸም እንዲያስችል የጅቡቲ መንግስት ከፈረንሳይ መንግስት ከሚተላለፍለት የ27% አክሲዮን በላይ በፈረንሳይ የግል ድርጅቶችና ሰዎች እጅ የሚገኘውን 23% አክሲዮን ወደ ራስ ማዛወር የመንግስቱ ግዴታና ኃላፊነት መሆኑን እንዲያውቅ ይህ ዝውውር ሊፈጸም የሚችልበትን መንገድ መፈለግና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት በንግግሩ ወቅት እንዲገለጽለት...

[141] ዝኒ ከማሁ፤ ዶ/ር ፈለቀ ገድለጊዮርጊስ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት፡ ሐምሌ 15፣ 1972





ተወሰነ። እንዲሁም የጅቡቲ ወገን 50% የአክሲዮን ድርሻ እንዲኖረው ከመስማማት ባሻገር በፈረንሳይ ዜጎች የተያዘውን የ23% የአክሲዮን ድርሻ ለማግኘት የግዛቱ መንግስት በሚወስደው እርምጃ ኢትዮጵያ የመተባበር ግዴታ እንደሌለባት ይጠቁማል። [142]

ከዚህ ጋር የተነሳው ነጥብ ለምን ለጅቡቲ የእኩል ባለመብትነት መብት ሊሰጣት ይገባል የሚለው ነበር። የክርክሩ ማጠንጠኛ የነበረው አብዛኛው የባቡሩ መስመር በኢትዮጵያ ውስጥ ከመሆኑም በላይ የባቡሩ እንቅስቃሴ የተመሠረተው ከኢትዮጵያ ከሚገኘው ገቢ መሆኑ ነው። ይህ አየታወቀ የኩባንያው ካፒታልና ሌላም ንብረት በሁለቱ መንግስታት በእኩልነት መያዙ ከኢትዮጵያ ይልቅ ለጅቡቲ ይጠቅማል የሚል ክርክር አስነሳ። ሆኖም ለዚህ ውሳኔ በኤክስፐርት ኮሚቴው በኩል የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው ሃገሪቱ ከኩባንያው የምታገኛቸው ተዘዋዋሪ ጥቅሞች ከኩባንያው አነስተኛ ትርፍ አንፃር የጅቡቲ 50% ድርሻ መያዝ ኢትዮጵያን እምብዛም አይጎዳም።

ሌላው አጽንኦት የተሰጠው ነጥብ የኩባንያውን ምዝገባ እና ዋና መሥሪያ ቤት የሚመለከተው ነበር። ጅቡቲ ባቀረበችው የስምምነት ረቂቅ እንደተመለከተው በሁለቱ አገሮች መሀከል የሚኖረው የትራንስፖርት ሥርዓት በሦስት ደረጃ ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን ኢንተርናሽናል ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የሚቋቋመው ቴክኒካል ኤጀንሲ ዋናው መሥሪያ ቤት ጅቡቲ እንደሚሆን ተገልጿል። ኢትዮጵያ የጅቡቲን ሃሳብ ውድቅ ከማድረግም በላይ ተለዋጭ የስምምነት ረቂቅ አቀረበች። የደርግ መንግስት ፍላጎት የነበረው ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመዘገብና ዋናው መሥሪያ ቤቱም አዲስ አበባ እንዲሆን ነበር። ይህ የተፈለገበት ምክንያት ኩባንያው ዜግነቱን የሚያገኘው በተመዘገበበት አገር ውስጥ በመሆኑ ነው። 'ዜግነት" የሚለው ቃል የአንድን አገር ብሔራዊ መብትና ግዴታ

[142] ዝኒ ከማሁ

እንዲሁም በብሔራዊ ሕግ መተዳደርን ስለሚያመለክት ባቡርን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች ከወንጀል ነክ ጉዳዮች በስተቀር ኩባንያው በተመዘገበበት አገር ሕግ (በኢትዮጵያ ሕግ) መዳኘት ይኖርባቸዋል።

በኤክስፐርት ኮሚቴው ግንዛቤ መሠረት ይህ ሃሳብ በጅቡቲ በኩል ተቀባይነት ካገኘ በሁለቱም ግዛቶች የሚነሱት ተመሳሳይ ጉዳዮች (ክሶች) ተመሳሳይ ፍርድ ስለሚያገኙ የተዛባ የፍርድ አሰራርን ለማስወገድ ይቻላል። ነገር ግን የኩባንያው ዋና መሥሪያ ቤት ዜግነቱ በተሰጠበት ወይም ኩባንያው በተመዘገበበት አገር ብቻ ሳይወሰን በሁለተኛው ወገን አገር ውስጥም ሊሆን ይችላል። በኤክስፐርት ኮሚቴው ግምት ጅቡቲ የኢትዮጵያን ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ ላትቀበለው ትችላለች። ሆኖም ኩባንያው ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲመዘገብ በመስማማት ዋናው መስሪያ ቤት ጅቡቲ እንዲሆን ወይም ዋናው መሥሪያ ቤት አዲሰ አበባ እንዲሆን በመስማማት ኩባንያው ጅቡቲ ውስጥ እንዲመዘገብና የጅቡቲ ዜግነት እንዲኖረው ጅቡቲ ልትጠይቅ ስለምትችል በጉዳዩ ላይ መንግስት አፋጣኝ ውሳኔ እንዲሰጥበት ተጠየቀ።[143]

ሌላኛው አጨቃጫቂ የነበረው አንቀፅ የሞኖፖል መብትን የተመለከተው ነበር። በጅቡቲ በኩል የቀረበው የስምምነት ረቂቅ ሁለቱ መንግስታት የምድር ባቡሩ መስመር በሚያልፍባቸው ክፍሎች ተወዳዳሪ የሚሆን ማንኛውንም ሌላ የሐዲድ መሥመር እንዳይሰሩ የሚከለክል ከ1952 ስምምነት በቀጥታ የተቀዳ ግዴታ እንዲኖር ፈለገ። የኤክስፐርት ኮሚቴው ከኢትዮጵያ ጥቅም አንፃር ይህንን ሃሳበ በሦስት መንገድ ለመተንተን ሙከራ አድርጓል። አንደኛው ከአዲስ አበባ የምድር ባቡሩ በሚያልፍባቸው ክፍሎች ውስጥ የሚዘረጋ ማናቸውም አዲስ መስመር በነዚህ ክፍሎች ውስጥ በማለፉ ብቻ ተወዳዳሪ ስለሚሆን እንዲሰራ ፈቃድ ላይሰጠው ነው። ከአዲስ አበባ ጅቡቲ

---

[143] ዝኒ ከማሁ





ከፍተኛ ትራፊክ በመኖሩ የተነሳ በነዚህ ክፍሎች የሚዘረጋ አዲስ መስመር የቀድሞውን መስመር ገቢ ባይነካም እንኳ ተወዳዳሪ ነው ማለት ነው። ሁለተኛው ከአዲስ አበባ ጅቡቲ ሳይሆን በሌሎች ክፍሎች የሚዘረጋ ማናቸውም መስመር ከጅቡቲ አዲስ አበባ ባለው መስመር ላይ ካለው ትራፊክ ጋር ግንኙነት ቢኖረውም ባይኖረውም በሌሎች ክፍሎች ውስጥ በማለፉ ብቻ ተወዳዳሪ መስመር ነው ሊባል ስለማይችል እንዲሠራ ሊፈቀድላት ይገባል። ስለዚህ ለምሳሌ በኮምቦልቻ በኩል ከአዲስ አበባ አሰብ አዲስ መስምር መዘርጋት ይቻላል ማለት ነው።

እንደ ኮሚቴው አስተያየት ከሁለቱ አማራጮች መካከል ሁለተኛው ትክክል ከሆነ ኢትዮጵያ ወደፊት የባቡር መስመር ለመዘርጋት በሚኖራት ዕቅድ ላይ ምንም ዓይነት ሥጋት አያመጣም። የጅቡቲው ረቂቅ ትክክለኛ መንፈስ አንደኛው አማረጭ ከሆነ ግን ኢትዮጵያ አሁን ባለው ሁኔታ (ከፍተኛ ትራፊክ እስካለ ድረስ) የባቡር መስመር መዘርጋት አትችልም ማለት ነው። በኮሚቴው እምነት የጅቡቲ ፍላጎት የመጀመሪያው አማራጭ ስለሚመስል ይህ አንቀጽ በስምምነቱ ውስጥ ከገባ ኢትዮጵያ ከአሰብ ወደብ ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም ዓይነት የባቡር መስመር መዘርጋት ስለማትችል የወደቡን ዕድገት በብርቱ ያሰናክለዋል። በሌላ በኩል ግን የዚህ አንቀጽ መኖር ለጅቡቲ ወደብ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ ስለሆነ ኢትዮጵያ ከ1952ቱ ስምምነት አንቀጽ 11 እና 12 እንዲከበርላት እንደምትፈልግ ሁሉ ጅቡቲም ይህ አንቀጽ በስምምነቱ ውስጥ እንዲሰፍርላት መጠየቋ አያጠራጥርም። ስለዚህ የዚህ አንቀጽ በስምምነቱ ውስጥ መስፈር ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያን በመጉዳት ጅቡቲን የሚጠቅም ስለሆነ ጅቡቲም ይህ አንቀጽ በግዴታ መግባት ይኖርበታል ብላ ልትከራከር ስለምትችል ጉዳዩ በመንግስት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተመለከተ።

ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ሦስተኛው አማራጭ በጅቡቲው ረቂቅ የሰፈረው "የምድር ባቡሩ መስመር ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ በሚያልፍባቸው" ክፍሎች ውስጥ ከሁለቱ

መንግስታት አንዱ ለዚሁ የምድር ባቡር ተወዳዳሪ የሚሆን መስመር መዘርጋት ቢፈልግ ለኢትዮ-ጅቡቲ ኩባንያ የተወሰነ የትራፊክ መጠን ዋስትና መስጠት አለበት" የሚለው አንቀጽ ነው፡፡ በዚህም አማራጩ መሠረት ኢትዮጵያ ለኩባንያው ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ዋስትና ከሰጠች ወደ አሰብም ሆነ ወደ ሌላ ወደ ማንኛውም አቅጣጫ መስመር ለመዘርጋት ስለምትችል ይህ አማራጭ ትኩረት እንዲሰጠው ሃሳብ ቀረበ፡፡

የኤክስፐርት ኮሚቴው በጥናት ሪፖርቱ ማጠቃለያ ያቀረበው አስተያየት ይበልጥ ትኩረትን የሚስብ ነው፡፡ የ1952ቱ ስምምነት ዳግማዊ ምኒሊክ በ1889 ለአልፍሬድ ኢልግ ከሰጡት ፈቃድ ጀምሮ በተደረጉ ቁጥራቸው ከአሥር የማያንሱ ውሎችና ማሻሻያዎች የተወሰደ መሆኑን ኮሚቴው ያስረግጣል፡፡ እንደ ኮሚቴው አገላለጽ በየጊዜው የተፈጸሙት ውሎች ይዞታ እንደሚያስረዳው እያንዳንዱ ውል ከሚቀድመው ውል ይልቅ የውጭ ዜጎችን ጥቅም እየቀነሰ በዚያው መጠን የኢትዮጵያን ጥቅም፣ ይዞታና ሥልጣን በጉልህ እያዳበረ ሲሄድ ቆይቷል፡፡ "ሌላ የሚያመዝን ምክንያት ከሌለ በስተቀር አባቶች የቀደዱትን ፈር በመከተል የኢትዮጵያን ጥቅምና ሥልጣን በበለጠ የማሻሻልና የማጠናከር ኃላፊነት አለብን" ሲልም አበክሮ ያሳስባል፡፡[144]

የምድር ባቡር ኩባንያውን ድርድር በአፋጣኝ የመጨረስ እና ከአንድ ስምምነት ላይ የመድረስ ፍላጎት ከኢትዮጵያ ይልቅ በጅቡቲ መንግስት በኩል የጎላ ነበር፡፡ ፕሬዚደንቱን ጨምሮ ሁሉም የጅቡቲ ባለሥልጣናት የስምምነቱን መጠናቀቅ ለሐሰን ጉሌድ ኢትዮጵያን መጎብኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጣቸው የደርግ አመራሮችን ማበሳጨቱ አልቀረም፡፡ በሁለቱ መንግስታት ልዑካን መካከል የሚደረገው ንግግር በታህሳሥ 1973 በአዲስ አበባ ቀጣይ ድርድሩም በየካቲት አጋማሽ በጅቡቲ ተካሄደ፡፡ የኤክስፐርት ኮሚቴው አባላት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ውስጥ እንዲካተቱ ተደረገ፡፡[145]

[144] ዝኒ ከማሁ





በጅቡቲው ድርድር ወቅት አጨቃጫቂ ከነበሩት ነጥቦች መካከል የኢትዮጵያ የቋሚ መብት ጥያቄ፣ የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት መቀመጫና የኩባንያውን ኪሣራ (deficit) መውረስ ጉዳዮች ይገኙበታል፡፡ በአቶ ጌታቸው ክብረት የሚመራው የኢትዮጵያ ልዑክ ከአዲስ አበባ ሲነሳ የተሰጠው መመሪያ ስለ ቋሚ መብት የሚደረገው ንግግር የ1952 ስምምነት አንቀጽ 11 እና 12 ላይ ብቻ የተመሠረተ እንዲሆን ያዛል፡፡ በጅቡቲው ድርድር መሐል ለመንግስት የተላለፈው የአቶ ጌታቸው አስተያየት እንደሚያስረዳው በጅቡቲ በኩል የቀረበው አማራጭ የኢትዮጵያን አቋም የሚያጠናክር ሲሆን የሚከተሉትን ነጥቦች እንደያዘ ተገልጿል፡ ወደ ጅቡቲ ወደብ በነፃ መግባት፣ መውጣትና መተላለፍ፤ እና ይህ የመተላለፍ መብት (transit right) ዘለቄታዊ ባህሪ (permanent character) እንደሚኖረው ጅቡቲ ዋስትና ትሰጣለች፡፡

የድርጅቱ ዋና ጽ/ቤት ጉዳይም ብዙ አከራካሪ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ሃሳብ በመሠረቱ በጊዜው የነበረው ሁኔታ (status qou) እንዲቀጥል ሲሆን ጅቡቲዎች ግን የኩባንያው ልዩ ልዩ የሥራ ተቋሞች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በሁለቱ አገሮች መካከል እንዲከፋፈሉ ተከራከሩ፡፡ "በድርድሩ መሠረት ኢትዮጵያ ሁሉንም ነገር ከወሰደችው ለሕዝባችን ምን ጥቅም አስገኘን ልንል ነው" በማለትም ከኢትዮጵያ የአቋም መለሳለስ (concession) ፈለጉ፡፡ በተለይም ዋናው ጽ/ቤት አዲስ አበባ የሚሆን ከሆነ ድሬዳዋ የሚገኘው የቴክኒክ ድርጅት ወደ ጅቡቲ እንዲዛወር ሲሉ በግልፅ ጠየቁ፡፡ የኢትዮጵያ ልዑክ በጊዜው ይህ የማይቻል መሆኑን የገለፀ ቢሆንም ለበላይ አካል ባስተላለፈው ሪፖርት ቢያንስ የኩባንያውን አንድ ዝቅተኛ አካል

[145] ው.ጉ.ሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ አርጋው ካብታሙ (ጅቡቲ) ለጥበቡ በቀለ (ው.ጉ.ሚ ቋሚ ተጠሪ)፡ ጥቅምት 2፣ 1973፡፡ ው.ጉ.ሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፤ አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ (ጅቡቲ) ለጥበቡ በቀለ ስለ ጅቡቲ የመደራደሪያ ነጥቦች፡ ጥር 14፣ 1973፤ ጥበቡ በቀለ ለአምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ - በኢትዮጵያ ልዑካኝ ዙሪያ፡ የካቲት 14፣ 1973

በጅቡቲ ተቀማጭ ማድረጉ ሚዛናዊ እንደሚሆንና የጅቡቲያኑን መከፋት ሊያለሳልስ እንደሚችል አሳሰበ።

ኩባንያው በየጊዜው ስለሚገጥመው የገንዘብ ኪሣራ ጉዳይም በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው የእኩል ተጋሪነት ጥያቄ በጅቡቲ በኩል ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም። ለተቃውሚቸው ካቀረቧቸው ምክንያቶች መካከል የምድር ባቡሩ መስመር ከሰባት እጁ ስድስቱ በኢትዮጵያ ውስጥ መገኘቱ፤ የሸቀጣ ሸቀጥና የመንገደኛው ትራፊክ ከመቶ ዘጠና በላይ የሚንቀሳቀሰው በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ፤ ባቡሩን ለማሻሻል ከሚገኘው እርዳታ አሁንም ዘጠና በመቶው ሥራ ላይ የሚውለው ኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑ፤ የሥራ ዕድልን በሚመለከት አብላጫው ተቀጣሪና ተጠቃሚዎቹ ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ወዘተ ይገኙባቸዋል። ከዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ልዑክ የእኩል ተጠቃሚነት መርህን እንዲቀበሉ ለማድረግ ተቸገረ። በጅቡቲ በኩል ተይዞ የነበረው አቋም የእኩል ተጠቃሚነት መብት ሲታሰብ ሃሳቡን የተቀበሉት የሉዓላዊነት እኩልነትን ለማንፀባረቅ እንጂ የኩባንያውን አትራፊነት ታሳቢ በማድረግ እና ትርፍ ለመካፈል ተስፋ ኖሮአቸው እንዳልነበር መረዳት ይቻላል።[146]

የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎች በተለይ ከቋሚ ተጠቃሚነት መብቶች አንፃር ከጅቡቲ የተገኘው ስምምነት የሃገሪቱን ጥቅሞች ለማስጠበቅ የሚያስችሉ እንደሆኑ እምነታቸውን በመግለፅ መንግስት እንዲቀበለው አሳሰቡ። ከአዲስ አበባ የመጣው ምላሽ ግን የድርድሩ ውጤት ቀደም ብሎ አቋም ከተያዘባቸው አካሄዶች የተለየ በመሆኑ ቡድኑ ድርድሩን አቋርጦ እንዲመለስ የሚያዝ ነበር።

ይህን ውሳኔ በዕኑ ከተቃወሙት መካከል በጅቡቲ የኢትዮጵያ አምባሳደር ይገኙበታል። ተደራዳሪ ቡድኑ በተመለሰበት ቀን (የካቲት 23) ባስተላለፉት ቴሌግራም እንደገለፁት ድርድሩ ከተጀመረ አንስቶ የጅቡቲ መንግስት ከመነሻ አቋሙ በጣም በማፈግፈግ በተለይም የቋሚ መብቶችና አንድ ወጥ ኩባንያን በሚመለከት የኢትዮጵያን ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን አስታውሰዋል። ኢትዮጵያ አንዳንድ የጅቡቲ ቅድመ ሁኔታዎች ለማቃለል በተለይም ስለ ኪሣራውና ስለ ኩባንያው ዘርፎች ክፍፍል ያቀረቧቸውን ጥያቄዎች በአዎንታዊ መልኩ እንደምታጤን በታህሳሱ የአዲስ አበባ ድርድር ወቅት ካሳየችው ፈቃደኝነት ማፈግፈጓ ጅቡቲዊያኑን እንዳስከፋቸው ከድርድሩ መቋረጥ በኋላ ከባለሥልጣናቱ ጋር ያደረጓቸውን ውይይቶች ጠቅሰው አብራርተዋል። የምድር ባቡሩን ስምምነት ለማጠናቀቅ ላለፉት ሦስት ዓመታት ጅቡቲ ካሳየችው ተነሳሽነትና በጎ ፈቃድ አንፃር እድሉን ማበላሸት አግባብ እንዳለሆነ የተከራከሩት አምባሳደሩ ስለ ጉዳዩ በአካል ተገኝተው ለማስረዳት ፈቃድ እስከመጠየቅ ደረሱ።[147]

ይህንን ግፊት ተከትሎ ድርድሩ በመጋቢት መጀመሪያ በጅቡቲ ቀጠለ። የምድር ባቡርና የወደብ መብትን በተመለከተ የጅቡቲ መንግስት "ከበፊት ጀምሮ የነበረውን የኢትዮጵያን ቀዳሚ የተጠቃሚነት መብት ይቀበላል" የሚለው የኢትዮጵያ አቋም ዋነኛው አከራካሪ ነጥብ ሆነ። የጅቡቲ ተደራደሪዎች la Republique de Djibouti Continu Dereconnaitr የሚለው አቀራረብ ከቀደመው ቅኝ ገዢ (ከፈረንሳይ) ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚያስታውስ ከመሆኑም በስተቀር ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ተጨማሪ ጥቅም አይኖርም በማለት "የጅቡቲ ሪፐብሊክ ለኢትዮጵያ የተጠቃሚነት መብት ዋስትና ይሰጣል" (la Republique de Djibouti Garantti D'Ethiopie le Droit) በሚለው አገላለፅ እንዲተካና የልዩ ተጠቃሚነት መብት (ex-traterritorial right) አለመኖሩን የሚጠቅስ ሀረግ እንዲኖር አበክረው ጠየቁ። የኢትዮጵያ ልዑካን በበኩላቸው ሀገራቸው ከጅቡቲ ጋር የነበራት ግንኙነት በቅኝ ገገርዎች ዘመን ብቻ

[146] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፤ ጊታቸው ክብረት (ጅቡቲ) ለዶ/ር ፈለቀ ገድለጊዮርጊስ፡ የካቲት 18፤ 1973

[147] ዝኒ ከማሁ፤ ዶ/ር ፈለቀ ለጌታቸው ክብረት፡ የካቲት 20፤ 1973። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 57-D3 3፤ አምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ ለዶ/ር ፈለቀ፡ የካቲት 23 እና 24፤ 1973

ሳይሆን ከዚያም በፊትና በኋላ መሆኑን በማስረዳት ተከራከሩ። ሆኖም በጅቡቲ በኩል የነበረውን ስሜት ለመቀየር ሳይቻል ቀረ።

የጅቡቲ ልዑካን በጉዳዩ ላይ ከበላዮቻቸው ለመመካከር በጠየቁት መሠረት ድርድሩ ለሰዓታት ከተቋረጠ በኋላ የጅቡቲ መንግስት የመጨረሻ ማሻሻያ ያደረገበትን አቋም አሳወቀ። ጅቡቲያውያኑ ከዚህ ያለፈ ማሻሻያ (compromise) ማድረግ የማይችሉ መሆናቸውን ከመግለፃቸውም ባሻገር ይህ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነትን ካላገኘ ድርድሩ እንደተቋረጠ ተቆጥሮ ሁለት ኩባንያ ይቋቋም ወደሚለው የመጀመሪያ ሃሳባቸው ለመመለስ እንደሚገደዱ አሳወቁ።

በአዲሱ ቀመር መሠረት የጅቡቲ ሪፐብሊክ ወደ ግዛቷ ለሚሄዱና ከግዛቷ ለሚመጡ የኢትዮጵያ ንብረቶችና ሸቀጣ ሸቀጦች ቋሚ የመግባትና የመተላለፍ (permanent right of access and transit) መብት እንዲኖራቸው ዋስትና እንደሚሰጥ ያመለክታል። ይህ መብት ኤክስትራ ቴሪቶሪያልነትን የማይነካ ወይም ከጅቡቲ ሉዐላዊነት ጋር የማይፃረር ሆኖ በአንድ ነፃ ወደብ በተለምዶ የሚሰጡ አቅርቦቶችንና አገልግሎቶችን ያጠቃልላል። በዚህም መሠረት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡና ከኢትዮጵያ የሚወጡ እቃዎች ከወደብ ቀረጥ በስተቀር ማንኛውንም የጉምሩክ ግብር፣ ሌላ ግብርና ታክስ አይከፍሉም ማለት ነው። በተጨማሪም እቃዎቹ ለአገሩ (ለጅቡቲ) እቃዎች የሚሰጠው አስተያየት እንደሚደረግላቸውም ተብራርቷል።

በጅቡቲ ማሻሻያ መሠረትም የኢትዮጵያ የንግድ ድርጅቶች ተግባራቸውን ለማከናወን በጅቡቲ ነፃ ወደብ ውስጥ መሬት ጠይቀው ለማግኘት ይችላሉ። የጅቡቲ ድርጅቶች ከጅቡቲ ለሚወጡና ወደ ጅቡቲ ለሚገቡ እቃዎች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የማስተላለፍና የጉምሩክ ግዴታ ሳይፈፀምባቸው የማለፊያና የማከማቻ መብት ይኖራቸዋል። ከዚህ በላይ የተገለፁት በተግባር የሚውሉበትን ሁኔታ ለማቃናትም የጅቡቲ መንግስት የተቀበላቸው ተቀማጭነታቸው በጅቡቲ የሚሆን የኢትዮጵያ ተወካዮች እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት





የተቀበላቸውና ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ የሚሆን የጅቡቲ ተወካዮች የጉምሩክ ፍተሻና የእቃዎችን የተለመደ እንቅስቃሴ ለማቃናት የጉምሩክ ሥራዎችን ያስፈጽማሉ።

ኢትዮጵያ በብርቱ የፈለገችው "እስከ አሁን እንደነበረው" (enjoyed so far) የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በጅቡቲ ዘንድ ፍፁም ተቀባይነት አጣ። የጅቡቲ አቋም የኢትዮጵያን ቋሚ መብቶች ለማክበር የመንግስታቸውን ዝግጁነትን የሚገልጽ ሲሆን ሊሰጡት የተዘጋጁት ዋስትና ላለፈው መብት ሳይሆን ለመጪው ጊዜ እንዲሆን በብርቱ ይሹ ነበር። የኢትዮጵያ ልዑክ ደግሞ የተሰጠው መመሪያ በአመዛኙ የቀደመውን መብት በማስከበሩ ላይ የሚያጠነጥን በመሆኑ ድርድሩ ሌላ አጣብቂኝ ገጠመው። በተጨማሪም ኩባንያው ሊደርስበት ስለሚችለው ኪሣራ ክፍያ ጉዳይ ጅቡቲ ከኪሣራው ከ10 በመቶ በላይ ለመቀበል አቅሟ እንደማይፈቅድና እንደማትፈልግ ማሳወቋም ሌላኛው ያለመግባባት ምንጭ ነበር። የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎች እና የኤምባሲው ዲፕሎማቶች ጅቡቲን ከዚህ በላይ መጠየቅ እንደማይቻልና በአፋጣኝ መመሪያ ካልተሰጠ ድርድሩም ሆነ የሁለቱ አገሮች ግንኙነት አደጋ ላይ እንደሆነ ገለፁ።[148]

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በኩል ለኢትዮጵያ ተደራዳሪዎች የተላለፈው መመሪያ ግን አሁንም የቀደሙ መብቶችን በማስከበሩ አስፈላጊነት ላይ ያተኮረ ነበር። መመሪያው የጅቡቲው ድርድር መሠረታዊ መብትን በሚመለከት በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በኩል ስምምነት ከተደረሰባቸው አማራጮች አንዱንም አለማቀፉን፣ የኪሣራ አከፋፈልን በሚመለከትም የኩባንያው ህልውና ሁለቱንም አገሮች እንደሚያገለግልና እንደሚጠቅም

---

[148] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፤ ከጅቡቲ ኤምባሲ ለውጉሚ፡ መጋቢት 1፣ 1973፤ ጌታቸው ክብረት (ጅቡቲ) ለዶ/ር ፈለቀ፡ መጋቢት 1፣ 1973፤ አርጋው ካብታሙ (ጅቡቲ) ለአምባሳደር ብርሃኑ፡ መጋቢት 1፣ 1973

[149] ዝኒ ከማሁ፤ ዶ/ር ፈለቀ ለጌታቸው ክብረት (ጅቡቲ)፡ መጋቢት 3፣ 1973

በመገንዘብ የቀረበውን የኢትዮጵያን አቋም ጅቡቲ አለመቀበሏ ስህተት እንደሆነ በአንክሮ ገለፀ። ስለሆነም ቀድሞ ከተወሰነው አቋም መሠረታዊ ለውጥ ማድረግ የሃገራቱን ጥቅም ሊያስጠብቅ ስለማይችል ከዚህ ቀደም የቀረቡትን አማራጮች በድጋሚ በማቅረብ ለማስረዳት የመጨረሻ ጥረት እንዲደረግ ትእዛዝ ተላለፈ።[149]

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ቀጥተኛ መረጃውን ሊያገኝ ባይችልም በተዘዋዋሪ እንደተረዳው ከላይ የተጠቀሰው የኢትዮጵያ መንግስት ግፊት የተወሰነ ውጤት ማስገኘት ችሏል። የጅቡቲ ባለስልጣናት የ1952 ስምምነት አንቀጽ 11 እና 12 ለኢትዮጵያ የሚሰጣቸውን መብቶች የሚተካ ረቂቅ እንዲሁም ስለ ኪሣራ አከፋፈል ተለዋጭ ሃሳብ በማቅረባቸው ሁለቱ ተደራዳሪዎች ከስምምነት መድረስ ቻሉ። ቋሚ መብትን በሚመለከት የቀረበውን የጅቡቲ የመጨረሻ ሃሳብ የኢትዮጵያ መንግስት ሙሉ በሙሉ የተቀበለው ሲሆን ዋነኛው ተደራዳሪ የስምምነት ፊርማቸውን እንዲያስቀምጡ (initial እንዲያደርጉ) ተፈቀደላቸው። ኪሣራን በሚመለከት ግን ሁለቱን መንግስታት የሚያነጋግረው የገንዘቡ ጉዳይ ሳይሆን የባቡሩ ደህንነት እንደሆነ በመግለጽ ጅቡቲያውያኑ በኢትዮጵያ ሰነድ የማይስማሙ ከሆነ ፕሬዚደንት ጉሌድ ኢትዮጵያን በሚጎበኙበት ወቅት ከሊቀ መንበር መንግስቱ ጋር ተነጋግረው እንዲስማሙ መወሰኑ ተገለጸ።[150] የጅቡቲው ድርድርም በዚሁ መንገድ ተጠናቀቀ። አጠቃላይ የትራንስፖርት ስምምነቱም በፕሬዚደንት ጉሌድ የኢትዮጵያ ጉብኝት ወቅት ተፈረመ።

በስምምነቱ መሠረት ኩባንያው የሚተዳደረው ከሁለቱ መንግስታት በእኩል የተውጣጡ 12 የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሲሆን የሁለቱ አገሮች የትራንስፖርት ሚኒስትሮች የሊቀ መንበርና የምክትል ሊቀ መንበርነቱን ተግባር በየዓመቱ በመቀያየር በዓመት ሁለት ጊዜ በአዲስ አበባና በጅቡቲ

---

[150] ገዛኸኝ ከማሁ፤ ዶ/ር ፈለቀ ለጌታቸው ክብረት (ጅቡቲ)፡ መጋቢት 5 እና 14፤ 1973





ከተሞች በመገናኘት የድርጅቱን እቅድና በጀቱን ያጸድቃሉ፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣሉ፣ ውጤቱንም ይቆጣጠራሉ።

የአዲስ አበባ-ጅቡቲ የምድር ባቡር መስመርን የተመለከተው የ1973 ስምምነት በተፈረመበት ወቅት ድርጅቱ ይገኝበት ከነበረው ሁኔታ ለማላቀቅና አገልግሎት መስጠቱን እንዲጀምር ለማድረግ ሁለቱ መንግስታት በጋራ የአውሮፓ የጋራ ገበያን እርዳታ ጠየቁ። በመጀመሪያ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን አንገብጋቢ ፕሮጀክቶች ለመለየትና የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ፕሮግራም ለመንደፍ አንድ የጣሊያን አጥኚ ቡድን ተመርጦ ባቀረበው ሪፖርት መሠረት 10 ሚሊዮን የአውሮፓ የገንዘብ ዩኒት (ECU) እርዳታ እ.ኤ.አ. በ1981 ተገኘ። በገንዘቡም የቆሙ ሎኮሞቲቮችና ጋሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልግ መለዋወጫ ዕቃ፣ የመንገደኛ ማጓጓዣ ሊቶሪና፣ የስልክ መሳሪያ እና ልዩ ልዩ የሀዲድ ፍተሻ መሳሪያዎች በመግዛት የኩባንያውን እንቅስቃሴ ለማሻሻል ተቻለ። ነገር ግን ከአውሮፓ የጋራ ገበያ የተገኘው እርዳታ የኩባንያውን አበይት ችግሮች ሊቀርፍ ባለመቻሉ በተጨማሪ ሁለቱ መንግስታት በጋራ ከፈረንሳይ መንግስት እርዳታ ጠይቀው በአጠቃላይ የ90 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር እርዳታና ብድር እ.ኤ.አ. በ1983 ተገኝቶ ለድርጅቱ ተጨማሪ መሳሪያዎች ግዢ እንዲውል ተደረገ።

በቅድሚያ በጣሊያኑ አጥኚ ቡድን የተነደፈውን ፕሮግራም ተግባራዊነት ለማስቀጠል ሁለቱ መንግስታት በድጋሚ የአውሮፓን የጋራ ገበያ እርዳታ በጋራ በመጠየቅ እ.ኤ.አ. በ1985 10 ሚሊዮን ECU በነፃ 5 ሚሊዮን ECU በ1.5% ወለድ ብድር ተገኝቶ የተለያዩ ግዢዎች ተከናወኑ። ከነዚህም መካከል የትራንስፖርት አቅምን ለማሻሻል ልዩ ልዩ ጋሪዎች፣ ያረጀውን ሃዲድ ለመቀየር የሚያስችል የብረት ሀዲድ ከነርብራቡ እና የኤሌክትሪክ መጠገኛ መሳሪያዎች ይገኙባቸዋል። ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ የተዘረጋው የሃዲድ መስመር በጣም ያረጀና በተሰራበት ወቅት በነበረው የቴክኖሎጂ ኋላቀርነት የተነሳ መስመሩ አቀበት፣ ጠመዝማዛና አነስተኛ ኩርባዎች የሚበዙበት ከመሆኑም በላይ የሀዲዱ ክብደት ቀላል በመሆኑ የመሸከም አቅሙ ዝቅተኛ ነበር። በተጨማሪም የሚተላለፍባቸው ድልድዮችና

ፋካዎች ከረጅም አገልግሎት የተነሳ በመዳከማቸው እንደገና በዝርዝር መታየታቸው አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በኩባንያው የአስተዳደር ምክር ቤት አጠቃላይ የመስመሩ ጥናት እንዲካሄድ በተወሰነው መሠረት ሁለቱ መንግስታት የጣሊያንን መንግስት በጋራ ጠይቀው ወደ 4 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እርዳታ በነፃ በመገኘቱ አንድ የጣሊያን ድርጅት ሥራውን በመስከረም 1981 እንዲጀምር ተደረገ::[151]

በ1980 የሁለቱ መንግስታት የጋራ የሚኒስትሮች መማክርት ጉባኤ በድጋሚ በወሰነው መሠረትም ለአውሮፓ ኢኮኖሚ ኮሚሽን (EEC) እና ለፈረንሳይ መንግስት በጋራ የ400 ሚሊዮን ECU የእርዳታ ጥያቄ ቀረበ:: ገንዘቡ በዋነኝነት የተፈለገው የባቡር ሐዲዱን ለማደስና ለመጠገን ነበር:: የፈረንሳይ መንግስት በተለይ ጥያቄውን ለመቀበለ ዝግጁነቱን የገለፀ ቢሆንም አፈፃፀሙን የሚያሰናክል እክል እንደነበር በኢትዮጵያ ባለሥልጣናት በኩል በሰፊው ታመነ:: ይህም በቀደመው ጊዜ ለምድር ባቡር ኩባንያው እንዲውል ታስቦ ኢትዮጵያ ከፈረንሳይ መንግስት የወሰደችውን የ54.7 ሚሊዮን የፈረንሳይ ፍራንክ ብድር ሳትከፍል መቅረቷ ነው:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም አዲስ የተጠየቀው የ250 ሚሊዮን ECU ብድር ለማግኘት እንዲቻል የቀደመውን ስለመክፈል ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ንግግር መደረግ እንደሚኖርበት አሳሰበ::[152]

ለዚህም ሲባል የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ኩባንያ የአስተዳደር ምክር ቤት ተወካዮች የፈረንሳይ መንግስት ለድርጅቱ

[151] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ፡ ልዩ ልዩ ስምምነቶች፤ ስለ ኢትዮ-ጅቡቲ የትራንስፖርትና መገናኛ ግንኙነት የቀረበ ማስታወሻ፡ ነሐሴ 1980

[152] ዝኒ ከማሁ:: ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፤ አምባሳደር አስፋው ለገሰ (ውጉሚ አፍሪካ መምሪያ ኃላፊ) ለእንግዳ ገብረመድህን (ፓሪስ ኤምባሲ ጉዳይ ፈፃሚ) እና አለማየሁ ራህመቶ (ብራስልስ ኤምባሲ ጉዳይ ፈፃሚ)፡ ታህሳሥ 29፣ 1980፤ ብርሃኑ ባየህ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) ለአሰግድ ወልደ አማኑኤል (የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር)፡ ሚያዝያ 24፣ 1980፤ ብርሃኑ ባየህ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት፡ ሰኔ 24፣ 1980





አበድሮት የነበረውን ገንዘብና ልዩ ልዩ ዕዳዎች እንዲሰርዝ በመስከረም 1981 በፓሪስ ንግግር አድርገው ነበር:: እንዲሰረዝ የተጠየቀው የዕዳ መጠን እስከ መስከረም 1980 ድረስ ወደ 13.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይጠጋል:: ከስብሰባው መልስ ኮሚቴው ባቀረበው ሪፖርት ላይ እንደተመለከተው የፈረንሳይ ወገን ድርድሩ የሚመለከተው የመንግስት ድርጅቶችን ዕዳ እንጂ የግል ድርጅቶችን የማይመለከት መሆኑን በመግለጽ በቀጥታ ከመንግስት ካዝና ወጪ ተደርገው የተሰጡ ብድሮች፣ ለኢትዮጵያና ፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያ ጡረተኞች እስከ መስከረም 1980 የተከፈለ የጡረታ አበል ዕዳ ለመሰረዝና ለወደፊትም ለጡረተኞች የሚከፈለውን ሂሣብ ለመቻል ተስማማ:: ይህ ከጠቅላላ ዕዳው ውስጥ 6.287.023 የአሜሪካን ዶላሩን ብቻ ይሸፍናል:: ቀሪው ዕዳ ግን ከነወለዱ እንዲከፈለው የፈረንሳይ መንግስት ጠየቀ::

የምድር ባቡር ኮሚቴው በበኩሉ የዕዳ ሰነዶቹ ሁሉም እ.ኤ.አ. ከ1958 በፊት የተገቡ በመሆናቸው በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል በ1952 (እ.ኤ.አ. 1959) በተፈረመው ስምምነት አንቀጽ 4 መሠረት ዋስትናው የፈረንሳይ መንግስት ብቻ መሆኑን፣ የአቅራቢዎችን ዕዳ በሚመለከት የፈረንሳይ የውጭ ንግድ ኢንሹራንስ የመድን አረቦን የተገባለት ሆኖ ድርጅቱ ለመክፈል ባለመቻሉ የመድን ድርጅቱ ኃላፊነቱን በመወጣት የከፈለ ስለሆነ እንደገና የሚጠየቅበት መንገድ አለመኖሩን፣ የኩባንያው አዲሶቹ ባለንብረቶች (ኢትዮጵያና ጅቡቲ) ከደሀ አገራት መካከል በመሆናቸው ድርጅቱ የተጠቀሱትን ዕዳዎች ለመክፈል አቅም እንደሌለው በመግለጽ ዕዳው በጠቅላላው እንዲሰረዝ ያቀረበው ተማጽኖ በፈረንሳይ በኩል ተቀባይነት በማጣቱ ድርድሩ ሳይሳካ ቀረ:: የኮሚቴው አባላትም በሪፖርታቸው መጨረሻ ላይ የሁለቱ አገራት መሪዎች በድርድሩ በቀጥታ ጣልቃ እንዲገቡና ፈረንሳይን ለማግባባት ጥረት እንዲያደርጉ አሳሰቡ::[153]

[153] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ፡ ምድር ባቡር 1 2፤ አሰግድ ወልደ አማኑኤል (የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር) ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡ የካቲት 14፣ 1981

የምድር ባቡሩን ደረጃ ለማሻሻል እነዚህ እርምጃዎች እየተወሰዱ በነበረበት ወቅት የምድር ባቡሩ ያሉበት ሌሎች ችግሮችም ለህልውናው ፈታኝ እየሆኑ ነበር። በሁለቱም አገሮች በባቡር መስመሩ፣ በባቡሩ እንቅስቃሴና በሚጓጓዙት ዕቃዎች ላይ የሚካሄደው ከፍተኛ የሥርቆት ወንጀል ለኩባንያው ህልውና ዋነኛው እንቅፋት ተደርጎ ተወሰደ። በተለይ የጅቡቲ መንግስት ለሀዲዱ ምንም ጥበቃ አለማድረጉ በኢትዮጵያ በኩል ችግሩን ለመቆጣጠር ሁለት የመፍትሄ አማራጮችን ለማቅረብ አስገደደ፡- ሁለቱ አገሮች በግዛታቸው የተጠናከረ የሕግ አስከባሪ ኃይል እንዲመድቡ ወይም ድርጅቱ የራሱን የጥበቃ ኃይል እንዲያቋቁም መፍቀድና ይህን ማድረጉ ለሚያስከትለው ወጪ መለስተኛ የታሪፍ ማስተካከያ ማድረግ። የምድር ባቡር ኩባንያው የገጠሙት ተጨማሪ እንቅፋቶች በጠረፍ አከባቢና በመሐል አገር የሚደረገው የተንዛዛ ፍተሻና ቁጥጥር ቀልጣፋ የባቡር እንቅስቃሴን ማስተጓጎሉ፣ የድርጅቱ የቴክኒክ ዲሬክተር (ሙሴ ባደር) አቅም ማጣትና ለግል ጥቅም ቅድሚያ መስጠት፣ በሁለቱ አገሮች የሚገኙ የድርጅቱ ንብረቶች ይዞታ አለመከበር ወዘተ ይገኙባቸዋል።[154]

ከኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ስምምነት መፈረምና ወደ ተግባር መግባት ቀጥሎ በኢትዮጵያ መንግስት የተወሰደው ዐቢይ እርምጃ ከአዲስ አበባ-አሰብ የባቡር መስመር ለመዘርጋት ያለመ ፕሮጀክት መንደፍና መንቀሳቀስ ነበር። ስለ ፕሮጀክቱ የቀረበ የጥናት መግለጫ እንደሚያመለክተው ከዚህ አቅድ በፊት በአገሪቱ ውስጥ የባቡር ትራንስፖርት መረብ (network) የሚዘረጋበትን ሁኔታ የሚመለከት አጠቃላይ ጥናት ተካሂዶ እንደነበር ያመለክታል።በዚህም መሠረት ሰሜንና ደቡብን፣ ምዕራብና ምሥራቅን እና ዋና ዋና የምርትና የአገለግሎት ክፍሎችን በባቡር ትራንስፖርት ለማገናኘት የሚቻልበት ሁኔታ በአጠቃላይ መልኩ ቀርቦ ነበር።

[154] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ልዩ ልዩ ስምምነቶች፤ ስለ ኢትዮ-ጅቡቲ የትራንስፖርትና መገናኛ ግንኙነት የቀረበ ማስታወሻ፡ ነሐሴ 1980





የአሰብ መስመር የትራንስፖርት ሥርዓት (system) ሲጠና የመጀመሪያው እንዳልነበርም ያመለክታል። ነገር ግን ፕሮጀክቱ ጠለቅ ባለና በተቀናጀ ሁኔታ በተለይም የምድር ባቡር አማራጭ በዝርዝርና በጥልቀት ባለመጠናቱ የመስመሩን ትክክለኛ አቅጣጫ ለመምረጥ፣ የዋጋውን ግምት ለመተመንና የአፈጻጸሙን ስልት ለመቀየስ የሚያስችል እንዳልነበር የጥናት ሪፖርቱ ይከራከራል።[155]



ምንጭ፡ ውጉሚ (የአዲስ አበባ-አሰብ ምድር ባቡር ጥናት አጭር መግለጫ፡ 1979)

[155] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር 1 2፣ የአዲስ አበባ-አሰብ ምድር ባቡር ጥናት አጭር መግለጫ፡ ግንቦት 1979




ምንጭ፡ ውጉማ (የአዲስ አበባ-አሰብ ምድር ባቡር ጥናት
አጭር መግለጫ፡ 1979)



የአዲስ አበባ–አሰብ ምድር ባቡር መሥመር መግለጫ

ኮሎኔል መንግስቱ የአሰብ-አዲስ አበባ የምድር ባቡር ፕሮጀክት በአገሪቱ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት በተለይም በውጭ ንግድ እንቅስቃሴና ደህንነት ላይ ሊጫወት የሚችለውን ወሳኝ ሚና በማጤን ዝርዝር አፈጻጸሙ በአስቸኳይ ተጠንቶ እንዲቀርብ አዘዙ:: በዚህም መሠረት መርሐ ግብሩ ከመሪ ዕቅዱ ምዕራፎች ጋር በማቀናጀት ተዘጋጀ:: የዕቅዱ የመጀመሪያ ምዕራፍ በ1977/78 የተከናወነ ሲሆን ውይይት ከተደረገበተ በኋላ የፕሮጀክቱ የኢኮኖሚና የቴክኒክ ጥናት ተጠናቆ ስለአተገባበሩ ውሳኔ ተሰጠበት:: ቀጣዩ ምዕራፍ ከ1980-83 ሊከናወን ታቅዶ የነበረ ሲሆን በነዚህ ዓመታት የዲዛይኑን ሥራ፣ የገንዘብ ፍለጋና የኮንስትራክሽን ዝግጅት ተግባሮችን ለማከናወን ታቅዶ ነበር:: በሦስተኛው ምዕራፍ (1983-89) የግንባታውን ሥራ ለመጀመርና ለማጠናቀቅ ታስቦ ነበር::

በመጀመሪያው ምዕራፍ የታቀደውን የፕሮጀክቱን ጥናት በሚመለከት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር አስፈላጊውን





የጥናት ዝርዝር መመሪያ አዘጋጀ:: ለዚህም ሲባል ራይትስ የተባለው ታዋቂ የሕንድ መንግስታዊ አጥኚ ኩባንያ በመጋበዝ የምድር ባቡሩን የቴክኖ-ኢኮኖሚ አዋጭነት (feasibility) ጥናት እንዲያከናውን ኮንትራት በመፈራረም የጥናቱ ሥራ እንዲካሄድ ተደረገ:: ይህ ወደ ሁለት ሚሊዮን ብርና አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ የፈጀ ጥናትም በተሳካ ሁኔታ ተጠናቆ በ7 ጥራዝ ቀረበ:: የተካሄደው ጥናት ምድር ባቡርን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አማራጮችን ጭምር ከመገምገሙም በላይ የፕሮጀክቱን ዝርዝር ትራፊክ፣ አቅምና መሥመር፣ የቴክኖሎጂ ይዘት፣ የዋጋ/ወጪ ዝርዝር፣ የአፈጻጸም ስልትና ደረጃ እንዲሁም ቅደም ተከተል ያጠቃልላል::

የአዲስ አበባ-አሰብ የምድር ባቡር ሦስት አማራጮችን ያገናዘበ ነበር:: እነሱም አዲስ አበባ-ደብረ ብርሃን-ኮምቦልቻና አሰብ (የኮምቦልቻ መስመር)፤ አዲስ አበባ-ናዝሬት-አዋሽ ወንዝን ሳያቋርጥ በሚሌ አድርጎ አሰብ (ከአዋሽ ሸለቆ በስተምዕራብ)፤ አዲስ አበባ-ናዝሬት-አዋሽ ወንዝን ሁለት ጊዜ በመሻገር በገዋኔ ዱፕቲና አሰብ (ከአዋሽ ሸለቆ በስተምሥራቅ) ሲሆኑ እያንዳንዱ መስመር ከልዩ ልዩ መመዘኛዎች አንፃር ከተገመገመ በኋላ ከአዋሽ ሸለቆ በስተምሥራቅ ያለው መስመር የተሻለ አማራጭ ሆኖ ተመረጠ::[156]

ፕሮጀክቱ እውን የመሆን ዕድል ባያገኝም በአዲስ አበባ-ጅቡቲ የምድር ባቡር መስመርና ኩባንያ ላይ ለረጅም ጊዜ የነበረውን ጥገኝነት በከፍተኛ ሁኔታ ይቀይር እንደነበር መገመት ይቻላል:: በዋነኝነት ግን የኢትዮ-ጅቡቲ የምድር ባቡር ድርጅት ከዘመናት ውጣ ውረድ በኋላ ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ለመሸጋገር ችሎ ነበር:: በሁለቱ አገራት ተቀባይነት ያገኘ ስምምነት ከመፈረሙም በላይ በሂደቱ ኢትዮጵያ መሠረታዊ መብቶቿን እና ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስከበር ቻለች:: የምድር ባቡሩን ሁለንተናዊ አደረጃጀት ለማሻሻል እና ዘመናዊ ገፅታ

---

[156] ዝኒ ከማሁ



የአዲስ አበባ–አሰብ ምድር ባቡር መሥመር መግለጫ

እንዲላበስ የማድረጉ ጥረትም ወደ መሳካቱ ደረጃ እየተሸጋገረ መጣ፡፡ በኢትዮጵያ በ1983 የተከናወነው የመንግስት ለውጥ የትግበራውን ሂደት በእጅጉ ቢያስተጓጉልም በቅርቡ የምድር ባቡሩ መስመር ጥገና በአዲስ መልክ ተጀምሯል፡፡

ከ1983 እስከ 1990ዎቹ አጋማሽ የነበረውን የምድር ባቡር ኩባንያ እንቅስቃሴ ለመዘገብ የሚያስችል የተሟላ መረጃ ባይገኝም የድርጅቱን ይበልጥ መዳከም መገመት ግን ይቻላል፡፡ ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎት እየተዳከመ በመምጣቱ እና ያሉት የትራንስፖርት መጓሪያዎችም ያረጁና በቂ አገለግሎት መስጠት የማይችሉ በመሆናቸው በ1990ቹ አጋማሽ በኢትዮ-ጅቡቲ መስመር (corridor) ያለው የጭነት ድርሻ ከ7-8% ብቻ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ የምድር ባቡሩን ለማሻሻል ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ይጠይቃል፡፡ ይህንን ማድረጉ ከሁለቱ መንግስታት አቅም በላይ ነው ከሚል እሳቤ በመነሳትም የኩባንያውን የአስተዳደርና የኦፕሬሽን ሥራዎች ልምድ፣ ችሎታና የካፒታል አቅም ላለው የግል ባለሃብት በረጅም ጊዜ ውል (concession) ለመስጠት በሁለቱ አገሮች በተደረሰው መግባባት መሠረት ስምምነት ተደርጎ ጸደቀ፡፡ ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻልም ከአውሮፓ ህብረት በተገኘ ዕርዳታ HIFAB Int. Consortium የተባለ አማካሪ ድርጅት ከግንቦት 1995 አንስቶ ጥናት ማድረግ ጀመረ [157]

ከምድር ባቡሩ ህልውና አንፃር መጻኢው ጊዜ ምን መልክ እንደሚኖረው መገመት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የወቅቱ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የምድር ባቡሩን ወሳኝ ሚና ይበልጥ እንደሚያጎላው እሙን ነው፡፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የምድር ባቡሩ እና የጅቡቲ ወደብ የኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ንግድ ዋነኛ መተላለፊያ የሆኑበት ደረጃ ላይ መድረሳቸው አያከራክርም፡፡ ስለሆነም ለዘመናት የተደከመባቸውን የሀገሪቱን የቀዳሚ ተጠቃሚነት መብቶች ለዘለቄታው ማስጠበቁ የዚህ የትውልድ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

---

[157] ውጉሚ፦ ኢትዮ-ጅቡቲ የጋራ ኮሚሽን ሀ 12፤ ሀይሌ አሰግዴ (የመሠረተ ልማት ሚኒስትር) ለመለስ ዜናዊ (ጠቅላይ ሚኒስትር)፡ ግንቦት 2፤ 1996





# ምዕራፍ ፭

# የጅቡቲ ወደብ፡ የጥገኝነታችን ቁልፍ

## 5.1. በጅቡቲ ወደብ የመጠቀም መብት በንጉሳውያን ዘመን

ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ ስታራምዳቸው ለነበሩት የባለቤትነት ጥያቄዎች እና የቋሚ ተጠቃሚነት መብቶች መሠረታዊው ምክንያት የጅቡቲ ወደብ እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ የጅቡቲው በር ከብሔራዊ ወደቦችም በላይ የኢኮኖሚ እና የደህንነት ዋስትና ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከአፄ ምንሊክ ጀምሮ ያሉ መሪዎች የዚህን ወደብ ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በመገንዘብ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ እንዲተዳደር ሲታገሉ ኖረዋል፡፡ ተከታታይ ትውልዶች በግዛቱ ጉዳይ ያደረጓቸው እልህ አስጨራሽ ትግሎች ቁልፍም ወደቡ ነው፡፡ ይህ ወደብ የጥንካሬያችን፣ የጥገኝነታችን፣ የማጣታችን እና የህልውናችን መገለጫ ሆኖ ኖሯል፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል አንድ ወደብ ሲቋቋም በሁለት አቢይ ነገሮች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ይታመናል፡፡ እነዚህም በባህር መገናኛ በኩል ሊሰጥ የሚችለው ጥቅምና ስትራቴጂ እና ሕይወቱን የሚጠብቅ የኂላ አገር መኖሩን ማረጋገጥ ናቸው፡፡ ሀብታም የሆኑ የኢትዮጵያ ተራራዎች ለጅቡቲ ወደብ መመሥረት የኂላ ደጀን ተደርገው እንደተወሰዱ ደግሞ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ጅቡቲ የኢትዮጵያ ግዛት አካል ነው የሚለው እሳቤ ቢያከራክርም ተግባራዊ ከሆኑ መመዘኛዎች በመነሳት ወደቡ የኢትዮጵያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በ1960ቹ አጋማሽ አከባቢ የጅቡቲ ወደብ ባለው ዝግጁነትና ትራፊክ ከፈረንሳይ ወደቦች መካከል የሦስተኛነትን ደረጃ የያዘ፤ ፈረንሳይ ይገዛቸው ከነበሩት አገሮች መካከልም ከዳካር ቀጥሎ ሁለተኛ፤ እንዲሁም ለመርከቦች ነዳጅ፣ ውሃና ስንቅ በማቅረብ ረገድም ከዓለም ወደቦች ስምንተኛ ነበር፡፡ ከቀይ ባህርና ከኤደን ባህረ

ሰላጤ ወደቦች መካከልም በዝግጁነትም ሆነ በትራፊክ መጠን ጅቡቲን የሚቀድመው የኤደን ወደብ ብቻ ነበር።

የጅቡቲ ወደብ በኢትዮጵያ ላይ ለነበረው ጥገኝነት ዋነኛ ማሳያዎች ፈረንሳይ በተለያየ ጊዜ ለኢትዮጵያ የሰጠቻቸው የልዩ ተጠቃሚነት መብቶች ናቸው። ለምሳሌ ያክል ከ1898/9 (እ.ኤ.አ. ከ1906) ጀምሮ በጅቡቲ በኩል የሚያልፉት የኢትዮጵያ የንግድ ዕቃዎች ከወደቡ ቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ መደረጉ፤ በጥር 1946 የፈረንሳይ መንግስት ከጅቡቲ ግዛቱ አንድ አስረኛውን (አፋምቦ) ቆርሶ ለኢትዮጵያ መመለሱ፤ በህዳር 1952 የኢትዮ-ፈረንሳይ የምድር ባቡር ኩባንያ ጥቅም ለሁለቱ መንግስታት እኩል እንዲሆን፣ ዋናው ጽህፈት ቤቱም ከፓሪስ ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር ከመደረጉም በላይ እ.ኤ.አ. እስከ 2016 ድረስ የሐዲድ መስመሩን የሚወዳደር ሌላ መስመር በአገር ውስጥ እንዳይዘረጋ ስምምነት መደረሱ፤ ከ1951 ወዲህ ፀረ-ሱማሌ የሆኑ የጅቡቲ ፖለቲከኞች (በተለይ አፋሮች) የግዛቱን የውስጥ አስተዳደር እንዲመሩ መደረጉ ወዘተ ይጠቀሳሉ።[158]

በታጁራ በኩል እግሯን ወደ ጅቡቲ ያስገባችው ፈረንሳይ ቀስ በቀስ አብዛኛውን የጠረፍ ግዛት ቅኝ ስታደርግ የኢትዮጵያ መሪዎች በተለይም የሸዋው ንጉሥ (በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት) ምንሊክ ይህን መከላከል በሚችሉበት ደረጃ ላይ አልነበሩም። ቀድሞ ለኢትዮጵያ መሪዎች ይገብሩ የነበሩ የጉባት፣ የታጁራና የራሒታ ሡልጣኖች ተራ በተራ በፈረንሳይ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውም ተከታታይ መንግስታት ቁልፍ የባህር በራቸውን እያጡ ለመሆኑ አመላካች ነበር። ሁኔታውን ለመቀልበስ የሚያስችል አቅም እንዳልነበራቸው በመረዳትም ንጉሥ ምንሊክ የፈረንሳይን ወዳጅነት ለማግኘት እና በሂደቱም ወደ ህንድ ውቅያኖስና ቀይ ባህር የሚያደርሳቸውን በር ለማግኘት ጥረት ማድረግ ጀመሩ።

[158] ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 2፤ በጅቡቲ ጉዳይ የቀረበ የጥናት ሪፖርት፡ ሰኔ 28፤ 1968





ለዚህም ምሳሌ ተደርጎ የሚወሰደው እ.ኤ.አ. በ1876 ለፈረንሳይ ፕሬዚደንት በጻፉት ደብዳቤ በታጁራ የነበራቸውን መብት በከፊል ለመልቀቅ መፍቀዳቸውን አሳወቁ። ንጉሠ ነገሥት በሆኑ በዓመቱ (ጥቅምት 1882) ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ሳድ ካርኖ በጻፉትም ደብዳቤ "በቀይ ባህር ያለውን የባህሩን ጠረፍ ፈረንሳይ መያዟን በምንቀበልበት በአሁኑ ጊዜ [የባህር በር] መብታችን ታውቆ አንድ ነጥብ ሊኖረን እንደሚገባ እናስታውቃለን። ይህንንም ለማግኘት የምንደሰት ስለሆነ በምንም ምክንያት የቀይ ባህር ጠረፋችን ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ እያስጠነቀቅን ነው" በማለት አስታውቀው ነበር።[159]

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፍ ስላላት መብት ለፈረንሳይ ጥያቄ ያቀረበች ሲሆን በጉዳዩ ዙሪያ ከፈረንሳይ መንግስት ጋር ለሦስት ዓመታት የዘለቀ ድርድር አካሂዳለች። በውጤቱም ፈረንሳይ ከጠረፍ ግዛቷ የባህር በር የሚሆን መሬት ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባትሆንም ኢትዮጵያ ከጅቡቲ ወደብ በስተደቡብ ያለውን የሱማሌና የኢሳ ምድረ በዳ የሆነውን አገር በሙሉ እንድታስተዳድር መቀበሏን እና የጅቡቲን ጠረፍ ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፋ ላለመስጠት መስማማቷን ያትታል። ከአድዋ ድል ማግስት ፈረንሳይ ከምንሊክ ጋር ወዳጅነቷን ለማጠንከር በማሰብ አዲስ ስምምነት ለመፈራረም በጠየቀችውም መሠረት በጥር 1889 (26 January 1897) የኢትዮጵያው መሪ ለፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ስምንት አንቀጾች ያሉት የወዳጅነት ስምምነት ልከው በፈረንሳይ መንግስት ተቀባይነት አገኘ፣ ጸደቀም። ከአንቀጾቹ መካከል አንዱ የፈረንሳይ መንግስት "የጅቡቲን በር እንደ ኢትዮጵያ የንግድ በር ማየት ይገባዋል" ይላል።

[159] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ጉዳዮች 1፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር ጠረፍ ላይ ስላላት መብት የተደረገ ጥናት (በ ፒ. ፔትሪዲስ እና በጓደኞቻቸው ተከለማርያም የተዘጋጀ)፡ ጥቅምት 1961, ገፅ 34-40።

ይህን ስምምነት መነሻ በማድረግም የሁለቱ መንግስታት ተወካዮች (ልዑል ራስ መኮንን እና ሙሴ ላጋርድ -የፈረንሳይ ሶማሌ ገገር) በጅቡቲ ከተማ "ለምንሊክና ለወራሾቻቸው" ስለ ተሰጠው ርስት በጥር 22፣ 1889 የተፈራረሙት ሰነድ በዋነኝነት የባህር በሩን መብት ያረጋግጣል። በውሉ መሠረትም፡-

> የጅቡቲ የፈረንሳዊ በር ለኢትዮጵያ መንግስት ንግድ መውጫ በር ስለሆነ፣ በቅርቡ አንድ ስፈ ቦታ የጃንሆይ ሰዎች እንዳይጉላሉና እንዳይቸገሩ ይሰጣቸዋል። ይህ ቦታ ለጃንሆይ ለንጉሠ ነገሥት ምንሊክ ለራስዎ ክርሳቸውም በኋላ ለወራሾቻቸው ይኖራል። በዚህም ቦታ የሚቀመጡ [ኢትዮጵያውያን] እንደ ፈረንሳዊ ሕግጋት ባገሩ ዳኛ ይዳኛሉ።

ይላል። ቀጥሎም በጥር 23፣ 1889 ራስ መኮንን እና ሙሴ ላጋርድ ሐረር ከተማ በተፈራረሙት ተጨማሪ ስምምነት የጅቡቲ ወደብ "ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለሚፈልጉት ነገር ሁሉ ለንግድም ለጦር መሳሪያም ለጃንሆይ ለሆነ ነገር ሁሉ በነፃ አለቀረጥ ያልፋል" ሲሉ ወሰኑ። እነኚህ ስምምነቶች በፈረንሳይ መንግስት የጸደቁ ሲሆን (ባይታተሙም) ጅቡቲ የኢትዮጵያ የንግድ በር (Débouché officiel) መሆኑን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት ሕጋዊ (official) በር መሆኑን ያረጋገጠ ነው ማለት ይቻላል።[160]

የጅቡቲ የውስጥ አስተዳደር ገዕታ በግዛቱ ከተፈጠረው የብሔረተኝነት ስሜት የተነሳ እየተቀየረ መምጣቱን ተከትሎ የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስት አዲስ የወደብ ውል ለማድረግ እንደፈለገ እና እንደተሳካለትም ባለፈው ምዕራፍ ተጠቅሷል። በግዛቱ ማንኛውም ዓይነት የውስጥ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ቢኖር የምድር ባቡሩ እና የወደቡ ስምምነት መፈረም ጅቡቲን ለዘለቄታው ለማስመለስ ለተነደፈው ፖሊሲ እንደዋስትና ተደርጎም ተቆጥሮ ነበር።

[160] ዝኒ ከማሁ, 40-41





የፈረንሳይ መንግስትም አዲሱን ስምምነት ለመፈራረም የራሱ ምክንያት ነበረው። ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብን መልሳ ካገኘች በኋላ ትኩረቷን ከጅቡቲ ላይ እንዳታነሳ ማረጋገጫ ሲሆን የሚችለው ለሃገሪቱ ተጨማሪ መብት መስጠትና በወደቡ ላይ ግንባታ እንድታከናውን መፍቀድ እንደነበር መገመት ይቻላል። ህዳር 2፣ 1952 (12 November 1959) በሁለቱ አገሮች መካከል የተፈረመውም ስምምነት ፈረንሳይ ከጥር 1889 ጀምሮ የገባቻቸውን ግዴታዎች ያብራራና የዘረዘረ የኢትዮጵያንም ጥቅም ይበልጥ ያጠናከረ ውል ነበር። አዲሱ ውል እንደ ምድር ባቡሩ ሁሉ የወደቡንም ጉዳይ የወሰነ ነበር። በዚህ ስምምነት ኢትዮጵያ በሠላምም ሆነ በጦርነት ጊዜ የጅቡቲን ወደብ ልትገለገልበት የምትችል መሆኑን የፈረንሳይ መንግስት ከማረጋገጡም (አንቀጽ 11) በላይ የግዛቱን ሥልጣን የሚመለከት ማናቸውንም ዓይነት መብት (extraterritorial right) ማግኘት ብቻ ሲቀር ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ ለማንኛውም ነፃ ወደብ የሚፈቀዱ መብቶችን እንድታገኝ (አንቀጽ 12) ተደረገ። አንቀጽ 12 በተለይ ዘርዘር ባለ መንገድ አገሪቱ በወደቡ ስለሚኖራት መብት ያትታል። እነሱም፡

ሀ) ወደ ኢትዮጵያ ለሚሄዱ ለማናቸውም ሰዎችና ዕቃዎች ሊጠቀሙ በሚችሉት የወደብ መዣሪያዎችና (installations) አገልግሎቶች (services) ለመጠቀምና ማናቸውንም ነገር ማከናወኛዎችና አገልግሎቶች በያይነቱ ነዳጆች፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና መበራት ውሃ ጭምር በማግኘትም በኩል ላገሩ ተወላጆች የሚደረገው የቀደምትነት መብትና የብልጫ አስተያየት በሚጠቅማት ረገድ የተረጋገጠላት ይሆናል።

ለ) ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡትና ከኢትዮጵያ ለሚወጡትም ለማናቸውም ዓይነት ዕቃዎች ከወደብ ቀረጥ በቀር ሌላ ማናቸውም ዓይነት የጉምሩክ ቀረጥ፣ ግብር ወይም ታክስ ሳይከፈልባቸውና እንዲሁም ከነዚሁ ዕቃዎች ላይ የወደቡን ቀረጥ ለመቀበያ ብቻ አስፈላጊ ሆኖ ከሚደረገው በቀር ማናቸውንም የወደብም ሆነ የጉምሩክ ፍተሻና ፎርማሊቲ ሳይጠየቁ የመገልገል መብት፤ ይህም ይሆን ዘንድ ከኢትዮጵያ በሚወጡት ወይም ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡት ዕቃዎች ላይ ኬላው እንኳ ቢቀር ወደ

ፈረንሳይ ሶማሌ ለሚገቡት ወይም ከዚሁ ግዛት ለሚላኩት ዕቃዎች በሚደረግላቸው ልክ ልዩ አስተያየት ይደረግላቸዋል። የኢትዮጵያ መንግስት የሚልካቸው ወይም በሱ አድራሻ የሚመጡት ዕቃዎች ሁሉ ከማናቸውም ዓይነት ፍተሻ ወይም ምርመራ ነፃ ናቸው።

ሐ) በነፃው ወደብ ክልል ውስጥ ልዩ ልዩ ዕቃዎች የሚዘጋጁባቸው ፋብሪካዎችና ሥራዎች ከዚህ ከፍ ብሎ ከተነገረው የወደብ ቀረጥና ይህንኑም ለማስከፈል ከሚደረገው የወደብ ምርመራ በቀር ሌላ ሳይጠየቁ ለሥራቸው የሚያስፈልጋቸውን ጥሬውን ሀብት/ጥሬ ዕቃ (matiéres premiers) ከውጭ አገር ለማስመጣትና ሠርተው ያዘጋጁትንም ዕቃዎች በዚሁ ዓይነት አኳኋን ለፈቃድና (patent) ወደፊት የተቋቋመም እንደሆን በእንዱስቱሪና ከንግድ ሥራ ከሚጠየቀው የጥቅም ግብር በቀር ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ታክስ ወይም ቀረጥ ለግዛቱ ሳይከፍሉ ወደ ውጭ አገር ወይም ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ይችላሉ።

መ) ከላይ በተነገሩት መብቶች ለመጠቀሚያ አስፈላጊ የሚሆኑትን ሠራተኞችና ሹማምንቶች የጉምሩክ ሠራተኞች ጭምር ተግባራቸውን ይፈጽሙ ዘንድ በነፃው ወደብ ክልል ውስጥ የማስገባት መብት፤

ሠ) እንዲሁም ከላይ የተገለጹትን መብቶች ለማስፈጸሚያ አስፈላጊ በሚሆኑት በነፃው ወደብ ውስጥ በሚገኙት መሣሪያዎችና ዕቃዎች የመገልገል መብት ናቸው።

ከላይ የተዘረዘረው ስምምነት ለኢትዮጵያ የመተላለፍ መብት (transit right) የሰጠ ከመሆኑም በላይ የጅቡቲ ወደብ ለኢትዮጵያ ነፃ ወደብ (free port) መሆኑን ያረጋግጣል። በሌላ አነጋገር በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ ላይ ቋሚ መብቶች (established rights) አሏት ማለት ነው።[161]

---

[161] ውጉሚ፡- 57-D3 1-A፤ ስለ ወደቡ የተደረጉ ስምምነቶች ዝርዝር፡ ነሐሴ 11፣ 1952። ውጉሚ፡- ኢጋድ 2፤ ስለ ኢትዮ-ጅቡቲ የትራንስፖርት ስምምነቶች የቀረበ የጥናት ጽሑፍ፡ መጋቢት 1972





ከህዳር 1952 ስምምነት በኋላ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ እንደቀድሞው መገልገሏ ቢቀጥልም ውሉ የሚያጎናጽፋትን የልዩ ተጠቃሚነት መብት በተለያየ ምክንያት ልታገኝ አልቻለችም። ከነዚህም በግዛቱ በፍጥነት እያደገ የመጣውን የውስጥ አስተዳደር መብት ጥያቄና የነፃነት ስሜት፤ ይህ ስምምነት መፈፀሙ ከጅቡቲያውያን፣ ከሶማሊያ እና በግብፅ ከሚመራው የዓረቡ ዓለም የገጠመው ተቃውሞ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ። በእስራኤልና በዓረብ አገሮች መካከል የተደረገውን የ1959 (እ.ኤ.አ. 1967) ጦርነት ተከትሎ የሲውዝ ካናል መዘጋትና ይህም ለተወሰኑ ዓመታት በጅቡቲ ወደብ ላይ ያስከተለው መቀዛቀዝ፤ ኢትዮጵያ የአሰብ ወደብን መልሳ ካገኘች በኋላ ደረጃውን በማሻሻል ለወጪ-ገቢ ንግዷ እንደ አንድ አማራጭ መጠቀም መጀመሯ ወዘተ በተጨማሪነት ሊነሱ ይችላሉ።

## 5.2. ደርግና የጅቡቲ ወደብ

በጅቡቲ ነፃነት ዋዜማ በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ግንዛቤ ከባድ ዕቃና የጦር መሳሪያ በማስመጣቱ ረገድ በጅቡቲ ወደብ ላይ ብቻ የነበረውን መመካት መቀነስ እንደሚያስፈልግና ለዚሁ ተግባር የአሰብ ወደብን በይበልጥ መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ እየታመነበት መጣ። ይህንንም የሚያስፈጽም ብሔራዊ ኮሚቴ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ትእዛዝ በግንቦት 1969 ተቋቋመ።[162] ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያና ሶማሊያ ጦርነት ወቅት የሐሰን ጉሌድ ጅቡቲ ከሲያድ ባሬ ማበሩ ከወደቡ አጠቃቀም አንፃር አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮ ነበር። የጦርነቱን ፍፃሜ ተከትሎ ጅቡቲ የቀደመውን መልካም ግንኙነት ለመመስረት ብትሞክርም የወደቡን አጠቃቀም በተመለከተ አዲስ ምዕራፍ መክፈቱ አልቀረም። እንደ ምድር ባቡሩ ሁሉ ወደቡንም በተመለከተ የ1952 ስምምነት በአዲስ እንዲተካ ይፈልግ የነበረው የጅቡቲ ሪፐብሊክ አቋም በወደቡ አጠቃቀም ዙሪያ ችግር መፍጠሩ አልቀረም።[163]

---

[162] ውጉሚ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ኃይሉ ይመኑ (ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀዳሚ ሚኒስትር) ለዶ/ ፊቀ ገድለጊዮርጊስ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)፡ ግንቦት 19፣ 1969

የአገሪቱን ወጪና ገቢ ንግድ ለማከናወን የአሰብ ወደብን በዋነኛነት የመጠቀሙ ውሳኔ አተገባበር እንደተጠበቀው የተሳካ አልነበረም:: የጅቡቲ የፖለቲካ ሁኔታ ግዛቱ ነፃ ከመሆኑም በፊት ሆነ በኋላ አስተማማኝ አለመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል አሰብን በዋነኛነት ለመጠቀም ለተነደፈው ፖሊሲ መነሻ ሆነ:: በዚህም መሠረት ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎች በአሰብ ወደብ በኩል እንዲገቡ እና በጅቡቲ ወደብ ተራግፈው የሚገኙት ዕቃዎች ዝርዝራቸው ታውቆና ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው በአስቸኳይ እንዲነሱ በተወሰነው መሠረትም ሲሰራበት ቆየ:: በ1970 አጋማሽ ግን የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያን ወጪና ገቢ ዕቃዎች በሚያመላልሱ መርከቦች ከአቅሙ በላይ ስለተጨናነቀ በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠንቅ ያስከተለበት ደረጃ ላይ ደረሰ::

የሁኔታውን ክባድነት የሚያመለክቱ ጉልህ ምክንያቶችን መጥቀሱ በቂ ይሆናል:: አንደኛው በኪራይ (ቻርተር) እህልና ማዳበሪያ ጭነው የሚመጡት መርከቦች እንደደረሱ ወደብ ውስጥ ገብተው ለማራገፍ ባለመቻላቸው ከሁለት እስከ ሦስት ወር ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው:: መርከቦቹ በሚቆሙበት ቀን ቁጥር አገሪቱ ለእያንዳንዱ መርከብ በቀን ከ4500-5500 የአሜሪካን ዶላር ለመክፈል ተገደደች:: በዚህም ሁኔታ እ.ኤ.አ. በ1977 መንግስት ከሦስት ሚሊዮን ብር በላይ መክፈል ግዴታ ሆኖበት ነበር:: እንዲሁም ማንኛውንም ዕቃ ጭነው የሚመጡ መርከቦች የአሰብ ወደብ መጨናነቅን ምክንያት በማድረግ ከመደበኛው የጭነት ዋጋቸው በላይ 30% በተጨማሪ ይከፈላቸው ነበር:: በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ በአንድ ዓመት ውስጥ ከአሥር ሚሊዮን ብር በላይ ለሆነ ተጨማሪ ወጪ ተዳረገች:: የነዚህ ጫናዎች ድምር ውጤት የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪዋን ማራቆት፣ በአገር ውስጥ ገበያ የዕቃ ዋጋ መናር፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርባቸው ዕቃዎች ዋጋ ከፍተኛ መሆን

[163] የጅቡቲ ሪፐብሊክ የምድር ባቡሩንና የወደቡን አጠቃቀም በተመለከተ አዲስ ድርድር ስለ ማድረግ ስለተከተለው አቋም ከላይ ተመልከት





እና ገበያ ማጣት፣ የወደቡን መጨናነቅ ምክንያት በማድረግ መርከቦች ወደ ኢትዮጵያ ወደቦች ለመምጣት አለመፈለግ ወዘተ ነበር:: በመንግስት በኩል በአሰብ ወደብ የነበረውን የዕቃ ክምችት በአፋጣኝ ወደ መሐል አገር ያንጉዝ ዘንድ በአዋጅ የተቋቋመው "የአሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ" ያስገኘው ውጤትም አመርቂ አልነበረም::[164]

ከዚህ አጣብቂኝ ለመውጣት ብቸኛው አማራጭ ተቀዛቅዞ የነበረውን በጅቡቲ ወደብ የመጠቀም እንቅስቃሴ እንደገና ማስጀመሩ እንደሆነ ታመነ:: በወቅቱ የሞምባሳን ወደብ የመጠቀም አማራጭም ቀርቦ ነበር:: ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ ለመጠቀም ያላት መብት የተጠበቀ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ከአዲሱ የጅቡቲ መንግስት ጋር መነጋገርና ቋሚ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚያስፈልግ በመንግስት በኩል ግንዛቤ ተወሰደ:: እስከዚያው ድረስ ግን አጣዳፊ የሆኑ ጉዳዮችን ለመቅረፍ ሲባል አንድ የመልዕክተኞች ቡድን ወደ ጅቡቲ ሄዶ ስለ ወደቡና ስለ ጅቡቲ-ጋላፊ መንገድ አጠቃቀም ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር እንዲነጋገር ተወሰነ:: በወቅቱ በጅቡቲ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ከተፈለገው ስምምነት ለመድረስ አመቺ እንዳልሆነ ቢገመትም በሁለቱ አገሮች ግንኙነት መቀዛቀዝ ጅቡቲ ይበልጥ ተጎጂ መሆኑን በማሳመን የኢትዮጵያንም በጎ ፈቃድ በማሳየት ወደ መግባባት እንዲደረስ መመሪያ ተሰጠ::

ለኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን የተሰጠው መመሪያ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ የምትፈልገው በአምስት ወር ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ እስከ 80 ሺህ ቶን የሚደርስ እህል፣ ዕቃና ሸቀጣ ሸቀጥ በጅቡቲ ወደብ እንዲራገፍ፤ በዚሁ

[164] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 1፤ ገብረየስ ባሻ (ኢትዮጵያ አማልጋሜትድ ሊሚትድ ሥራ አስኪያጅ) ለትራንፖርተና መገናኛ ሚኒስቴር፡ ጥር 3፣ 1970፤ ኃይሉ ይመኑ

(በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀዳሚ ሚኒስትር) ለዶ/ር ክ/ል ፈለቀ ገድለጊዮርጊስ - ስለ አሰብ ትራንስፖርት ልዩ ኮሚቴ፡ ሰኔ 26፣ 1970

ጊዜ ውስጥም እስከ 50 ሺህ ቶን የሚደርስ ቡናና ጥሬ ጥሬ ሌላም በጅቡቲ ወደብ በኩል ወደ ውጭ መላክ እንዲቻል የጅቡቲ መንግስት አስፈላጊውን እንዲያሟላ ነበር። የጅቡቲ-ጋላፊ መንገድንም ስለመጠቀም በተመለከተ በጅቡቲ ወደብ በኩል ከውጭ የሚገባውንም ሆነ ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት፣ ዕቃና ሸቀጣ ሸቀጥ በዚሁ አውራ መንገድ ማከናወን የሚቻልበትን መንገድ እንዲያጠና ታዟል። ለመደራደሪያ የቀረበው ዝርዝር መመሪያ እንደሚያመለክተው የንግድ እቃዎችን በሁለቱ አገራት መካከል በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማጓጓዝ እንዲቻል በየሳምንቱ ከመቶ ያላነሱ ካሚዮኖች በሁለቱም አቅጣጫ እንዲንቀሳቀሱ መፍቀድ፤ ለመንገድ አጠቃቀም የሚከፈለው ታሪፍ ዘላቂ ስምምነት ላይ እስኪደረስ ድረስ ለጊዜው በጅቡቲ እና በኢትዮጵያ ግዛት ክልል ውስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎች በየሃገራቱ ታሪፍ ለሚገኙባቸው መንግስታት እንዲከፈል ይጠይቃል።

ለዚህ ጥያቄ የጅቡቲ መንግስት በመልሱ ከኢትዮጵያ ይጠይቃል ተብሎ የተገመተው በየብስና በአየር ትራንስፖርት እንዲላክለት የሚፈልጋቸው እንደ እህል፣ ቡናና ስኳር የመሳሰሉት ቁሶች በርግጥ እንደሚደርሱት አስተማማኝ ዋስትና ማግኘት፤ በጅቡቲና በአዲስ አበባ እንዲሁም በጅቡቲና በድሬዳዋ መሀከል የነበረው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራውን እንዲጀምርና ለጅቡቲ የሚያስፈልገው ጫት፣ ሥጋና ፍራፍሬ እንደሚደርሰው ማረጋገጥ፤ እና በትራንስፖርቱ ሥራ ላይ ለሚሰማሩት የሁለቱም አገር ዜጎች የቪዛ ጥያቄን ማስቀረት እንደሚሆን ተገመተ።[165]

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ቡድን ከጅቡቲ ሪፐብሊክ ባለሥልጣኖች ጋር ከመጋቢት 19-29፣ 1970 በሁለቱ አገሮች መካከል ስላለው የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነት ንግግር አድርጎ ለአምስት ወራት የሚዘልቅ የመግባቢያ ቃል ጉባኤ (Procès-verbal) ለመፈራረም ቻለ። የኢትዮጵያ ልዑክ ባቀረበው አጀንዳ

[165] ውጉማ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 1፤ የአሰብ ወደብ በመጣበቡ የጅቡቲ ወደብን ስለመጠቀም የቀረበ የጥናት ጽሑፍ፡፡ የካቲት 4፣ 1970





ቅደም ተከተል መሠረት መጀመሪያ ንግግር እንዲደረግበት የተፈለገው በወደቡና በጋላፊ መንገድ ስለመጠቀም ሲሆን በሁለቱ አገሮች መካከለ ስላለው የኢኮኖሚና የንግድ ግንኙነት የሚደረገው ንግግር ወደ መጨረሻ ደረጃ ተወሰደ። ኢትዮጵያውያኑ ይህንን ያደረጉበት ምክንያት መንግስት በአፋጣኝ የሚፈለገው በወደቡና በመንገዱ መጠቀምን ስለነበር በጅቡቲ በኩል በአንፃሩ የሚፈለገው ደግሞ የንግዱ እንቅስቃሴ እንዲጀመር በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ስለ ወደቡና ስለ መንገዱ የጅቡቲ መንግስት ያለውን አስተያየት ለማወቅና የንግዱ ጉዳይ ላይ ሲደረስ አቋማቸውን ለማጠንከር ወይም ለማለሳለስ አለበለዚያም ጨርሶ ንግግሩን ለማቋረጠ እንዲያስችል በማሰብ እንደነበር ተገልጿል።

በንግግሩ ወቅት ኢትዮጵያ በወደቡና በመንገዱ ስለመጠቀም ያነሳችው ጥያቄ ከጅቡቲ አዎንታዊ ምላሽ በማግኘቱ ለቡድኑ ቀድሞ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ኢትዮጵያ ለጅቡቲ የምትልካቸው እህል፣ ቡና፣ ስኳር፣ ጫት፣ ሥጋና ፍራፍሬ እንደቀድሞው በመንገድና በአየር በጊዜው እንደሚደርሰ ማረጋገጫ ተሰጠ። የጅቡቲ መንግስትን በተለይ ለማስደሰት ሲባልም በሶማሊያ ጦር የፈራረሰው የሀዲድና የድልድይ ጥገና አልቆ ቢበዛ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ የጅቡቲ-አዲስ አበባ ባቡር መንገድ ሥራውን እንደሚጀምር ተገለጸላቸው።[166]

ተደራዳሪ ቡድኑ ከንግግሩ ፍፃሜ በኋላ ለመንግስት ያቀረበው ሪፖርት በሁለቱ አገራት መካከል የተፈረመውን ስምምነት መሠረታዊ ነጥቦች ይተነትናል። ወደቡንና የጋላፊን መንገድ አስመልክቶ ከጅቡቲ የቀረቡ መደራደሪያዎችን በማገናዘብ መንግስት ውሳኔ እንዲሰጥባቸውም ጥያቄ ቀረበ። አንደኛ የኢትዮጵያ የጭነት መኪኖች በጅቡቲ ግዛት ውስጥ በሚመላለሱበት ጊዜ ለሚያደርሱት አደጋ የመድን ዋስትና

[166] ውጉማ፡- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ስለ ጅቡቲ ንግግር የቀረበ ሪፖርት፡ ሚያዝያ 6፣ 1970፡፡ የልዑካን ቡድኑ በአምባሳደር ብርሃኑ ዲንቃ (በውጉማ የአፍሪካ መምሪያ ኃላፊ) የተመራ ሲሆን ዶ/ር አሰፋ መድኃኔ (ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ) በአባልነት ይገኙበት ነበር፡፡

(insurance) መግባት ያለባቸው ጅቡቲ ውስጥ ከሚገኝ የኢንሹራንስ ኩባንያ መሆን እንዳለበት የጅቡቲ መንግስት ጠይቋል:: ካሚዮኖቹ•በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ኢንሹርድ ሆነው ጅቡቲ ውስጥ አደጋ ካደረሱ ተጠያቂ የሚሆን የኢትዮጵያ የመድን ድርጅት ወኪሉን በጅቡቲ እንዲያስቀምጥ ተብሎ በኢትዮጵያ መልዕክተኞች የቀረበውን ሐሳብ ሳይቀበሉት ቀርተዋል:: በጅቡቲ ጥያቄ ኢትዮጵያ የምትስማማ ከሆነ ለእያንዳንዱ የጭነት መኪና ለአምስት ወር የሚያስፈልገው ወጪ 600 ብር ይሆናል:: ሁለተኛ ካሚዮኖቹን ይዘው የሚመላለሱት ሹፌሮችና ረዳቶቻቸው ካሁን ቀደም እንደተለመደው በወደቡ ክልል ውስጥ ለማደር ስለማይችሉ ማረፊያ ቦታ እንዲዘጋጅላቸውና ለውሎ አበል የሚያስፈልጋቸው ተመን ከወዲሁ እንዲወሰን ተጠየቀ::

በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ የሚላኩትን ልዩ ልዩ ሸቀጦች በጅቡቲ ውስጥ በአንድ መጋዘን አስቀምጦ ለአገሬው የጅምላ ነጋዴዎች (whole sellers) ለማከፋፈል እንዲችል የንግድ ሚኒስቴር አንድ መጋዘን ተከራይቶ ወይም ሠርቶ ሥራውን የሚያከናውን አንድ ወኪል እንዲያስቀምጥ የቀረበውን ሐሳብ የጅቡቲ መንግስት ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ:: ይህ ቢፈቀድ ኖሮ የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑ ነጋዴዎችን ለይቶ ለመጥቀምና የጅቡቲን የፖለቲካ ሂደት በኢኮኖሚ ተጽዕኖ ሥር ለማዋል ያስችላል ተብሎ ታምኖበት ነበር:: የልዑካን ቡድኑ ያቀረበው ተለዋጭ ሐሳብ ድሬዳዋ ላይ አንድ መንግስታዊ የሆነ ላኪ ድርጅት (exporting agency) ማቋቋምና ከጅቡቲ የሚመጡትን ነጋዴዎች በተለያየ ሁኔታ በመመልከት ተመሳሳይ የፖለቲካ ውጤት ማግኘት እንደሚቻል ያሳስባል::

የጅቡቲ መንግስት በድርድሩ ወቅት ከኢትዮጵያ አፋጣኝ ምላሽ የጠየቀባቸው ጉዳዮችም ነበሩ:: ከዚህ ቀደም ከኢትዮጵያ ሲደርሳቸው የነበረው እህል፣ ቡና፣ ስኳር፣ ፍራፍሬ፣ ጫት ወዘተ መጠኑ ከቀድሞው እንዳይቀንስባቸውና ዋጋውም እንዳይጨምር፤ በተለይ በስኳር በኩል እጥረት ስላለባቸው የሚላክላቸው መጠን ወደ 10,000 ቶን በዓመት ከፍ እንድሊላቸው አጥብቀው ከመጠየቃቸውም በላይ የሚሸጥላቸውም በቀድሞው ዋጋ ከሆነ





ኢትዮጵያ ገበያውን በሙሉ ሞኖፖላይዝ ማድረግ እንደምትችል አረጋግጠዋል:: የጅቡቲ ነጋዴዎች እና ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አንዳንድ ችግሮች ስለሚገጥማቸው በኢትዮጵያ በኩል ለወደፊቱ ደህንነት እንዲሰማቸው እንዲደረግና በሥራቸው ችግር እንዳይገጥማቸው እርዳታ እንዲደረግላቸው ጠየቁ::[167]

የመልዕክተኞች ቡድኑ ያቀረባቸውን የውሳኔ ሐሳቦች ለመመርመርና መመሪያ ለመስጠት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሚኒስትሮችና የሥራ ረዳቶቻቸው ሚያዝያ 16፣ 1970 በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ አድርገው መወሰድ ስለሚገባቸው አቋሞች ተወያዩ:: በስብሰባው መጨረሻ የተላለፉ ውሳኔዎች ወደቡንና የጋላፊ መንገድን አስመልክቶ በጅቡቲ በኩል የቀረቡትን ቅድመ ሁኔታዎች መንግስት በጊዜያዊነት ሙሉ ለሙሉ የተቀበለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ይህም ለጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት ተገልጾ አስፈላጊው ሥራ በአስቸኳይ እንዲጀመር አሳሰበ:: መመሪያዎቹ የተዘጋጁት በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ጊዜያዊ ግንኙነት በተናጠል በመገምገም በመሆኑ በሥራ ላይ በሚውሉበት ወቅት ከመንግስት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓላማና ሂደት ጋር እየተዛመደ እንዲከናወን ተወሰነ:: አጠቃላይ ሁኔታው አገሪቱ የገባችበትን አጣብቂኝ በግልጽ ያመላክታል::[168]

ነገር ግን በጅቡቲ ወደብ በኩል ይከናወን የነበረው የአገሪቱ የወጪ-ገቢ ንግድ በመንግስት ውክልና በተሰጠው የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት (Maritime Transit Services Agency - MTS) ቁጥጥር እየወጣ በግለሰቦች እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መከናወን መጀመሩ ሌላ ችግር ፈጠረ:: በጊዜው እየተፈጸመ የነበረው የማጭበርበር ሥራ እና ይህ ያስከተለው የውጭ ምንዛሪ ብክነት በመንግስት

[167] ዝኒ ከማሁ

[168] ውንማ:- ጅቡቲ ልዩ ልዩ ፋይሎች 2 1፤ ኃይሉ ይመኑ (ሚኒስትሮች ምክር ቤት ተቀዳሚ ሚኒስትር) ለዶ/ር ፈለቀ (ውንማ)፡ ሚያዝያ 30፣ 1970

በኩል እርምጃ እንዲወሰድ አስገደደ። የእርምጃው አንዱ አካል የነበረውም መቀመጫቸውን በጅቡቲ ያደረጉ ወደ ሃያ በሚጠጉ የግል ኩባንያዎች ይካሄድ የነበረውን የትራንዚት፣ ዕቃ የመጫንና የማራገፍ ሥራ ፈቃድ በመሠረዝ አጠቃላይ እንቅስቃሴው በማሪታይም ትራንዚት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን ቁጥጥር ሥር እንዲውል ማድረግ ነው። ውሳኔው ዕቃ የመጫንና የማራገፉን እንዲሁም የትራንዚት ሥራውን በመንግስት ቁጥጥር ሥር ከማድረጉም ባሻገር ፈቃዳቸው የተሰረዘባቸው የማሪታይም ድርጅቶችና የዕቃ አስተላላፊዎች በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውንም ሰነድ ለህጋዊው ተወካይ እንዲያስረክቡ ታዘዙ። ውሳኔው ነፃ ውድድርን ከማስቀረቱ ባሻገር ጅቡቲያውያንን ሥራ አጥ በማድረጉ እና የጅቡቲ መንግስት በግብር መልክ ያገኝ የነበረውን ገቢ በመቀነሱ ከጅቡቲ ወገን ተቃወሞ ቢያስነሳም እነዲጸና ሆነ።[169]

በአጠቃላይ በምድር ትራንስፖርትና በመገናኛ ዘርፍ በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረው አለመግባባት በወደቡና በጋላፊ መንገድ አጠቃቀም ላይ የበኩሉን ተጽዕኖ እያስከተለ እስከ መጋቢት 1973 ስምምነት ድረስ ዘለቀ። ከፕሬዚደንት ጉሌድ ጉብኝት አስቀድሞ በተደረጉ ድርድሮችና በተፈረሙ መግባባቶች የመንገድ ትራንስፖርትን በተመለከተ በሁለቱ አገሮች መካከል ግንኙነቱን ለማጠናከር እና የጋላፊን መንገድ በይበልጥ ለመጠቀም ከመግባባት ተደረሰ። ነገር ግን ስምምነቱን ተከትሎ በጅቡቲ በኩል ለቀረበው "የሚጓጓዘው ዕቃ በጅቡቲና በኢትዮጵያ በተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች መካከል እኩል ይከፋፈላል" የሚል ሃሳብ ኢትዮጵያ አሉታዊ ምላሽ በመስጠቷ ስምምነቱ እስከ ግንቦት 1973 ድረስ ሳይፈረም ቀረ።

የመጋቢት 1973 ስምምነትን ተከትሎ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል ያለውን የባህር ትራንፖርት ግንኙነት ለማጠናከር

169 ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 1፤ አር.ጋው ካብታሙ (ጅቡቲ) ለውጉሚ፡ መስከረም 23፣ 1972። ውጉሚ፡- ጅቡቲ 51-D3 3፤ አር.ጋው ካብታሙ ለውጉሚ፡ ጥቅምት 4፣ 1972





ከሁለቱ ወገን የተውጣጣ የቴክኒክ ኮሚቴ ባቀረበው ሃሳብ መሠረት ጥረት መደረጉ አልቀረም። አንደኛው ያለመግባባት ነጥብ የነበረው የወደብ ታሪፍን ይመለከታል። የጅቡቲ ወደብ ከኮንቴኔር ታሪፍ በስተቀር የቀሩት በግል ይካሄዱ ስለነበር በታሪፉ ላይ ቁጥጥር እንዳይኖር እና ግለሰቦች እንደ ገበያው ሁኔታ እንዲለዋውጡት አድርጎ ነበር። የታሪፍ ክፍያዎች በመጠንና በዓይነት በመለያየታቸውም እንደ ሱር ቻርጅ፣ ትርፍ ሰዓት፣ የበዓላት ክፍያ ወዘተ ዋናውን ታሪፍ ስላቃወሱ የቴክኒክ ኮሚቴው ወጥ ወደሆነ የአከፋፈል ሥርዓት ለመድረስ ሳይችል ቀረ።

በወደብ ዕቃ ማከማቸትንም በተመለከተ በጅቡቲ በኩል አስፈላጊው የዕቃ ማከማቻ ቦታ እንዲዘጋጅ ከስምምነት ቢደረስም የወደብ ኪራይን በተመለከተ የነፃ ጊዜ ለወጪና ገቢ ዕቃ 60 ቀን እንዲሆን በኢትዮጵያ በኩል የቀረበው ሃሳብ በጅቡቲ ጥያቄ በይደር ተላለፈ። የጅቡቲን ወደብ ቀዝቃዛ መጋዘን ለመጠቀም በጅቡቲ የቀረበው ሊሻሻል የማይችል የቀን አነስተኛ ክፍያ 200 /FD/m3 እንዲሁ ተጨማሪ ያለመስማማት ምንጭ ነበር።

በመጨረሻ የሁለቱ አገሮች የጋራ የሚኒስትሮች ጉባዔ መስከረም 1979 ተሰብስቦ ኢትዮጵያ የጅቡቲ ወደብን በሚገባ ለመጠቀም በምትችልበት ሁኔታ ላይ ዝርዝር ውይይት ተደረገ። በዚህም መሠረት በወደቡ ለመጠቀም እንዲቻል መሟላት ያለባቸው እንደ የባቡሩ የማጓጓዝ አቅም፣ የደህንነቱና አስተዳደሩ መጠናከር፣ የኮንቴነር፣ የማራገፊያ ዲፖና የኮንቴነር የመጫኛና የማራገፊያ መሳሪያዎች የመሳሰሉት ሁሉ በወቅቱና እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሟሉ ከስምምነት ተደረሰ። የአሰብና የጅቡቲን ወደቦች አሠራር ለማቀናጀትና ታሪፋቸውን ለማቀራረብ እንዲሁም በሁለቱ አገሮች መካከል ስለአለው የትራንስፖርት ሁኔታ፣ የኢትዮጵያን የገቢና ወጪ ንግድ ስለማስፋፋትና በጅቡቲ ወደብ በኩል ይበልጥ መጠቀም ስለሚቻልበት መንገድ ከስምምነት ደረሱ።

አገልግሎት ክፍያን የማከናወኑን ሥራ ጠቅልሎ ይዞ የነበረው የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት (MTS) የችግሮቹ ዋነኛ መንስኤ ነበር። የድርጅቱ ሁለገብ ሥልጣን (monopoly) በሥራ አፈጻጸሙ ላይ አፍራሽ በሆነ መልኩ በመንጸባረቁም በጅቡቲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንዲሁም ከጅቡቲ መንግስት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው።[172]

ኢትዮጵያ የገጠማት ትልቁ ችግር ግን የጅቡቲ መንግስት በሂደት በወደቡ አጠቃቀም ዙሪያ እያሳየ የመጣው የባለቤትነት ስሜት እና የነገሮችን አካሄድ በብቸኝነት የመወሰን ዝንባሌ ነው። ሁኔታው የኢትዮጵያን አማራጭ አልባነትና ጥገኝነት በግልጽ አሳየ። ጅቡቲ በድጋሚ የአገሪቱን መወረር ተከትላ የመክዳት ዝንባሌ አሳየች። በኢትዮ-ሶማሊያ ጦርነት ወቅት ከተከሰተው ችግር የአሁኑ ልዩነቱ ኢትዮጵያ ሙሉ ለሙሉ በጅቡቲ በጎ ፈቃድ ሥር መዋሏ ነበር። ከጦርነቱ መጀመር በፊት እስከ 1.7 ሚሊዮን ቶን ጭነት ያስተናግድ የነበረው የጅቡቲ ወደብ በድንገት 3.1 ሚሊዮን ቶን ጭነት እንዲያስተናግድ ተገደደ። ከዚህም ውስጥ አብዛኛው መዳረሻው ኢትዮጵያ የሆነ የጦር መሳሪያ እና ቁሳቁስ ይገኝበታል።[173]

በሐምሌ 1990 በጅቡቲ የትራንስፖርትና ቴሌኮሙኒኬሽን ሚኒስትር የተመራ ልዑክ በኢትዮጵያ የሥራ ጉብኝት ባደረገበት ወቅት በጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ አንድ የመግባቢያ ቃለ ጉባኤ ተፈርሞ ነበር። በቀጣይነትም አተገባበሩን የተመለከተ የአፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ እንዲወጣ ተደረገ። በወቅቱ በተደረገው ግምገማም ኢትዮጵያ በእጅጉ ትፈልጋቸው የነበሩ ከወደቡ መጨናነቅና መጣበብ ጋር የተገናኙ ችግሮችን የማስወገዱ ጥረት በጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት በጅቡቲ ችላ በመባላቸው አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኘ። የዚህ ችግር

[172] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ የጋራ ኮሚሽን ሀ 10፤ አምባሳደር ሣህለወርቅ (ጅቡቲ) ለሥዩም መስፍን፡ ሰኔ 2፣ 1990

[173] Bollee, 482.





መንስኤ የመርከብ ወኪሎች ለኮንቴነር ማቆያ የተመደበላቸውን ነፃ የ30 ቀን ጊዜ (grace period) በማሳለፍ፡ ቁጥራቸው የበዛ ኮንቴኔሮች ተከማችተው በወደቡ ውስጥ መቆየታቸውና ተደራርበው መጨናነቅ መፍጠራቸው ነበር። አንዱ ከመግባባት የተደረሰበት ነጥብ ኢትዮጵያ ያቀረበችው አስተማማኝ የኮንቴነር መለያ ዘዴ መዘርጋት ነበር።

በስተመጨረሻ ግን ጅቡቲያውያን የወደቡ ባለሥልጣናት ከኢትዮጵያ ግምት ውጭ የራሳቸውን መፍትሔ ይዘው ቀረቡ። ከነዚህም መካከል ኮንቴኔሮችን በወደቡ የማቆያ ነፃ ጊዜ ከ30 ቀን ወደ 15-20 መቀነስ እና ከቀነ ገደቡ በላይ የሚያቆዩ የኮንቴኔር ባለቤቶች (የመርከብ ድርጅቶች/ወኪሎች) የሚከፍሉትን የኪራይ ዋጋ ማናር ይገኙበታል። የዚህ እቅድ ተግባራዊ መሆን በአጭር ጊዜ በኢትዮጵያ አስመጪዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት በማሰብ በመንግስት በኩል ተቀባይነት አጣ።

ለኮንቴኔር ማራገፍና መጫን ሥራ ለወደቡ የሚከፈለው ክፍያ በሰዓት ሳይሆን በክብደት መጠን እንዲሆን ቀደም ሲል በተደረገ ስምምነት የተወሰነ እና ሕግ ሆኖ የጸደቀ ቢሆንም የቀደመው አሠራር እንዲቀጥል መደረጉ፤ የኢትዮጵያ ተሽከርካሪዎች ከወደቡ እስከ ድንበር ድረስ በጅቡቲ ሹፌሮች ብቻ እንዲነዱ በጅቡቲ ባለሥልጣናት መወሰኑ ወዘተ በጅቡቲ ወገን ከተፈጠሩ ተጨማሪ እንቅፋቶች መካከለ ዋነኞቹ ናቸው።[174]

ይባስ ብሎ የጅቡቲ ወደብ ቦርድ ጥር 20፣ 1991 ባካሄደው ስብሰባ በግል ድርጅቶች ላይ ከየካቲት መጨረሻ ጀምሮ ተፈጻሚ የሚሆን አዲስ ተመን አጸደቀ። የወደቡ ቦርድ ውሳኔ መመሪያውን በማያከብሩ ድርጅቶች ላይ እስከ ንግድ ፈቃድ መቀማት የሚደርስ እርምጃ ለመውሰድ መዛቱ አጠቃላይ ሁኔታውን አወሳሰበው። ብሎም የጅቡቲ መንግስት የወደቡን አስተዳደር ለማሻሻል በሚል የሥራ አመራሩን ለዱባይ ወደብ

[174] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ የጋራ ኮሚሽን ሀ 10፡ አምባሳደር ሣህለወርቅ ለካሳሁን አየለ (የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር እና የኢምፖርት/ኤክስፖርት አስተባባሪ ብሔራዊ ኮሚቴ ሰብሳቢ)፡ ጥር 13፣ 1991

[175] ዝኒ ከማሁ፤ አምባሳደር ሣህለወርቅ ለካሳሁን አየለ፡ የካቲት 17፣ 1991

በተመን ጭማሪው ድርድር ወቅት በሁለቱ መንግስታት መካከል የተከሰተው ውዝግብ እና መሽክክር፣ በኢትዮጵያ የግል መገናኛ ብዙሃን ከፍተኛ ሽፋን የተሰጠው የጅቡቲ የማን አለብኝነት አመለካከት ወዘተ በወቅቱ ኢትዮጵያ የነበረችበትን አጣብቂኝ በግልጽ ያመለክታል። ከታሪፍ ስምምነቱ ማግስት በወደቡ የጅቡቲ መንግስት ተወካይ በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነትን ተከትሎ በአፍሪካ ቀንድ መሠረታዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ የአቅም መሸጋሸግ መከሰቱን ጠቁመው ከዚህ በኋላ ትልቅና ትንሽ የሚባል አገር እንደማይኖርና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ መሆኑን አመለከቱ። መንግስት የወደቡን አስተዳደር ለዱባይ ወደብ በመስጠቱ የጅቡቲ ወደብ በቀጣናው ተወዳዳሪ መሆን እንደቻለ ኢትዮጵያም የሚያዋጣትን አይታ ወደ ሌላ ወደብ መሄድ እንደምትችል በአደባባይ እስከመናገር ደረሱ። ከኢትዮጵያ ወገንም የንግዱ ማህበረሰብ ለመንግስት በላከው ደብዳቤ የተደረገው ከፍተኛ የወደብ አገልግሎት ኪራይ ጭማሪ እና በወደብ አጠቃቀም ላይ የሚታዩ አንዳንድ የአሠራር ችግሮች አነጋጋሪ መሆናቸውን ጠቅሶ በጉዳዩ ላይ የራሱን ጥናት ማድረግ ስለጀመረ በመንግስት በኩል ትብብር እንዲደረግለት እስከመጠየቅ ደረሰ።[178]

ጅቡቲያውያን አዲሱን የወደብ ተመን ማሻሻያ ተከትሎ የተሰማቸው ደስታና አገር አቀፍ ፈንጠዝያ ሳይበርድ ኢትዮጵያ አስደንጋጭ የአጸፋ እርምጃ ወሰደች። በሰኔ 1993 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ door to door ወይንም through bill of landing የሚል መመሪያ አስተላለፈ። ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን ለጅቡቲ አቻው ባስተላለፈው ደብዳቤ እንደተመለከተው በኮንቴኔር ለሚመጣ ካርጎና ለተሽከርካሪዎች ከዚህ በፊት ይሠራበት የነበረው የትራንዚት ድክላራሲዮን እንዲቀር መደረጉንና ወደ አገር ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ሰነድ የእቃው ዝርዝር መግለጫ (freight/cargo manifest)

[178] ዝኒ ከማሁ፤ አምባሳደር ማህለወርቅ (ጅቡቲ) ለውጉሚ፡ የካቲት 13፣ 1993፤ ሁሴን ሺበሺ (የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ) ለውጉሚ፡ መጋቢት 14፣ 1993





ብቻ መሆኑን ይገልጻል። ባለንብረቶች ለሚያንጉዙት ዕቃም ተቀማጭ ገንዘብ እንዲያስይዙ ይገደዳሉ። የመመሪያው ዋነኛ ዓላማ በጅቡቲ ወደብ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለሚገቡ እቃዎች የማስተላለፉን ሥራ በባህር ትራንዚት ድርጅት ሙሉ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ እና ተመሳሳይ የውጭ ድርጅቶችን (አብዛኛው የጅቡቲያውያን) ከፉክክር ውጭ ማድረግ ነበር።

እርምጃው በጅቡቲ በኩል ከፍተኛ ሽብር ከመፍጠሩም በላይ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ በግልጽ እስከማሳወቅ ደረሱ። በተለይ የሁለቱ አገሮች መሪዎች በናይሮቢ ኬንያ በተገናኙ ጊዜ (ግንቦት 1993) ከወደብ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ የተከሰተው ውጥረት መፍትሔ እስኪበጅለት ሁኔታው በነበረበት ይቀጥል (status quo) የሚለው መግባባት በኢትዮጵያ በኩል መጣሱ እንዳሳዘናቸው የጅቡቲው ፕሬዚደንት ገለጹ። ሊወስዱ ካቀዷቸው የማሻሻያ እርምጃዎች መካከልም በኮንቴኔር ለሚመጣ ዕቃ ዝርዝር መግለጫ (declaration) ስለሌለው የጅቡቲን ግዛት ሲሻገር አገር ውስጥ ቢቀር አሊያም ስለ ዕቃው ዓይነት ዋስትና ስለሌለ ኮንቴኔሩን ሊከፍቱና በፈለጉት ሊቀይሩ እንደሚችሉ፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የመድን ዋስትና ቦንድ እንደሚጠይቁ፤ በነሱ ጥያቄ መሠረት ቀደም ሲል የቀረውን እስከ ድንበር ድረስ የጉምሩክ ተቆጣጣሪዎቻቸው ዕቃዎቹን አጅበው እንዲሄዱ እንደሚደረግ ወዘተ ይገኙባቸዋል። ሌላው እርምጃ ቀደሞ በተሽከርካሪ ዋስትና ዙሪያ ከተደረሰው መግባባት በተጻራሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በቶን 15,000 የጅቡቲ ፍራንክ ያስከፍል የነበረውን ታሪፍ በፈቃዳቸው በቶን 80,000 የጅቡቲ ፍራንክ አደረጉት።[179] ጠቅላላ ሁኔታውም ከቁጥጥር ውጭ የመውጣት አዝማሚያ እያሳየ መጣ።

የጅቡቲ አጸፋ የኢትዮጵያን የባህር ትራንዚት ድርጅት MTS ለመጉዳት ያቀደና በሂደቱም በወደቡ

[179] ዝኒ ከማሁ፤ አምባሳደር ማህለወርቅ ለዶ/ር ተቀዳ አለሙ (ውጉሚ ምክትል ሚኒስትር)፡ ሰኔ 12፣ 1993

አጠቃቀም የኢትዮጵያን ጥገኝነት ለማጉላት ያለመ ነበር። እ.ኤ.አ. ሐምሌ 15፣ 2001 (ሐምሌ 1993) ፕሬዚደንት ጉሌድ ለዚህ የሚያመች እና በ60 ቀን ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ አራት ደንቦችን በፊርማቸው አጽድቀው ሚኒስትሮቻቸው በሙሉ አረፍት እንዲወጡ አደረጉ። በናይሮቢው ንግግር ወቅት (ግንቦት 1993) ከኢትዮጵያው መሪ ጋር በተደረሰው መግባባት የወደብ አጠቃቀም ችግሩን ለማጥናትና መፍትሄ ለመፈለግ የተቋቋመው የጋራ የቴክኒክ ኮሚቴ በሐምሌ ሊሰበሰብ ቢታቀድም በጅቡቲ በኩል እንደማይመች ተገልጾ ለመስከረም መጀመሪያ እንዲሆን ተጠየቀ። ይህም የተሰጠው ቀነ ገደብ ካለቀ በኋላ እንዲሆን የታሰበበት መሆኑን ያመላክታል።

የኢትዮጵያ የባህር ትራንዚት ድርጅት በ1960 የተቋቋመ ሲሆን መዋቅሩም በተከታታይ መንግስታት በተለያየ ጊዜ ማሻሻያ ተደርጎበታል። በጅቡቲ አንድ ቅርንጫፍ ያለው ሲሆን ከፈረንሳይ ቅኝ ጀምሮ ከመርከብ የመጫንና የማውረድ (stevedoring)፣ የመርከብ ውክልና እና የትራንዚት ሥራን ሲያከናውን ቆይቷል። በሐምሌ 1993 የጅቡቲ መንግስት ካወጣቸው ደንቦች አንደኛው MTSን ከመጫንና ማውረድ ተግባሩ የሚያወጣው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ የትራንዚት እና የመርከብ ድርጅት ውክልናን ለማካሄድ የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት እንደሚጠበቅበት ያሳያሉ። አንደኛው አማራጭ ቅድመ ሁኔታ MTS ቅርንጫፍ መሆኑ ቀርቶ በጅቡቲ የተመዘገበ ድርጅት እንዲሆን ማድረግ ሲሆን ይህ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ሊከናወን እንደማይችል ይታወቃል። አለበለዚያም ዋና መ/ቤቱ ጅቡቲ ባይሆንም ተመሳሳይ የሆነ የጅቡቲ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ሊንቀሳቀስ ከቻለ (reciprocity) ብቻ MTS ሥራውን ሊቀጥል ይችላል።

የጅቡቲ ወደብ አስተዳዳሪዎች የደንቦቹን መውጣት ተከትሎ ከኢትዮጵያ ነጋዴዎች ጋር የተናጠል ውይይት በማድረግ ውሳኔው የመንግስት ተቋምን እንጂ ግለሰቦችን እንደማይጎዳ ለማስረዳት ጥረት ማድረጋቸው የአካሄዳቸውን አደገኛነት





የሚያመላክት ተደርጎ በኢትዮጵያ በኩል ታመነ። የወደቡ ባለስልጣናት በተለይ ግለሰብ ነጋዴዎች ከጅቡቲ አቻዎቻቸው ጋር በመቀናጀት በትራንዚት፣ መጫንና ማውረድ እንዲሁም በመርከብ ውክልና ዘርፍ እንዲሰማሩ ማበረታታታቸው መንግስትን ከንግዱ ማህበረሰብ መነጠልን ያለመ እንቅስቃሴ ተደርጎ ተወሰደ። የጅቡቲ መንግስት ካወጣቸው ደንቦች በተጨማሪም በወደቡ አከባቢ የሚገኘውንና በአብዛኛው ኢትዮጵያ የምትገለገልበትን ደረቅ ወደብ (dry port) ለደቡብ አፍሪካ ድርጅት በኮንትራት ሰጡ።[180]

አጠቃለይ ደንቦቹና ውሳኔዎቹ በተለይ የባለሥልጣናቱን እና የጅቡቲ ወደብ አስተዳዳሪ የሆነውን የዱባይ ወደብ ባለሀብቶች የጥቅም ትስስር ይፋ በማውጣቱና ብዙሃኑን የጅቡቲ ወገን በማግለሉ በጅቡቲ ከፍተኛ ውዝግብ ማስከተላቸው ለኢትዮጵያ መተንፈሻ ጊዜ ፈጠረ። ኢትዮጵያን ለመጉዳት ታስቦ የወጣው ደንብ በጅቡቲ ውስጥ ሌላ ገጽታ በመያዙ ተግባራዊነቱ ለሁለት ወራት እንዲራዘም ተደረገ።

የደንቦቹ ተግባራዊ መሆኛ ቀነ ገደብ የሚጠናቀቀው እ.ኤ.አ. ጥቅምት 25፣ 2001 (ጥቅምት 1994) ቢሆንም በጅቡቲ በኩል ኢትዮጵያን በተመለከተ የጋራ የቴክኒክ ኮሚሽኑ በጉዳዩ ላይ ተመካክሮ ከአንድ ውሳኔ እስኪደርስ በቀደመው አሰራር ለመቀጠል መስማማታቸው ተጨማሪ የእፎይታ ጊዜ ፈጠረ። ነገር ግን የቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ እስከ ጥር መጨረሻ 1994 ድረስ አልተካሄደም። በ1994 በኢትዮጵያ የመንግስት አወቃቀር ለውጥ በመደረጉ ምክንያት ቀድሞ የባህር ዘርፍ ጉዳዮችን ይከታተል የነበረው የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር መሆኑ ቀርቶ ኃላፊነቱ በአዲስ መልክ ለተቋቋመው ለመሠረተ ልማት ሚኒስቴር መተላለፉ የተወሰነ የአሰራር መንተት ማስከተሉ አልቀረም። የጅቡቲን ጉዳይ በተለይም ከወደቡ ጋር በተያያዘ የነበሩ ጉዳዮችን በኃላፊነት የሚከታተል አካል አልነበረም።

---

180 ዝኒ ከማሁ፤ አምባሳደር ማህለወርቅ ለአምባሳደር ቆንጂት ሥነ ጊዮርጊስ (ውጉሚ አፍሪካ መምሪያ ኃላፊ)፡ ሐምሌ 17 እና 24፣ 1993፤ አምባሳደር ማህለወርቅ ለሥዩም መስፍን፡ ነሐሴ 14፣ 1993

የወደቡን ሁኔታ እና የጋራ የቴክኒክ ኮሚቴ ስብሰባ በተመለከተ በኢትዮጵያ በኩል በሚመለከታቸው የመንግስት መሥሪያ ቤቶች መካከል የዝግጅት ውይይት ሲካሄድ የቆየው በየካቲት መጨረሻ (የካቲት 28 እና 29) መሆኑ የጉዳዩን ባለቤት አልባነት በግልጽ ያመላክታል፡፡ በመጨረሻም በመሠረተ ልማት ሚኒስቴርና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተደረጉ ተከታታይ የምክክር ስብሰባዎች በወደቡ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የንግድና ኢኮኖሚ ዘርፎች ከጅቡቲ ጋር ማሰሪያ የሚሆን ስምምነት ለማድረግ ጥረት እንዲደረግ ተወሰነ፡፡ የወደቡን ጉዳይ በተመለከተም በጅቡቲ በኩል ያለውን እሳቤ (expectation) መሠረት በማድረግ የስምምነት ረቂቅ የማዘጋጀቱ ኃላፊነት ለውጭ ጉዳይ እና ለመሠረተ ልማት ሚኒስቴሮች ተሰጠ፡፡

የመሠረተ ልማት ሚኒስቴርም የጅቡቲ ወደብን ጉዳይ የሚከታተል ክፍል ያቋቋመውና እስከዚያ ድረስ የተከናወኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ የጀመረው ጥቅምት 1994 ነበር፡፡ መንግስት በጋራ የምክክር ስብሰባው ወቅት የሚቀርብ የስምምነት ረቂቅ ለማዘጋጀት እየጣረ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት በጅቡቲ ወደብ ውስጥ የሚያከናውነውን የመጫንና የማውረድ ሥራ እ.ኤ.አ. ከጥር 5፣ 2002 (ታህሳሥ 1994) ጀምሮ እንዲያቆም በወደቡ አስተዳደሪዎች ታዘዘ፡፡ በመካከሉም ጅቡቲ የራሷን የስምምነት ረቂቅ በመደራደሪያነት አቀረበች፡፡

የጅቡቲው ሰነድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ለአፍሪካ አገሮች እንደ ናሙና እንዲያገለግል ካዘጋጀው የወደብ አጠቃቀም ንድፈ ሐሳብ በቀጥታ የተቀዳ ሲሆን በተለይ ዓለም አቀፍ የባህር ትራንዚት ውሎችን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ የረቂቅ ውሉ አሉታዊ ገጽታ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል የቆየውን የጉርብትና፣ የባህልና የታሪክ ትስስር እንዲሁም የኢኮኖሚ ቁርኝት ከግምት ያላስደባ መሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ከድምዳሜ ተደረሰ፡፡ የጅቡቲ መንግስት የጋራ የመማክርት ኮሚቴው ይህን ሰነድ እንደ መነሻ የሚቀበል ከሆነ በMTS ላይ የተጣለውን እገዳ





እስከ የካቲት መጀመሪያ እንደሚያራዝም አስታወቀ፡፡ ስብሰባውም እስከ አዲሱ ቀነ ገደብ ማብቂያ መከናወንና ሁለቱም ወገኖች ከስምምነት መድረስ ግዴታቸው እንደሆነ የጅቡቲ መንግስት ባወጣው መግለጫ አሳሰበ፡፡ ኢትዮጵያ ያቀረበችውን ባለ ሦስት አማራጭ ረቂቅ ስምምነት ለውይይቱ መነሻ እንዲሆን እንኳ አልፈለገም፡፡[181]

የኢትዮጵያ ረቂቅ የሚከተሉትን አማራጮች ያካትታል፡- አንደኛው አማራጭ ሁለቱም አገሮች ወደቡን በጋራ እንዲጠቀሙና የጅቡቲ መንግስት ድርሻ 51% የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ 49% እንዲሆን፤ ሁለቱም ወገኖች ወደቡን ለጋራ ልማት እና ለረጅም ጊዜ የጋራ ጥቅም እንዲገለገሉበት፤ ወደቡን በጋራ ለመጠቀም እንዲቻል የወደቡ አጠቃላይ መገልገያ ዕቃዎች ዋጋ ሁለቱ አገሮች በሚመርጡት የተለየ አካል እንዲገመት፤ የወደቡ መገልገያ ዕቃዎች ዋጋ በሁለቱ አገሮች ከሚቋቋመው የጋራ አክሲዮን ማህበር ካፒታል 51% ድርሻ እንዲኖረው፤ እና ኢትዮጵያ የጋራ አክሲዮን ድርሻዋን ስምምነቱ ተግባራዊ ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ በ18 ወራት ከፍላ እንደምታጠናቅቅ ይዘረዝራል፡፡

አማራጭ ሁለት የጅቡቲ መንግስት በወደቡ ውስጥ የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን የሚያቀላጥፍ ነፃ ቀጠና (Free Zone) እንደሚሰጥ፤ ቀጠናውም ከማናቸውም የጉምሩክ ታሪፍና ሌሎች ቀረጦች ነፃ እንደሚሆን፤ የኢትዮጵያ መንግስት በዚህ ሥፍራ ላይ የሚሰሩ ሠራተኞችን ራሱ እንደሚቀጥር፣

[181] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 2፤ አህመድ ያሲን (የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ) ለውጉሚ፡ ጥቅምት 2፣ 1994፤ አምባሳደር ሣህለወርቅ ለውጉሚ፡ ጥቅምት 11 እና 22፣ 1994፣ ህዳር 4፣ 1994፤ አምባሳደር ሣህለወርቅ ለዶ/ር ተቀዳ አለሙ፡ ህዳር 12፣ 1994፤ ጅቡቲ ኤምባሲ ለውጉሚ፡ ጥር 2፣ 1994፤ ብርሃኑ ግዛው (ጅቡቲ ኤምባሲ ተጠባባቂ ጉዳይ ፈፃሚ) ለውጉሚ፡ ጥር 13 እና 21፣ 1994፤ ጅቡቲ ኤምባሲ ለውጉሚ፡ የካቲት 2 እና 5፣ 1994

ሥራውን እንደሚቆጣጠርና እንደሚመራ፤ ለቀጠናው የሚረዱ የመሠረተ ልማት አውታሮችን (የውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ የመገናኛ መሣሪያዎች ወዘተ) በማቅረቡ ረገድ የጅቡቲ መንግስት እንደሚተባበር ያትታል።

ሦስተኛው አማራጭ የወጪና ገቢ ዕቃዎች እንቅስቃሴን በጅቡቲ ወደብ በኩል ለማካሄድ የጅቡቲ መንግስት ለኢትዮጵያ ዋስትና እንደሚሰጥ፤ በወደቡ የሚያልፉ የኢትዮጵያ ወጪና ገቢ ዕቃዎች ከማንኛውም የጉምሩክ ታሪፍና ቀረጥ ነፃ እንደሚሆኑ፤ በወደቡ ያሉትን መሣሪያዎችና የጅቡቲን ነፃ ቀጠና ኢትዮጵያ እንድትጠቀም የጅቡቲ መንግስት ዋስትና እንደሚሰጥ፤ የጅቡቲ መንግስት የኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ዕቃዎች በወደቡ ላይ በቅድሚያ እንዲስተናገዱ እንደሚያደርግ፤ የኢትዮጵያ ዕቃዎች በጅቡቲ ወደብ ለ180 ቀናት ሳይጫኑ ሊቆዩ እንደሚችሉና ከነዚህ ቀናት ውስጥ 60 ቀናት ከክፍያ ነፃ እንደሚሆኑ፤ የጅቡቲ መንግስት በወደቡ አሠራር ላይ ለውጥ ለማድረግ ሲፈልግ የኢትዮጵያን መንግስት እንደሚያማክር፣ በመጨረሻም ለውጡን ከማድረጉ ከ90 ቀናት በፊት ለኢትዮጵያ መንግስት እንደሚያሳውቅ ወዘተ ያትታል። አማራጮቹን በማዘጋጀቱ ሂደት በኢትዮጵያ በኩል የነበረው ግንዛቤ የመጀመሪያ ሁለቱን የጅቡቲ መንግስት ይቀበላል ተብሎ እንደማይጠበቅ ነገር ግን ለሦስተኛው እንደ መደራደሪያ ሊያገለግል እንደሚችል ያመለክታል።

ለረጅም ጊዜ ሲተላለፍ የቆየው የሁለቱ አገራት የጋራ የሚኒስትሮች የምክክር ስብሰባ ከጥር 30 እስከ የካቲት 2፣ 1994 በአዲስ አበባ ተደረገ። ውይይቱና ድርድሩ በሦስት ኮሚቴዎች ተከፍሎ የተከናወነ ሲሆን የወደቡ ጉዳይ በሁለቱ ወገን የልዑካን መሪዎች የተመራው የመጀመሪያው ኮሚቴ የሥራ ድርሻ ነበር። በሁለተኛው ኮሚቴ የታዩት ጉዳዮች በአብዛኛው በከፍተኛ ባለሥልጣናት ደረጃ ከተያዘው የወደብ ጉዳይ ጋር የተያያዘና የወደቡ ችግር እልባት ሲያገኝ የሚፈቱ ሆነው ስለታዩ ብዙም ትኩረት አልተሰጣቸውም።

ወደብን በተመለከተ በተደረገው ድርድር ጅቡቲ የኢትዮጵያን የመጀመሪያዎቹን ሁለት አማራጮች ውድቅ ያደረገች ቢሆንም





በሦስተኛው አማራጭ ላይ የቀረቡትን ነጥቦች ከጅቡቲው ረቂቅ ሰነድ ጋር በማስታረቅ ለመነጋገር ፍላጎት አሳየች። የጅቡቲ ወገን ያቀረበው ረቂቅ ስምምነት በንግድ ኮሪደሩ በትራንዚት ላይ በሚከናወን የጭነት አገልግሎት አጠቃቀም ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን የኢትዮጵያው ሦስተኛ አማራጭ ደግሞ ወደቡን ባለበት ሁኔታ በተሻለ መልኩ በጊዜያዊነት መጠቀም በሚያስችልየበወደብ አጠቃቀም (Modus Vivends) ላይ ብቻ ያተኩራል። የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎችም ይህንኑ የሚያስታርቅና ሁለቱንም ያዋሃደ ሰነድ የሚያዘጋጅ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲሰየም በመስማማታቸው ጉዳዩ በይደር ተላለፈ።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የተደራዳሪዎች ቡድን ካቀረባቸው የመጀመሪያዎቹ ሁለት አማራጮች መካከል በአንዱ መሠረት የወደብ አጠቃቀሙ ጉዳይ የሚፈታ ከሆነ የሁለቱንም አገሮች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያሸጋግር ተከራክሮ ነበር። እንዲሁም በሁለቱ አገሮች ምርቶች ላይ የሚጣለውን ታሪፍ ሙሉ በሙሉ የሚያነሳ ልዩ የንግድ ስምምነት (Preferential Trade Agreement) እና የሁለቱን አገር ዜጎች አንዱ በሌላኛው ውስጥ እንደ ባለሀብት ተቆጥሮ የሃገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚሰጣቸውን መብት ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢንቨስትመንት ስምምነት ሰነድ ለጅቡቲ ወገን አቅርቦ ነበር። ይሁንና ስለወደብ አጠቃቀም የቀረቡት የመጀመሪያዎቹ ሁለት አማራጮች ተቀባይነት ባለማግኘታቸው በሰነዶቹ ላይ ንግግር ሳይደረግ ቀረ። የጋራ ኮሚቴው ቀጣይ ስብሰባ በሚያዝያ 1994 በጅቡቲ እንዲደረግ ቀን ቀጠሮ ተያዘለት።[182]

ከአዲስ አበባው ድርድር በኋላ በኢትዮጵያ በኩል ለሚቀጥለው ስብሰባ ዝግጅት ተጀመረ። ወደቡን በተመለከተ የጅቡቲው ሰነድ በሁለቱ አገሮች መካከለ ያለውን ልዩ ሁኔታ ባያንጸባርቅም ከወደቡ አጠቃቀም በተጨማሪ ከወደቡ እስከ ኢትዮጵያ ድንበር ድረስና ዕቃው እስከሚደርስበት የመጨረሻ

[182] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 2፤ የኢትዮ-ጅቡቲ ከፍተኛ የጋራ ስብሰባ ሪፖርት፡ የካቲት 1994

ቦታ ያለውን የትራንስፖርትና የትራንዚት አሠራር (corridor) ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ የአማራጩን ጠንካራ ጎን እንደሚያሳይ ግንዛቤ ታወሰደ። የጅቡቲው ሰነድ ኢትዮጵያ ካቀረበችው ሦስተኛው አማራጭ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በዝርዝር ተመልክቶ አስታራቂ የሚሆን አማራጭ ስምምነት እንዲዘጋጅ ተወሰነ።

በተጨማሪም የባህርና ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት በአዲሱ የጅቡቲ ሕግ መሠረት ከመርከብ ዕቃ የመጫንና ማራገፍ ሥራው በመታገዱ ይህ እገዳ እንዲነሳለት በቀጣይ ድርድሮች ጥረት እንዲደረግ፤ በጅቡቲ ወደብ የሚስተናገደው የኢትዮጵያ ዕቃ ስለጨመረ ለዶክመንቴሽንና ለስታትስቲክ ሥራዎች ማከናወኛ ተጨማሪ ክፍያ ስለመጠየቅ በጅቡቲ በኩል በአዲስ አበባው ድርድር ወቅት የተነሳው ሃሳብ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽና በጥቃቅን ምክንያት የአገልግሎት ክፍያ ለመጨመር መሞከር የወደቡን ዋጋ በማናር በአጠቃላይ የወደቡን አዋጭነት ጥያቄ ውስጥ እንደሚያስገባው ተገልጾ ተጨማሪ ክፍያው ተግባራዊ እንዳይሆን ጥረት እንዲደረግ፤ ለ21 ዓመት ያህል በአብዛኛው በኪሣራ በጅቡቲ ውስጥ አገልግሎት ሲሰጥ የነበረውን የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በአዲስ መልክ ለማቋቋም በጅቡቲ በኩል የወጣው ሕግ [በጅቡቲ የኢንሹራንስ ሥራ ለመስራት የሚቻለው ከጅቡቲያውያን ኩባንያ ጋር የ50% የሽርክና ባለቤትነት በመያዝ ወይም የውጭ ኩባንያ ከሆነ የ100 ሚሊዮን የጅቡቲ ፍራንክ ወይንም 4.8 ሚሊዮን ብር ያህል ብር በጅቡቲ ብሔራዊ ባንክ በመያዣነት ማስቀመጥ] ተከትሎ ድርጅቱን በአዲሱ ሕግ መሠረት በሽርክና እንዲቋቋም፤ እና የጅቡቲ ወገን በሁለቱም አማራጮች የተመሠረተ የመድን ድርጅት ከሚሰበሰበው አረቦን ገቢ ላይ በየዓመቱ 20% ላልተከፈለ የጉዳት ካሣ መጠባበቂያ በባንክ ዋስትና እነዲያስይዝ የሚለው ነጥብ እንዲቀር ጥረት እንዲደረግ ሐሳብ ቀረበ።[183]

ቀጣዩ የጋራ የሚኒስትሮች ስብሰባ ከመጋቢት 30 እስከ ሚያዝያ 4፣ 1994 በጅቡቲ ተደረገ። የኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን

[183] ዝኒ ከማሁ





በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ በአቶ ግርማ ብሩ የተመራ ሲሆን ከእልህ አስጨራሽ ድርድር በኂላ በሁለቱ አገሮች መካከል 41 አንቀጾች ያሉት የወደብና የትራንስፖርት አገልግሎት ስምምነት እና ሌሎች የኢኮኖሚና የንግድ ጉዳዮችን የያዘ የስምምነት ቃለ ጉባኤ ተፈረመ።[184]

በድርድሩ መጀመሪያ የወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ በአዲስ አበባው ስብሰባ በተደረሰው መግባባት መሠረት የሁለቱን አገሮች አማረጮች ያገናዘበ ረቂቅ ሰነድ በኢትዮጵያ በኩል ተዘጋጅቶ ቀርቦ ነበር። ሰነዱ የወደብ አጠቃቀምንና የትራንዚት አገልግሎትን የሚያካትት Modus Vivendi on the Utilization of the Port of Djibouti and Services to Cargo in Transit በሚል ርዕስ የተጠናቀረ ነበር።

በድርድሩ ወቅት አወዛጋቢ ከነበሩ ነጥቦች መካከል አንዱ ኢትዮጵያ መሠረታዊ ጥቅሞቿን ለማስከበር ያነሳቻቸው አንቀጾች ናቸው። በመጨረሻ በተፈረመው ስምምነት አንቀጽ 2 እንደተብራራው የጅቡቲ ሪፐብሊክ ለኢትዮጵያ ቋሚ የሆነ የባህር በር መብት (access to the sea) እንዲሁም ከኢትዮጵያ የሚመነጩ እና ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ዕቃዎች በጅቡቲ ግዛት ውስጥ መተላለፍ እንዲችሉ ከጣልቃ ገብነት የፀዳ የመተላለፍ ነፃነት (unhindered freedom of transit) ለመስጠት ዋስትና ሰጠ። ከዚህም በተጨማሪ ከኢትዮጵያ የሚመነጩ እና ወደ ኢትዮጵያ የሚጓጓዙ ዕቃዎች ከግብር እና ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው በጅቡቲ ወደብ በኩል እንዲተላለፉ እና ለነዚህም ዕቃዎች የጅቡቲ ወደብ ቅድሚያ መስጠት ያለበት መሆኑ በመርህ ደረጃ እንዲቀመጥ ተደረገ። በጅቡቲ ወደብ ውስጥ ያለውን የነፃ ቀጠና አገልግሎት (Free Zone Facility) ጨምሮ በወደቡ ውስጥ

[184] ውጉሚ፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ወደብ አጠቃቀም 1 2፤ የወደብ አጠቃቀም እና የትራንዚት አገልግሎት ስምምነትን በተመለከተ ጋሻው ደበበ (ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የውጭ ንግድ መምሪያ ኃላፊ) እና ግርማ ብሩ (የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር) ለውጉሚ፡ ሚያዝያ 8 እና 30፣ 1994፣ ሰኔ 3፣ 1994

በጅቡቲ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያና የፈረንሳይ ግንኙነት ልዩ ገፅታ ነበረው። በመጋቢት 1889ኙ ውል አፄ ምንሊክ በወደቡ፣ በባቡር መሥመሩና በአሳል ሐይቅ የኢትዮጵያን የልዩ ተጠቃሚነት መብት ሲያስጠብቁ ፈረንሳይ በበኩልዋ ግዛቱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፋ ላለመስጠት ግዴታ ገባች። የፈረንሳይ መሠረታዊ ፍላጎት ከጅቡቲ ባሻገር ያለውን የኢትዮጵያን ሐብት መቆጣጠር እንደነበር ግልጽ ነው። እንደ ባለያኖቹ ሁሉ በቀይ ባህር ረባዳ በረሃዎች ተወስኖ መቅረቱ ፋይዳው አነስተኛ ነበር። ከጣሊያን ተጋሬ እርምጃ በተቃራኒው ግን የኢትዮጵያን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በእጅ አዙር ጥቅማቸውን ማራመድ የፈረንሳይ መንግስታት ተመራጭ አካሄድ ሆነ። የወዳጅነት እና የትብብር ስምምነቶችን በመፈራረም በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የልዩ ተጠቃሚነት መብት ለማግኘት ያደረጓቸው ተከታታይ ጥረቶች ለዚህ ዋነኛ አመላካች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ለረጅም ጊዜ የዘለቀው የምንሊክና የፈረንሳይ ወዳጅነት ብሎም የጅቡቲ በኢትዮጵያ ምርቶች ላይ ጥገኛ መሆን ለዚህ ጉልህ ድርሻ አበርክቷል።

እስከ አሳል ሐይቅ ብቻ ይደርስ የነበረው የፈረንሳይ ሱማሌ ቅኝ ግዛት አሁን ያለበት የድንበር ዳርቻ ለመድረስ ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። አማራጭ ያልነበረውን የኢትዮጵያን ጥገኝነት (በተለይ የጦር መሣሪያ ለማግኘት) በመንተራስ ምንሊክን ማሳመኑ ከባድ አልነበረም። ጅቡቲን በተመለከተ ለአስቸኳይ ስትራቴጂካዊ ጥቅም ሲባል ዘላቂ መብትን አሳልፎ የመስጠቱ አባዜ ከዚህ ይጀምራል። በሂደት እንደታየውም አሁን ለተደረሰበት አጠቃላይ ጥገኝነት ዋነኛው ምክንያቱ ተከታታይ መንግስታት በሁኔታዎች አስገዳጅነት አሳልፈው በሰጡአቸው መብቶች ሳቢያ ነው።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግስትም ቢሆን ጅቡቲን በተመለከተ ያደረጋቸው ድርድሮች ከተጽዕኖዎች የፀዱ አልነበሩም። የፈረንሳይን ወዳጅነት እና በጎ ፈቃድ ማግኘቱ የኢትዮጵያን ጥቅሞች ለማረጋገጥ ወሳኝ ነበር። ይህ በተለይ ከነፃነት በኋላ





ኦጋዴንንና ኤርትራን ለማስመለስ በተደረገው ትግል ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። አፋምቦን ለማስመለስ ከተደረገው ርብርብ ባሻገርም ሌሎቹ ነጥቦች በለዘብታ ለመያዛቸው ዋነኛው ምክንያት ይህ ፈረንሳይን ወዳጅ አድርጎ የማቆየቱ ፍላጎት ነበር። የኤርትራና ጅቡቲ ድንበርን በመካለሉ ሂደት የታየው ቸልተኝነት የዚህ አሳቤ አንዱ ነጸብራቅ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። አጠቃላይ ውጤቱም በጥቂት ኪሎ ሜትሮች ይቆጠር የነበረው የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ለታለመለት ዓላማ በቂ የሆነ የግዛት ክልል ማግኘቱ ነው። ኢትዮጵያም ዋነኛ የመደራደሪያ አቅሟን (ፈረንሳይን በጠባብ ግዛት አፍኖ ማስቀረት) አሳልፋ ሰጠች። ጅቡቲ ድንበር እና ህጋዊ ሰውነት አበጀ።

የፈረንሳይን ይሁንታ ለማግኘት ሲባል የተጀመረው የኢትዮጵያ መንግስታት ጥቅምን አሳልፎ የመስጠት በጎ ፈቃደኝነት እስከ 1966ቱ አብዮት ዘልቋል። የቅኝ ግዛት ዘመን አብቅቶ ፈረንሳይ ጅቡቲን ስትለቅ ግዛቱ ለኢትዮጵያ ይመለሳል የሚለው እምነት በመሪዎቹ ዘንድ ተአማኒነት ማግኘቱ በጉልህ ተንጸባርቋል። በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካው እየተጠናከረና የግዛቱ ፖለቲካ ከሚፈለገው መሥመር እየወጣ በመጣበት ወቅት እንኳን ፈረንሳይን ያለማስቀየሙ አሳቤ ጎልቶ ይታይ ነበር። የፖለቲካ መሪዎቹ ወደ ሶማሊያ ያዘነበለ ፖሊሲ ማራመዳቸው ግልጽ እየሆነ በመጣበት፣ የሶማሊያ ሪፐብሊክ የተስፋፊነት እርምጃ አመርቂ ውጤት እያመጣ እንደሆነ በተጨባጭ እየተስተዋለ፣ ኢትዮጵያ የምታራምደው የግዛት ይገባኛል አቋም በአህጉሩና በተቀረው የዓለም ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነቱ እየቀዘቀዘ መሆኑ እየታወቀ፣ ፈረንሳዮች ከቃላቸው ይልቅ ጥቅማቸውን ለዘለቄታው ለማስጠበቅ የተለያየ አማራጭ መጠቀማቸው በግልጽ እየተስተዋለ ወዘተ የቅኝ ገዢውን አመኔታ እና ይሁንታ መሻቱ የኢትዮጵያ መተማመኛ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል።

የጅቡቲ መጻኢ እድል ከኢትዮጵያ ፍላጎት እያፈነገጠ የመምጣቱ እውነታ አገሪቱ ለረጅም ጊዜ ያራመደችውን ፈረንሳይን ያለማስቀየም ፖሊሲ ሊለውጠው አልቻለም። ምንም

ስለነበርና የጅቡቲ መሪዎችም የመደራደር አቅማቸውን ልክ ተረድተውት ስለነበር የተፈለገው ውጤት እስኪገኝ ላቅ ያለ ትግልን መጠየቁ አልቀረም። ጅቡቲ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ በጎ ፍቃድ መነጠሉ ግልጽ ሆነ፤ ይልቁንም የግዛቱ መሪዎች የራሳቸውን ፍላጎት በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ተነሳሽነቱም ሆነ አቅሙ እንዳላቸው አሳዩ።

ኢትዮጵያ በጅቡቲ ላይ የነበራትን ተሰሚነት ለመመለስ ብሎም የግዛቱ መሪዎች ዘለቄታዊ ጥቅማቸው ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረ መሆኑን ለማስረዳት ዘርፈ ብዙ ትግል ጠይቋል። ከሶማሊያ ጋር የተደረገው ጦርነት እና የኢትዮጵያ አሸናፊነት በተለይ የጉሌድ መንግሥት የመረጠው የወገንተኝነት መንገድ የተሳሳተ እንደነበረ ጉልህ አመላካች ሆኗል። በጦርነቱ ማግስትም ኮሎኔል መንግስቱ ሶማሊያ ጅቡቲን ለማጥቃት ከሞከረ ጦራቸውን ለዳግም ውጊያ እንደሚያሰልፉ በይፋ መግለፃቸው ዋነኛ መልዕክቱ ለጅቡቲ እንደነበር መገመት ይቻላል። የአፋር ወጣቶችን የማሰልጠኑና የማስታጠቁ እንዲሁም የጎሳውን ፖለቲከኞች በተለያዩ ፓርቲዎች የማደራጀቱ ሥራም በግዛቱ የውስጥ ፖለቲካ ላይ ኢትዮጵያ ልትጫወት ለምትችላቸው አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ሚናዎች አመላካች ነበር። የአሰብ ወደብን የማጠናከሩ ጥረት፣ የአሰብ አውራጃን ወደ ልዩ አስተዳደር ክልል የማሳደጉ እርምጃ እና አዲስ የባቡር መሥመር ለመዘርጋት መወጠኑም የበኩሉን ጫና ማሳደሩ አልቀረም። ድምር ውጤቱም ጅቡቲያውያን ከኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ የተነጠለ ህልውና ሊኖራቸው እንደማይችል እና ተቃራኒው መንገድም አፍራሽ ገጽታው እንደሚያመዝን እንዲረዱ አደረጋቸው። በ1970ቹ እና በ1980ቹ መጀመሪያ የታየው የመተባበርና የመግባባት መንፈስ ከዚህ የመነጨ ነበር።

አጠቃላይ ውጤቱም ሁለቱም አገራት በጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ መንቀሳቀስ መጀመራቸው ነው። ኢትዮጵያ ያለ ጅቡቲ ወደብና የምድር ባቡሩ ህልውናዋ በእጅጉ አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚወድቅ አመነች። ከብሔራዊ ወደቧ በበለጠ የጅቡቲው በር ወሳኝ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው ከግንዛቤ ተወሰደ። በጅቡቲ በኩልም የግዛቱ ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ጥገኛ እንደሆነ፤ ፖለቲካውም ቢሆን በኃያሉ





ጎረቤታቸው በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ታመነ። ኢትዮጵያ ለዘለቄታው ወደቡንና የምድር ባቡሩን ላለመጠቀም ብትወስን መጎዳታቸው እንደማይቀር ብሎም አገሪቱ ከአፋር ጎሳ ፓርቲዎች ጋር ያላት ትብብርም የግዛቱን የውስጥ አስተዳደር የማተራመስ አቅም እንዳለው መገመቱ ብዙም አላዳገታቸውም። በወደቡና በምድር ባቡሩ ዙሪያ የተደረጉ ስምምነቶችም እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች ከግምት ያስገቡ ነበሩ። በደርግ የመጨረሻ አሥር ዓመታት ውስጥም በሁለቱ መንግሥታት መካከል በጋራ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሠረተ ጥብቅ ወዳጅነት እንዲፈጠር ሆነ።

እንደ 1960ቹ አጋማሽ ሁሉ በ1983 በኢትዮጵያ የተከሰተው የመንግሥት ለውጥ በሁለቱ አገራት ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩ አልቀረም። በጋራ ድንበሮቻቸው ላይ የተከሰተው የአፋር ንቅናቄ እና ይህንንም ተከትሎ የተስተዋለው መወነጃጀል፣ የኢትዮጵያ መንግስት ከአዲሲቷ ኤርትራ ጋር የፈጠረው ጥብቅ ወዳጅነት እና የአሰብ ወደብን የመጠቀም መብት በጅቡቲ ላይ ያሳደረው ስጋት፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ በጥምረት በቀጠናው ፖለቲካ (በተለይ በሶማሊያና ሱዳን ጉዳይ) ውስጥ የነበራቸው ሚና ወዘተ ለጥርጣሬውና መቃቃሩ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ኢትዮጵያና ጅቡቲ የተረጋጋ የግንኙነት መሥመር ከመዘርጋታቸው በፊት የተለመደውን የውዥንብር ጊዜ ማሳለፍ ነበረባቸው። ነገር ግን ቆይቶ የተመሠረተው መግባባት ረጅም እድሜ አልነበረውም። የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እንደቀደመው የኦጋዴን ጦርነት ሁሉ የሁለቱን አገራት ግንኙነት በብርቱ ፈተነ። ጅቡቲ በይፋ ያራመደችው የገለልተኝነት መርህ እና የፕሬዚደንት ጉሌድ አፕቲዶን የሽምጋይነት ሚና (በኋላ ከፕሬዚደንት ኢሳያስ ጋር በድንበር ጉዳይ ቅራኔ ውስጥ መግባታቸው ላይቀር) በጦርነቱ ሂደት ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ እንደፈለገችው እንዳትጠቀም ምክንያት ሆነ።

በ1969/70 የኦጋዴን ጦርነት እና በ1990-92 የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት እንደተስተዋለው በግጭቶቹ ጅቡቲ

የገለልተኝነት ፖሊሲ እንደምታራምድ አስታውቃ ነበር። የግዛቱ መሪ ጉሌድ አፕቲዶንም በነኚህ ወቅቶች የተወሰነ የአስታራቂነት ሚና ለመጫወት መሞከራቸው አልቀረም። ከአፍሪካ ቀንድ ውስብስብ የአገራት የግንኙነት ታሪክ አንፃር አጣብቂኝ ውስጥ ላለመግባት ይህ የገለልተኝነት መርህና የሽምጋይነት ሚና ሁለም የክልሉ መንግስታት በተለያዩ ጊዜያት ሊተገብሩት ተንቀሳቅሰዋል። ዋናው ነጥብ ግን የጅቡቲ ገለልተኝነት በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ፀረ-ኢትዮጵያ ገጽታን መላበሱ ነው። ለዚህም በሁለቱም የችግር ወቅቶች አገሪቱ ራሷን ለመከላከል በአስቸኳይ የምትፈልጋቸው የጦር መሳሪያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶች በወደቡ እንዳይስተናገዱ ወይም በፍጥነት እንዳይተላለፉ መደረጋቸው አንዱ ማስረጃ ነው። የሶማሊያን ወረራ ለመቀልበስ የተቻለው መሳሪያ በአውሮፕላን በማጓጓዝ እንደነበርና ለጦርነቱ ፍጆታ በእጅጉ ይፈለግ የነበረው ከወዳጅ መንግስት የተገኘ ድፍድፍ ነዳጅ የአሰብ ወደብ ሊያስተናግደው ስላልቻለ በደቡብ የመን እንዲከማች መደረጉ የጅቡቲን የገለልተኝነት አሳቤ ተአማኒነት ከጥርጣሬ ያስገባል። ተመሳሳይ እክሎች በቅርብ ጊዜም መከሰታቸው የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅሞች በተመለከተ የግዛቱን ዘላቂ የወዳጅነት አቋም ለመጠራጠር መንገድ ይከፍታል።

ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንግስታት ያራምዷቸው የነበሩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከፈጠሯቸው መወሳሰቦች ባሻገር በጅቡቲ በር እንደተፈለገው ለመጠቀም አለመቻሉ በአገሪቱ ላይ አሉታዊ ገጽታ ማሳደሩ አልቀረም። የምጽዋና አሰብ ወደቦች ኖሩም አልኖሩ በጅቡቲ ወደብና በባቡር መሥመሩ ለመገልገል አለመቻል በኢትዮጵያ ላይ ዘርፈ ብዙ እክል ሲፈጥር ቆይቷል። በየዘመናቱ የተከሰቱ የፍጆታ እቃዎች እጥረት እና የዋጋ ግሽበት ለዚህ ዋነኛው ማስረጃ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።
በተለይ ከ1992 በኋላ የተስተዋለው የኑሮ ውድነት መሠረታዊ መገለጫ የአገሪቱ የውጭ ንግድ ግንኙነት በጅቡቲ መልካም ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ስለነበር ነው። ጊዜው ደግሞ የግዛቱ መሪዎች ይህን የወሳኝነት ሚና የተገነዘቡበትና በምልዓት ለመተርጎም መንቀሳቀስ የጀመሩበት ነበር።





የኢትዮጵያ ጥገኝነት ሌላው ገፅታ አገሪቱ የተፈለገውን ያክል የወጭ ኢንቨስትመንት መሳብ ያለመቻሏ ነው።ከዚህ ረገድ በተለይ ከ1992 በኋላ የተደረጉ ጥረቶች በተጠበቀው ደረጃ ላለመሳካታቸው አንዱ ምክንያት የኢትዮጵያ ወደብ አልባነት የሚያስከትለው ተጨማሪ ወጪ ነው። አገሪቱ ያላት እምቅ አቅም እና ርካሽ የሰው ኃይል በምንም መልኩ በሁለተኛ ወገን የባህር በር በኩል የሚደረገው መተላለፍ (ያውም ለአስተማማኝነቱ ሙሉ ዋስትና ለማይሰጥ) የሚያስከትለውን ከፍተኛ ወጪ ሊያካክስ አልቻለም። የውጭ ባለሐብቶችን ለመሳብ የተደረጉ ጥረቶችም ለመጪዎቹ ጊዜያት በዚሁ ዓይነት መቀጠላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው።

ኢትዮጵያውን ለዘመናት እንዲኖሯቸው የተመኟቸው ከባድ ኢንዱስትሪዎች፣ ፋብሪካዎችና ቀጥተኛ የመተላለፊያ መስመሮች እውን እንዳይሆኑ ከጅቡቲ ጋር ያለው የግንኙነት መወሳሰብ የበኩሉን ድርሻ ሲያበረክት ቆይቷል። ይህም ዕውነታ አጠቃላይ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ኋላ ቀር ግብርና ላይ ብቻ የተመሠረተ አደረገው። መንግስታት ለግል የፖለቲካ ፍጆታዎቻቸው ማማያነት አግዝፈው ያቀረቧቸው ፋብሪካዎችም ቢሆኑ ከጨርቃ ጨርቅ፣ መጠጥና ሲሚንቶ ውጤቶች ማምረቻነት ያለፉ አልነበሩም። የሕዝብ ቁጥሯ በእጅጉ ለጨመረባትና የዕለት ተዕለት የሸቀጥ ፍላጎቷ ላሻቀበባት አገር ከተፈጥሮ የሚገኘው ቀጥተኛ ምርት በቂ ሊሆን አይችልም። ለዘመናዊ ህይወት ግብዓት የሚሆኑ ቁሳቁሶችን ጨምሮ ነዳጅና ሌሎች የግንባታና የፍጆታ ዕቃዎችንም ከውጭ ማስገባት የውዴታ ግዴታ ይሆናል፤ ያውም በኪራይ ወደብ በኩል። በኢትዮጵያ የተመረቱትንም ከማጓጓዣ ዋጋ ውድነት የተነሳ በውጭ ገበያ ተወዳድሮ ለመሸጥና ትርፍ ለማግኘት ከማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል። የጅቡቲ መንግስት በተከታታይ ያሳየውና እያሳየውም ያለው የወደብ ታሪፍ ጭማሪና ሌሎችም መሰናክሎች የኢትዮጵያን ትልልቅ ኢንደስትሪዎችን የማስፋፋትና የውጭ ባለሐብቶችን የመሳብ ምኞት ከማሰናከሉ አንጻር ጉልህ ድርሻ እየተጫወተ ቆይቷል።

ላለፉት ሃያ ዓመታት በግልጽ እንደተስተዋለው ጅቡቲ በኢትዮጵያ ጥቅሞች ላይ ያላት የወሳኝነት ሚና በእጅጉ እየጎለበተ መጥቷል። በተለይ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማግስት ሁኔታው እየከፋ መምጣቱ እሙን ነው። ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው የአገሪቱ ወደብ አልባ መሆን እና ሙሉ በሙሉ በጅቡቲ በር ላይ ጥገኛ መሆኗ ነው። ከዚህም አንፃር በተለዋጩ ለግዛቱ በምናቀርባቸው ምርቶች አማካኝነት (ጫት፣ ፍራፍሬ፣ ስኳር ወዘተ) ይገኝ የነበረው ተሰሚነት ተመጣጣኝ የሆነ ሚዛን ሊደፋ አልቻለም። በጅቡቲ የውስጥ ፖለቲካ ውስጥ የነበረን ሚናም በእጅጉ ተመናምኗል። በመሆኑም ለተከታታይ የወደብ ታሪፍ መጨመርና በጅቡቲ መልካም ፈቃድ ሥር የመዋል አባ ፈንታ የመዳረጋችን እውነታ እያፈጠጠ መጥቷል። ይህንን ለመቀነስ አማራጭ የጎረቤት አገራት ወደቦችን (ሱዳን፣ ሶማሊላንድ እና ሞምባሳ) ለመጠቀም እንቅስቃሴ ቢኖርም አንፃራዊ ወጤታቸው ወደፊት የሚታይ ይሆናል። ግን የጅቡቲን ሁለንተናዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ይተካሉ ብሎ ማሰቡ አስቸጋሪ ነው። የግል ወደብ ከማግኘት በመለስ ጅቡቲ ምትክ የሌለው የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ በር ሆኖ መቀጠሉ አያጠራጥርም። ስለሆነም በረጅም የትግል ጥረቶች የተረጋገጡ ታሪካዊ እና ተፈጥሮአዊ መብቶችን ማስከበሩና ማስቀጠሉ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ይሆናል።

ከታሪክ ሂደቱ ጅቡቲን በተመለከተ ሁሌም የነበሩና አሁንም ያሉ ነባራዊ እውነታዎችን (constants) እና እንደ መንግሥታቱና የአከባቢው ነባራዊ ሁኔታ የሚለዋወጡ ክስተቶችን (variables) መለየት ይቻላል። ከዳግማዊ ምንሊክ ጀምሮ እስከ ጊዜያችን የነበሩ የኢትዮጵያ መንግስታት ከሚያራምዱት የውጭ ፖሊሲ እና ከሚከተሉት መርህ የመነጨ አካሄድ ሲያራምዱ ቆይተዋል። ጅቡቲን እንደ ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛት ከሚቆጥረው የመጀመሪያው አቋም አንስቶ ያሉ የፖሊሲ ለውጦች እንደ መንግሥታቱ እሳቤና መርህ የሚቀያየሩ ናቸው። ይህንንም ተከትሎ ግዛቱን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተከተለችው ወጥ ፖሊሲ እንዳልነበር መገንዘብ ይቻላል። ይልቁንም ሁሉም





የመንግስት/አገራቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ካላቸው የጋራ ግንዛቤ በመነጨ የየራሳቸውን መንገድ ለመተግበር መረጡ እንጂ።

ሁሉንም መንግሥታት የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር የጅቡቲ በር ለአገሪቱ ህልውና አማራጭ የሌለው የባህር በር መሆኑን መረዳታቸው እና ይህንኑም ለማስቀጠል መንቀሳቀሳቸው ነው። ወደቡን እና የምድር ባቡሩን ለዘለቄታው ለመገልገል ሲባልም ከተለያዩ የግዛቱ ባለመብቶች ጋር የጥቅም ድርድር (concessions) ለማድረግ ተገደዋል። አፄ ምንሊክ በቀይ ባህር ደቡባዊ ጠረፍ ለፈረንሳይ ከፈቀዱት ተጨማሪ ግዛት አንስቶ በተለያየ ጊዜ የተስተዋለው ለጅቡቲ ፖለቲከኞችና መንግሥታት የተደረጉ የመሬት ስጦታዎች፣ የገንዘብ እና ቁሳቁስ ልገሳዎች እንዲሁም በግዛቱ የውስጥ ፖለቲካ ውስጥ በመግባት የተሰሩ ሥራዎች ይህንን አገራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በማሰብ ነው። ተከታታይ ዲፕሎማሲያዊ እርምጃዎች፣ አልፎ አልፎ የሚደረጉ ወታደራዊ ትንኮሳዎች (በድንበር አከባቢ) እና በተለይ የአፋር ጎሳን በመጠቀም የተደረጉ ተጽዕኖዎች የዚሁ ጥረት ተግባራዊ ገፅታዎች ናቸው።

ይህንን ምዕራፍ ከመቋጨታችን በፊት ከአጠቃላይ የታሪክ ሂደቱ አንፃር ስለመጪው የግንኙነት አቅጣጫ አስተያየት ለመስጠት መሞከሩ አግባብ ነው። ተወደደም ተጠላ በቀጣይ ዓመታት ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ ሆና እንደምትቀጥል ግልጽ ነው። ከኤርትራ ጋር ከአንድ ዓይነት መግባባት እስካልተደረሰና ከሌሎች ጎረቤት አገራት ሊፈጠር እየተሞከረ ያለው የኢኮኖሚ ትስስር አስተማማኝ ቁመና እስኪያገኝ ድረስ ጅቡቲ ብቸኛ የንግድ በር ሆና መቀጠሉም እንደዚሁ። ተለዋጭ የንግድ በር እና ከውጭው ዓለም የመገናኛ መሥመር በሌለበት ሁኔታ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ የመደራደሪያ አቅሟን ማጎልበት ይጠበቅባታል። የጨዋታው ህግም ሌላኛውን ወገን ስለ የጋራ ትብብሩ አስፈላጊነትና የሰጥቶ መቀበል መርህ (reciprocity) ማሳመንን ይሻል፤ ይህ ባልሆነ ጊዜም የአጸፋ እርምጃ የመውሰድ አቅሙ እንዳለ በብቃት ማስረዳትንም ይጠይቃል።

Crisp. Jeff. "The Politics of Repatriation: Ethiopian Refugees in Djibouti. 1977-83." in *Review of African Political Economy*. No. 30 (Sept. 1984).

Daniel D. Kendie. "Towards Northeast African Cooperation: Resolving the Ethiopia-Somalia Disputes." in *Northeast African Studies*. Vol. 10. No. 2 (2003).

Dereje Feyissa. "Centering the Periphery? The Praxis of Federalism at the Margins of the Ethiopian State." in *Ethiopian Journal of Federal Studies*. Vol. 1. No. 1 (June 2013)

Dupuy. T.N. *The Almanac of World Military Power*. Dunn Loring. Virginia. 1970.

Hollick. Julian Crandall. "French Intervention in Africa in 1978." in *The World Today*. Vol. 35. No. 2 (Feb. 1979).

Kadamy. Mohamed. "Djibouti: Between War and Peace." in *Review of African Political Economy*. Vol. 23. No. 70 (Dec. 1996).

Killion. Tom C. "Railroad Workers and the Ethiopian Imperial State: the Politics of Workers' Organization on the Franco-Ethiopian Railroad. 1919-1959". In *International Journal of African Historical Studies*. Vol. 25. No. 3 (1992).

Laitin. David D. "Somali Territorial Claims in International Perspective." in *Africa Today*. Vol. 23 (April-June 1976).

Lewis. I.M. and Harold G. Marcus. "After the Referendum: Prospects in the *Horn*". *Africa Report* (April 1967).

Lewis. I.M. "The Referendum in French Somaliland". *The World Today (July 1967).*



Marks. Thomas A. "Djibouti: France's Strategic Toehold in Africa." In *African Affairs*. Vol. 73. No. 290 (Jan. 1974).

Merid Wolde-Aregay. "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508-1708. with Special Reference to the Galla Migration and Their Consequences." PhD Thesis in History (University of London. School of Oriental and African Studies. January 1971).

"New Trouble for French Colony on Red Sea". *MERIP Reports*. No. 45 (March 1976).

Ododa. Harry. "Somalia's Domestic Politics and Foreign Relations since the Ogaden War of 1977-78." in *Middle Eastern Studies*. Vol. 21. No. 3 (July 1985).

Pankhurst. Richard. *Economic History of Ethiopia*. 1800-1935. Addis Ababa. 1968.

Sbacchi. Alberto. "Towards the Recognition of the Italian Empire: Franco-Italian Negotiations. 1936-1940." in *Africa: Rivista trimestrale di studi e documentazione dell'Istituto italiano per l'Africa el'Oriente*. Anno 30. No.3 (Sept. 1975).

Schraeder. Peter J. "Ethnic Politics in Djibouti: From 'Eye of the Hurricane' to 'Boiling Cauldron'". in *African Affairs*. Vol. 92. No. 367 (April 1993).

Schwab. Peter "Cold War on the Horn of Africa." In *African Affairs*. Vol. 77. No. 306 (Jan. 1978).

Seyoum Haregot. *The Bureaucratic Empire: Serving Emperor Haile Selassie*. Red Sea Press: Trenton. New Jersey. 2013

Shehim. Kassim and James Searing. "Djibouti and the Question of Afar Nationalism." In African Affairs. Vol. 79. No. 315 (April 1980).

Shiferaw Bekele. "The Ethiopian Railroad and British Finance Capital. 1896-1902." in *Africa:Rivista trimestrale di studi edocumentazione dell'Istituto italiano per l'Africa el'Oriente*. Anno 46. No.3 (Sept. 1991).

Shilling. Nancy A. "Problems of Political Development in a Ministate: The French Territory of the Afars and the Issas. " in *The Journal of Developing Areas*. Vol. 7. No. 4 (Jul. 1973).

Spencer. John H. *Ethiopia. the Horn of Africa and US Policy. Published by Institute for Foreign Policy Analysis* (Cambridge. Massachusetts. September 1977.

Thompson. Virginia and Richard Adloff. *Djibouti and the Horn of Africa*. Stanford. 1968.

Touval. Saadia. *Somali Nationalism*. Cambridge. 1963.

Yasin. Yasin Mihammed. "Political History of the Afar in Ethiopia and Eritrea." in *Africa Spectrum*. Vol. 43. No. 1 (2008).

ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ የግዛት ዳርቻ ከባህሩ ይደርስ ነበር። አስፈላጊው አቅም ስላልነበረን … የጠረፍ ግዛቶቻችን በአረቦች እጅ ወደቀ። አሁንም የባህር ዳርቻ ግዛታችንን በኃይል የማስመለስ እቅድ የለንም። ነገር ግን ክርስቲያን የሆናችሁ ወንድሞቻችን የባህር ጠረፍ ግዛታችንን እንደምትመልሱልን ካልሆነም ቋሚ የባህር መዳረሻ በር እንደምትሰጡን እናምናለን። … ጥንታዊው የአገራችን ግዛትም ከሐምቦስ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እስከ አሳል ባህር፤ ከዚያም ከጥንት ጀምሮ ገባራችን የሆነውን የሞሐመድ አንፈሪን ግዛት ወደኛ በመተው እስከ አራፋል ይደርሳል።

አፄ ምንሊክ

ጅቡቲ በኢኮኖሚ፣ በሶሺያልና በፖለቲካ፣ በስትራቴጂ፣ እንዲሁም በታሪክና በጂኦግራፊ አቀማመጥ የኢትዮጵያ አካል ናት። ኢሳና አዳል የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነገዶች በብዛት የሚገኙት በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ሳለ፣ በጅቡቲ የሚኖሩት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ኢሳና አዳል አካላቸው ተቆርጦ ገሚስ ጎናቸው ወደሌላ እንዲሆን አይፈልጉም፤ ኢትዮጵያም አትፈቅድም። የጅቡቲ ሕዝብ ስለራሱ ነፃነት ራሱ መወሰን አለበት ስትል ኢትዮጵያ የደገፈችው፣ የጅቡቲ ሕዝብ ለራሱ ጠቃሚ ባልሆነው በተቃራኒው መንገድ እንደማይውልና ከማን ጋር እንደሚኖርም ሳያመዛዝን አይቀርም በሚል እምነት ነው። ኢትዮጵያ የጅቡቲ ሕዝብ ጥቅሙ ወዳልሆነ አቅጣጫ እንዳይወድቅ፣ ከኢትዮጵያም እንዳይለይ ለማድረግ ተገቢ የሚሆነውን እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ ሃሳብ አላት።

አፄ ኃይለ ሥላሴ

… የሶማሊያ አድኃሪ መንግስት በጅቡቲ ላይ ያለውን የይገባኛል ፍላጎቱን ካልለወጠና አሁን ከሚያካሂደው ፀረ-ሠላምና ፀረ-ሕዝብ አድራጎቱ ካልተቆጠበ ለሌላ ፍልሚያ የሚጋብዘን መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። …

ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም

OLand Printing Press
0118294188/0921785932

65 ብር